ስምንተኛ ክፍል ላይ፣ ተማሪዎች በወቅታዊ የጸሃፊዎች አስተዋጽዖዎች በኩል እየሰፋ የሚገኘውን የበለጸገ፣ በባህላዊ ሁኔታ ብዝሃ የሆነውን የስነጽሁፍ ቅርስን ትምህርት ይቀጥላሉ። ተማሪዎች የተለያዩ የአጻጻፍ ቅርጾችን፣ የክፍል ውይይቶችን፣ ድራማዎችን እና ሌላ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም የንባብ ግንዛቤያቸውን ለማሰስ እና ለማሳየት ይጠቀሙበታል። ጎን ለጎን የሚሄዱ ሴከሰቱ፣ ሁለንተናዊ ትምህርቶች ከሌሎች የይዘት አካባቢዎች ጋር ስነጽሁፍን አብረው ያስኬዳሉ። ቀልጣፋ የአጻጻፍ ስትቲቴጂዎች፣ ትክክለኛ የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀም እና ውጤታማ የንግግር-የማቅረብ ክህሎቶች በግለሰብ፣ በትንሽ ቡድን እና በአጠቃላይ የክፍል ፕሮጀክቶች በኩል ንቁ በሆነ ተሳትፎ ይጎለብታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የቋንቋ ስነጥበባት ኦነርስ 6**

ካሪኩለሙ ግለሰባዊ ለውጥ በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ይዞራል። ተማሪዎች የጸሃፊውዎችን የህይወት ታሪክ በማንበብ እንዲሁ፣ በተመረጡ የሰዎች ህይወት ውስጥ ለውጥን በማየት የለውጥ ጽንሰ ሃሳብን ይማራሉ። ተማሪዎች የችሎታ ማጎልበትን እንዲያገኙ እይታን ለማግኘት እንዲረዳ፣ ትምህርቶቹ በውይይቶች እና በአንጸባራቂ አጻጻፍ በኩል የራሳቸውን ማንነቶች እንደ ጎበዝ ተማሪዎች እንዲያስሱ ያበረታታቸዋል። ተጨማሪ ምርጫዎች እና እንቅስቃሴዎች ደራሲዎች እና ተማሪዎች በንባባቸው እና በጽሁፋቸው ውስጥ የግለሰባዊ ለውጥ ላይ አጽንዖት መስጠታቸውን ቀጥለዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የቋንቋ ስነጥበባት ኦነርስ 7**

ካሪኩለሙ ማህበረሰባዊ ለውጥ በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ይዞራል። በስነጽሁፍ ትምህርት በኩል፣ ተማሪዎች በአጠቃላይ በአለም ላይ እና በተወሰነ ደግሞ በአሜሪካ ስለሚከናወነው ለውጥ እንዲሁም የተራ ሰዎች ሕይወትየጦርነት ክስተቶች እንኳን እየታዩ እንዴት እንደሚቀየር ይማራሉ። ተጨማሪ ምርጫዎች እና እንቅስቃሴዎች በማህበራዊ ለውጥ ላይ ያለ አጽንዖት መስጠትን ቀጥለዋል እና ተማሪዎች የጉልህነት ችግርን ለመመርመር ይበረታታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የቋንቋ ስነጥበባት ኦነርስ 8**

ካሪኩለሙ አለም አቀፋዊ ለውጥ በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ይዞራል። ተማሪዎች የፍጹም አለም ሃሳቦች ለምን በለውጥ ውስጥ እንዳለፈ፣ የፍጹም አለም መፈለግን በዘመናት ውስጥ እንዲሁም በግላዊ እና በማህበረሰባዊ ደረጃዎች ለመያዝ እና ለማቆየት ያሉትን ትግሎች ይመረምራሉ። ተጨማሪ ምርጫዎች እና እንቅስቃሴዎች በአለም አቀፍ ለውጥ ላይ ያለ አጽንዖት መስጠትን ቀጥለዋል እና ተማሪዎች ዩቶፒያን በግላዊ ህልሞች እና ግቦች በኩል እንዲያስሱ ይበረታታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የማንበብና መጻፍ ማበልጸግ 6**

ተማሪዎች ለዚህ ኮርስ ሊመዘገቡ ወይም እንዲመዘገቡ ሊመከሩ ይችላል። ይህ ኮርስ የንባብ እና የጽሁፍ ብቃቱ መሰረታዊ የንባብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን እና ስትራቴጂዎችን ለማጠናከር ፍላጎት እንዳለ ለሚያሳይ ተማሪ ነው። በቀጥታ መመሪያ፣ የመልቲሚዲያ አተገባበሮች እና ልብወለድ እና ኢ-ልብወለድን ጨምሮ ለበርካታ የንባብ ነገሮች ተጋላጭነት፣ ተማሪው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የንባብ እና የጽሁፍ መስፈርቶችን ለማሟላት የተዋጣለት ይሆናል።

የክፍል መመሪያ የአንባቢዎቹን ችሎታ ቃላትን እንዲፈቱ፣ ጽሁፍ እንዲረዱ፣ የንባብ እና የጽሁፍ መዝገበ ቃላትን እንዲያሰፉ እና ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለመማር የማንበብ ስትራቴጂዎችን እንዲተገብሩ ያሻሽላል። የአጻጻፍ መመሪያ እና የአጻጻፍ እድሎች የተማሪዎን ሃሳቦችን የማደራጀት እና በግልጽ የመግለጽ ችሎታውን ያሻሽላሉ። የግል ተማሪዎች ፍላጎቶች እንደተሟሉ ለማረጋገጥ፣ ለማንበብና መጻፍ ድጋፍ በርካታ አቀራረቦች ይገኛሉ። እነዚህ አቀራረቦች የመልቲሚዲያ እውቀትን፣ የስኬት መብረርን ወይም የራስ-ሰር ክህሎት ፕሮግራምን ሊያካትቱ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የማንበብና መጻፍ ማበልጸግ 7**

ተማሪዎች ለዚህ ኮርስ ሊመዘገቡ ወይም እንዲመዘገቡ ሊመከሩ ይችላል። ይህ ኮርስ የንባብ እና የጽሁፍ ብቃቱ መሰረታዊ የንባብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን እና ስትራቴጂዎችን ለማጠናከር ፍላጎት እንዳለ ለሚያሳይ ተማሪ ነው። በቀጥታ መመሪያ፣ የመልቲሚዲያ አተገባበሮች እና ልብወለድ እና ኢ-ልብወለድን ጨምሮ ለበርካታ የንባብ ነገሮች ተጋላጭነት፣ ተማሪው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የንባብ እና የጽሁፍ መስፈርቶችን ለማሟላት የተዋጣለት ይሆናል። የክፍል መመሪያ የአንባቢዎቹን ችሎታ ቃላትን እንዲፈቱ፣ ጽሁፍ እንዲረዱ፣ የንባብ እና የጽሁፍ መዝገበ ቃላትን እንዲያሰፉ እና ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለመማር የማንበብ ስትራቴጂዎችን እንዲተገብሩ ያሻሽላል። የአጻጻፍ መመሪያ እና የአጻጻፍ እድሎች የተማሪዎን ሃሳቦችን የማደራጀት እና በግልጽ የመግለጽ ችሎታውን ያሻሽላሉ። የግል ተማሪዎች ፍላጎቶች እንደተሟሉ ለማረጋገጥ፣

ለማንበብና መጻፍ ድጋፍ በርካታ አቀራረቦች ይገኛሉ። እነዚህ አቀራረቦች የመልቲሚዲያ እውቀትን፣ የስኬት መብረርን ወይም የራስ-ሰር ክህሎት ፕሮግራምን ሊያካትቱ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**የማንበብና መጻፍ ማበልጸግ 8**

ተማሪዎች ለዚህ ኮርስ ሊመዘገቡ ወይም እንዲመዘገቡ ሊመከሩ ይችላል። ይህ ኮርስ የንባብ እና የጽሁፍ ብቃቱ መሰረታዊ የንባብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን እና ስትራቴጂዎችን ለማጠናከር ፍላጎት እንዳለ ለሚያሳይ ተማሪ ነው። በቀጥታ መመሪያ፣ የመልቲሚዲያ አተገባበሮች እና ልብወለድ እና ኢ-ልብወለድን ጨምሮ ለበርካታ የንባብ ነገሮች ተጋላጭነት፣ ተማሪው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የንባብ እና የጽሁፍ መስፈርቶችን ለማሟላት የተዋጣለት ይሆናል። የክፍል መመሪያ የአንባቢዎቹን ችሎታ ቃላትን እንዲፈቱ፣ ጽሁፍ እንዲረዱ፣ የንባብ እና የጽሁፍ መዝገበ ቃላትን እንዲያሰፉ እና ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለመማር የማንበብ ስትራቴጂዎችን እንዲተገብሩ ያሻሽላል። የአጻጻፍ መመሪያ እና የአጻጻፍ እድሎች የተማሪዎን ሃሳቦችን የማደራጀት እና በግልጽ የመግለጽ ችሎታውን ያሻሽላሉ። የግል ተማሪዎች ፍላጎቶች እንደተሟሉ ለማረጋገጥ፣ ለማንበብና መጻፍ ድጋፍ በርካታ አቀራረቦች ይገኛሉ። እነዚህ አቀራረቦች የመልቲሚዲያ እውቀትን፣ የስኬት መብረርን ወይም የራስ-ሰር ክህሎት ፕሮግራምን ሊያካትቱ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ንባብ**

ይህ ኮርስ ፈጣን የመማር እና የቋንቋ መቅሰምን ኢላማ ውስጥ ለሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ላሉ የ EL ተማሪዎች ያስተዋውቃል። ኮርሱ ታዳጊ ሆነው እየተነሱ ለሆኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀት የጀማሪ ደረጃ ላይ ያሉ እና እንደ ፎኖሎጂካል ግንዛቤ፣ የህትመት ጽንሰ ሃሳብ፣ የቃላት ስብስብ እድገት፣ የንባብ ግንዛቤ እና ትርጉም፣ ጽሁፍ፣ ንግግር እና ማዳመጥን የመሳሰሉ የተግባራዊ ስነጽሁፍ ክህሎታቸውን ለማዳበር ለሚፈልጉ አንባቢዎች የተነደፈ ነው። ኮርሱ የተማሪ እንቅስቃሴ የመማር ተከታታይነትን ከመነሻ መሰረታዊ የቋንቋ ማግኛ እስከ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ውስጥ ያሉትን የሚመራ እና ራሱን የቻለ መተላለፍ ደረጃን ጨምሮ ይደግፋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6, 7, 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

# ቤተሰብ እና የተጠቃሚ ሳይንሶች

የተማሪ የመሪነት ክህሎቶች በት/ቤት ላይ በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የስራ ማሳያ፣ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ስራ ትምህርት እና/ወይም የ Community Leaders of America (FCCLA) ውስጥ በመሳተፍ ሊዳብር ይችላል። የህብረት ስራ ትምህርት ዘዴ ለሁሉም የሙሉ አመት ኮርሶች ይገኛል። የሙሉ ጊዜ ተማሪ የክፍል ውስጥ ትምህርትን እና ቢያንስ 396 ሰዓት የሚሆን የመስክ ላይ ስልጠና በተፈቀደ መደብ ላይ ተከታታይ ከሆነ ማማከር ጋር አመቱን በሙሉ አጣምሮ ይወስዳል። ተማሪው ለእርሱ ወይም ለእርሷ የህብረት ትምህርት ተሞክሮ ተጨማሪ ክሬዲት ሊቀበል ይችላል ወይም ትችላለች።

**ቤተሰብ እና የተጠቃሚ ሳይንሶች I**

ተማሪዎች የግል፣ የቤተሰብ፣ የስራ እና የማህበረሰብ ሚናዎችን እና ሃላፊነቶችን ለማስተዳደር መሰረት ያገኛሉ። ተማሪዎች እንደ ግላዊ የግብ ማሳካት፣ በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሃላፊነቶች እንዲሁም ለግል ደህንነት እና ጤና ተጠያቂነት ላይ ባሉ አካባቢዎች አይ ያተኮራሉ። እንዲሁም እነሱ የፋይናንሻል ማኔጅመንትን ተሞክሮን፣ የልብስ ማስተካከልን፣ የምግብ ዝግጅትን፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር አዎንታዊ እና እንክብካቤ ያለባቸውን ግንኙነቶች እና ከሙያ ዳሰሳ ጋር የተያያዙ የራስ ግምገማን ይዳስሳሉ። ተማሪዎች ኮርሱን እየገፉ ሲሄዱ ችግር ፈቺ እና የመሪነት ክህሎቶችን ይተገብራሉ። ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ እንግሊዝኛ፣ ማህበራዊ ሳይንሶች፣ ፋይን ስነጥበባት እና ቴክኖሎጂ በኮርሱ ውስጥ በሙሉ የተሳሰሩ ናቸው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ቤተሰብ እና የተጠቃሚ ሳይንሶች II**

ተማሪዎች በማህበራዊ ሚናቸው ላይ ሃላፊነት የሚሰማው እና አዎንታዊ አካሄዶችን ለማጎልበት እንዲረዳቸው ከፍተኛ የሆነ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ይጠቀማሉ። በላብራቶሪ ተሞክሮዎች እና ከጓደኞች ጋር ባሉ የተነቃቁ እንቅስቃሴዎች፣ ተማሪዎች በግላዊ እድገታቸው እንዲሁም በቤተሰብ ክፍል ውስጥ ያለውን ግንኙነታቸው እና ሚናቸው ላይ ያተኩራሉ። ተማሪዎች ለኮሌጅ እና ለግል ሃላፊነቶች ለመዘጋጀት ኮምፒውተሮችን፣ ቴክኖሎጂን፣ ሂሳብን፣ ሳይንስን እና  የቋንቋ ስነጥበባትን ይጠቀማሉ። በሃብት አስተዳደር፣ በአመጋገብ እና ጤንነት፣ በግብ አዘገጃጀት እና የስራ አሰሳ ላይም አጽንዖት ተሰጥቷል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ቤተሰብ እና የተጠቃሚ ሳይንሶች III**

ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ላላቸው ግለሰባዊ ሚናዎች እንዲሁም ማህበረሰቡ እንዴት የግል እድገት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ ያተኩራሉ። ተማሪዎች የለውጥ አስተዳደር እና የግጭት መፍቻ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ እና እንዴት አለም አቀፍ አሳሳቢ ጉዳዮች ማህበረሰቦች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርሱ ይመረምራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የአመጋገብ እና የጤንነት ልምዶች እውቀትን ያሳድጋሉ እንዲሁም የሸማች እና ቤተሰብ ግብአቶችን ከፍተኛ በማድረግ የቤት ውስጥ ችግሮች እንዴት እንደሚፈቱ ይማራሉ። ተማሪዎች የመሪነት ችሎታቸውን እንዲሁ ይጨምራሉ እና በጎ ፈቃደኝነት እንዴት ማህበረሰቦችን እንደሚረዳ ይዳስሳሉ። ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ ሳይንሶች፣ እና ቴክኖሎጂ በኮርሱ ውስጥ በሙሉ የተሳሰሩ ናቸው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

# የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና የቤተሰብ ህይወት

የጤና፣ የሰውነት ማጎልመሻ እና የቤተሰብ የህይወት ፕሮግራም አላማ ተማሪዎች በህይወት ዘመናቸው በአካል ንቁ እና ጤናማ የሚሆኑበትን እውቀት፣ ክህሎቶች እና የራስ መተማመን እንዲያጎለብቱ ነው።

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በሞተር/የእንቅስቃሴ እውቀት እና ክህሎቶች፣ በአካል እንቅስቃሴ እና የአካል ብቃት እውቀት እና ክህሎቶች፣ ግላዊ እና ማህበራዊ ሃላፊነቶች እና የአካል ብቃት

እንቅስቃሴን ለበርካት ጥቅሞቹ ዋጋ መስጠት በደረጃዎች-በተመሰረተ ትምህርት ላይ ይደገፋል።

ACPS ግለሰባዊ የአካል ብቃትን ኢላማ ያደረገ የካበተ ፕሮግራምን ለተማሪዎች ያቀርባል። ተማሪዎች የእንቅስቃሴ መጠንን ለመማር የአካላዊ እንቅስቃሴ ደረጃን እና የልብ ምት መቆጣጠሪያዎችን በመለካት ፔዶሜትሮችን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በት/ቤቱ ውስጥ እና ውጪ አካላዊ እንቅስቃሴን ለመለማመድ እና ለማጣጣም በርካታ እድሎች ቀርቦላቸዋል።

የጤና ትምህርት በደረጃዎች ላይ የተመሰረተ መመሪያን በማቅረብ በአካላዊ ጤና፣ አእምሮአዊ-ስሜታዊ ጤና እና ቤተሰባዊ-ማህበራዊ ጤና ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች ወደ ጤናማ ባህሪያት የሚመሩ እና አደገኛ ባህሪያትን የሚቀንሱ ክህሎቶችን በመማር እና በመተግበር ለጤና ማስታወቂያ የራሳቸው ተሟጋቾች ይሆናሉ።

**ተስማሚ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**

ይህ ኮርስ ለአጠቃላይ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ተጨማሪ ነው። በመደበኛ የሰውነት ማጎልመሻ የትምህርት ክፍሎች ለመሳተፍ የማይችሉ ተማሪዎች የእድገት እንቅስቃሴዎች፣ ጨዋታዎች፣ ስፖርቶች እና ሪትሞች ኮርስ ሊቀርብላቸው ይችላል። ንቁ ተሳትፎ በበርካታ የመዝናኛ ስፖርቶች ውስጥ ይበረታታል። ተማሪዎች ለተሳታፊው የተወሰኑ ሁኔታዎች የሚስማሙ ደንቦችን እና ቴክኒኮችን ለስፖርቶች ይማራሉ። በዚህ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች መደበኛ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና/ወይም አስፈላጊ ሲሆን የጤና ትምህርት ክፍሎችን ሊቀላቀሉ ይችላሉ። ግቡ ተማሪዎች ችሎታቸውን ከዕለት ተዕለት አኗኗር ጋር እንዲያለማምዱ ለመርዳት ነው። የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ግድግዳዎችን ተሻግሮ መውጣትን፣ ፒርዶሜትሮችን፣ የልብ ምት መቆጣጠሪያዎችን፣ የኢንላይን ስኬቶችን፣ የተራራ ብስክሌቶችን እንዲሁም ከቤት ውጪ እንቅስቃሴዎችን የመጠቀም እድል ይኖራቸዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና የቤተሰብ ህይወት 6**

ተማሪዎች የህይወት ዘመን ጤናማነትን እና የአካል ብቃትን የሚያመጡ ክህሎቶችን፣ እውቀትን፣ አስተሳሰቦችን እና ባህሪያትን ያጎለብታሉ። እንቅስቃሴዎች የሚያካትቱት ተማሪዎች መሰረታዊ ደንቦችን የሚማሩበት እና በስፖርት ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ መሪ ክህሎቶችን እንዲለማመዱ የተለያዩ የኤሮቢክ፣ የእንቅስቃሴ፣ የሪትም/ የዳንስ እና የጨዋታ ተሞክሮዎችን ነው። ተማሪዎች በመተባበር ይሰራሉ፣ አዎንታዊ የስፖርተኛ ሰው አይነት ባህሪን ያሳያሉ እንዲሁም ጤናማ የህይወት አካሄድን ያስተዋውቃሉ። ጤና እና የቤተሰብ ህይወት ተማሪዎች ስለአመጋገብ፣ ደህንነት እና አደጋ ስለመከላከል፣ በሽታ ስለመከላከል እና መቆጣጠር፣ አልኮል እና አላግባብ የመድሃኒት አጠቃቀምን ስለመከላከል እና የግል ጤናን እና የአካል ብቃትን ስለማስተካከል ያለ መረጃን በአንድ አመት በሚረዝመው ኮርስ ውስጥ አካቱቷል። የቤተሰብ ህይወት ይዘት በቤተሰብ ግንኙነቶች፣ በጾታዊ ደህንነት፣ በአረጋጋጭ ባህርይ፣ በስሜታዊ እና አካላዊ የጉርምስና ገጽታዎች፣ የሰው መራባት እና የሰው እድገት እና መጎልበት ላይ ያተኩራል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና የቤተሰብ ህይወት 7**

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እንቅስቃሴዎች በሪትም ፣ በዳንስ እና ግለሰብ፣ በሁለት እና በቡድን ስፖርቶች ማስተማር እና ተሳትፎ ከክህሎት እድገት ጋር ይቀጥላል። የግላዊ አካል ብቃት እና ጤና ጽንሰ ሃሳቦች በልምዶች ባሉ የአካል እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በጤና ክፍል

ነው። የጤና ትምህርት ይዘት ለተማሪዎች ጥሩ ጤንነትን እንዲጠብቁ፣ ጥል የመፍታት ክህሎቶች እና የህይወት ክህሎቶች ስልጠናን ከመድሃኒቶች እና አልኮል ጋር የተገናኙ የአደጋ ምክንያቶችን በተሻለ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል። የቤተሰብ ህይወት ክፍል የሰው ልጅ መራባት፣ ተላላፊ በሽታዎች፣ ኤች አይቪ ኤድስ፣ መታቀብ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ ግንኙነት እና ግላዊ የግብ አቀማመጥን ይሸፍናል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

#### የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና የቤተሰብ ህይወት 8

ተማሪዎች የአካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና ማህበራዊ ጤናን የሚረዱ የአካላዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የግል የአካል ብቃት እቅዶችን ያጎለብታሉ። ክህሎቶች ይገመገማሉ እና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማበረታታት በበለጠ ውስብስብ የአካል ብቃቶች እና ስፖርቶች ተሳትፎ ይሻሻላሉ። የጤና ትምህርት በህይወት ክህሎት ስልጠና፣ ግላዊ ጤና እና አካላዊ እድገት እንዲሁም ኤችአይቪ/ኤድስን ጨምሮ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል ያለ መረጃን ይሸፍናል። የቤተሰብ ህይወት ክፍል መታቀብ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ የጓደኛ ግፊት፣ ወሲባዊ በደል እና ትንኮሳ እና ግንኙነቶችን መለወጥ እንዲሁም ተማሪዎችን ከባህርያዊ እስከ ግላዊ እሴቶች ድረስ እንዲያዛምዱ በመርዳት ሽፋን ይሰጣል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# የሂሳብ ዋና ኮርሶች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ ለአልጄብራ I፣ ለጂኦሜትሪ እና ለአልጄብራ II የ SOL የሂሳብ ሙከራዎች አሉ።

#### ሂሳብ 6

የሂሳብ 6 ኮርስ የ6ኛ ክፍል የቨርጂኒያ የሂሳብ መማሪያ ደረጃዎች ዋና ይዘት ሚዛናዊ የሆነ እና አጠቃላይ አሰሳ ነው እንዲሁም የአልጄብሪክ አስተሳሰብን መሰረቶች የሚያደርጉ የሂደት መቆሚያዎች ናቸው። ይህ ኮርስ የሚያካትተው፤ በክፍልፋዮች፣ በዴሲማሎች እና በፐርሰንቶች ባሉት ግንኙነቶች ትኩረት ጋር ያሉ ቁጥር እና የቁጥር ስሜት፤ ስሌት እና ከራሽናል ቁጥሮች የክንውን ትኩረት ጋር የሚኖር ግምት፤ ከስፋት፣ ከዙሪያ፣ ከመጠን እና የገጽታ ስፋት ጋር ችግር መፍታት ላይ ያተከረ መለካት፤ በባህሪያት እና ግንኙነቶቻቸው ትኩረት ጋር ያለ ጂኦሜትሪ፤  የስታቲስቲክስ ተግባራዊ መተግበሮች ትኩረት ጋር ያለ ፕሮባቢሊቲ እና ስታቲስቲክስ፤ እና በተለዋዋጮች፣ እኩልታዎች እና ባህሪያት ትኩረት ጋር ያሉ አካሄዶች፣ ፈንክሽኖች እና አልጄብራ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

#### ሂሳብ 7

የሂሳብ 7 ኮርስ የ7ኛ ክፍል የቨርጂኒያ የሂሳብ መማሪያ ደረጃዎች ዋና ይዘት ሚዛናዊ የሆነ እና አጠቃላይ አሰሳ ነው እንዲሁም ተማሪዎች አጂጄብራን እንዲማሩ በበለጠ በስሳብ ውስጥ የሚያዘጋጁ የሂደት መቆሚያዎች ናቸው። ኮርሱ የሚያካትተው፤ በክፍፍላዊ ምክንያታዊነት ላይ ካለ ትኩረት ጋር ያለ ቁጥር እና የቁጥር ስሜት፤ በኢንቲጀር ክንውኖች እና በክፍፍላዊ ምክንያታዊነት ውስጥ ባለ ትኩረት ማስላት እና መገመት፤ በክፍፍላዊ ምክንያታዊነት ላይ ባለ ትኩረት የሚኖር ልኬት፤ በቁጥሮች ላይ ባሉ የግንኙነቶች ትኩረት ጋር

ያለ ጂኦሜትሪ፤ በአተገብበራቸው ላይ ያተኮረ ፕሮባቢሊቲ እና ስታቲስቲክስ፤ እና አካሄዶች፣ በሊኒየር እኩልታዎች ላይ ያተኮሩ ፈንክሽኖች እና አልጄብራ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ሂሳብ 6

**ሂሳብ 8**

ይህ ኮርስ በክፍል ደረጃ ለሚሰሩ ተማሪዎች ነው። የተማሪዎችን የቁጥር ስሜት እና ተመጣጣኝ ምክንያታዊነት ማሳደግን በመቀጠል፣ ይህ ኮርስ በአልጄብራ መሰረቶች ላይ ያተኩራል፣ ይህም የሚያካትተው (1) ፈንክሽኖችን እና ባህሪያቸውን በመመርመር፤ (2) እኩሌታዎችን በሁለት ተለዋዋጮች ግራፍ በመስራት፤(3) ራሽናል ቁጥሮችን በመጠቀም መልቲስቴፕ ሊኒየር እኩሌታዎችን መፍታት፤ እና (4) የገሃዱ አለም ህይወት ውሂብን ግምቶች እና ትንበያዎችን ማድረግ። ተማሪዎች የስምንተኛ ክፍል SOL ሙከራን ይወስዳሉ። ለዚህ ኮርስ ያለው ግብ በ 9ኛ ክፍል ለአልጄብራ 1 ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የተዘጋጁ ተማሪዎችን ማግኘት ነው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ሂሳብ 6

ሂሳብ 7

**ሂሳብ ኦነርስ 6**

የሂሳብ ኦነርስ 6 ኮርስ የ 6ኛ ክፍል የቨርጂኒያ ሂሳብ ደረጃዎች ዋና ይዘት እና በስሳብ ውስጥ የሂደት መቆሚያዎች ናቸው። ኮርሱ በይዘቱ አካባቢ ጥልቅ የሆነ ማበልጸግን ለመፍቀድ እየፈጠነ በሚሄድ መንገድ እየተሰጠ ነው። ሂሳብ ኦነርስ 6 አጽንዖት የሚሰጠው በችግር መፍቻ በኩል መሻሻሎችን እንዲሁም በጥልቀትየጎለበቱ ውይይቶችን እና ማስመሰያዎች ላይ ነው። ትኩረት በሁሉም አምዶች ውስጥ በቁጥር እና በቁጥር ስሜት ይከፋፈላሉ፤ ስሌት እና ግምት፤ ልኬት እና ጂኦሚትሪ፤ ፕሮባቢሊቲ እና ስታቲስቲክስ፤ እና ንድፎች፣ ፈንክሽኖች እና አልጄብራ ናቸው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ሂሳብ ኦነርስ 7**

የሂሳብ ኦነርስ 7 ኮርስ የ7ኛ ክፍል የቨርጂኒያ ሂሳብ ደረጃዎች ዋና ይዘት እና በስሳብ ውስጥ የሂደት መቆሚያዎች ናቸው። ኮርሱ በይዘቱ አካባቢ ጥልቅ የሆነ ማበልጸግን ለመፍቀድ እየፈጠነ በሚሄድ መንገድ እየተሰጠ ነው። ትምህርቱ የሂሳብ 7 የመማር ደረጃዎች እውነተኛ አተገባበር እና ጥልቅ የሆነ ስሌትን በመፍታት ተማሪውን የበለጠ የማይታዩ የአልጄብራ እና የጂኦሜትሪ ሃሳቦች እንዲዘጋጁ የማድረግ ሃሳብንም ያዘለ ነው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6, 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ሂሳብ 6

**የሂሳብ ድጋፍ**

በገላጮች፣ በሞዴሎች፣ በስኬቾች እና በዲያግራሞች በመጠቀም፣ ተማሪዎች የሂሳብ ጽንሰሃሳቦችን እና ሂደቶችን መረዳት በማጎልበት መረጃን እንዲይዙ እና እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል። ይህንን በማድረግ፣ ተማሪዎች በአልጄብራ እና ጂኦሜትሪ የወደፊት

ትምህርት ውስጥ የጽንሰ ሃሳብ መሰረትን እየፈጠሩ ሂሳብን በበለጸገ እና ትርጉም በሚሰጥ መንገድ እንዲሞክሩት እድል ያገኛሉ። ተማሪዎች ለዚህ ኮርስ ሊመዘገቡ ወይም እንዲመዘገቡ ሊመከሩ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# ሙዚቃ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

### የላቀ ዝማሬ

የላቀ ዝማሬ በሙዚቃ መማር እና በድምጽ ቴክኒክ ከፍተኛ ደረጃዎች ላይ ለደረሱ ተማሪዎች ይቀርባል። የኮርሱ ይዘት ተማሪዎች ቴክኒካዊ፣ ሙዚቃዊ እና የአፈጻጸም ክህሎቶችን እንዲያጎለብቱ የተነደፈ ነው። በዚህ ኳየር የተጠናው ሙዚቃ ፈታኝ ነው እና በአባላቶቹ ክፍል ላይ የልህቀት ፍላጎትን ይፈልጋል። ተማሪዎች በበጋ እና በጸደይ ኮንሰርቶች፣ በአካባቢያዊ እና የስዲትሪክት የዜማ ፌስቲቫሎች እና በሌላ የክንውን እድሎች ውስጥ እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። የተከናወነ ሙዚቃ የታሪካዊ ጊዜያትን እና የሙዚቃ ዘይቤዎችን ይሸፍናል። ከመደበኛው የክፍል ጊዜ በተጨማሪ፣ የላቀ የዝማሬ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በሳምንት አንድ ቀን ወይ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ ይለማመዳሉ። **የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

መካከለኛ ዝማሬ እና ኦዲሽን

### የጅማሮ ባንድ

ተማሪዎች የመጫወቻ መሳሪያዎችን ስልቶችን በመማር የስብስብ እና የግል ክንውኖችን ያጎለብታሉ። የድምጽ ጥራት እና ቴክኒካዊ ፋሲሊቲ ጎልብተዋል። ተማሪዎች በራሳቸው አፈጻጸሞች እና በባንዱ አፈጻጸሞች ላይ ይወያያሉ እና ገንቢ በሆነ መንገድ አስተያየት ይሰጣሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የጅማሮ ዝማሬ

ዜማ የቀረበው የሙዚቃእውቀታቸውን እና የድምጽ ክህሎታቸውን እያጎለበቱ በመቀጠል ለመዝናናት መዝፈን ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው። የኦክታቭ ሙዚቃ እና እራሱን የቻለ የዝማሬ ክፍልን ማንበብ ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። የዜማ አባላት በሙዚቃ ዳይሬክተሩ በሚወሰነው መሰረት በክረምት እና ጸደይ ኮንሰርቶች እንዲሁም በአካባቢ እና በዲስትሪክት ፌስቲቫሎች ውስጥ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የጅማሮ ኦርኬስትራ

ተማሪዎች ዝቅ ማለትን እና ጣቶችን መጠቀም ክህሎቶችን ያጎለብታሉ እንዲሁም ቁጥጥር ያለበት የድምጽ ጥራትን ያሳያሉ። በስብስብ ትወና ላይ ምድብ ክፍል አተገባበርን ይማራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የሙዚቃ ቃላትን ለመመልከት እና በተለያዩ የሙዚቃ ጽሁፍ ውስጥ በመተግበር የሙዚቃ ስታይሎችን ግንዛቤ ያጎለብታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የኮንሰርት ባንድ

ጥቂት የትወና ተሞክሮ ያላቸው ተማሪዎች ለዚህ ኮርስ ብቁ ናቸው። ተማሪዎች የተለያዩ የባንድ ስነጽሁፍ ስታይሎችን በመጠቀም ግላዊ እና የቡድን አፈጻጸም ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ልክ የሆነ አተነፋፈስ፣ የድምጽ ጥራት፣ ኢንቶኔሽን፣ አነጋገር፣ የድምጽ ከፍ ዝቅ የማለት እድገት እና የሙዚቃ ማንበብ ክህሎቶች አጽንዖት ተሰጥቷል። ይህን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተማሪውን ለ Symphonic ባንድ ምደባ ማዘጋጀት አለበት።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የቀድሞ ሙዚቃ መመሪያ ወይም ኦዲሽን

### የኮንሰርት ኦርኬስትራ

አንዳንድ የመጫወት ልምድ ላላቸው ተማሪዎች፣ ይህ ኮርስ ዝቅ በማድረግ፣ ጣቶችን በመጠቀም እና በጥሩ ኢንቶኔሽን እና ሪትም ሙዚቃን በማንበብ ውስጥ ያሉ ክህሎቶችን ማሻሻሉን ይቀጥላል። በዚህ ኮርስ ውስጥ ያለ ስኬት በ Symphonic ኦርኬስትራ ውስጥ ያለን ምደባ መምራት አለበት።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የቀድሞ ሙዚቃ ተሞክሮ ወይም ኦዲሽን

### ፈጣን ዝማሬ

መካከለኛ ዝማሬ የድምጽ ክህሎቶቻቸውን ለማጎልበት እና ለመፈጸም ለሚፈልጉ ብቁ ተማሪዎች ቀርቧል። ተገቢ በሆኑ የድምጽ ቴክኒኮች፣ በምት እና ዜማ የሙቅቃ ማንበብ ክህሎቶች እና የስብስብ መዝፈን እድገት ላይ አጽንዖት አለ። አባላት በክረምት እና በጸደይ ኮንሰርቶች እንዲያከናውኑ ይጠበቃል እንዲሁም በዳይሬክተሩ እንደሚወሰነው በአካባቢያዊ እና ዲስትሪክት ፌስቲቫሎች ላይ እንዲሳተፉ እድሎች ሊሰጣቸው ይችላሉ። የተከናወነ ሙዚቃ የታሪካዊ ጊዜያትን እና የሙዚቃ ዘይቤዎችን ይሸፍናል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የቀድሞ ሙዚቃ ተሞክሮ ወይም ኦዲሽን

### ሲምፎኒክ ባንድ

ተማሪዎች የተለያዩ የሙዚቃ ስነጽሁፍን ስታይሎችን በማጥናት በሙሉ ባንድ፣ የግል እና የስብስብ ዝግጅቶች ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ጥሩ ቃና፣ ደምጽን ከፍ እና ዝቅ ማድረግ፣ አነጋገር እና ዘይቤን ማጎልበት ይቀጥላሉ። የሲምፎኒክ ባንድ በት/ቤት ኮንርሰቶች እና አካባቢያዊ፣ በዲስትሪክት እና ክልላዊ ፌስቲቫሎች ውስጥ ይሳተፋል። ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የስብስብ ባንድ ፕሮግራም ለማዘጋጀት የመሰብሰብ መሰረቶች ትውውቅ ይደረግላቸዋል። አንዳንድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ቀርበዋል። ከመደበኛው የክፍል ጊዜ በተጨማሪ፣ የሲምፎኒክ ባንድ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በሳምንት አንድ ቀን ወይ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ ይለማመዳሉ። የሲምፎኒክ ባንድ ተማሪዎች በጃዝ ባንድ ውስጥ ለመሳተፍ ሊመርጡ ይችላሉ ይህም ከት/ቤት በፊት ወይም በኋላ በሳምንት አንድ ቀን ልምምድ እንዲሁ ያደርጋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የኮንሰርት ባንድ እና ኦዲሽን

**ሲምፎኒክ ኦርኬስትራ**

ኮርሱ አንድ አመት ወይም ከዚያ በላይ የስትሪንግ ጥናት ተሞክሮን በተሳካ ሁኔታ ላጠናቀቁ ተማሪዎች ጣትን እና ዝቅ ማለትን ያሉ ክህሎቶችን ለማዳበር ሲቀጥሉ በበርካታ የሙዚቃ ስታይሎች እና ጊዜያት ውስጥ ያከናውናሉ። ሙዚቃዊ ትርጉም እና የስብስብ ሙዚቃ ጫወታ ተለጥጧል እና ለህዝባዊ ክንውኖች ያሉ እድሎች ቀርበዋል። ተማሪዎች የነጠላ፣ የስብስብ እና የኦልኬስትራ ስነጽሁፍን በማጥናት የአጨዋወት ጥሩ ቃና፣ ደምጽን ከፍ እና ዝቅ ማድረግ፣ አነጋገር እና ዘይቤን ማጎልበት ይቀጥላሉ። የክፍል II እና III ስነጽሁፍን በእይታ ማንበብ ይችላሉ እንዲሁም የሙዚቃ ምልክቶችን፣ ቁልፍ ፊርማዎችን እና ቴምፖን መለየት ይችላሉ። የኦርኬስትራ አባላት በት/ቤት ኮንሰርቶች ውስጥ እና በአካባቢ እና ክልላዊ ፌስቲቫሎች ውስጥ ይሳተፋሉ። ከመደበኛው የክፍል ጊዜ በተጨማሪ፣ የሲምፎኒክ ኦርኬስትራተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በሳምንት አንድ ቀን ወይ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ ይለማመዳሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የኮንሰርት ኦርኬስትራ ወይም ኦዲሽን

# ሳይንስ

## አጠቃላይ ሳይንስ

የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ ፕሮግራም የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ለማሟላት የተነደፈ ነው። መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እና የላቀ (ኦነርስ) የትምህርት ፕሮግራም በማህበራዊ ትምህርቶች ውስጥ ይሰጣል። 6ኛ ክፍል ላይ ያለው ትኩረት በአካባቢ፣ በውሃ፣ በመሬት እና በህዋ ሳይንስ ላይ ነው። 7ኛ ክፍል ላይ፣ ተማሪዎች ከህይወት ሳይንስ ጋር በሚገናኙ ጥናቶች ላይ በህያው አለም ውስጥ ባለው ለውጥ፣ ዑደቶች፣ አካሄዶች እና ግንኙነቶች አጽንዖቶች ጋር በመሆን ይሳተፋሉ። 8ኛ ክፍል ላይ፣ የቁስ አካል፣ ፊዚክስ እና ሃይል ተፈጥሮ እና አወቃቀር ላይ ጥናት ይደረጋል። ተማሪዎች ከ 6፣ 7 እና 8ኛ ክፍል የሳይንስ ይዘትን ያካተተ አጠቃላይ የ SOL ፈተናን 8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ ይወስዳሉ።

## የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኦነርስ ፕሮግራም

ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ የመደበኛ የትምህርቶች ፕሮግራም እንደ አማራጭ፣ የላቀ ወይም ኦነርስ አማራጮች ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ይገኛል። እነዚህ ኮርሶች የታዘዙትን የ ACPS ካሪኩለም እና የቨርጂኒያ ሳይንስ SOL ይከተላሉ። እነሱ በከፍተኛ ደረጃ ለተነቃቁ ተማሪዎች ይመከራሉ። ተማሪዎች ከገሃዱ አለም ችግሮች ጋር የተገናኙ የትንሽ-ቡድን እና የግለሰብ ምርምር ፕሮጀክቶችን ለማድረግ የሙከራ ንድፍ ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የሳይንስን ሚና በህይወታቸው ላይ መገንዘባቸውን ያሳድጋሉ። እያንዳንዱ ተማሪ ወደ ት/ቤት ሳይንስ ዝግጅት እና የ ACPS የሳይንስ ዝግጅት ውስጥ ለመግባት እንዲችል የሳይንስ ፕሮጀክት ማቅረብ እና መተግበር ይጠበቅበታል።

የ Talented and Gifted (TAG) አገልግሎቶችን በሳይንስ ለመቀበል የተለዩ ተማሪዎች በአጠቃላይ ሳይንስ፣ በህይወት ሳይንስ ወይም በአካላዊ ሳይንስ የኦነርስ ክፍሎች መርሃግብር ተይዞላቸዋል። ለናሙና የሁለተኛ ደረጃ ሳይንስ የኮርስ ተከታታዮች፣ እዚህ ጋር ይመልከቱ።

**አጠቃላይ ሳይንስ 6 ወይም ኦነርስ አጠቃላይ ሳይንስ 6**

ጠቅላላ ሳይንስ የሚያተኩረው የጸሃይ ሃይል ሚና በመሬት ስርዓቶች፣ ውሃ በአካባቢ ውስጥ፣ በአየር ላይ እንዲሁም በከባቢ አየር

እንዲሁም መሰረታዊ የኬሚስትሪ ጽንሰ ሃሳቦችን ነው። ተማሪዎች በሃይል እና ቁስ አካል ለውጦች በኩል የለውጥን ሃሳብ ያስሳሉ። ትምህርቱ የጸሃይ ስርአት እና የህዋ ዳሰሳ የበለጠ ዝርዝር ግንዛቤ ላይ እንዲሁ ያተኩራል፤ የተፈጥሮ ሀብቶች አስተዳደር፣ ከህዝባዊ ፖሊሲ ጋር ያለው ግንኙነት እና የእርሱ ዋጋ/ጥቅም የንግድ ልውውጥ እና የሳይንሳዊ ዘዴ፣ መላምቶችን በመናገር ውስጥ እና የሚደገፉ እና ራሳቸውን የቻሉ ተለዋዋጮችን በመግለጽ ትክክለኛነትን አጽንዖት መስጠት። ተማሪዎች የግምቶች እና የማጠቃለያዎች ትክክለኛነትን ሙከራ ይማራሉ። ትምህርቱ በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በማድረግ ላይ ያለ ጥያቄ ላይ ያተኩራል። ሃሳቦችን የሚያረጋግጥ ወይም የሚፈታተን የሳይንሳዊ ምርምር አስፈላጊነት አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ ስለዚህ፣ ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን ለሳይንስ የዝግጅት ውድድር መግቢያ እንዲያጎለብቱ ይበረታታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

### የህይወት ሳይንስ 7 ወይም ኦነርስ የህይወት ሳይንስ 7

የህይወት ሳይንስ በተንቀሳቃሽ አለም ውስጥ ያሉትን  ለውጦች፣ ዑደቶች፣ አካሄዶች እና ግንኙነቶች የበለጠ ውስብስብ ግንዛቤ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች የህዋስ ድርጅትን እና የፍጥረታትን ክፍፍሎች፣ በፍጥረታት፣ በህዝቦች፣ በማህበረሰቦች እና በስነ-ምህዳሮች ውስጥ ያሉትን ተለዋዋጭ ግንኙነቶች፣ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፍ የዘር መረጃ ያለ ለውጥን በማሰስ ከእነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ጋር የተገናኙ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ይገነባሉ። ትምህርቱ በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በማድረግ ላይ ያለ ጥያቄ ላይ ያተኩራል። ሃሳቦችን የሚያረጋገጥ ወይም የሚፈታተን የሳይንሳዊ ምርምር አስፈላጊነትአጽንዖት ተሰጥቶታል፤ ስለዚህ፣ ተማሪዎች ለሳይንስ የዝግጅት ውድድር ለመግባት የምርምር ፕሮጀክቶችን እንዲያጎለብቱ ይበረታታሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

### አካላዊ ሳይንስ 8 ወይም ኦነርስ አካላዊ ሳይንስ 8

6ኛ እና 7ኛ ክፍል የተሰጡትን የተለዋዋጮች እና የተደጋገሙ ሙከራዎች ግልጽ ትኩረት ትምህርቶች ጋር የአካላዊ ሳይንስ ስልታዊ ምርመራ ላይ ባሉ ክህሎቶች ላይ መገንባቱን ይቀጥላል። ተማሪዎች በማስረጃ እና በውሂብ ማጠቃለያዎችን ያረጋግጣሉ። ትምህርቱ የቁስ አካል ተፈጥሮ እና መዋቅር ላይ እንዲሁም የአካላዊ ሳይንስ መርሆዎች የሚገመት አጽንዖት ጋር የሃይል ባህሪያት ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ ላይ ያተኩራል። የሚሸፈኑ ዋና አካባቢዎች የሚያካትቱት ፒሮዲሲቲ (ፐሬዲክ ቴብል)፤ አካላዊ እና ኬሚካላዊ ለውጦች፤ የኑክሌር መብላላቶች፤የሙቀት መጠን እና ሙቀት፤ ድምጽ፣ ብርሃን፣ ኤሌክትሪክ እና ማግኔጢስ፤ እና ሰራ፣ ሃይል እንዲሁም እንቅስቃሴ ናቸው። ትምህርቱ በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በማድረግ ላይ ያለ ጥያቄ ላይ ያተኩራል። ሃሳቦችን የሚያረጋግጥ ወይም የሚፈታተን የሳይንሳዊ ምርምር አስፈላጊነት አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ ስለዚህ፣ ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን ለሳይንስ የዝግጅት ውድድር መግቢያ እንዲያጎለብቱ ይበረታታሉ።

መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እና የኦነርስ የትምህርት ፕሮግራም በማህበራዊ ትምህርቶች ውስጥ ይሰጣል። የ Talented and Gifted (TAG) አገልግሎቶችን በማህበራዊ ትምህርቶች ለመቀበል የተለዩ ተማሪዎች በ U.S. ታሪክ 1፣ U.S. ታሪክ II እና ሲቪክስ እና ኢኮኖሚክስ የኦነርስ ክፍሎች መርሃግብር ተይዘላቸዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

# የማህበራዊ ትምህርቶች

መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እና የኦነርስ የትምህርት ፕሮግራም በማህበራዊ ትምህርቶች ውስጥ ይሰጣል። የ Talented and Gifted (TAG) አገልግሎቶችን በማህበራዊ ትምህርቶች ለመቀበል የተለዩ ተማሪዎች በ U.S. ታሪክ 1፣ U.S. ታሪክ II እና ሲቪክስ እና ኢኮኖሚክስ የኦነርስ ክፍሎች መርሃግብር ተይዞላቸዋል።

### ሲቪክስ እና ኢኮኖሚክስ

ይህ ኮርስ በሃገር፣ በስቴት እና በአካባቢ ደረጃዎች ያሉ የመንግስት ተቋማት አወቃቀር እና ስራቸው ላይ ያተኩራል፤ በአሜሪካ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ውስጥ የዜጋው ሚና፤ እና የአሜሪካ ኢኮኖሚ አወቃቀር እና አፈጻጸም።

ኦነርስ ኮርሶች በእያንዳንዱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ባለ ደረጃ በማህበራዊ ትምህርቶች ውስጥ ይቀርባል። የኦነርስ የማህበራዊ ትምህርቶች ካሪኩለም የታዘዘውን የ ቨርጂኒያ የማህበራዊ ትምህርቶች SOL በመከተል ከፍተኛ ይዘትን በፍጠነ እርምጃ ውስጥ ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች የራሳቸውን እና የሌሎችን አስተሳሰብ እንዲተነትኑ በከፍተኛ ደረጃ አስተሳሰብ ላይ ይታሰፋሉ እና ከፍተኛ የምክንያታዊነት እና የችግር ፈቺ ስትራቴጂዎችን ያጎለብታሉ። በመጀመሪያ ምንጭ ሰነዶች፣ በገሃዱ አለም ክስተቶች ማስመሰያዎች እና ከደረጃ በላይ ልብወለድ ያልሆኑ መርጃ መሳሪያዎች በኩል (ቅንጭብጭቦች እና መጽሃፎች)፣ ተማሪዎች ታሪካዊ፣ ጂኦግራፊያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችን በመተንተን ግንዛቤ ያላቸው እና በሲቪክ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ለመሳተፍ የተነቃቁ ዜጎች ይሆናሉ። በኦነርስ ኮርሶች የተመዘገቡት ተማሪዎች በላቀ አመዳደብ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ ላይ ለስኬታቸው አስፈላጊ ለሆነው ለ Document Based Questions (DBQs) ክህሎት ያሉ ምላሾችን ጨምሮ በተለያዩ ቅርጸቶች በልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ በሰፊው ይጽፋሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### ሲቪክስ እና ኢኮኖሚክስ ኦነርስ

ለ 8ኛ ክፍል የኦነርስ ማህበራዊ ትምህርቶች ካሪኩለም ውስጥ፣ ተማሪዎች ማህበራዊ ፖለቲካዊ፣ ህጋዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶችን በመዋቅራቸው እና ተግባሮቻቸው መሰረት ይተነትናሉ። አመቱን በሙሉ፣ ተማሪዎች እየጨመሩ ለሚሄዱ ውስብስብ DBQs ምላሽ ይሰጣሉ። ተማሪዎች ከበርካታ ምንጮች የታሰበባቸውን የዜና ርዕሶች ትንታኔ እና ግምገማ ላይ ይሳተፋሉ እና በዜናው ላይ ባሉት ርዕሶች እና በኮርስ ይዘቱ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ያሳያሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የ U.S. ታሪክ I

ይህ ኮርስ ከቅድመ-ኮሎምቢያ ዘመን እስከ 1865 ያለውን የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች የሰዎችን፣ የቦታዎችን እና የህይወት አንድ የመማር አካሂዶችን ከዩናይትድ ስቴትስ የታሪክ አምድ ውስጥ በላቁ ደረጃዎች የሲቪክ፣ ጂኦግራፊ እና ኢኮኖሚክስ ጽንሰ ሃሳቦች ያስሳሉ። ይህ ኮርስ 7ኛ ክፍል ላይ ይቀጥላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የ U.S. ታሪክ I ኦነርስ

ተማሪዎች የቀድሞ የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክን ለማጥናት እና ሁለቱን ህብረቱን ያጠነከሩበትን እና ያዳከሙበትን ሃሳቦች እና ክስተቶች በመገንዘብ የታሪካዊ እና ጂኦግራፊያዊ የትንታኔ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች በዩናይትድ ስቴትስ የታሪክ

አምድ ውስጥ በላቁ ደረጃዎች ኢ-ልብወለድ መጽሃፍን በማንበብ የሲቪክ፣ጂኦግራፊ እና ኢኮኖሚክስ ጽንሰ ሃሳቦችን ያስሳሉ። ዋና የሰነዶች ምንጮን በመጠቀም፣ ዩናይትድ ስቴትስን ቅርጽ ያስያዟትን ሰዎች እና ክስተቶች ይተነትናሉ። በኦነርስ ኮርሶች ላይ የተመዘገቡ ተማሪዎች DBQ ይተዋወቃሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

#### የ U.S. ታሪክ II

ተማሪዎች 6ኛ ክፍል የጀመረውን የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ ጥናት በመቀጠል ከ 1865 እስከ አሁን ያሉትን ዋና ዋና አዝማሚያዎች እና ክስተቶች ይመረምራሉ። Great Depression፣ ሁለተኛው የአለም ጦርነት፣ ቀዝቃዛው ጦርነት፣ የሰብዓዊ መብቶች እንቅስቃሴ እና የቬትናም ጦርነትን ጨምሮ በ 20ኛው ክፍለዘመን ክስተቶች ላይ አጽንዖት ተሰጥቷል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

#### የ U.S. ታሪክ II ኦነርስ

ተማሪዎች የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክን በ 20ኛው ክፍለዘመን ሲያጠኑ በታሪካዊ እና ጂኦግራፊያዊ ትንተናዎች ያላቸውን ክህሎቶች ማዳበር ይቀጥላሉ። በሚከተሉት የጎለበቱ ክህሎቶች ላይ ይገነባል የ U.S ታሪክ I፣ ተማሪዎች የ 19ኛው እና 20ኛው ክፍለዘመኖች መጨረሻ ላይ ያሉትን ክስተቶች በመተንተን እና በመገምገም የዩናይትድ ስቴትስ እድገት እንዴት ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ የአለም ክስተትን ቅርጽ እንዳስያዘ ሙሉ መረዳት ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች በጽሁፋቸው እና በቃል ትንታኔያቸው ውስጥ የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ ሰነዶችን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በየሩቡ አመት ለበለጠ ከፍተኛ DBQዎች ምላሽ ይሰጣሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# የቴክኖሎጂ ትምህርት

#### የቴክኖሎጂ መግቢያ

ተማሪዎች መሳሪያዎችን፣ ጉልበትን፣ እቃዎችን፣ ሰዎችን፣ ጊዜን፣ መረጃን እና ስርዓቶችን በማካተት የሁሉንም ቴክኖሎጂ ግብአቶች ይማራሉ። እየመጡ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት እና የወደፊት የቴክኖሎጂ ለውጦችን በመገመት የቴክኖሎጂን ተጽዕኖ ይመረምራሉ። የችግር ፈቺ ሂደቱ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እና ተማሪዎች በመለካት፣ በመሳል እና መሰረታዊ የእጅ መሳሪያ መተግበሪያ ክህሎቶችን በመጠቀም ተማሪዎች አነስተኛ ምርቶችን ያመርታሉ። እንዲሁም እነሱ ኮምፒውተሮችን በመጠቀም ሮኬተሪን፣ ህዋን፣ ሮቦቲክስ እና ሌላ የቴክኖሎጂ አይነቶችን ለመዳሰስ ቡድኖች ሆነው ይሰራሉ። **የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

#### ፈጠራዎች እና ልዩ ስራዎች

ተማሪዎች ፈጠራዎችን እና አድዲስ ግኝቶችን ያስሳሉ እና እነሱ እንዴት ከአዳዲስ ምርቶች፣ ሂደቶች እና ስርአቶች ጋር እንደሚገናኙ ያስረዳሉ። እነዚህን እድገቶች ከተማሩ በኋላ፣ እነሱ፣ ማህበረሰባቸው ወይም አለም ያጋጠሟቸውን ወቅታዊ የቴክኖሎጂ ችግሮች ያስሳሉ እና የንድፍ ሂደትን በመተግበር አዳዲስ ምርቶችን እና ፈጠራዎችን እንደ መፍትሄ ለማጎልበት ስልታዊ ሂደቶችን ይተገብራሉ። ተማሪዎች ሞዴል ወይም ፕሮቶታይፕ ይገነባሉ እንዲሁም በምዘና ወይም በፕሮቶታይፑ ሙከራ በኩል ሞዴሉን ይገመግማሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7

**ርዝመት፦** አንድ ሴሚስተር

**ቴክኖሎጂያዊ ስርአቶች**

በአለም አቀፍ የቴክኖሎጂ እይታ ውስጥ፣ ተማሪዎች ቴክኖሎጂያዊ ስርአቶች እንዴት እንደሚሰሩ በአጠቃላይ በማግኘት ስርአቶችን ለመፍጠር ግብአቶችን እና ቴክኒኮችን ያጣምራሉ። ተማሪዎች የቴክኖሎጂያዊ ስርአቶችን ያስሳሉ፣ ይነድፋሉ፣ ይተነትናሉ እንዲሁም ይገመግማሉ። ስርአቶችን በማነቃቃት እና ተጽዕኗቸውን በመገምገም፣ ተማሪዎች የቴክኖሎጂያዊ ዓለምን ችግሮች እና እድሎች እንዴት እንደሚቀርቡ እይታዎችን ያገኛሉ። እንዲሁም እነርሱ ቲቴክኖሎጂ የታገዙ ስራዎችን ያስሳሉ። ተማሪዎች አንድ ችግር ለመፍታት የተወሰኑ ቴክኖሎጂያዊ ስርአቶችን (መረጃ፣ ግንኙነት፣ ኮንስትራክሽን፣ መጉጓዣ፣ ጉልበት እና ኀይል ወይም ባዮቴክኖሎጂ) ይነድፋሉ። ፕሮጀክቶች የሚያካትቱት የፎቶግራፍ ፖርትፎሊዮዎች፣ የቪዲዮ ፕሮዳክሽኖች፣ ማግኔታዊ የማንሻ መኪናዎች፣ ስልኮች እና የኮንስትራክሽን ሞዴሎችን ነው።

ሁሉም ኮርሶች አንድ ሙሉ አመት ናቸው። ተማሪዎች በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ አመት ቆይታቸው ስለአለም ቋንቋዎች ጥናት እንዲጀምሩ እና እንዲቀጥሉ በጥብቅ ይበረታታሉ። ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የአለም ቋንቋዎችን በሰስት፣ በአራት ወይም በአምስት አመት ትምህርት ውስጥ ለጨረሱ አመልካቾች በተሻለ ሁኔታ ይመለከቷቸዋል። ተማሪዎች የአለም ቋንቋን (ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ላቲን፣ እና ስፓኒሽ) ለመማር የተለያዩ እድሎችን ያገኛሉ፤

በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ውስጥ የተወሰደ ማንኛዉም የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የያዘ ኮርስ ውጤቶች ከተማሪው ትራንስክሪፕት ውስጥ እንዲቀር እና ተማሪው ለኮርሱ የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት ወይም የተረጋገጠ ክሬዲት እንዳያገኝ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከሌላ ት/ቤት ክፍሎች ወደ ACPS ለተላለፉ ተማሪዎች፣ ተገቢ የሆነ የጅማሬ ቋንቋ ምደባ ብቁ የሆነ ምዝገባ በመጠባበቅ ላይ ሆኖ ይቀርባል።

- እየመጡ ያሉ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች 6ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋን መማር ሊጀምሩ ይችላሉ እና የተመሳሳይ ቋንቋ ሰስት አመት ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ተማሪው ስድስተኛ ክፍል ላይ ሌላ ትምህርት ለማጥናት እንዲሁ ሊመርጥ ይችላል እና 7ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋ ትምህርትን ሊጀምር ይችላል፣ ይህም የዚህን ኮርስ ሁለት አመታት ጥናት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቀ በኋላ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያገኛል።
- የዚህን ኮርስ የሁለት አመት ትምህርት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ እየመጡ ያሉ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።
- በአለም ቋንቋ ትምህርት ቀድሞውኑ የተመዘገቡ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲትን ለማግኘት የሁለተኛ አመት ትምህርትን መቀጠል አለባቸው። የአለም ቋንቋ ትምህርታቸውን እስካሁን ያልጀመሩ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በስምንተኛ ክፍል አመት ውስጥ የስፓኒሽ I በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 8

**ርዝመት፦** አንድ ሴሚስተር

# ቲያትር

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

**ንግግር እና ቲያትር I**

ንግግር እና ቲያትር I የቲያትራዊ ጥናት ፕሮዳክሽን፣ የቲያትር ታሪክን እና ድራማዊ የስነጽሁፍ መግቢያን ለተማሪዎች ለማቅረብ የተነደፈ ነው። በምርምር፣ በእቅድ አወጣጥ፣ በስክሪፕቲንግ፣ በፕሮዳክሽን እና በአፈጻጸም ተሞክሮዎች በኩል፣ ተማሪዎች ሃሳቦችን ለመገናኘት፣ ለጥልቅ አስተሳሰብ እና ለትብብር የችግር አፈታት ያሉ ክህሎቶችን ያገኛሉ። ይህ ኮርስ ለበለጠ የቲያትራዊ ትምህርት ተማሪዎችን በማዘጋጀት ለበርካታ የቲያትር አይነቶች አድናቆትን ይሰጣል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ንግግር እና ቲያትር II**

ተማሪዎች መሰረታዊ የቲያትር ክህሎቶችን ይማራሉ። ኮርሱ የሚያካትተው በቲያትር ታሪክ ላይ ያሉ ክፍሎች እንዲሁም ተከታዮቹ ክፍሎች በትወና ክህሎቶች ላይ ነው፤ የአንድን ድምጽ፣ አካል፣ እና ምናብ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል መማር፤ የትወናዎች መዋቅር እና አተዋወናቸው፤ እና የ መድረክ አካባቢ። ተማሪዎች ቲያትር እንዴት ሕይወትን እንደሚያንጸባርቅ ይማራሉ እንዲሁም ለቲያትር ትምህርት የግል ስነስርአትን ያጎለብታሉ። የንግግር እና ቲያትር I ን 6ኛ ክፍል ላይ ማጠናቀቅ ለዚህ ክፍል ቅድመ ሁኔታ አይደለም።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ንግግር እና ቲያትር III**

ተማሪዎች በዳይሬክቲንግ፣ የትወና ጽሁፍ እና የቲያትርን ቴክኒካል አካላት በመማር ባሉ ክፍሎች በኩል የቲያትር ፕሮዳክሽንን በመመርመር ማሰሳቸውን ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በማህበረሰብ ውስጥ እንዲሁም ለስራዎች እንደ መግቢያ ያለ ቲያትርን እንዲሁ ያስሳሉ። የንግግር ክፍል የቃል- ግንኙነት ክህሎቶችን ለማሻሻል ይጠቅማል። ተማሪዎች በርካታ ውጤታማ አቀራረቦችን እንዴት መገንባት እና ማቅረብ እንደሚቻል ይማራሉ። የንግግር እና ቲያትር I ን 6ኛ ክፍል ላይ እና የንግግር እና ቲያትር II ን 7ኛ ክፍል ላይ ማጠናቀቅ ለዚህ ክፍል ቅድመ ሁኔታዎች አይደሉም።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

# ምስላዊ ስነጥበብ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

**ስነጥበብ 7**

ተማሪዎች ባለሁለት አቅጣጫ፣ ባለሶስት አቅጣጫ እና የግራፊክ አርትስ/መልቲሚዲያ ምስላዊ ስነጥበባትን ይማራሉ። ተማሪዎች የፈጠራ አገላለጽ እና ሃሳቦችን እንዲሁም ስሜቶችን ለማገናኘት ችግር ፈቺ ክህሎቶችን በመተግበር አጽንዖት የሚሰጡ የስነጥበብ ስልቶችን ሙከራ ያደርጋሉ። በሁሉም እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ ትምህርቱ የስነጥበብ አካላትን እና የንድፍ መርሆዎች ላይ አስፍተው ያስተምራሉ። ተማሪዎች የስነጥበብ ታሪክን ባህላዊ አውድ ይማራሉ እና ሌላ የእውቀት መስኮችን የማከለ ፕሮጀክት ያጠናቅቃሉ። ተገቢ የስነጥበብ የቃላት ስብስብን እና የራሳቸውን የህይወት ተሞክሮዎች

በመጠቀም ተማሪዎች ስነጥበብን ይገመግማሉ እንዲሁም ይተነትናሉ እንዲሁም የስነጥበብ ሙያዎችን ይዳስሳሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ስነጥበብ 8**

ልዩ ባለ ሁለት አቅጣጫ፣ ሶስት አቅጣጫ እና ግራፊክ አርትስ/መልቲሚዲያ ኮርሶች 8ኛ ክፍል ላይ ይሰጣሉ። በእያንዳንዱ አካባቢ ካለው ሚዲያ እና ቴክኒኮች ትምህርት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ስነጥበብን እንዴት ትችት እንደሚያቀርቡበት እና በታሪክ ውስጥ ስለበርካታ አርቲስቶች እንደሚያጠኑ ይማራሉ። ተማሪዎች የራሳቸውን የአርቲስቲክ ግንዛቤ ሲያጎለብቱ እና በህይወት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ነገሮችን በአዲስ አይነት እይታ ሲመለከቱ፣ ውበት አጽንዖት ይሰጠዋል። የሙሉ አመት የስነጥበብ ተማሪዎች በትላልቅ ደረጃ ፕሮጀክቶች ውስጥ በት/ቤቱ ውብ አካባቢን ለመፍጠር ይሳተፋሉ። ስለ ስነጥበብ ስራዎች ይማራሉ እና ፖርትፎሊዮዎችን እና የስዕል መጽሃፎችን ሁለቱንም ይይዛሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ስነጥበብ 8A**

ይህ ኮርስ ጠንካራ የስነጥበብ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የታለመ ነው። ተማሪዎች በበርካታ የስነጥበብ ሚዲያ በኩል የንድፍ ስሱ እና ውስብስብነትን ያጎለብታሉ። ፈጠራ በባለሁለት እና በባለሶስት አቅጣጫ ስነጥበብ፣ በመልቲሚዲያ ቴክኖሎጂ እና ንድፍ ውስጥ ካሉ ትምህርቶች ጋር ይበረታታል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 8

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

**ምስላዊ ስነጥበብ 6**

ለ6ኛ ክፍል  የዝውውር ጊዜ ውስጥ፣ ተማሪዎች ሃሳቦችን ይገልጻሉ እና ምስሎችን በበርካታ ሚዲያ በንድፍ መርሆዎች ይፈጥራሉ። ተማሪዎች የስነጥበብ ቴክኒኮችን ይለማመዳሉ እና የስነጥበብ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች በደንብ የታወቁ የስነጥበብ ስራዎችን እንዲሁ ይተነትናሉ፣ ይተረጉማሉ እንዲሁም ይገመግማሉ። ኮርሱ ዋና  የስነጥበብ እንቅስቃሴዎችን እና ስታይሎችን፣ ግብዓቶችን፣ ዘዴዎችን እና የግለሰብ አርቲስቶቹን ርዕሰ ጉዳይ ጨምሮ የስነጥበብ ታሪክን እንዲሁ ይሸፍናል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6

**ርዝመት፡-** አንድ ሴሚስተር

# የአለም ቋንቋዎች

ሁሉም የአለም ቋንቋ ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ። ሁሉም ኮርሶች አንድ ሙሉ አመት ናቸው። ተማሪዎች በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቆይታቸው የአለም ቋንቋዎችን ለመጀመር ወይም ለመቀጠል በደንብ ይበረታታሉ። ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የአለም ቋንቋዎችን በሶስት፣ በአራት ወይም በአምስት አመት ትምህርት ውስጥ ለጨረሱ አመልካቾች በተሻለ ሁኔታ ይመለከቷቸዋል። ተማሪዎች የአለም ቋንቋን (ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ላቲን፣ እና ስፓኒሽ) ለመማር የተለያዩ እድሎችን ያገኛሉ፤

- እየመጡ ያሉ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች 6ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋን መማር ሊጀምሩ ይችላሉ እና የተመሳሳይ ቋንቋ ሶስት አመት ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ተማሪው ስድስተኛ ክፍል ላይ ሌላ ትምህርት ለማጥናት እንዲሁ ሊመርጥ ይችላል እና 7ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋ ትምህርትን ሊጀምር ይችላል፣ ይህም የዚህን ኮርስ ሁለት

አመታት ጥናት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቀ በኋላ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያገኛል።

- የዚህን ኮርስ የሁለት አመት ትምህርት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ እየመጡ ያሉ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።
- በአለም ቋንቋ ትምህርት ቀድሞውኑ የተመዘገቡ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲትን ለማግኘት የሁለተኛ አመት ትምህርትን መቀጠል አለባቸው። የአለም ቋንቋ ትምህርታቸውን እስካሁን ያልጀመሩ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በስምንተኛ ክፍል አመት ውስጥ የስፓኒሽ I በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።

በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ውስጥ የተወሰደ ማንኛዉም የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የያዘ ኮርስ ውጤቶች ከተማሪው ትራንስክሪፕት ውስጥ እንዲቀር እና ተማሪው ለኮርሱ የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት ወይም የተረጋገጠ ክሬዲት እንዳያገኝ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከሌላ ት/ቤት ክፍሎች ወደ ACPS ለተላለፉ ተማሪዎች፣ ተገቢ የሆነ የጅማሬ ቋንቋ ምደባ ብቁ የሆነ ምዝገባ በመጠባበቅ ላይ ሆኖ ይቀርባል።

**የአለም ቋንቋ ክሬዲት በፈተና**

ከስድስተኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ከእንግሊዝኛ ውጪ በሆኑ ቋንቋዎች መረዳት እና መግባባት ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች ለአለም ቋንቋዎች እስከ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን የማግኘት እድል አሁን አላቸው። መመዘኛዎች የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ ከ 100 በሆኑ ቋንቋዎች ይገኛሉ። የአለም ቋንቋ ክሬዲት በፈተና የሚለው በአመት አንድ ጊዜ በመኸር ወቅት ይቀርባል። ለበለጠ መረጃ እባክዎ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ት/ቤቶችን ድረገጽ በ www.acps.k12.va.us/worldlanguagecreditላይ መጎብኘት ይችላሉ።

**ቻይንኛ IA**

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች በተግባራዊ ስራዎች በኩል የማንድሪያን ቻይንኛ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡ፣ እንዲጽፉ እና እንዲረዱ የሚያስችላቸውን ችሎታ ያጎለብታሉ። በኢላማው ቋንቋ የግንኙነት ክህሎቶችን ማጎልበት አጽንዖት ተሰጥቶታል። በኮርሱ መጨረሻ፣ ተማሪዎች ስለቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ቀናቸው፣ ጊዜያቸው፣ የአየር ጸባይ፣ የት/ቤት ህይወት እና ጉዞን በተመለከተ ዝርዝር ውይይት ማድረግ ይገባቸዋል።
የቀለለ የቻይንኛ ቁምፊዎችን (በሜይንላንድ ቻይና ጥቅም ላይ ያለው) በመጠቀም ተማሪዎች 150 ቁምፊዎችን ማንበብ እና መጻፍ ይማራሉ። **የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5
**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7
**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቻይንኛ IB**

ተማሪዎች ስለራሳቸው እና በአቅራቢያቸው ስላለ አካባቢ የመገናኘት ችሎታን መሰረታዊ የቋንቋ መዋቅሮችን በያዙ ቀላል አርፍተነገሮች በመጠቀም ማጎልበታቸውን ይቀጥላሉ። ይህ ግንኙነት በሁሉም አራቱም የቋንቋ ክህሎቶች፡- ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ በመረጃ ተደግፏል። ተማሪዎች በቃል የሚግባቡበት ችሎታ እና አጻጻፍ እድገት የኮርሱ ትኩረት ሆኖ ይቆያል። ተማሪዎች ከግል እና ከቤተሰብ ህይወት፣ ከት/ቤት እና ከማህበረሰብ ህይወት ጋር የተገናኙ የትምህርት ጭብጦችን መፈተሽ እና መማር ይቀጥላሉ። በኮርሱ መጨረሻ፣ ተማሪዎች የ 300 የቻይንኛ ቁምፊዎች በቀላል የአረፍተነገር መዋቅሮች ውስጥ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ ጋር ሰፊ እውቀት ኖሯቸዋል።
**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5
**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7, 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቻይንኛ IA

**ፈረንሳይኛ IA**

ተማሪዎች መሰረታዊ መዝገበ ቃላትን እና የቋንቋ መዋቅሮችን ለእለት ተእለት ሁኔታዎች ይማራሉ። ይህ ኮርስ ከባህል ጋር ያለውን ግንኙነት አስፍቶ ያያል ይህም ተጨማሪ ነገሮችን እና አግባብነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች በመጠቀም ቋንቋውን ትክክለኛ በሆነ አካሄድ ለማቅረብ ያስችላል። ተማሪዎች ባገኙት የባህል እውቀት እና የአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፦ መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ መጻፍ የእድገት እና አፈጻጸም በኩል የቋንቋ ብቃትን ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6, 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ፈረንሳይኛ IB**

ተማሪዎች የፈረንሳይኛ ቋንቋ እና ባህል ጥናትን፣ ለዕለት ተዕለት ሁኔታዎች አስፈላጊ የሆኑ የቃላት ስብስብ እና አወቃቀሮችን በመማር ይቀጥላሉ። የመዝገበ ቃላት እና ሰዋሰው መዋቅሮች በእውነተኛ የህይወት አውዶች ቀርቧል እና በተለዩ የግንኙነት ስራዎች ዙሪያ ጎልብቷል። እንደ ቤተሰብ፣ ከት/ቤት በኋላ ያሉ እንቅስቃሴዎች እና ሱቆችን የመሳሰሉ በወጣቶች ህይወት፣ ፍላጎቶች እና ተሞክሮዎች ላይ ያተኮሩ ርዕሶች በመመሪያው ውስጥ ተካትተዋል እንዲሁም ከኢላማ ባህል በመነሳት ምርቶች እና ልምዶች ተወስደዋል። በቋንቋ-መማር ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ እንዴት እንደሚዋቀር፣ እንዲሁም የባህል እና የቋንቋ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ የመረዳት እይታዎችን ያገኛሉ። ተማሪዎች እንዲሁ ከትምህርት ክፍል ውጪ ላሉ ለበርካታ የመዝናኛ፣ ትምህርታዊ እና የስራ ፈረንሳይኛ ጠቀሜታዎች አድናቆትን አሳድገዋል። ይህ ኮርስ ከባህል ጋር ያለውን ግንኙነት አስፍቶ ያያል ይህም ተጨማሪ ነገሮችን እና አግባብነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች በመጠቀም ቋንቋውን ትክክለኛ በሆነ አካሄድ ለማቅረብ ያስችላል። ተማሪዎች ባገኙት የባህል እውቀት እና የአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፦ መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ መጻፍ የእድገት እና አጠቃቀም በኩል የቋንቋ ብቃትን ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 7, 8

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ፈረንሳይኛ IA

**ጀርመንኛ IA**

ተማሪዎች መሰረታዊ መዝገበ ቃላትን እና የቋንቋ መዋቅሮችን ለእለት ተእለት ሁኔታዎች ይማራሉ። ይህ ኮርስ ከባህል ጋር ያለውን ግንኙነት አስፍቶ ያያል ይህም ተጨማሪ ነገሮችን እና አግባብነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች በመጠቀም ቋንቋውን ትክክለኛ በሆነ አካሄድ ለማቅረብ ያስችላል። ተማሪዎች ባገኙት የባህል እውቀት እና የአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፦ መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ መጻፍ የእድገት እና አጠቃቀም በኩል የቋንቋ ብቃትን ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 6, 7

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ጀርመንኛ IB**

ደረጃ I ጀርመንኛ በንግግር ብቃት እድገት እና የጀርመን ተናጋሪ ባህሎች ውስጥ ያለውን መረዳት ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች በመስማት፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ ውስጥ ያሉ ጎራዎች

ውስጥ ጠንካራ እና አጠቃላይ መሰረት ይገነባሉ። የመዝገበ ቃላት እና ሰዋሰው መዋቅሮች በእውነተኛ የህይወት አውዶች ቀርቧል እና በተለዩ የግንኙነት ስራዎች ዙሪያ ጎልብቷል። እንደ ቤተሰብ፣ ከት/ቤት በኋላ ያሉ እንቅስቃሴዎች እና ሱቆችን የመሰሰሉ በወጣቶች ህይወት፣ ፍላጎቶች እና ተሞክሮዎች ላይ ያተኮሩ ርዕሶች በመመሪያው ውስጥ ተካትተዋል እንዲሁም ከኢላማ ባህል በመነሳት ምርቶች እና ልምዶች ተወስደዋል። በቋንቋ-መማር ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ እንዴት እንደሚዋቀር፣ እንዲሁም የባህል እና የቋንቋ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ የመረዳት እይታዎችን ያገኛሉ። ተማሪዎች እንዲሁ ከትምህርት ክፍል ውጪ ላሉ ለበርካታ የመዝናኛ፣ ትምህርታዊ እና የስራ ጀርመንኛ ጠቀሜታዎች አድናቆትን አሳድገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ጀርመንኛ IA

### ላቲን IA

ተማሪዎች መሰረታዊ መዝገበ ቃላትን እና የቋንቋ መዋቅሮችን በጥንታዊ ሮም ውስጥ  ያለውን ህይወት ለመረዳት ይማራሉ። ይህ ኮርስ ከባህል ጋር ያለውን ግንኙነት አስፍቶ ያያል ይህም ተጨማሪ ነገሮችን እና አግባብነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች በመጠቀም ቋንቋውን ትክክለኛ በሆነ አካሄድ ለማቅረብ ያስችላል። ተማሪዎች የቋንቋ ብቃትን በዋነኛነት የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎቶችን በማጎልበት እንዲሁም ባህላዊ እውቀትን በማካበት ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### ላቲን IB

ተማሪዎች የግንኙነት ብቃት እድገትን እና የሮም ባህል ግንዛቤያቸው ላይ አተኩረው ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በመስማት፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ በኩል ያሉ ጎራዎች ውስጥ ጠንካራ እና አጠቃላይ መሰረት ይገነባሉ።

የመዝገበ ቃላት እና ሰዋሰው መዋቅሮች በታሪካዊ እና በእውነታው ህይወት አውድ ውስጥ ቀርቧል እና በተወሰኑ የግንኙነት ስራዎች ዙሪያ አድገዋል። በታሪክ፣ በባህል፣ በስነጽሁፍ እና በእለት ተእለት ህይወት ላይ ያተኮሩ ርዕሶች በመመሪያው ውስጥ ተካትተዋል እንዲሁም ከኢላማ ባህል በመነሳት ምርቶች እና ልምዶች ተወስደዋል። በቋንቋ-መማር ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ እንዴት እንደሚዋቀር፣ እንዲሁም የባህል እና የቋንቋ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ የመረዳት እይታዎችን ያገኛሉ። ተማሪዎች እንዲሁ ከትምህርት ክፍል ውጪ ላሉ ለበርካታ የመዝናኛ፣ ትምህርታዊ እና የስራ የላቲን ጠቀሜታዎች አድናቆትን አሳድገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ላቲን IA

### ስፓኒሽ IA

ተማሪዎች መሰረታዊ የቃላት ስብስብ እና የቋንቋ መዋቅሮችን ለዕለት ተዕለት ሁኔታዎች በማግኘት የስፓኒሽ ጥናታቸውን ይጀምራሉ። ይህ ኮርስ ከባህል ጋር ያለውን ግንኙነት አስፍቶ ያያል ይህም ተጨማሪ ነገሮችን እና አግባብነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች በመጠቀም ቋንቋውን ትክክለኛ በሆነ አካሄድ ለማቅረብ ያስችላል። ተማሪዎች ባገኙት የባህል እውቀት እና የአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፡- መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ መጻፍ እድገት በኩል የቋንቋ ብቃትን ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### ስፓኒሽ IB

ተማሪዎች የስፓኒሽ ቋንቋ ጥናትን፣ ለዕለት ተዕለት ሁኔታዎች አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ የቃላት ስብስብ እና የቋንቋ አወቃቀሮችን በመማር ይቀጥላሉ። ይህ ኮርስ በንግግር ክህሎቶች እድገት እንዲሁም የባህላዊ እውቀት መስፋፋት ላይ አጽንዖት በመስጠት በርካታ ረጂ መሳሪያዎችን እና አግባብ የሆኑ የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎችን በመጠቀም ቋንቋውን በእውነተኛ አካሄድ ያሳያል። ተማሪዎች ባገኙት የአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፡- መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ መጻፍ የእድገት እና አፈጻጸም በኩል የቋንቋ ብቃትን ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ IA

### ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች IA

ይህ ኮርስ ስፓኒሽ በቃላቸው ብቁ ሆነው ለሚናገሩ ነገር ግን ከተወሰነ ደረጃ እስካለመቻል የደረሰ የንባብ እና የመጻፍ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የቋንቋውን የአወቃቀር እና የጽሁፍ ገጽታዎች ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ አጽንዖት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች የጽሁፍ ጥንቅሮች ማጎልበት ይጀምራሉ እና ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች ጋር ይተዋወቃሉ። ተማሪዎች እንዲሁ በሂስፓኒክ ባህል መካከል ያሉትን ልዩነቶች እና ተመሳሳይነቶች ያላቸውን ግንዛቤ እና አድናቆት ይጨምራሉ። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ ተማሪዎች ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች II ወደሚለው ሊያድጉ ይችላሉ። ስፓኒሽ በክፍል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 6, 7

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በስፓኒሽ ንግግር ላይ የቃል ብቃት እንዲሁም ስፓኒሽ ማንበብ እና መጻፍ ላይ ያለ የተወሰነ ብቃት። በምደባ ሙከራ የሚታወቅ ብቃት።

### ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች IB

ይህ ኮርስ የስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች IA ቀጣይ ነው እና የተነደፈውም ስፓኒሽን በቃል ብቁ ለሆኑ ነገር ግን ውስን የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የቋንቋውን የአወቃቀር እና የጽሁፍ ገጽታዎች ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ አጽንዖት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች የጽሁፍ ጥንቅሮች ማጎልበት ይጀምራሉ እና ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች ጋር ይተዋወቃሉ። ተማሪዎች እንዲሁ በሂስፓኒክ ባህል መካከል ያሉትን ልዩነቶች እና ተመሳሳይነቶች ያላቸውን ግንዛቤ እና አድናቆት ይጨምራሉ። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ ተማሪዎች ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች II ወደሚለው ሊያድጉ ይችላሉ። ስፓኒሽ በክፍል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 7, 8

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች IA ወይም በንግግር ስፓኒሽ የቃል ብቃት እና በመሰረታዊ ስፓኒሽ የማንበብ እና የመጻፍ ብቃት በስኬት ማጠናቀቅ። በምደባ ሙከራ የሚታወቅ ብቃት።

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶች

## የአካዳሚክ ድጋፍ ኮርሶች

**የህይወት ክህሎቶች**

ይህ ኮርስ ጤና እና አመጋገብ፣ የስራ ዝግጅት፣ የቤት ጥገና እና የማህበረሰብ አሰሳን ጨምሮ በእኛ ዋና አካባቢዎች ላይ ያተኩራል። የሚሸፈኑ ጽንሰሃሳቦች የሚያካትቱት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተወሰኑት መሰረታዊ ጤና እና ስለአለም ግንዛቤ፣ የቅጥር ባህሪያትን ማጠናከር፣ የሜኑ እቅድ ማውጣት፣ የምግብ ዝግጅት እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን መመስረትን ነው። ይህ ኮርስ ለክሬዲት ከአንድ በላይ ጊዜ ሊወሰድ ይችላል።

ራሱን የቻለ አኗኗር እና ተግባራዊ ክህሎቶችን ለማግኘት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ፕሮግራሚንግ ከአካል ጉዳት ጋር ለሚኖሩ ተማሪዎች እንደ አጠቃላይ የአካዳሚክ ፕሮግራም አካል በመሆን ቀርቧል። የአካዳሚክ እና የተግባራዊ ክህሎቶች የመጡት ለሁሉም ተማሪዎች ከቀረቡት ደረጃዎች ዋና ካሪኩለም ጋር አብረው ከተሰለፉት ነው።

የ Virginia Alternative Assessment Program (VAAP) የሚደግፈውን በእነርሱ የ Individualized Education Programs (IEPs) እና የተሰለፉ የትምህርት ደረጃዎች ላይ በተዘረዘሩት በሁሉም የሚፈለግ አካባቢ ተማሪዎች የተለየ መመሪያ እንዳገኙ ለማረግገጥ የተለየ መመሪያ ቀርቧል። እነዚህ ክፍሎች ለተማሪዎች እንደ ግንኙነት፣ ህብረት፣ መርሃግብርን መከተል፣ ችግር መፍታት፣ የራስ ተነሳሽነት እና ራስን የቻን አኗኗርን የመሳሰሉ በማህበረሰብ እና በወደፊት የስራ ቦታ ውስጥ ለስኬት አስፈላጊ የሆኑ ስኬቶችን የመለማመድ እድሎችን ይሰጣል። ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎች በተማሪዎች IEPs ውስጥ ካሉት የመተላለፊያ እቅዶች ጋር አብረው የሚሄዱ ራሳቸውን የቻሉ የአኗኗር ክህሎቶችን በመማር እና በመተግበር እድሎች ይሰጧቸዋል። ትምህርቱ በአጠቃላይ ትምህርት ወይም በተለየ የትምህርት ክፍሎች ይቀርባል። የመገናኛ እና ሌላ ክህሎቶችን ለመጠቀም ያሉ ተጨማሪ እድሎች በስራ ናሙና አወሳሰድ እና ኢንተርንሺፕ በኩል በማህበረሰቡ ውስጥ ቀርበዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ተማሪ በስራ መዘጋጃ ካሪኩለም መሳተፍ አለበት።

**አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች የጓደኛ ማማከር**

የጓደኛ ማማከር ጠቅላላ የትምህርት ተማሪዎች ስለበርካታ የአካል ጉዳቶች እንዲገነዘቡ የሚያስችላቸው፣ ከአካል ጉዳት ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ለመሟገት ስለመማር እንዲሁም በት/ቤታችን በትንሽ ቡድን ውስጥ ከተማሪዎች ጋር በክፍል ውስጥ መስተጋብር ስለመፍጠር ያለ ኮርስ ነው። የጓደኛ አማካሪዎች በእለታዊ አኗኗር፣ በማህበራዊ፣ አካዳሚያዊ፣ ሙያዊ እና ማህበራዊ ክህሎቶች እርዳታ ለመስጠት ሃላፊነት ይወስዳሉ። እንደ ጓደኛ አማካሪዎች፣ ተማሪዎች በበርካታ አወቃቀሮች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያሉትን አካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች እንዴት መምራት እንደሚቻል ይማራሉ፣ እንደ ተሟጋቾች፣ የጓደኛ አማካሪዎች ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ሰዎች ከግምት ውስጥ የማስገባት አንድ አይነት መብት እንዳላቸው እና ሁሉም ሰዎች የተሰጣቸው እንደሆነ በማክበር ምሳሌ ይሆናሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ለአካዳሚክ አላማዎች ያለ ግብአት (RAP)**

በ Resource for Academic Purposes (RAP) ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በትንሽ የቡድን ይዘት መመሪያ ትምህርቶች ውስጥ በአጠቃላይ የትምህርት ይዘት ክፍሎቹ ጊዜ በይዘቱ ከመሳተፍ

አስቀድሞ የቃላት ስብስብ፣ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ክህሎቶች እና የኢላማ ይዘትን የፊት ማከማቻ መረጃ ቅድሚያ የሚያስተምሩት ላይ ይሳተፋሉ። በዋና የይዘት ክፍሎች ውስጥ ባለ ለውጥ ላይ በመመስረት፣ ተማሪዎች የተማሪ ፍላጎቶችን ለመፍታት የዳግም ማስተማር እድሎች እንዲሁ ይኖሯቸዋል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የተሻሻሉ ተግባራዊ የሚሆኑ ተንቀሳቃሽ ክህሎቶችን እያጎለበቱ ውጤታማ የመማር ስትራቴጂዎችን ያውቃሉ እንዲሁም ይተገብራሉ። በ RAP ክፍል ያለው ምደባ በ IEP ሂደት ውስጥ የትምህርት ቤቱን ሰራተኛ እና ወላጆችን በትብብር የውሳኔ ማድረግ ሂደት ውስጥ በማካተት ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

### የማህበራዊ ክህሎቶች - ኦቲዝም

ይህ ኮርስ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ተንቀሳቃሽ የኦቲዝም ወይም የአስፐርገር ሲንድረም ላለባቸው ተማሪዎች ፍላጎት የድርጅታዊ እና ማህበራዊ ክህሎቶች እጥረትን በመቅረፍ ለማሟላት የተነደፈ ነው። ኮርሱ የግላዊ ችግር መፍቻ እና ማህበራዊ ግንኙነት ያላቸው ክህሎቶች ማሳደግ ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው እና ከባለስልጣን አካላት ጋር ያሉትን ማህበራዊ መስተጋብሮቻቸውን መረዳት ለማሳደግ እና ለማብቃት ወደምርቃት ሲደርሱ በበርካታ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

### የማህበራዊ ክህሎቶች - ስሜታዊ ጉዳት

የማስተማሪያ ፕሮግራሙ ዋና ነገር የክህሎት ማሰራጫት ሞዴል ነው። ይህ በምርምር ላይ የተመረኮዘ ፕሮግራም ተማሪዎች ከእርስ በእርስ ግጭቶች ጋር ያለውን ብቃት ለማጎልበት፣ ራስን መቆጣጠር ለመጠቀም መማር እና ለአወንታዊ የክፍል ሁኔታ አስተዋጽዖ ለማድረግ እንዲረዳ የተነደፈ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

### አካዳሚያዊ ስኬት

ይህ ኮርስ በወሰኝ ድርጅት ውስጥ የተማሪን እድገት እና ክህሎቶችን፣ የግብ እቅዶችን እንዲሁም ዋና የክፍል ይዘት ብቃትን ለመደገፍ የተነደፈ ነው። ተማሪዎች ራሱን የቻለ የጊዜ አጠቃቀም፣ የስራ ማጠናቀቅ እና የራስ ሙግት ክህሎቶችን በመጨመር ለአካዳሚያቸው እና ለድህረ ምረቃ እቅዶቻቸው የሃላፊነት ግምታቸውን ጨምረው በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

እንደ IEP አገልግሎት (90 ደቂቃዎች 5x በሳምንት ሁለቴ‹ ጥናት እና ድርጅት) ሆኖ መጻፍ አለበት

# በአካዳሚ የተወሰኑ ኮርሶች

**STEM አሰሳዎች I**

ይህ ልምድ ያለው ኮርስ ተማሪዎች በእውነተኛው አለም የምህንድስና እና የቴክኖሎጂ ችግሮች እንዲሁም አካባቢያቸው፣ ስቴታቸው፣ ሃገራቸው እና አለም አቀፍ ማህበረሰባቸው ላይ ተጽዕኖ በሚያደርግ መልኩ ወደውስጥ ያስገባቸዋል። ኮርሱ በትክክለኛ ሳይንቲስቶች፣ መሃንዲሶች፣ የቴክኖሎጂ ስፔሻሊስቶች እና የሂሳብ ሊቆች የተቀጠሩ የአዕምሮ ልምዶችን እንዲጠቀሙ ተማሪዎችን ያበረታታል። ተማሪዎች በአሌክሳንድሪያ ውስጥ ባለው ህይወት አግባብነት ያለው ችግርን ለመለየት በቡድኖች ሆነው ይሰራሉ እንዲሁም በተለዩ የኮርስ ጭብጦች ወጥነት ያላቸው ይሆናሉ። እያንዳንዱ ችግር-መፍትሄ፣ ምርመራ እና የውሳኔ ማድረግ ሁኔታ የንድፍ ሳይክል ፕሮቶኮልን ይጠቀማል እና በላብራቶሪ እና በመስክ ተሞክሮዎች ጥምር አጠቃቀም ላይ ይካሄዳል። የተማሪው አካላዊ የስራ ቦታ ከንድፍ እና የህንጻ ፕሮጀክቶች ጋር የተገናኙ የቴክኖሎጂ አይነቶች እና የፈጠራ ሂደቶች የተግባር ተሞክሮዎችን ለማግኘት መዳረሻ እንዲያገኙ ይፈቅዳል። ከአካባቢው የ STEM ቢዝነሶች እና ድርጅቶች ጋር ያሉ አጋር መሆን የኢንዱስትሪ ኤክስፐርቶች ችግር ለመፍታት እንዲተባበሩ ወደ ክፍሉ ያስገባቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

**የጋራ መስፈርቶች፦**

STEM አካዳሚ ተሳትፎ

**STEM ሴሚናር**

የ STEM ሴሚናር ተማሪዎች በቀድሞ የ STEM ኮርሶች የተማሯቸውን ከተግባራዊ የክህሎቶች እና እውቀት አተገባበር እድል ጋር ላማቅረብ የታለመ ነው። በ STEM ባለሙያዎች ከገጠሟቸው የሙያዊ እና ስነምግባራዊ ጉዳዮች ግንዛቤን ከማሳደግ በተጨማሪ፣ ተማሪው በችግር ፈቺ፣ በምርምር፣ በግንኙነት፣ በውሂብ ትንተና፣ በቡድን ስራ እና በፕሮጀክት ማኔጅመንት ያለውን ክህሎት ለማጥራት ይማራል። በት/ቤት ላይብረሪ ስልጠና በኩል ወይም እንደ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ትምህርት፣ የአገልግሎት ትምህርት፣ ማማከር እና የስራ ማጥላት የመሳሰሉ በስራ ላይ የተመሰረቱ የመማር ዝግጅቶች በኩል ትምህርቱ ይሰጣል። ተማሪዎች በ STEM መስኮች ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ያሉ የትምህርት አማራጮች ላይ እንዲሁ ይዳስሳሉ። ይህ ኮርስ የሚከተሉትን እድሎች ያካትታል፤ ሀ) አፓረንትሺፖች፣ አማካሪዎች፣ የባለሙያ ማሳያ፣ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ትምህርት፤ ለ) በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ የመማር እድሎች፤ ሐ) የት/ቤት፣ የማህበረሰብ ወይም የአገልግሎት የመማር ተሞክሮዎች፤ መ) የማጠቃለያ የምርምር ፕሮጀክት ከኤሌክትሮኒክ ፖርትፎሊዮ እና የመጨረሻ የ STEM ንፅፅር ማቅረቢያ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

STEM አሰሳዎች I፣ CTE STEM መንገድ

**የከተማ ህብረት ኢንተርንሺፕ I፦ የኮሌጅ ስኬት ክህሎቶች**

ይህ ኮርስ Urban Alliance ከተባለ ለትርፍ ካልተቋቋመ ድርጅት ጋር በመተባበር የቀረበ ሲሆን ሲኒየር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንወደ ኮሌጅ እና ወደ ሙያዎች እንዲተላለፉ ውጤታማ የሆነ የፕሮግራሚንግ ታሪክ ያለው ነው እንዲሁም እርሱ በ NOVA የኮሌጅ ክሬዲት የሚፈለግ የሆነው SDVIOO ኮርስ ነው። በዚህ ኮርስ ውስጥ የተሸፈኑት ርዕሶች የሚያካትቱት፤ የቃለመጠይቅ ክህሎቶች፣ የስራ ማመልከቻ አጻጻፍ፣ ሙያዊ ስነምግባር፣ የሙያ ምዘና እና አሰሳ፣ የጥናት ክህሎቶች፣ የጊዜ አጠቃቀም እና የፋይናንሻል እውቀት ናቸው። ተማሪዎች በሚከፈላቸው፣ የባለሙያ

ኢንተርንሺፖች ላይ እና በቀጣይነት በሚሰጠው ስልጠና እና አመቱን ሙሉ ባለው ድጋፍ ላይ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት የስድስት ሳምንት የቅድመ ስራ ስልጠና ያገኛሉ። ሁሉም ተማሪዎች በኢንተርንሺፖች ምክር ያገኛሉ። ተማሪዎች በትምህርት አመቱ 12 ሰአታት/ሳምንት እንዲሁም በክረምት ወቅት ከምርቃት በኋላ 32 ሰአታት/ሳምንት ይሰራሉ። ተለማማጆች በኮርሱ ፕሮግራም ቆይታ እስከ ሁለት ጭማሪዎችን የመቀበል እድል በማግኘት ይከፈላቸዋል እንዲሁ ይገመገማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

### በስራ ቦታ ላይ የተመሰረተ የመማር እና የኮሌጅ ዝግጅት

በስራ ላይ የተመሰረተ መማር እና የኮሌጅ አሰሳ የኮሌጅ አካዳሚያዊ ትምህርትን ከስራቦታ ክህሎቶች ጋር ከ16-ሳምንት የስራ ላይ የመማር ተሞከሮ ጋር አጣምሯል። በ 1ኛው ሩብ አመት፣ ተማሪዎች ምርምር ያካሂዳሉ፣ የስራ ማመልከቻ ይጽፋሉ፣ ለሁለተኛ እና ሶስተኛ ሩቦች የኢንተርንሺፕ ምደባ ለማግኘት በቃለመጠይቆች ላይ ይሳተፋሉ። በኢንተርንሺፕ ጊዜያቸው፣ ተማሪዎች የተወሰኑ የስራ ፍላጎቶችን በማሰስ አስፈላጊ የስራ ቦታ ብቃቶችን ያጎለብታሉ። ሩብ አመት 4 ለኮሌጅ ማመልከቻዎች የመማር እና የድርሰት አጻጻፍ ማንጸባረቅ ላይ ያተኩራል። በኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶች እና ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ባሉ ተቋማት እና ሙያዊ የስራ አካባቢዎች ውስጥ ለህይወት ዘመናቸው የሚያዘጋጃቸውን የገሃዱ አለም ሁኔታዎች እና አላማዎች የሚያገኙበትን የአካዳሚክ እውቀት እንዲያመለክቱ እድል ይኖራቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በአለም አቀፍ አካዳሚ ብቻ ያሉ የ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች

# የላቀ አመዳደብ ጫፍ

### AP ምርምር

በ AP ካፕስቶን የዲፕሎማ ፕሮግራም ውስጥ ሁለተኛ ኮርስ የሆነው የ AP ምርምር ተማሪዎች የግለሰብ ፍላጎትን አካዳሚያዊ ርዕስ ለመዳሰስ እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል። ተማሪዎች የምርምር ጥያቄን ይነድፋሉ፣ ያቅዳሉ እና አመቱን የሚቆይ ምርምር ያካሂዳሉ። በዚህ ጥያቄ መሰረት፣ ተማሪዎች የምርምር ዘዴን በመማር፣ የስነምግባር ምርምር ልምዶችን በመተግበር እና መረጃን በማዳረስ፣ በመተንተን እና በማዋሃድ በ AP ሴሚናር ኮርስ ውስጥ ያገኙትን ክህሎቶች ያጎለብታሉ። ተማሪዎች በክህሎት እድገታቸው ላይ ያንጸባርቃሉ፣ ሂደቶቻቸውን ይሰንዳሉ፣ እንዲሁም በፖርትፎሎዮዋቸው ነጸብራቅ የምርምር ስራ ቅርሶቹን ያስተካክላሉ። ኮርሱ ከ 20 በላይ የሆኑ ገጾች ያሉት የአካዳሚክ ወረቀትን እና የቃል መከላከያ ጋር ያለ ዝግጅትን ይዟል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

AP ሴሚናር

### AP ሴሚናር

በ AP ሴሚናር ውስጥ፣ ተማሪዎች ከበርካታ አመለካከቶች የገሃዱን አለም ችግሮች ይመረምራሉ፣ ተአማኒነት ያላቸው እና ትክክለኛ በመረጃ የተደገፉ ምክንያቶችን ለማጎልበት መረጃን ከተለያዩ ምንጮች ይሰበስባሉ እንዲሁም ይተነትናሉ። በ AP ምርምር ውስጥ፣ ተማሪዎች የምሁር አካዳሚያዊ ቴሲስ ለማዘጋጀት እና

ለመከላከል ራስን የቻለ ምርምር ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን ክህሎቶች እና ስነስርዓት ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

# በተናጠል አወሳሰን ላይ የተመሰረተ ማጎልበቻ (AVID)

AVID ማለት ከስድስት እስከ 12ኛ ክፍል ስርዓት የሆነ ለአራት አመት የኮሌጅ ብቁነት የአካዳሚክ መሃከል ውስጥ ተማሪዎችን የሚያዘጋጅ ነው። በተማሪዎች ውስጥ ያለውን ምርጥ ነገር የማቅረብ እና የስኬት ክፍተትን የመዝጋት የተረጋገጠ የክትትል መዝገብ አለው። የ AVID ፕሮግራም አንድ የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የሚያስገኝ ተመራጭ ኮርስ አካትቷል።

### AVID የጓደኛ ማጠናከሪያ ትምህርት

AVID የጓደኛ አስተማሪዎች በተወሰኑ ብሎኮች የ AVID 9፣ 10፣ 11፣ or 12 ክፍሎች ውስጥ ይሰራሉ። አስተማሪዎች የተማሪዎችን ግራ የመጋባት ጥያቄ ጥብቅ ከሆነው ክፍላቸው ነጥብ በመጠቀም  በዋና የትምህርት አይነት ውስጥ ትናንሽ የተማሪ ቡድኖችን ያመቻቻሉ።

የጓደኛ የጓደኛ አስተማሪዎች፦

- በ 45-ደቂቃ አጋዥ ስልጠና ወቅት በ 1:5 የቡድን መጠን ውስጥ ትናንሽ ቡድኖችን ማመቻቸት
- መልስ ሳይሰጡ መፍትሄ እንዲያገኙ በመርዳት በጥያቄያዊ አስተሳሰብ እና አጠያየቅ በኩል ተማሪዎችን መምራት
- የተማሪ ትብብርን እና ችግር መፍታትን በ 10 የደረጃ ሂደት በኩል ይደግፉ
- በጓደኞች መካከል የመሪነት ክህሎቶች አጠቃቀም እና ልምምድ
- የአጋዥ ስልጠና በሌሉባቸው ጊዜያት የአስተማሪ ረዳት (TA) ሆነው ያገለግሉ
- በ AVID ተመራጭ አካባቢ ውስጥ በመሆን ጠቃሚ የኮሌጅ እውቀት መረጃን እንደ ቦነስ ማግኘት
- በጣቢያ ላይ ያለ ስልጠና ለ AVID አጋዥ ስልጠና ሂደት በሴፕቴምበር ውስጥ ይቀርባል። የተማሪ ጓደኛ አስተማሪዎች ለሴሚስተር ወይም ለአመት ቁርጠኛ መሆን ይችላሉ። በእረፍት ጊዜ፣ የጓደኛ አስተማሪዎች ጊዜውን ለማጥናት ወይም ለሌሎች ከት/ቤት ጋር ለተገናኙ ስራዎች ይጠቀማሉ።

**ጥቅሞች፦ እንደ ጓደኛ አስተማሪ ይህ ለአገልግሎት መማር ሰአታት እና ለልዩ የመሪነት እድል ተጠያቂ ሊሆን ይችላል። የጓደኛ አስተማሪዎች ከ AVID ዲስትሪክት ዳይሬክተር እንዲሁ የእውቅና ደብዳቤ ይቀበላሉ። በተጨማሪም፣ .5 ወይም 1 አማራጭ ክሬዲትን ማግኘት ይችላሉ። በጓደኛ የማጠናከሪያ ትምህርት ማመልከቻ ላይ ቦነስ ሊሆን እንደሚችል አይርሱ።

*** የጓደኛ ማጠናከሪያ ትምህርቶች ከ AVID የማጠናከሪያ ትምህርት ሃላፊነቶች ጋር ውጤቶች በሚመደቡበት የተማሪ ስራ ውጤት አሰጣጥ ወይም የተማሪውን ሚስጥራዊ መረጃ ማግኘትን ሳያካትት ተመሳሳይ ነገር ይይዛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 0.5-1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

አንድ ሴሚስተር

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

እየመጣ ያለ 11 ወይም 12 AVID ተማሪ መሆን አለበት

**በተናጠል አወሳሰን ላይ የተመሰረተ ማጎልበቻ (AVID) -**

**ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**

ሶስቱ የዚህ ኮርስ ክፍሎች የአካዳሚክ መመሪያ፣ የማጠናከሪያ ትምህርት ድጋፍ እና አነቃቂ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ይህ ኮርስ በሁለተ ኛደረጃ ት/ቤት ውስጥ ስኬታማ የሚሆኑባቸውን ስትራቴጂዎች ያቀርባል እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ላሉት እድሎች በደንብ እንዲዘጋጁ ያደርጋል። እርሱ የድርጅታዊ ክህሎቶችን፣ ምሌሳያዊ ስራን እንዴት መፍጠር እንደሚቻል፣ አእምሮአዊ አደጋን መውሰድ፣ በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና የኮሌጅ መዳረሻ አማራጮችን እና የኮሌጅ ስኬትን ለመጨመር ያሉ አስፈላጊ ደረጃዎች። የ AVID ተማሪዎች የላቀ ምደባ (AP) እና ሌላ ትክክለኛ ኮርሶችን ሲወስዱ በአካዳሚያዊ ሁኔታ ይደገፋሉ።

ዝቅተኛውን GPA የሚያካትቱ የኮርስ ተጠባቂ ነገሮች በመኖራቸው ምክንያት በጥብቅ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰአታት መስፈርቶች፣ የኮሌጅ እና የስራ ተሳትፎዎች እና የሲኒየሮች ፖርትፎሊዮን ቢያንስ አንድ ወይም ከዛ በላይ ኮርሶች ላይ በመመዝገብ የ AVID ተመራጭ ኮርስ ለውጤት አሰጣጥ አላማዎች ኦነርስ (H) የኮርስ ክብደትን ይዟል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

የተማሪ የመሪነት ክህሎቶች በት/ቤት ላይ በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የስራ ማሳያ፣ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ስራ ትምህርት እና/ወይም የ Future Business Leaders of America (FBLA) ውስጥ በመሳተፍ ሊዳብር ይችላል። የህብረት ስራ ትምህርት ዘዴ ለብዙዎቹ የሙሉ አመት የቢዝነስ ኮርሶች ይገኛል። ተሳታፊ ተማሪ የክፍል ውስጥ ትምህርትን እና ቢያንስ 396 ሰዓት የሚሆን የመስክ ላይ ስልጠና በተፈቀደ መደብ ላይ ተከታታይ ከሆነ ማማከር ጋር አመቱን በሙሉ አጣምሮ ይወስዳል። ተማሪው ተጨማሪ ክሬዲት ለህብረት ስራ ትምህርት ተሞክሮው ሊቀበል ይችላል።

**የሳይበር ደህንነት መሰረቶች**

የሳይበር ደህንነት እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ድርጅት እና ሃገር ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ይህ ኮርስ ግላዊ፣ ድርጅታዊ እና ሃገራዊ መረጃን መጠበቅ ላይ አጽንዖት ሰጥቶ በማደግ ላይ እና ሁሉን አቀፍ በሆነ የቴክኖሎጂ አካባቢ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተማሪዎች ስለሳይበር ደህንነት መርሆዎች ይተዋወቃሉ፣ እየመጡ ስላሉ ቴክኖሎጂዎች ዳሰሳ ያደርጋሉ፣ አስጊ ነገሮችን እና የመከላከያ እርምጃዎችን ይመረምራሉ እንዲሁም በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያሉ ብዝሃነት ያላቸው ከፍተኛ ክህሎት፣ ከፍተኛ ደሞዝ እና ከፍተኛ የስራ እድል ፍላጎቶችን ይመረምራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11

# የስራ ዝግጅት ኮርሶች

**የስራ ዝግጅት-ድህረ ምረቃ**

የሙያ ዝግጅት የድህረ ምረቃ ኮርስ ዝግጅት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ለስራ ናሙና ተሞክሮዎች የመነሻ ተጋላጭነት እና ከአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከተመረቁ በኋላ ትርጉም ያላቸው እና የሚያረኩ ስራዎችን እንዲያገኙ አስፈላጊ ክህሎቶችን የመገንባት መመሪያ የነበራቸው እንዲዘጋጁ የተነደፈ ነው። ይህ ኮርስ

ተግባራዊ፣ አካዳሚያዊ እና ገላጭ እንቅስቃሴዎችን በማጣመር ይዟል። የሙያ እና የጉዞ ክህሎቶቻቸውን እንዲያጠሩ ለመርዳት እና ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ድጋፍ ለመስጠት የታለመ ነው። በኢንተርንሺፖች እና/ወይም በውድድራዊ ቅጥር ላይ ይሳተፋሉ፣ በመስክ ጉዞዎች ላይ ይሳተፋሉ እና በህይወት ግቦች ውስጥ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መረጃዎችን ከተለያዩ አካባቢያዊ ኤጀንሲዎች ለማግኘት በተጋበዙ ተናጋሪዎች ዝግጅቶች ላይ ይገኛሉ። ይህ ክፍል ለውጤት ወይም ለማለፍ/መውደቅ ሊወሰድ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የስራ ዝግጅት 12

### የስራ ዝግጅት 9

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በተለያዩ ምዘናዎች የራሳቸውን የስራ ክህሎቶች ለመለየት ይማራሉ። የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ የማዘጋጀት ሂደትን እና ለቅጥር መጠቀም እና ማመልከት እንዲሁም ቅጥርን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን በተጨማሪ ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

### የስራ ዝግጅት 10

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ገደብ ውስጥ በየሰስት እስከ አራት ሳምንታት ውስጥ በስራዎች ውስጥ ይዞራሉ። በስራ ጣቢያው ላይ፣ ተማሪዎች አቅጣጫዎችን መከተል፣ ማህበራዊ ክህሎቶች እና ራስን መቻልን ጨምሮ በተለያዩ የስራ ክህሎቶች ላይ ይሰራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የስራ ዝግጅት 9

### የስራ ዝግጅት 11

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቅጥር ለማድረግ የሚያስፈልጉ የስራ ዝግጁነት ክህሎቶችን መማር ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉት ስራዎች በየሰስት-አራት ሳምንታት ይዞራሉ። በስራ ጣቢያው ላይ፣ ተማሪዎች የህዝባዊ ጎዞ መዳረሻ፣ የገንዘብ ክህሎቶች እና መርሃ ግብር መያዝ እንዲሁም አቅጣጫዎች፣ ግንኙነት፣ ማህበራዊ ክህሎቶች እና ራስን መቻልን በመሳሰሉ በርካታ ክህሎቶች ላይ ይሰራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የስራ ዝግጅት 10

### የስራ ዝግጅት 12

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ከስድስት እስከ ስምንት ሳምንታት በሚቆዩ በርካታ የስራ መዘውሮች ላይ በመሳተፍ የስራ ናሙና ማድረግን ይቀጥላሉ። በእነርሱ የስራ ተሞክሮ ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች ስራ እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የመማር እና የስራ ዝግጁነት ክህሎቶች መማር እና ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ። ተማሪዎች ወደ ቅጥር የሚወስዷቸው ልምምዶች ውስጥ ተመድበዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የስራ ዝግጅት 11

# የኮሌጅ ሰሚት

**የኮሌጅ ሰሚት**

በዚህ ኮርስ ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮሌጅ ዝግጁነት ክህሎታቸውን ለማጠናከር እና በኮሌጅ ምርጫው በኩል ድጋፍ ለማግኘት እና የስራ ማመልከቻ ማጎልበትን እና የገንዘብ እርዳታ መረጃን እንዲሁም ከፍተኛ የአካዳሚክ ኮርሶች ክንውንን ጨምሮ የማመልከቻ ሂደትን ከዓደኛ ሃላፊዎች ጋር አብረው ይሰራሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

# የኮሌጅ ሙከራ ዝግጅት

**የኮሌጅ ሙከራ ዝግጅት**

ይህ ኮርስ ለተማሪዎች የ SAT/ ACT ቅጽ እና አወቃቀር ለተማሪዎች ለመግለጥ፣ ዒላማ ያላቸው የሙከራ ስትራቴጂዎችን ለተማሪዎች ለመስጠት፣ የተማሪዎችን አካላዊ እና አእምሮአዊ ዝግጁነት ለማድረግ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የሙከራ ክፍል ቁልፍ የሆነ ይዘትን ለመገምገም የተነደፈ ነው። ሁሉም የሙከራ ክፍሎች በዚህ ኮርስ ውስጥ ይሸፈናሉ። የኮርስ ይዘት መሰረታዊ የሂሳብ፣ የሰዋሰው እና የንባብ ክህሎቶችን እንዲሁ ያሻሽላል። ተሳታፊዎች ግብ ማስቀመጥን፣ የጊዜ አያያዝን እና የኮሌጅ ድርሰት ስትራቴጂዎች እና ቴክኒኮች እንዲሁ ይማራሉ። ተሳታፊዎች ወደ 60 ደቂቃ የሚሆን ራሱን የቻለ የሙከራ ልምምድ በየሳምንቱ እንዲያጠናቅቁ ይጠበቃል። በተጨማሪም፣ የሙከራ ስትራቴጂዎችን ለመለማመድ እና የይዘት ዝግጅትን ኢላማ ለማድረግ ተሳታፊዎች ትክክለኛ የሁኔታዎች ፈተናን ለመውሰድ እድሉን ያገኛሉ።

ለዚህ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች ለ SAT ወይም ACT በሴሚስተሩ መጨረሻ በወጣው የመርሃ ግብር ቀን እንዲመዘገቡ ይጠበቃል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

# CTE: የፋይናንስ አካዳሚ (AOF)

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የ AOF ፕሮግራም በ National Academy Foundation (NAF) ስፖንሰር ተደርጓል። ተማሪዎች በሚከተሉት ኮርሶች ውስጥ ከመመዝገባቸው በፊት ወደ AOF ፕሮግራም ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው። በፋይናንሻል አገልግሎቶች ውስጥ ኮርሱቹ በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቁ፣ የ NAF የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

**AOF ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ**

ተማሪዎች የትምህርት፣ የትራንስፖርት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የታክሶች፣ የኢንሹራንስ እና የጡረታን ያካተቱ የወደፊት ወጪዎችን እቅድ ከማውጣት በተጨማሪ ለቁጠባዎች፣ በጀት ለማድረግ፣ ለክሬዲት እና ዴብት ማኔጅመንት እና ኢንቨስቲንግ የገንዘብ አስተዳደር ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች ኢንሹራንስን እንደ አደጋ አስተዳደር ይተነትናሉ፣ የታክስ ስራዎችን ይተገብራሉ እንዲሁም የውርስ ፋይናንስ ምንነቶችን ይመረምራሉ። ተማሪዎች አክሲዮኖችን፣ በንዶችን፣ የጋራ ፈንዶችን፣ሪልስቴትን፣ ኢንሹራንስን እና የታክስ መሸፈኛ መሳሪያዎችን ለማካተት የኢንቨስትመንት መሳሪያዎች ላይ ምርምር ያካሂዳሉ። ለማጠናቀቂያ ፕሮጀክት፣ ተማሪዎች ቁጠባን፣ ኢንቨስት ማድረግን፣ መበደርን፣ አደጋ ማስተዳደርን እና ጡረታን እንዲሁም፣ የቤቶች እቅድ ማውጣትን በማካተት ለገንዘብ እቅዶች ዝግጁ ይሆናሉ። ተማሪዎች የ w!se Financial Literacy

Certification (FLC) ፈተና እና CTECS የስራ ቦታ የዝግጁነት ክህሎቶች ምዘናን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

AOF የፋይናንስ አገልግሎቶች መግቢያ

### AOF የቢዝነስ እና አለም አቀፍ ፋይናንስ መግቢያ

ይህ ኮርስ የቢዝነስ ዋና የተግባር አካባቢዎችን ሚና እና በእነሱ መካከል ስላሉት ግንኙነቶች ለተማሪዎች ያስተዋውቃል። ተማሪዎች አለም አቀፍ የፋይናንስ ችግሮች እነሱን እና አለምን እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ እንዲሁ ይማራሉ። ድርጅታዊ ጽንሰ ሃሳቦች እና ቴክኒኮች ይመረመራሉ። የቢዝነስ ድርጅቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ቴክኖሎጂያዊ ተጽዕኖዎች ይገመገማሉ። እንደማጠናቀቂያ ፕሮጀክት፣ ተማሪዎች ዝርዝር የአዋጪነት እና የቢዝነስ እቅዶችን ይገነባሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

AOF ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ፣ እና ሁሉንም የኮሌጅ ምደባ መስፈርቶች ያሟላል።

### AOF የፋይናንስ አገልግሎቶች መግቢያ

ተማሪዎች በፋይናንስ አገልግሎቶች ኢንዱስትሪ ያሉ የሙያ አማራጮችን ይማራሉ እና ለ 21ኛው ክፍለ ዘመን የስራ ቦታ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልገውን የስራ ቦታ ሙያዊ የሆኑ እና የሚተላለፉ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች የኤሌክትሮኒክ ፖርትፎሊዮዎችን ይፈጥራሉ፣ የሙያ እቅዶችን ያጎለብታሉ፣ የሙያ ክላስተሮችን ያስሳሉ፣ የአጭር እና የረዥም ጊዜ ግቦችን ይለያሉ፣ የእርስ በእርስ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ፣ የውሳኔ አደራረግ ሂደትን ይተገብራሉ እና የጊዜ አጠቃቀምን፣ ቴክኖሎጂን፣ የቡድን ስራን እና የግንኙነት ክህሎቶችን ያሳያሉ። ተማሪዎች እንደ ባንኪንግ፣ ማኔጅመንት፣ ፋይናንስ፣ እንግዳ መቀበል፣ ኢንሹራንስ እና ሪል ስቴት ያሉ በተወሰነ ሴክተር እና ስፋት የሚገኙ የሁለቱንም ስራዎች ተፈጥሮ ይማራሉ። ተማሪዎች በ Commonwealth One Federal Credit Union ውስጥ ይሰራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቅበላ ወደ ፋይናንስ አካዳሚ

# CTE: ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የተማሪ የመሪነት ክህሎቶች በት/ቤት ላይ በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የስራ ማሳያ፣ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ስራ ትምህርት እና/ወይም የ Future Business Leaders of America (FBLA) ውስጥ በመሳተፍ ሊዳብር ይችላል። የህብረት ስራ ትምህርት ዘዴ ለብዙዎቹ የሙሉ አመት የቢዝነስ ኮርሶች ይገኛል። ተሳታፊ ተማሪ የክፍል ውስጥ ትምህርትን እና ቢያንስ 396 ሰዓት የሚሆን የመስክ ላይ ስልጠና በተፈቀደ መደብ ላይ ተከታታይ ከሆነ ማማከር ጋር አመቱን በሙሉ አጣምሮ ይወስዳል። ተማሪው ተጨማሪ ክሬዲት ለህብረት ስራ ትምህርት ተሞክሮው ሊቀበል ይችላል።

**አካውንቲንግ I**

ተማሪዎች ለሽርክናዎች እና ለኩባንያዎች የሚያስፈልጉትን የአካውንቲንግ ሂደቶች እና ልምዶች ያስሳሉ። የመመሪያ ምዕራፎች የሚያካትቱት ለመቀበል የሚቻሉ አካውንቶች፣ ለመክፈል የሚቻሉ አካውንቶች፣ የደመወዝ ክፍያ፣ ታክሶች እና የገንዘብ መግለጫዎች ናቸው። የፌዴራል ታክስ ህጎች ለደመወዝ ክፍያ ዝግጅት አጽንዖት ሰጥተዋል። የአካውንቲንግ ሂደቶችን ለማጠናከር በራስ-ሰር የሆነ የተቀናጀ የአካውንቲንግ ስርአት ጥቅም ላይ ይውላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**የላቀ አካውንቲንግ II**

ተማሪዎች ለኩባንያዎች እና የፋይናንስ ተቋማት የሚያስፈልጉ የአካውንቲንግ ሂደቶችን እና ልምዶችን ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ ያገኛሉ። ተማሪዎች የገንዘብ ሪፖርቶችን ሲተነትኑ እና ሲፈቱ ስፕሪድሺቶችን ያጎለብታሉ። የአካውንቲንግ መሰረታዊያንን ለማጠናከር በራስ-ሰር የሆነ የተቀናጀ የአካውንቲንግ ስርአት ጥቅም ላይ ይውላል። ምዕራፎች የሚያካትቱት የቆጠራ ጥገና፣ የረጅም እና የአጭር ጊዜ ኢንቨስትመንቶች፣ የስቶክ ኢንቨስትመንቶች፣ የክፍፍሎች ስርጭት፣ የወጪ እና የማኔጅመንት አካውንቲንግ እና የታክስ ዝግጅት ናቸው። ፕሮጀክቶች የሚያካትቱት የገንዘብ መዝገቦችን ለድርጅት መጠበቅ እንዲሁም የንዑስ የአካውንቲንግ ድርጅት ለመመስረት ፕሮፖዛል ማቅረብ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አካውንቲንግ I

**የላቀ የኮምፒውተር መረጃ ስርዓቶች II**

ይህ ኮርስ የስቴት ማይክሮሶፍት አይቲ አካዳሚ አካል ነው ይህም የክፍል ውስጥ እና የመስመር ላይ ትምህርትን፣ ተግባራዊ ላብራቶሪዎችን እና በመቶዎች የሚቆጠሩ ኮርሶችን፣ መጽሃፎችን እና የቅርብ ሃብቶችን መዳረሻ ያካትታል። እነዚህ ግብዓቶች ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲቶችን እንዲያገኙ እና በአለም ላይ ባሉ ቀጣሪዎች የሚታወቁ ምስክርነቶች ያላቸውን የስራ ታሪክ ማመልከቻዎችን ለማሻሻል የሚረዳቸውን የ Microsoft Office Specialist (MOS) የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንዲዘጋጁ ይረዳሉ። ተማሪዎች ችግር ፈቺ ክህሎቶችን በላቀ የተቀናጀ የሶፍትዌር መተግበሪያዎች የታተሙ፣ ኤሌክትሮኒክ እና የድር ህትመቶችን ጨምሮ የእውኑ አለም ጉዳዮች ላይ ይተገብሩታል። ተማሪዎች የላቀ የኮምፒውተር ጥገና እንቅስቃሴዎች፣ የድረገጽ ማበልጸግ፣ ፕሮግራሚንግ፣ ኔትወርኪንግ፣ እያደገ ያለ ቴክኖሎጂ እና የቅጥር ክህሎቶችን ለመዳሰስ በግል እና በቡድን ይሰራሉ። ፕሮጀክቶች የሚያካትቱት ስፕሪድሺቶች፣ ምስላዊ እና የጽሁፍ አቀማመጥ፣ ዳታቤዝ፣ ወርድ ፕሮሰሲንግ እና ቻርቲንግን ነው። ተማሪዎች የ MOS የምስክር ወረቀት ፈተናን የመውሰድ እድል አላቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የኮምፒውተር መረጃ ስርዓቶች I

**የላቀ ግራፊክ ዲዛይን እና መልቲሚዲያ II**

ተማሪዎች በዴስክቶፕ የታተመ፣ በይነተገናኝ መልቲሚዲያ እና የድርገጽ ፕሮጀክቶችን ለመፍጠር፣ የላቁ ክህሎቶችን ያዳብራሉ። ተማሪዎች ውስብስብ ከሆነ ሃርድዌር እና ሶፍትዌር ጋር ይሰራሉ፣ በገሃዱ አለም ያሉ ፕሮጀክቶች ላይ ይተገብራሉ። የክፍል መመሪያ የተማሪውን ትምህርታዊ ተሞክሮዎች ለማስፋት በተፈቀደ ቦታ ላይ

በስራ ላይ ከሚኖር ስልጠና ጋር ተጣምሮ በትምህርት አመቱ በሙሉ ተከታታይ ማማከር ይደረግለታል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ግራፊክ ዲዛይን እና መልቲሚዲያ I

### የቢዝነስ ህብረት ስራ ኢንተርንሺፕ

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ያገኙትን የክፍል እውቀት ለገሃዱ አለም የስራ ተሞክሮ እንዲተገብሩት ያስችላቸዋል። የኢንተርንሺፕ ተሞክሮ የተማሪውን የአሁን የሙያ ፍላጎት በሚያንጸባርቅ መልኩ ከቢዝነስ ጋር የተገናኘ መስክ ውስጥ የቢዝነስ ኮርስን ከቅጥር ጋር ያጣምራል እና/ወይም ዋጋ ያለው የስራ ተሞክሮ ተማውዎች እንዲያገኙ እድል ይሰጣል፣ የቅጥር ክህሎቶችን ያሻሽላል እና የ 21ኛው ክፍለዘመን የስራቦታ ክህሎቶችን ያጎለብታል። ይህ ኮርስ ከሌላ የቢዝነስ ኮርስ ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪ ለቢዝነስ ኮርስ በጣምራ መመዝገብ አለበት

### የቢዝነስ ህግ

ተማሪዎች የአሜሪካዊያንን ህጋዊ ስርአት ይመረምራሉ እና የዜጎችን መብቶች እና ግዴታዎች ይማራሉ። ተማሪዎች ቢዝነስ እና ግለሰቦችን የሚገዙ ህጎች ጋር የተገናኙ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጽንሰ ሃሳቦችን በማሰስ ተግባራዊ እውቀት እና የህይወት ክህሎቶች ያገኛሉ። የትኩረት አካባቢዎች የሚያካትቱት ስምምነቶች፣ የሸማች ጥበቃ፣ የወንጀል ህግ፣ የማሰቃየት ህግ፣ አለም አቀፍ ህግ፣ የቤተሰብ/የቤት ህግ፣ የስራ ህግ እና በህጋዊ ስራዎች ውስጥ ያሉ ስራዎችን ነው።

ተማሪዎች ለቢዝነስ ኮሌጅ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ በቢዝነስ ህግ ውስጥ እንዲመዘገቡ ተጠቁሟል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

### ቢዝነስ አስተዳደር

ተማሪዎች ለቢዝነስ ባለቤትነት፣ እቅድ ማውጣት፣ ክንውኖች፣ ማርኬቲንግ፣ ፋይናንስ እና የሰው ግንኙነቶች ያስሳሉ። የመመሪያ ምዕራፎች በተጨማሪ የሚያካትቱት የቢዝነስ ባለቤትነት፣ ኔኔጅመንት እና የገንዘብ ሃላፊነቶች አይነቶችን ነው። ችግር መፍታት እና ስነምግባራዊ የውሳኔ አወሳሰን የኮርሱ ዋና ክፍሎች ናቸው። ተማሪዎች ለቢዝነስ ኮሌጅ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ በቢዝነስ ማኔጅመንት ውስጥ እንዲመዘገቡ ተጠቁሟል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

### የኮምፒውተር መረጃ ስርዓቶች I

ይህ ኮርስ የስቴት ማይክሮሶፍት አይቲ አካዳሚ አካል ነው ይህም የክፍል ውስጥ እና የመስመር ላይ ትምህርትን፣ ተግባራዊ ላብራቶሪዎችን እና በመቶዎች የሚቆጠሩ ኮርሶችን፣ መጽሃፎችን እና የቅርብ ሃብቶችን መዳረሻ ያካትታል። እነዚህ ግብዓቶች ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲቶችን እንዲያገኙ እና በአለም ላይ ባሉ ቀጣሪዎች የሚታወቁ ምስክርነቶች ያላቸውን የስራ ታሪክ ማመልከቻዎችን ለማሻሻል የሚረዳቸውን የ Microsoft Office Specialist (MOS) የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንዲዘጋጁ ይረዳሉ። ተማሪዎች ችግር ፈቺ ክህሎቶችን በወርድ ፕሮሰሲንግ፣ በስፕሪድሺቶች፣ በዳታቤዞች፣ በመልቲሚዲያ አቀራረቦች እና በተቀናጀ የሶፍትዌር እንቅስቃሴዎች የእውኑ አለም ጉዳዮች ላይ ይተገብሩታል። ተማሪዎች የኮምፒውተር

ጽንሰ ሃሳቦችን፣ኦፕሬቲንግ ሲስተሞችን፣ ኔትወርኮችን፣ ቴሌኮሚኒኬሽኖችን እና እያደገ ያለ ቴክኖሎጂ እና የቅጥር ክህሎቶችን ለመዳሰስ በግል እና በቡድን ይሰራሉ። ተማሪዎች የ MOS ምስክር ወረቀት ፈተናን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11

### የዲጂታል ማመልከቻዎች

ይህ ኮርስ እውነተኛ የህይወት ውጤት ላይ የተመሰረቱ የአቀራረብ ክህሎቶች ዲጂታ ዜግነት፣ መሰረታዊ የኮምፒውተር ክንውኖች፣ ኪቦርዲንግ፣ የመተግበሪያ ሶፍትዌር (ወርድ ፕሮሰሲንግ፣ ስፕሬድሺትስ፣ መልቲሚዲያ መተግበሪያዎች፣ ዳታቤዞች) እና የሙያ አሰሳን እንዲያጎለብቱ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተነደፈ ነው። ይህ ኮርስ በካሪኩለሙ ዙሪያ ሊተገበሩ የሚችሉ ክህሎቶችን ያስተዋዉቃል እንዲሁም ከ 21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ አግባብነት ያለው ዝግጅትን ያቀርባል። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች ጥብቅ የሆነ እና አግባብነት ያለው የኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀት ፈተና ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የተማሪ ክህሎቶች በስራ- ላይ የተመሰረቱ የመማር እንቅስቃሴዎች እና/ወይም የወደፊት የአሜሪካ ቢዝነስ መሪዎች (FBLA) ላይ በመሳተፍ ሊሻሻል ይችላል።

ማስታወሻ: ይህ ኮርስ በአካባቢው የት/ቤት ክፍል ከጸደቀ ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት ሊቀርብ ይችላል። የኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀቱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ አይተገበርም። በዲጂታል መተግበሪያዎች ማዕቀፍ ውስጥ የተያዙት ተግባራት ከበርካታ የ FBLA የንፅፅር ክስተቶች ጋር ይያያዛሉ። ለዝርዝሮች ወይም ለተግባር በተግባር የ FBLA ግንኙነት የ FBLA ድረገጽንያጣቅሱ።

ይህ ኮርስ ቀድሞ የኮምፒውተር እና ኪቦርዲንግ መተግበሪያዎች ይባል ነበር።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቅድመ ሁኔታዎች የሉም። በ CIS እና CTE አሟይ ተከታታይ ሊቀጥል ይችላል

### ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ

ተማሪዎች ለቢዝነስ እና ለግላዊ የገንዘብ አስተዳደር የውሳኔ አደራረግ ክህሎቶችን ለመሞከር መሰረታዊ ማይክሮኢኮኖሚክስ እና ማክሮኢኮኖሚክስን ያስሳሉ። ምዕራፎች የሚያካትቱት የአፓርታማ ስምምነቶች፣ ሞርጌጆች፣ የመኪና ፋይናንስ ማድረግ፣ ባንኪንግ፣ የህይወት እና የጤና እንክብካቤ ኢንሹራንስ፣ ሪልስቴት፣ የጡረታ እቅዶች፣ ስቶኮች፣ በንዶች፣ የግምጃ ቤት ገንዘቦች፣ አበሎች፣ የጋራ ፈንዶች፣ የጡረታ ገንዘቦች፣ የግል ብድሮች፣ የክሬዲት ካርዶች፣ ትምህርታዊ እዳዎች፣ የሸማች መብቶች እና ግንዛቤዎች እና የፌዴራል፣ የስቴት እና የከተማ ታክስ ምዘናዎች ናቸው። እንደሚጠናቀቅ ፕሮጀክት፣ ተማሪዎች ቁጠባ፣ ኢንቨት ማድረግ፣ መበደር፣ የአደጋ አስተዳደር እና ጡረታ እንዲሁም የንብረት እቅድ ማውጣትን የሚያካትቱ የፋይናንስ እቅዶች ይዘጋጃሉ። ተማሪዎች የ w!se Financial Literacy Certification (FLC) ፈተና እና CTECS የስራ ቦታ የዝግጁነት ክህሎቶች ምዘናን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ይህ ኮርስ የኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ ምርቃት መስፈርትን ያሟላል ይህም የቨርቹዋል ኮርስ መስፈርት እና የኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀት መስፈርት ነው።

**ግራፊክ ዲዛይን እና መልቲሚዲያ I**

ተማሪዎች ንድፍ በማውጣት እና በዴስክቶፕ የሚታተሙ ፕሮጀቶችን፣ የመልቲሚዲያ አቅርቦቶችን/ፕሮጀክቶችን እና ድረገጾችን በኢንዱስትሪ ደረጃ በተቀመጠ የመተግበሪያ ሶፍትዌር በመጠቀም መፍጠር። ተማሪዎች ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ያሉ የአቀማመጥ እና ንድፍ መርሆዎችን ይተገብራሉ። ተማሪዎች በኮርሱ ውስጥ የሚዘጋጁ የስራ ማመልከቻ ደብዳቤዎችን እና የተለያዩ በዴስክቶፕ የሚታተሙ፣ የመልቲሚዲያ እና የድረገጽ ፕሮጀክቶችን ያካተቱ ፖርትፎሊዮዎችን ይፈጥራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**የተማሪ የእርዳታ ዴስክ**

አሁን በተማሪ የእርዳታ ዴስክ በኩል የህብረት ስራ ትምህርት ልምድ እየቀረበ ነው። ሚናው የሚያካትተው ችግር መፍታት እና በተማሪው የሚመራ የተማሪ እርዳታ ዴስክ፣ ለጓደኞች እና ለአስተማሪዎች የቴክኒካዊ ችግሮችን መፍቻ፣ የተማሪ ስልጠና ግብዓቶችን እቅድ ማውጣት እና መፍጠር፣ እና ለአመታዊ የዲጂታል የመማር ቀን እና የኮዲንግ ሳምንት እቅድ ማውጣት።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፡-**

የኮምፒውተር መረጃ ስርዓቶች I፣ የላቀ የኮምፒውተር መረጃ ስርዓቶች II፣ ባለሁለት ምዝገባ የኔትወርኪንግ ሃርድዌር ክንውኖች I እና II፣ ኮምፒውተር እና የሳይበር ደህንነት መፍትሄዎች ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው የ CTE ኮርስ

# CTE: ቤተሰብ እና የተጠቃሚ ሳይንሶች

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የተማሪ የመሪነት ክህሎቶች በት/ቤት ላይ በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የስራ ማሳያ፣ ኢንተርንሺፖች፣ የህብረት ስራ ትምህርት እና/ወይም የ Community Leaders of America (FCCLA) ውስጥ በመሳተፍ ሊዳብር ይችላል። የህብረት ስራ ትምህርት ዘዴ ለሁሉም የሙሉ አመት ኮርሶች ይገኛል። የሙሉ ጊዜ ተማሪ የክፍል ውስጥ ትምህርትን እና ቢያንስ 396 ሰዓት የሚሆን የመስክ ላይ ስልጠና በተፈቀደ መደብ ላይ ተከታታይ ከሆነ ማማከር ጋር አመቱን በሙሉ አጣምሮ ይወስዳል። ተማሪው ለእርሱ ወይም ለእርሷ የህብረት ትምህርት ተሞክሮ ተጨማሪ ክሬዲት ሊቀበል ይችላል ወይም ትችላለች።

**የልጅ እድገት**

ይህ ኮርስ የልጅ እድገትን (አካላ፣ ስነ-ልቦናዊ እና የእውቀት) ቁልፍ ምልክታዎች ዋና እይታን ከመጸነስ እስከ እድገት ያሉ ጽንሰ ሃሳቦች እና ምርምርን ያቀርባል። ተማሪዎች ከእውቀት፣ ሞተር፣ ማህበራዊ፣ የቋንቋ፣ ስሜታዊ፣ ግለሰባዊ እና የሞራል ማጎልበት ጋር የተገናኙ የእድገት ቲዮሪዎችን ይማራሉ። እድገት የሚከናወንባቸው ሁኔታዎች እና አካባቢዎች አዎንታዊ እድገትን በሚደግፉ በእነዚያ ምክንያቶች ላይ አጽንዖት ማድረግን አካትቶ ውይይት ይደረግባቸዋል። የተመዘገቡ ተማሪዎች የልጅ እንክብካቤ ባለሙያዎችን እና የሚገናኙ መስኮችን ሚናዎች እና ሃላፊነቶች ይተነትናሉ፤ እንዲሁም የሰው ልጅ እድገትን እና ማጎልበትን ከፍ የሚያደርጉ ልምዶችን ይገመግማሉ።

እነዚህ ባለሙያዎች እንዴት የልጅ ጤናማ እድገት እና መጎልበት ፍላጎቶችን እንደሚያሟሉ ተማሪዎች እንዲሁ ትኩረት ይሰጣሉ።

ተማሪዎች ወደላቀ የጨቅላ ልጅነት ትምህርት ኮርስ ለመሸጋገር ኮርሱን C ወይም የተሻለ በማምጣት ማለፍ ይገባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የምግብ አሰራር ስነጥበባት II

ተማሪዎች በክላሲካል የአበሳሰል ዘዴዎች ላይ (መፍላት፣ መጥበስ፣ ጥልቅ የስብ አጠባበስ፣ እንፋሎት ማድረግ፣ ማደን፣ መጥበስ) እና የልዩ ምግቦች፣ የብሄረሰብ ምግብ አበሳሰል፣ የ U.S. ክልላዊ የምግብ አበሳሰል፣ ሾርባ፣ ወጦች እና ሳላዶች ዝግጅት ላይ ትምህርት ያገኛሉ። ተማሪዎች በመሰረታዊ የእርሾ ዱቄት መጋገር፣ በመጋገሪያ እና በቀላል የኬክ ማስዋብ ውስጥ ትምህርት እንዲሁ ያገኛሉ። ተማሪዎች ይህንን ኮርስ ሲያጠናቅቁ የ ServSafe Food Safety እና NOCTI Cook II የኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀቶችን ይወስዳሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የምግብ አሰራር ስነጥበባት መግቢያ I

### ባለሁለት ምዝገባ የላቀ የጨቅላ ልጅነት ትምህርት እና አገልግሎቶች II

የዚህ ክፍል ዋና ትኩረት ለ Child Development Associate (CDA) ምስክርነት በተግባር በተደገፈ፣ የመስክ ላይ የጨቅላ ልጅነት ትምህርት ተሞክሮ(ተሞክሮዎች) በኩል ለማመልከት ደረጃዎችን ማጠናቀቅ ነው። የጥልቀት ትኩረት በትምህርት እና ስልጠና እንዲሁም በስራ ፈጠራ እድሎች፣ በጥልቀት ማሰብ እና ተግባራዊ ችግር መፍታት በጨቅላ የልጅነት ትምህርት ላይ ይገኛል። ተማሪዎች የክፍል መመሪያን እና የስራ ላይ ማማከርን በተፈቀደ ቦታ ላይ ከተከታታይ ማማከር ጋር በትምህርት አመቱ በሙሉ ያጣምራሉ። ተማሪዎች በአሌክሳንድሪያ ከተማ ህዝባዊ ት/ቤቶች የቀን እንክብካቤ ክፍሎች ውስጥ እንዲሁ የመስራት እድል አላቸው። የተማሪ ተሞክሮዎች የሚያጠቃልሉት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደቡት፤ በእድገት ደረጃ አግባብ የሆኑ የትምህርት እቅዶችን መንደፍ እና የሁሉንም ተማሪ አስፈላጊ ነገሮች እና ፍላጎቶች ማሟላት፤ የልጅ ቁጥጥር እና ክትትል፤ የመዝገብ አያያዝ፤ እንዲሁም የጥቆማ ሂደቶች ናቸው። ተማሪዎች በሳምንታዊ ትምህርቶች፣ የዓደኛ እይታዎች እና ከእንግዳ ተናጋሪዎች ያሉ ዝግጅቶች ላይ እንዲሁ ይሳተፋሉ። ኮርሱ ተማሪዎችን ከት/ቤት ወደ ስራ ለሚያደርጉት ሽግግር ያዘጋጃቸዋል እና ከታዳጊ ልጆች ጋር አብረው ለመስራት እውነተኛ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች ይመከራል። አዎንታዊ አመለካከት፣ መልካም የስራ ባህል (በት/ቤት ውስጥ እና በስራ ላይ)፣ እና በትክክል በቦታው ላይ መገኘት ያስፈልጋል። ተማሪዎች የራሳቸውን የዘመነ የሳንባ ነቀርሳ (TB) ክትባት እንዲወስዱ፣ CPR እና በጣቢያ ላይ የሚሰጠውን የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና እንዲያጠናቅቁ እና በስልጠና ጣቢያቸው ለመስራት የጀርባ ታሪክ ፍተሻ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። ተማሪዎች የ National Occupational Competency Testing Institute (NOCTI) ኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀትን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ። ተማሪዎች የዚህ ምስክር ወረቀት ፈተና በስኬት ማለፍ ጋር ተያይዞ ሶስት የኮሌጅ ክሬዲቶች ሊቀበሉ ይችላሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

**የምግብ አሰራር ስነጥበባት መግቢያ I**

ይህ ኮርስ በእንግዳ አቀባበል/የምግብ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ ተማሪዎችን ለመግቢያ ደረጃ ቅጥር ያዘጋጃል። ተማሪዎች መሰረታዊ የባለሙያ የምግብ አሰራር ክህሎቶች፣ የመጋገር፣ የምግብ አገልግሎት ንጽህና፣ የማድቤት ደህንነት፣ የምግብ ዝግጅት፣ የጠረጴዛ አገልግሎት እና የሜኑ እቅድ አወጣጥን ይማራሉ። ተማሪዎች ለስኬታማ ቅጥር እንዲሁ የቢዝነስ ክህሎቶችን ያገኛሉ እና ግብ በማስቀመጥ እና በሙያ እድገት እንቅስቃሴዎች በኩል ያጎለብታሉ እና ልምድ ያገኛሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

**የጨቅላ ልጅነት ትምህርት እና አገልግሎቶች መግቢያ I**

ይህ ኮርስ በጨቅላ የልጅነት ትምህርት ሙያ ፍላጎት ላላቸው እና/ወይም በመስኩ የተገናኘ ሙያን በመማር ትምህርታቸውን ለመቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው። ኮርሱ ስለ ህጻናት እድገት ጽንሰ ሃሳቦች እና መርሆዎች፣ የአሁን የጨቅላ ህጻናት የትምህርት ጉዳዮች፣ በልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የሚሰሩ አስተማሪዎችን ሚና፣ የምዘና/ የማስተዋል ክህሎቶች እና የሚያድግ ተገቢ የሆነ ካሪኩላ እና ትምህርቶችን ለተማሪዎች ያስተዋዉቃል። በአሁን ሰአት ፕሮግራሙ ከ Campagna Center of Alexandria, Virginia ጋር አጋርነት ፈጥሯል ይህም በካምፓስ እና በማህበረሰብ ውስጥ ባለው የአገልግሎቶች ቤተሰቦች ላይ ይገኛል። ተማሪዎች በአሌክሳንድሪያ ከተማ ህዝባዊ ት/ቤቶች የቀን እንክብካቤ ክፍሎች ውስጥ እንዲሁ የመስራት እድል አላቸው። ተማሪዎች በተግባር ላይ አሰሳ እና በልዩ ፕሮጀክቶች ቡድኖች በኩል በሙያ ማጎልበት እና ሙያዎች ጋር በተገናኙ የቀደምት ልጅነት ሙያዎች ላይ ያተኩራሉ። የክፍል ውስጥ ትምህርትን በእኛ የጣቢያ ላይ የቅድመ ትምህርት ቤት ላብራቶሪ የአገልግሎት መማሪያ እድልን በመጠቀም፣ ተማሪዎች በዚህ አመት ሁለተኛው ሩብ አመት ርዝመት ኮርስ ከስድስት ሳምንት እስከ አምስት አመት ከሚሆናቸው ታዳጊ ልጆች ጋር አብረው ይሰራሉ። ተማሪዎች የራሳቸውን የዘመነ የሳንባ ነቀርሳ (TB) ክትባት እንዲወስዱ፣ CPR እና በጣቢያ ላይ የሚሰጠውን የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> ተማሪዎች የጨቅላ ልጅነት ትምህርት I ኮርስ መግቢያን በ GPA 2.0 ወይም ከዚያ በተሻለ በማለፍ ወደ ባለሁለት ምዝገባ/የላቀ የጨቅላ ልጅነት ትምህርት II ኮርስ መሸጋገር አለባቸው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**አስተማሪዎች ለነገ**

Virginia Teachers for Tomorrow (VTfT) የተማሪ ፍላጎትን፣ ግንዛቤን እና የማስተማር ሙያ ማድነቅን ለማጠናከር የተነደፈ ነው እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በትምህርት ውስጥ ያሉትን ሙያዎች እንዲያስሱ ይፈቅዳል። ተማሪዎች ለማስተማር መሰረት ይገነባሉ፤ የማስተማርን ታሪክ፣ አወቃቀር እና አገዛዝ ይማራሉ፤ በ VTfT ክፍል ውስጥ እና በመስክ ተሞክሮ ሙያዊ የማስተማር ቴክኒኮችን ይተገብራሉ፤ እና በማስተማር ተሞክሯቸው ላይ ያንጸባርቃሉ። ተጨማሪ ትምህርታዊ የመሪነት እድሎች የተማሪ አደራጅ በሆነው የ Educators Rising በኩል ቀርቧል። ተማሪዎች ከጣቢያ ውጪ ክትትል የሚደረግበት ልምምድ ውስጥ እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የጨቅላ ልጅነት ትምህርት እና አገልግሎቶች I መግቢያ ቅድመ ሁኔታዎች ለዚህ ኮርስ የቨርጂኒያ ትምህርት ክፍል መመሪያዎችን ይከተላል ይህም የሚያካትተው፦ 1. ተማሪው ግዴታ 2.5 GPA ማምጣት አለበት። የማመልከቻ ሂደት 3ትን ያጠናቅቁ። ሶስት የአስተማሪ ድጋፎችን (የአሁን እና የቀድሞ) እና 4 ያስገቡ። በዚህ ኮርስ ውስጥ የእነርሱን ፍላጎት የሚዘረዝር ዝርዝር ጽሁፍ ያስገቡ። ሁሉም ተማሪዎች የመግቢያ ኮርስ የሆነውን "የጨቅላ ልጅነት ትምህርት መግቢያ"ን የወሰዱ መሆን አለባቸው። 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ብቻ

# CTE: ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የተማሪ የመምሪያ ክህሎቶች በት/ቤት በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የሰራተኛን እንቅስቃሴዎች በመከታተል፣ በኢንተርንሺፖች፣ በክሊኒካዊ ተሞክሮዎች እና/ወይም በ Health Occupations Student Association (HOSA) ላይ በመሳተፍ ሊሻሻሉ ይችላል። ተማሪው ተጨማሪ ክሬዲት ለህብረት ስራ ትምህርት ተሞክሮው ሊቀበል ይችላል።

ተማሪዎች በ T.C. Williams በሚገኘው የገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ ከ George Washington School of Medicine and Health Science ጋር በጋራ በቀረቡት ኮርሶች ላይ የማመልከት እድል እንዲሁ አላቸው። ለበለጠ መረጃ ይህንን ገጽ ይመልከቱ።

**ባለሁለት ምዝገባ የባዮቴክኖሎጂ መሰረቶች በጤና እና በህክምና ሳይንሶች ውስጥ**

ይህ በባዮቴክኖሎጂ እና በጤና ኢንፎርማቲክስ ተርታ የመጀመሪያው የኮርስ መንገድ ነው፣ እና የ STEM ፕሮግራም አካል ከሆነው ከባዮቴክኖሎጂ ኮርስ ጋር በጥምረት ምዝገባ ይካሄዳል። ኮርሱ ህይወት ያላቸው ነገሮችን ወይም አካሎቻቸውን ለመቀየር፣ አትክልቶችን እና እንስሳትን ለማሻሻል እና ለተወሰኑ አላማዎች የረቂቅ ተህዋስያን እድገት ላይ የሚጠቅሙ በርካታ ቴክኒኮች ላይ ያተኩራሉ። የተማሪ እንቅስቃሴዎች ከባዮፕሮሰሲንግ እስከ DNA ትንታኔ፣ እስከ ህክምና፣ ባዮሜካኒካል ስርአቶች እና አካባቢው ድረስ ይከልላል። ተማሪዎች ስለ ባዮቴክኖሎጂ የስራ አይነቶች ግንዛቤዎች እና መረዳትን ያገኛሉ። ተማሪዎች ከ George Washington University ጋር ለልዩ ፕሮጀክቶች በጋራ የመስራት እድል ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ መመዝገብ ወይም ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት

### ባለሁለት ምዝገባ የድንገተኛ ሚዲካል ቴክኒሻን I እና II

ይህ በድንገተኛ የሜዲካል አገልግሎቶች ተከታታይ ውስጥ የሚሰጥ የመጀመሪያ መንገድ ነው፣ ተግባራቱ የሚወክሉት የሃገራዊ እና የ Emergency Medical Services (EMS) ሃገራዊ ደረጃዎችን ነው። በመጀመሪያው ሴሚስተር ድንጋጤን፣ የደረት መግፋት የነፍስ ማዳን ስራን እና ስቃይን ጨምሮ የታካሚን እንክብካቤ ክህሎቶችን በመገምገም እና በማስተዳደር፣ ተማሪዎች የ EMS፣ አናቶሚ፣ ፊዚዮሎጂ እና የሜዲካል ቃላትን ያስሳሉ እንዲሁም ይተገብራሉ። በሁለተኛው ሴሚስተር ውስጥ ተማሪዎች በእውቀታቸው እና በክህሎቶቻቸው ላይ በ EMS ክንውኖች፣ የሜዲካል አስቸኳይ ጊዜያት እና ልዩ የታካሚ ቁጥሮች ላይ ትኩረት በማድረግ መሰረታዊ የህይወት ድጋፍን በማቅረብ ይገነባሉ። ከት/ቤት ሰአታት ውጪ ቢያንስ 10 የታካሚ ግንኙነቶችን ያካተተ ክትትል የሚደረግበት የመስክ ልምድ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ዩኒፎርም እንዲለብሱ ሊጠየቁ ይችላሉ እና ተጨማሪ ክፍያዎጭ ሊጠየቁ ይችላሉ።

በቨርጂኒያ ኮድ 12VAC5-31-1501 መሰረት ተማሪዎች ቢያንስ 85% የዳይዳክቲክ እና የላብ ኮርስ እይታዎችን ማጠናቀቅ ይገባቸዋል። ሁሉንም የኮርስ መስፈርቶች እና የአስተማሪ ማረጋገጫ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ የቨርጂኒያ ስቴት ሳይኮሞተር ፈተናን እና የ National Registry of Emergency Medical Technicians (NREMT) የእውቀት ፈተናን ለመውሰድ ብቁ ሊያደርግ ይችላል። ተማሪዎች ለመሰረታዊ የህይወት ድጋፍ አቅራቢ (በቨርጂኒያ ኮድ ውስጥ EMS.TR.14B እና 12VAC5-31-1501 ያለውን ያጣቅሱ) ያሉትን የተግባራዊ ቦታ መግለጫ መስፈርቶች ማሟላት ይገባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ መመዝገብ ወይም ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት

### ባለሁለት ምዝገባ የድንገተኛ ሜዲካል ቴክኒሻን III

ይህ ኮርስ የ ባለሁለት ምዝገባ የድንገተኛ ጊዜ የሜዲካል ቴክኒሺያን I እና II ላጠናቀቁ፣ የአስተማሪ ፈቃድ ያገኙ እና ከቨርጂኒያ Office of Emergency Medical Services (OEMS) የ EMT የምስክር ወረቀት ሊያገኙ የቻሉ ተማሪዎች የታለመ ነው። ተማሪዎች በ emergency medical services (EMS) ትምህርት መሰረቶች ላይ ይገነባሉ እና ለምስክር ወረቀት ወይም ለዳግም ምስክር ወረቀት የትምህርት መስፈርቶችን ያሟላሉ። ተማሪዎች እንደ እሳት ቁጥጥር፣ የህግ አፈጻጸም እና የድንገተኛ ጊዜ አስተዳደር ያሉ ሌላ ህዝባዊ የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች ጋር ስለመጣመር እንዲሁ ይማራሉ። ኮርሱ ስልጠና የተሰጥረባቸው እንዲሁም የተመሩ ተሞክሮዎችን አካትቷል። ተማሪዎች የኮርሱን ትምህርታዊ እና የላብራቶሪ ገጽታዎችን ቢያንስ 85% ማጠናቀቅ አለባቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ባለሁለት ምዝገባ የድንገተኛ ሚዲካል ቴክኒሻን I እና II

### ባለሁለት ምዝገባ የጤና ኢንፎርማቲክስ

ተማሪዎች የኤሌክትሮኒክ ጤና እንክብካቤ መረጃ ደህንነትን የማስጠበቅ አስፈላጊነት ላይ የማሰስ እድል ያገኛሉ። ተማሪዎች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለውን የጤና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT)፣ የ Electronic Health Record (EHR)፣ ቴሌሜዲስን፣

ስነምግባራዊ እና ግላዊ ጉዳዮች እንዲሁም የሳይበር ደህንነት እና የውሂብ መጣስን ያዘሉ የጤና ኢንፎርማቲክስን ገጽታዎች ያስሳሉ። ተማሪዎች የጤና እንክብካቤ ኢንዱስትሪ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ በርካታ ቴክኖሎጂዎችን እና አዝማሚያዎችን ይተዋወቃሉ። የጤና ኢንፎርማቲክስ ከ 2012-2024 ድረስ በቨርጂኒያ ስቴት ውስጥ የ 21% የሰራተኞች ፍላጎት መጨመር የሚያሳይ እያደገ ያለ ፈጣን መስክ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ወይም በ STEM አካዳሚ መመዝገብ፣ ወይም የጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ወይም የሳይበር ደህንነት መሰረቶችንማጠናቀቅ፣ እና የኮሌጅ ባለሁለት መስፈርቶችን ማሟላት

**ባለሁለት ምዝገባ የጤና እና የህክምና ሳይንሶች መግቢያ**

ይህ በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ ለተማሪዎች የመግቢያ ኮርስ ነው እና ከ The George Washington University School of Medicine and Health Sciences ጋር በመተባበር ለኮሌጅ ክሬዲት ይሰጣል። ይህ ኮርስ ተማሪውን ለበርካታ የጤና እንክብካቤ ሙያዎች በማስተዋወቅ በሁሉም የጤና እና የሜዲካል ሳይንሶች የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ርዕሶች የሚያካትቱት፤ አካላዊ ቴራፒ፣ የመተንፈሻ ቴራፒ፣ የጥርስ ቴክኒሺያን፣ ፋርማሲስት፣ የፋርማሲ ቴክኒሺያን፣ ሜዲካል ረዳት፣ ኢኬጂ ቴክኒሺያን፣ ሃኪም እና ሌሎችንም ነው። ተማሪዎች የሰው ፍላጎቶች፣ ጽንሰ ሃሳብ፣ አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ፣ የሜዲካል ቃላት፣ ወሳኝ ምልክቶችን እንዴት እንደሚለካ፣ ለስኬት ያሉ የስራ ክህሎቶች እና የስራ ፍለጋን እንዴት እንደሚከናወን ይማራሉ። የመስክ ጉዞዎች የሚያካትቱት ወደ GW ጉዞዎች፣ አካባቢያዊ ሆስፒታሎች እና/ወይም ሌላ የህክምና ግንኙነት ያላቸው ስፍራዎችን መጎብኘት ነው። ተማሪዎች የመጀመሪያ እርዳታን እንዲሁም የ CPS የምስክር ወረቀትን እንዲሁ ሊያገኙ ይችላሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ለገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ተቀባይነት አግኝቷል እና የበጋ የማገናኛ የኮሌጅ መዘጋጃ ፕሮግራምን አጠናቅቋል

**ባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ I**

ይህ በሜዲካል ላብራቶሪ ሳይንሶች ተርታ የመጀመሪያው መንገድ ኮርስ ነው። ተማሪዎች በህክምና ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ ውስጥ ለበርካታ የጤና እንክብካቤ የሙያ መንገዶች አግባብ የሆኑ መሰረታዊ እውቀት እና ክህሎቶችን ያገኛሉ። እነሱ የሜዲካል ምርምርን እና ክሊኒካዊ ተሞክሮን የሚደግፉ ለምርመራ እና የቴራፒዩቲክ ላብራቶሪ ሂደቶች ተዋውቀዋል። ከሜዲካል ቴክኖሎጂ መስክ ጋር የተገናኙ የደህንነት፣ የጥራት ማረጋገጫ እና የስነምግባር ጉዳዮችን እንዲሁ ይመረምራሉ። ተማሪዎች ከ George Washington University ጋር ሊተባበሩ እና በየአመቱ በሚዘጋጀው በእነርሱ የ Loudoun ካምፓስ ላይ በባዮሜዲካል ላብራቶሪ ሳይንሶች የበጋ የኢመርዥን የክረምት ፕሮግራም ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ መመዝገብ ወይም ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት

**ባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ II**

ተማሪዎች በባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ I ያገኟቸውን መሰረታዊ እውቀት እና ክህሎቶች ላይ ይገነባሉ። ተማሪዎቹ በሄማቶሎጂ፣ ክሊኒካል ኬሚስትሪ፣ ክሊኒካል ማይክሮባዮሎጂ፣ ኢሚዩኖሄማቶሎጂ እና ኢሚዩኖሎጂ/ሴሮሎጂ አካባቢዎች በብቃት ለመከወን የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መርሆዎችን ይጠቀማሉ። ብቁነት የሚያካትተው የሂደት ቴክኒኮችን በትክክል ማከናወን፣ የሂደቶችን ጽንሰ ሃሳብ መገንዘብ እና ውጤቶችን መተርጎም ይጨምራል። ሳምንታዊ የላብራቶሪ እንቅስቃሴዎች በክሊኒካዊ አወቃቀር በተለመደው መልኩ የሚታዩት በተደጋጋሚ በሚወሰዱት ሙከራዎች የተማሪው ብቁነት ላይ አተኩረው ነው። ተማሪዎች የፊሎቦቶሚ የምስክር ወረቀት ፈተናን ለመውሰድ ተሞክሮ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል። ተማሪዎች ከጣቢያ ውጪ ባሉ ቦታዎች ላይ ለመስራት የሳንባ ነቀርሳን ጨምሮ በክትባቶች ላይ የቅርብ ጊዜን መውሰድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ዩኒፎርሞች እና ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ተማሪዎች ከ George Washington University ጋር ሊተባበሩ እና በየአመቱ በሚዘጋጀው በእነርሱ የ Loudoun ካምፓስ ላይ በባዮሜዲካል ላብራቶሪ ሳይንሶች የበጋ የኢመርዥን የክረምት ፕሮግራም ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ I

**ባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ቃላት**

የሜዲካል ቃላት ኮርስ ተማሪዎች ደህንነቱ ለተጠበቀ የታካሚ እንክብካቤ የተለመዱ የሜዲካል ቃላትን እንዲማሩ ለማድረግ የተነደፈ ነው። ርዕሶች በምክንያታዊ አቀማመጥ ቀርበዋል ይህም ከእያንዳንዱ የአካል ስርዓት አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ በመጀመር ወደ ፓቶሎጂ የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ክሊኒካዊ ሂደቶች፣ቴራፒቲክ ጣልቃገብነቶች እና ፋርማኮሎጂ አልፈዋል። ተማሪዎች ጽንሰ ሃሳቦችን፣ ቃላትን እና የእያንዳንዱን ርዕስ ምህጻረ ቃላትን ይማራሉ። ይህ ኮርስ በ NOVA በኩል ለባለሁለት ምዝገባ ክሬዲት ቀርቧል እና ሁሉም ተማሪዎች ይህንን ኮርስ ለኮሌጅ ክሬዲት መውሰድ ይገባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የጤና እና የሜዲካል ሳይንሶች መግቢያ እና ሁሉንም የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶች ያሟላል

**ባለሁለት ምዝገባ የሜዲካል ቃላት ከአናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ ጋር**

ይህ በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ ሁለተኛው መሰረታዊ ኮርስ ነው። ተማሪዎች ለከፍተኛ ደረጃ የአካዳሚ ኮርሶች የተለመዱ የህክምና ቃላትን እና አናቶሚን እንዲማሩ ይረዳቸዋል። ርዕሶች በምክንያታዊ አቀማመጥ ቀርበዋል ይህም ከእያንዳንዱ የአካል ስርዓት አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ በመጀመር ወደ ፓቶሎጂ፣ የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ክሊኒካዊ ሂደቶች፣ቴራፒቲክ ጣልቃገብነቶች እና ፋርማኮሎጂ አልፈዋል። ተማሪዎች ጽንሰ ሃሳቦችን፣ ቃላትን እና የእያንዳንዱን ርዕስ ምህጻረ ቃላትን ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባለሁለት ምዝገባ የጤና እና የህክምና ሳይንሶች መግቢያ እና የገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ አካል

### ባለሁለት ምዝገባ የነርስ ረዳት I

ይህ በነርሲንግ የመንገድ ተርታ ውስጥ የመጀመሪያው ኮርስ ነው። ይህ 11ኛ ክፍል ደረጃ ላይ የሚጀምረው ከሁለት አመት የስራ ዝግጅት ፕሮግራም የመጀመሪያው አመት ነው። ካሪኩለሙ የነርሲንግ ስራን ከጤና እንክብካቤ ስርዓት ጋር እንደሚገናኝ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ጤናማ እድገት እና መሳልበትን፣ ቀላል የሰውነት አወቃቀር እና አሰራር፣ የህክምና ቃላት፣ የተለመዱ የሰውነት መታወኮች እና በሽታ፣ ስነምግባራዊ እና ህጋዊ ጉዳዮች፣ የደንበኛ መብቶች፣ የግንኙነት እና የእርስ በእርስ ክህሎቶች፣ ደህንነት እና የድንገተኛ ጊዜ እርምጃዎች፣ የነርስ ረዳት ሚና በረጅም ጊዜ እንክብካቤ ውስጥ፣ የጤና እንክብካቤ አወቃቀሮችን እና የኢንፌክሽን ቁጥጥርን ይማራሉ። ለዚህ ኮርስ የሚያስፈልጉ ክህሎቶች እጅ መታጠብ፣ ጋወኖችን መልበስ እና ማውለቅ፣ ማስኮች፣ የደህንነት መነጽሮች እና ጓንቶች። ተማሪዎች የመጀመሪያ እርዳታ እና የ cpr የምስክር ወረቀት እንዲሁ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። በጸደይ፣ ተማሪዎች የነርሲንግ ልምምድ፣ የትምህርታዊ መስፈርቶች፣ ታሪካዊ ትርጉሞች እና የነርሲንግ ሚናዎች እና ሃላፊነቶችን ጨምሮ በርካታ የነርሲንግ ሙያ ገጽታዎችን ይዳስሳሉ። ተማሪዎች ለነርሲን ቤቶች እና ሆስፒታሎች የመስክ ጉዞዎችን ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ ኮርስ ተማሪዎችን ለ ነርስ ረዳት IIያዘጋጃል ይህም የ National Nurse Aide Assessment (NNAAP) ለመውሰድ የሚያስፈልገውን የክሊኒካዊ ተሞክሮን ያካትታል። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ መመዝገብ ወይም ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት

### ባለሁለት ምዝገባ የነርስ ረዳት II

ይህ ኮርስ የስራ ዝግጅት ፕሮግራም ሁለተኛ አመት ሲሆን በካቴተር እንክብካቤ፣ የእንቅስቃሴ ክልል፣ የአንጀት እና የፊኛ ስልጠና፣ የህይወት እንክብካቤ መጨረሻ፣ የህጻናቶች እና የጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ የተመረጡ ሂደቶች እና የማስገባት እና የማስወጣት ሂደቶችን ከፍተኛ የክህሎት ስልጠና ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች የአጣዳፊ ሜዲካል- የቀዶ ጥገና ታማሚ፣ በጠና የታመመ እና እድሜው የገፋ ሰው ከፍተኛ ክሊኒካዊ እንክብካቤ ጋር የተገናኙ በሽታዎችን እና የአካል ስርአቶችን ይማራሉ። ፈቃድ ባለው የነርሲንግ ቤት ውስጥ በስራ ላይ ያለ መመሪያ የኮርሱ ክፍል ነው። የነርስ ረዳት ፕሮግራምን በማጠናቀቅ፣ ተማሪው በሆስፒታሎች እና በነርሲንግ ቤቶች ውስጥ የተመሰከረለት የነርስ ረዳት ሆኖ ለመቀጠር የሚመራውን የነርስ ረዳት የምስክር ወረቀት ፈተና ለመውሰድ ብቁ ይሆናል። ተማሪዎች ለፈቃድ ማግኘት ፈተና የሚያስፈልጉትን የፕሮግራም ሰአታት እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ። በክሊኒካዊ ተሞክሯቸው ተማሪዎች ዩኒፎርም እንዲያደርጉ እና የአለባበስ ደረጃዎችን እንዲያከብሩ ይጠየቃሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባለሁለት ምዝገባ የነርስ ረዳት I

**ባለሁለት ምዝገባ የስፖርት ህክምና I**

ይህ በስፖርት ህክምና ተርታ ውስት የመጀመሪያው የኮርስ መንገድ ነው፤ ተማሪዎች በመጀመሪያ እርዳታ/ CPR/AED ውስጥ የምስክር ወረቀት ሊያገኙ ይችላሉ ኮርሱ እንደ ሰው አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ እንዲሁም የሜዲካል ቃላትን ያሉ የተማረ እውቀትን ያሰፋል እንዲሁም የአመጋገብ፣ የባዮሜካኒክስ፣ የጉዳቶች እና የህመሞች እንዲሁም በስፖርት ህክምና ውስጥ ያሉ ህጋዊ እና ስነምግባራዊ ጉዳዮችን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች በስፖርት ህክምና መስክ ውስጥ ያሉ የወደፊት ስራዎችን እንዲሁ ይመረምራሉ። ተማሪዎች የ ACPS አትሌቲክ ሰልጣኞችን በትምህርት አመቱ በተለያዩ ክስተቶች ሙያተኞች እንዲያሳዩአቸው እና እንዲረዷቸው እድል ሊኖቻቸው ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ ውስጥ መመዝገብ ወይም ጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት

**ባለሁለት ምዝገባ የስፖርት ህክምና II**

ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ ተማሪዎች የ National Academy of Sports Medicine- Certified Personal Trainer (NASM-CPT) ፈተናን ለመውሰድ ብቁ ይሆናሉ። ይህ ኮርስ በስፖርት ህክምና I ላይ እንደ እንቅስቃሴ ፊዚዮሎጂ፣ ባዮሜካኒክስ፣ የእንቃስቃሴ ፕሮግራም ንድፍ እና የጉዳት መከላከል፣ ምዘና፣ ህክምና እና አስተዳደር ያሉ ርዕሶች ላይ ባለ መሰረታዊ እውቀት ላይ ይገነባል። ተማሪዎች ልምምድ ማጠናቀቅን ጨምሮ ለስፖርት ህክምና ስራ ይዘጋጃሉ። ተማሪዎች በትምህርት አመቱ በሚኖሩት በርካታ ክስተቶች ላይ የ ACPS አትሌቲክ አሰልጣኞችን በባለሙያ ለማሳየት እና ለመርዳት እድሎች ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ባለሁለት ምዝገባ የስፖርት ህክምና I

**ባለሁለት ምዝገባ የቀዶጥገና አገልግሎቶች I**

ይህ በቀዶ ጥገና ተርታ የመጀመሪያው መንገድ ኮርስ ነው። ተማሪዎች የስቴራይል ሂደቶችን እውቀት ያገኛሉ። ይህ ኮርስ በጤና እንክብካቤ ፋሲሊቲ ከጀርም ነጻ የሆኑ መሳሪያዎችን፣ እቃን እና አቅርቦቶችን ከጀርም ነጻ ማድረግ እና ማከፋፈል ላይ ያተኩራል። የተማሪ መመሪያ በስቴራይል የማቀነአበሪያ ክፍል እና በማእከላዊ የአገልግሎት ስፍራ ውስጥ ባለ ስራ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተማሪዎች ስቴራላይዜሽን እና ክምችትን ለመጠበቅ እንደ ቡድን ይሰራሉ፣ ስለማይክሮባዮሎጂ እና የኢንፌክሽን ቁጥጥር ይማራሉ እንዲሁም የስቴራይል ማቀናበርን እና የተበከለውን ማጽዳት መርሆዎችን እና ልምዶችን ይተገብራሉ። በኮርሱ ውስጥ የተካተቱት በአናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ፣ የቀዶ ጥገና ሂደቶች፣ የጤና እንክብካቤ መሳሪያ እና የአቅርቦት ሰንሰለት ማስተዳደር ክፍሎች ናቸው። ተማሪዎች ለስቴራይል የማቀነባበሪያ ቴክኒሻኖች አለም አቀፍ የምስክር ወረቀት ለመቀመጥ እንዲዘጋጁ የ 400 ሰአት ኤክስተርንሺፕን ለመጀመር ሊመርጡ ይችላሉ። ሙሉ የምስክር ወረቀት 400 ሰአታትን ካጠናቀቁ እና ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምረቃ በኋላ ይሰጣል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ መመዝገብ ወይም የጤና እና ሜዲካል ሳይንሶች መግቢያን ማጠናቀቅ እና የኮሌጁን ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶች ማሟላት

**ባለሁለት ምዝገባ የቀዶጥገና አገልግሎቶች II**

ይህ በቀዶ ጥገና አገልግሎቶች ተርታ ውስጥ ሁለተኛው ኮርስ ነው። ተማሪዎች በቀዶ ጥገና አገልግሎቶች I የተማሯቸውን ክህሎቶች ያሰፋሉ እና የፔሪዮፓቲቭ ሂደትን ይረዳሉ። የጤና ባለሙያዎች በክንውን ክፍል ውስጥ ከሚያደርጉት አስተዋጽዎ ጋር የሚሰራ እውቀት እና የሚናዎች ግንዛቤን ተማውዎች ያገኛሉ። ተማሪዎች ለቀዶ ጥገና ታካሚ የሚቀርበውን የተሻለውን እንክብካቤ ለማቅረብ ምን እንደሚያስፈልግ ይማራሉ። ትምህርቱ የቀዶ ጥገና ሂደቶች፣ የቀዶ ጥገና መሳሪያዎች፣ ስቴራይል ቅንብሮች፣ የቀዶ ጥገና እውቀት፣ የቀዶ ጥገና አሴፕሲስ እና በክንውን ክፍሉ ውስጥ ደህንነት እና ውጤታማነት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ቀድሞ የጀመሯቸውን በውጪ ያላቸውን ልምምድ ማጠናቀቅ፣ ከዚህ ኮርስ ወደ አሶሲዬት ወይም ተማሪዎች ለቀዶ ጥገና ቴክኖሎጂስት የፈቃድ ፈተና እንዲቀመጡ ወደሚያዘጋጃቸው ፕሮግራም መተላለፍ፣ ወይም ከፍተኛ ዲግሪን መከታተል ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 3

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

DE ስቴራይል ሂደት

**የጤና እና የሜዲካል ሳይንሶች መግቢያ**

ይህ ኮርስ ተማሪውን ለበርካታ የጤና እንክብካቤ ሙያዎች በማስተዋወቅ በሁሉም የጤና እና የሜዲካል ሳይንሶች የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ርዕሶች የሚያካትቱት አካላዊ ቴራፒ፣ የመተንፈሻ ቴራፒ፣ የጥርስ ቴክኒሺያን፣ ፋርማሲስት፣ የፋርማሲ ቴክኒሺያን፣ ሜዲካል ረዳት፣ ኢኬጂ ቴክኒሺያን፣ ሃኪም እና ሌሎችንም ነው። ተማሪዎች የሰው ፍላጎቶች፣ ጽንሰ ሃሳብ፣ አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ፣ የሜዲካል ቃላት፣ ወሳኝ ምልክቶችን እንዴት እንደሚለካ፣ ለስኬት ያሉ የስራ ክህሎቶች እና የስራ ፍለጋን እንዴት እንደሚከናወን ይማራሉ። የመስክ ጉዞዎች የሚያካትቱት አካባቢያዊ ሆስፒታሎችን እና/ወይም ሌላ የህክምና ግንኙነት ያላቸው ስፍራዎችን መጎብኘት ነው። ተማሪዎች የመጀመሪያ እርዳታን እንዲሁም የ CPS የምስክር ወረቀትን እንዲሁ ሊያገኙ ይችላሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11

# CTE: Junior Reserve Officers' Training Corps (JROTC)

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

**JROTC I**

የ Junior Reserve Officers Training Corps (JROTC) ፕሮግራም ዩኒፎርም የለበሰ ድርጅት ሲሆን ይህም አንድ ካዴት እንዴት የታዘዘ ዩኒፎርም እንደሚያደርግ እና ግለሰባዊ አለባበሱን እንደሚጠብቅ በከፊል ይዳኛል። ስለዚህ፣ በሁሉም ካዴቶች ንጹህ እና በደንብ የተያዘ መልክ ለ JROTC መሰረታዊ ነው እና ለውጤታማ የካዴትስ ክፍሎች አስፈላጊ የሆነው የሞገስ እና ጥበብ ግንባታ ላይ አስተዋጽዎ ያደርጋል።

ማስታወሻ: ሁሉም ካዴቶች ለካዴት መመሪያ ደንብ 145-2፣ በቀን ፌብሩዋሪ 2012 የነበረውን ያከብራሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**JROTC II**

የ Junior Reserve Officers Training Corps (JROTC) ፕሮግራም ዩኒፎርም የለበሰ ድርጅት ሲሆን የሚዳኘውም አንድ

ካዴት እንዴት የታዘዘ ዩኒፎርምን በከፊል እንደሚያደርግ እና ግላዊ እይታውን እንደሚጠብቅ ነው። ስለዚህ፣ በሁሉም ካዴቶች ንጹህ እና በደንብ የተያዘ መልክ ለ JROTC መሰረታዊ ነው እና ለውጤታማ የካዴትስ ክፍሎች አስፈላጊ የሆነው የሞገስ እና ጥበብ ግንባታ ላይ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ማስታወሻ: ሁሉም ካዴቶች ለካዴት መመሪያ ደንብ 145-2፣ በቀን ፌብሩዋሪ 2012 የነበረውን ያከብራሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**JROTC III**

የ Junior Reserve Officers Training Corps (JROTC) ፕሮግራም ዩኒፎርም የለበሰ ድርጅት ሲሆን የሚዳኘውም አንድ ካዴት እንዴት የታዘዘ ዩኒፎርምን በከፊል እንደሚያደርግ እና ግላዊ እይታውን እንደሚጠብቅ ነው። ስለዚህ፣ በሁሉም ካዴቶች ንጹህ እና በደንብ የተያዘ መልክ ለ JROTC መሰረታዊ ነው እና ለውጤታማ የካዴትስ ክፍሎች አስፈላጊ የሆነው የሞገስ እና ጥበብ ግንባታ ላይ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ማስታወሻ: ሁሉም ካዴቶች ለካዴት መመሪያ ደንብ 145-2፣ በቀን ፌብሩዋሪ 2012 የነበረውን ያከብራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1-4

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**JROTC IV**

የ Junior Reserve Officers Training Corps (JROTC) ፕሮግራም ዩኒፎርም የለበሰ ድርጅት ሲሆን የሚዳኘውም አንድ ካዴት እንዴት የታዘዘ ዩኒፎርምን በከፊል እንደሚያደርግ እና ግላዊ እይታውን እንደሚጠብቅ ነው። ስለዚህ፣ በሁሉም ካዴቶች ንጹህ እና በደንብ የተያዘ መልክ ለ JROTC መሰረታዊ ነው እና ለውጤታማ የካዴትስ ክፍሎች አስፈላጊ የሆነው የሞገስ እና ጥበብ ግንባታ ላይ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ማስታወሻ: ሁሉም ካዴቶች ለካዴት መመሪያ ደንብ 145-2፣ በቀን ፌብሩዋሪ 2012 የነበረውን ያከብራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1-4

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# CTE: ማርኬቲንግ

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የተማሪ የመምሪያ ክህሎቶች በት/ቤት በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የሰራተኛን እንቅስቃሴዎች በመከታተል፣ በኢንተርንሺፖች፣ በህብረት ስራ ትምህርት እና/ወይም በ DECA ላይ በመሳተፍ ሊሻሻሉ ይችላል። የህብረት ስራ ትምህርት ዘዴ ለሁሉም የሙሉ አመት የቢዝነስ ኮርሶች ይገኛል። የተሳታፊ ተማሪ የክፍል መመሪያን እና በትምህርት አመቱ በሙሉ ቢያንስ 396 የስራ ላይ በተፈቀደ ባለሙያ ክትትል ካለው ማማከር ጋር የሚሰጥ ስልጠናን አጣምሮ ይዟል። ተማሪው ለእርሱ ወይም ለእርሷ የህብረት ትምህርት ተሞክሮ ተጨማሪ ክሬዲት ሊቀበል ይችላል ወይም ትችላለች።

**የላቀ የፋሽን ማርኬቲንግ II**

ተማሪዎች ለፋሽን ማርኬቲንግ እና ለላቁ ጠቅላላ የማርኬቲንግ ክህሎቶች ልዩ የሆኑ ለአልባሳት እና ለመለዋወጫ ኢንዱስትሪ የሚተገበሩ የላቁ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች የባለሙያ አሻሻጥን፣ የሽያጭ ማስታወቂያን እና ግዢን እንዲሁም መሸጫ እና የገበያ ጥናትን ይማራሉ። የምርት አገልግሎት ቴክኖሎጂ እና ማማከር አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። ተማሪዎች በላቀ የማርኬቲንግ ስራዎች እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ በሚሰጥ ትምህርት ይዘጋጃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የፋሽን ማርኬቲንግ I

**የላቀ ማርኬቲንግ II**

ይህ ኮርስ በማርኬቲንግ መስክ ውስጥ ጥልቅ የሆነ ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች በግብይት ድብልቅ፣ መግዛት፣ ፋይናንስ ማድረግ፣ የሰው ሃይል፣ አለም አቀፍ ግብይት፣ ዋጋ እና እየመጡ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ በማተኮር በማማከር እና የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በላቀ የማርኬቲንግ ስራዎች እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ በሚሰጥ ትምህርት ይዘጋጃሉ። ተማሪዎች የ National Retail Federation Customer Service ወይም ሽያጭ ፈተናን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ማንኛዉም የማርኬቲንግ ኮርስ

**ባለሁለት ምዝገባ የላቀ የስራ ፈጠራ**

ይህ ኮርስ በላቀ የስራ ፈጠራ ስትራቴጂዎች ላይ ለማተኮር ለሚመኙ ተማሪዎች የተነደፈ ነው። የኮርሱ ትኩረት በቢዝነስ እቅድ ላይ እና የትናንሽ ቢዝነስ ማኔጅመንት እድገት ላይ ነው። ተማሪዎች ቢዝነስ ይመሰርታሉ፣ ይገበያያሉ እንዲሁም ይይዛሉ። ተማሪዎች የአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መደብርን የመያዝ፣ የማስተዋወቅ እና የማሳደግ ሃላፊነትን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ባለሁለት ምዝገባ የስራ ፈጠራ፡- ቢዝነስ ማኔጅመንት እና አስተዳደር፣ እና ሁሉንም የኮሌጅ ምደባ መስፈርቶች ያሟላል

**ባለሁለት ምዝገባ የስራ ፈጠራ፡- ቢዝነስ ማኔጅመንት እና አስተዳደር**

ይህ ኮርስ ከ National Foundation for Teaching Entrepreneurship (NFTE) ጋር በመተባበር ቀርቧል። የስራ ፈጠራ ለተማሪዎች የተለየ ኮርስ ሲሆን ፍላጎቱም አንድ ቀን ባለቤት መሆንና የራሳቸውን ቢዝነሶች ማስተዳደር ነው። ኮርሱ የቢዝነስ ድርጅትን፣ ህጋዊ እና የአካውንቲንግ ግምት ውስጥ የሚገቡ ነገሮችን፣ የአካባቢ ምርጫን፣ ፋይናንሲንግ እንዲሁም ማርኬቲንግ ማወቅ ላይ የሚጠይቁ የቢዝነስ እቅድ ማጎልበት ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች የቢዝነስ እቅዳቸውን ለማጎልበት ከባለሙያ አማካሪዎች ጋር በጋራ ይሰራሉ እና በአካባቢ፣ በክልል እና በሃገራዊ ውድድሮች ላይ የቢዝነስ እቅዳቸውን ለማሳየት እድል ይኖራቸዋል፦፤

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪዎች ሁሉም የኮሌጅ ምደባ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።

**ትምህርት ለመቀጠር I**

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ከት/ቤት ሲሸጋገሩ፣ የቴክኒካዊ ክህሎቶችን ሲያገኙ እና የስራ ቦታን ሲለማመዱ ስለስራዎች እና ቀጣይነት ስላላቸው የትምህርት አማራጮች መረጃ እንዲኖራቸው ያስተምራቸዋል። ተማሪዎች የስነምግባር ባህሪያትን እና የሙያ ምርምርን፣ የስራ ማግኘትን፣ የስራ ቦታ ግንኙነትን፣ የራስ ግንዛቤን፣ የራስ ተሟጋችነትን፣ የደንበኛ አገልግሎትን እና የህይወት ክህሎቶችን ይማራሉ። ተማሪዎች የቨርጂኒያ የስራ ቦታ ዝግጁነት ክህሎቶችን በጥልቀት ያጠናሉ እና የ CTECS የስራ ቦታ ዝግጁነት ክህሎትን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**ትምህርት ለመቀጠር II**

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ከት/ቤት ሲሸጋገሩ፣ የቴክኒካዊ ክህሎቶችን ሲያገኙ እና የስራ ቦታን ሲለማመዱ ስለስራዎች እና ቀጣይነት ስላላቸው የትምህርት አማራጮች መረጃ እንዲኖራቸው ያስተምራቸዋል። ተማሪዎች የስነምግባር ባህሪያትን እና የሙያ ምርምርን፣ የስራ ማግኘትን፣ የስራ ቦታ ግንኙነትን፣ የራስ ግንዛቤን፣ የራስ ተሟጋችነትን፣ የደንበኛ አገልግሎትን እና የህይወት ክህሎቶችን ይማራሉ። ተማሪዎች የቨርጂኒያ የስራ ቦታ ዝግጁነት ክህሎቶችን በጥልቀት ያጠናሉ እና የ CTECS የስራ ቦታ ዝግጁነት ክህሎትን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**የፋሽን ማርኬቲንግ I**

ይህ በአልባሳት እና በመለዋወጫ ማርኬቲንግ እና መሸጫ ውስጥ የሙያ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተለየ ኮርስ ነው። ተማሪዎች እንደ ግላዊ መሸጥ፣ የሽያጭ ማስታወቂያ፣ መግዛት፣ አካላዊ ስርጭት፣ የገበያ እቅድ አወጣጥ እና የምርት/የአገልግሎት ቴክኖሎጂ የመሳሰሉ በአልባሳት እና በመለዋወጫዎች መስክ ውስጥ ለቅጥር ልዩ የሆኑ ክህሎቶችን ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**የእንግዳ አቀባበል እና የቱሪዝም ማርኬቲንግ**

ይህ ኮርስ መስህቦችን፣ ሎጅ ማድረግን፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴን እና ምግብ እና መጠጥን አካትቶ የእንግዳ ተቀባይነት እና የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ክፍሎችን ይመረምራል። ሌላ ርዕሶች የሚያካትቱት መስተንግዶ እና ቱሪዝም በአካባቢያዊ፣ በስቴት እና አለም አቀፍ አካባቢዎች ላይ የሚያሳድሩት የታሪክ፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ተጽዕኖዎች። ተማሪዎች በግንኙነት አካባቢዎች፣ በደንበኛ አገልግሎት፣ በማርኬቲንግ፣ በኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ እና በማኔጅመንት ስራዎች ላይ ብቃቶችን ያጎለብታሉ እንዲሁም በተግባራዊ የገሃዱ አለም አተገባበሮች ላይ እድሎችን እንዲያገኙ ይደረጋል። ክልላዊ የሰው ሃይል ኢንቨስትመንት ቦርዶች ለተናጋሪው በእነዚያ አካባቢዎች ውስጥ ስለ አካባቢ እድሎች እንዲያወራ ያቀርብለታል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**የፋሽን ስራዎች መግቢያ**

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በአልባሳት፣ መለዋወጫ እና የልብስ ንድፍ፣ ምርት እና የግብይት ኢንዱስትሪ መለየት እና ማሰስ ላይ ያተኮራሉ። የትምህርት ክፍሎች የሚያካትቱት በልብስ ኢንዱስትሪው ውስጥ ባሉት ሁሉም አካባቢዎች ላይ የሚገኙትን ግንኙነቶች፤ የተገናኙ አለም አቀፍ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች፤ አልባሳት፣ መለዋወጫ እና የቴክስታይል ቴክኖሎጂ ፤ በተገናኙ አካባቢዎች ውስጥ ያሉ የስራ ፈጠራ እድሎችን ጨምሮ የሙያዎች ዳሰሳ፤ እና በአልባሳት ሙያዎች ስኬት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶች እና ግላዊ ባህሪያት፣ መለዋወጫ፣ እና ቴክስታይል ንድፍ፣ ምርት እና የማርኬቲንግ ኢንዱስትሪ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10

**ማርኬቲንግ የህብረት ስራ ልምምድ**

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ያገኙትን የክፍል እውቀት ለገሃዱ አለም የስራ ተሞክሮ እንዲተገብሩት ያስችላቸዋል። የኢንተርንሺፕ ተሞክሮ የተማሪውን የሙያ ፍላጎት የሚያንጸባርቅ፣ እና/ወይም ተማሪዎች ዋጋ ያለው የስራ ተሞክሮ እንዲያገኙ እድል የሚሰጥ፣ የቅጥር ክህሎቶችን የሚያሻሽል እና የ 21ኛው ክፍለ ዘመን የስራ ቦታ

ክህሎቶችን የሚያጎለብት ከግብይት ጋር ባለ መስክ ውስጥ ከቅጥር ጋር የግብይት ኮርስን አጣምሮ ይዟል። ይህ ኮርስ ከሌላ የማርኬቲንግ ኮርስ ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ተማሪ ለማርኬቲንግ ኮርስ በጣምራ መመዝገብ አለበት።

### ስፖርት እና የመዝናኛ አስተዳደር

ተማሪዎች ቀደም ብለው በያዟቸው የስፖርት፣ የመዝናኛ እና ጊዜ የማሳለፊያ ማርኬቲንግ እውቀት ላይ ይገነባሉ። ይህ ኮርስ በምርምር፣ በፋይናንስ፣ በኢኮኖሚ፣ በስነምግባር እና በህጋዊ ጽንሰሃሳቦች በሚደገፉ የማኔጅመንት እና የእቅድ አወጣጥ መርሆዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተማሪዎች ለክስተት እቅድ ለማውጣት እና ለማስፈጸም፣ ስፖርቶችን፣ መዝናኛን ወይም የመዝናኛ ግብይት ምርቶችን/ቢዝነስን ለማቋቋም፣ እና የሙያ እቅድ ለማውጣት ይችላሉ። ከይዘቱ ጋር የሚገናኙ የአካዳሚክ ክህሎቶች (ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ እንግሊዝኛ፣ እና ታሪክ/ ማህበራዊ ሳይንስ) የዚህ ኮርስ አካል ናቸው። ኮርሱን የሚደግፉ የኮምፒውተር/የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች ይጠናሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ስፖርት እና የመዝናኛ ማርኬቲንግ

### ስፖርት እና የመዝናኛ ማርኬቲንግ

ይህ በስፖርት ወይም በመዝናኛ ኢንዱስትሪዎች የሙያ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተለየ ኮርስ ነው። መሰረታዊ የማርኬቲንግ ጽንሰ ሃሳቦችን ከመማር በተጨማሪ፣ ኮርሱ እንደስፖንሰርሺፕ፣ ማረጋገጫዎች፣ የዝግጅት እቅድ መንደፍ እና ማስተዋወቅ ያሉ የስፖርት እና የመዝናኛ ማርኬቲንግ መስኮች ውስጥ ለቅጥር የተለዩ እውቀት እና ክህሎቶችን ያቀርባል። ተማሪዎች ከት/ቤት ጋር የተገናኘ የማርኬቲንግ እንቅስቃሴን ያሳድጋሉ እንዲሁም ይተገብራሉ። ተማሪዎች በስፖርት እና በመዝናኛ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ስላሉ የሙያ እድሎች መረጃ እንዲሁ ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

# CTE: የቴክኖሎጂ ትምህርት

ሁሉም የ CTE ኮርሶች ከኢኮኖሚክስ እና ከግላዊ ፋይናንስ በስተቀር በተመራጭ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ

የተማሪ የመምሪያ ክህሎቶች በት/ቤት በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የሰራተኛን እንቅስቃሴዎች በመከታተል፣ በኢንተርንሺፖች እና/ወይም እንደ Skills USA ወይም Technology Student Association (TSA) ባሉ የተማሪ ድርጅቶች ላይ በመሳተፍ ሊሻሻሉ ይችላል። ተማሪው ተጨማሪ ክሬዲት ለህብረት ስራ ትምህርት ተሞክሮው ሊቀበል ይችላል።

**የላቀ የአርክቴክቸራል ስዕል እና ንድፍ II**

ተማሪዎች የአርክቴክቸራዊ ንድፍ መሰረቶችን ያስሳሉ እና የስራ ስዕሎችን፣ የግንባታ ስልቶችን እና የህንጻ ንድፍን የሚቆጣጠሩ ኮዶችን ግንዛቤ ያሳድጋሉ። የንድፍ ሂደትን ይማራሉ እና ለአርክቴክቸራዊ ፕሮጀክቶች የንድፍን አካላት እና መርሆዎችን ይተገብራሉ። የህንጻ ሁሉም አይነት ሞዴሎችን እና ምሳሌዎችን በማምረት፣ ተማሪዎች የአርክቴክቸራል የንድፍ መፍትሄዎችን Computer Aided Drafting and Design (CADD) በመጠቀም ይፈጥራሉ። የኮርስ ተከታታይነቱ በአርክቴክቸር እንዲሁም በቅድመ ቅጥር እና የተሳትፎ ክህሎቶች ውስጥ በባለሙያዎች የሚተገበሩትን ግዴታዎች እና ስራዎች ላይ ያተኩራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቴክኒካል ስዕል እና ንድፍ I

**የላቀ የምህንድስና ስዕል እና ንድፍ I**

ተማሪዎች ለምርት ንድፍ፣ ለስልት ማሳያ፣ መግጠሚያ፣ የፈጠራ ባለቤትነት እና የመዋቅር ስዕሎች የምህንድስና የንድፍ ሂደትን እና የግራፊክ ቋንቋ አጠቃቀምን ያስሳሉ። ተማሪዎች ኮምፒውተሮችን፣ ካልኩሌተሮችን እና የገላጭ ጂኦሜትሪን ይጠቀማሉ እና የንድፍ ችግሮችን ለመፍታት የተመሰረቱ ደረጃዎችን ያከብራሉ። በኮርሱ ቆይታ፣ ተማሪዎች በወደፊት ትምህርታቸው እና ሙያቸው ስለኮርሱ ጥቅሞች ለመማር ሴሚናሮችን ያደርጋሉ፣ መሃንዲሶችን ያገኛሉ እና ቴክኒካዊ የንድፍ ተቋማትን ይጎበኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቴክኒካል ስዕል እና ንድፍ I

**ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ I**

ይህ ኮርስ ስለመብረር፣ የህዋ ጉዞ እና ደጋፊ ቴክኖሎጂዎች መግቢያን ለተማሪዎች ያቀርባል። ተማሪዎች የበረራ ታሪክን፣ ኤሮዳይናሚክስን፣ የአውሮፕላን አካላትን፣ የመብረር ሁኔታዎችን፣ አየር መንገድን እና የበረራ ክንውኖችን፣ ህዋን፣ ሮኬትን እና የበረራ እና የህዋ ኢንዱስትሪዎችን ጨምሮ ተግባራዊ የሆኑ የመማር ጽንሰ ሃሳቦችን አካሄድ ይጠቀማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11

**ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ II**

ይህ ኮርስ የላቀ የበረራ አሰሳን፣ የህዋ ጉዞን እና ደጋፊ ቴክኖሎጂዎችን በችግር መፍቻው ዙሪያ ባሉ ተግባራዊ የአቀራረብ ማዕከል በኩል ያቀርባል። ተማሪዎች አውሮፕላን ክንውኖች ያሉ ጽንሰ ሃሳቦችን ያስሳሉ፤ የአውሮፕላን ንድፍ፣ የበረራ ደህንነት እና ጥገባ፤ የአየር

ማረፊያ መሰረተ ልማት፤ እና small unmanned aircraft systems (sUAS)።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ I

### ባለሁለት ምዝገባ ባዮቴክኖሎጂ እና ፎረንሲክስ መሰረቶች

ይህ ኮርስ የገዢው የጤና ሳይንሶች አካዳሚ አካል በሆነው የ ባለሁለት ምዝገባ የባዮቴክኖሎጂ መሰረቶች በጤና እና በሜዲካል ሳይንሶች ኮርስ ጋር አብሮ ይመዘገባል። ይህ ኮርስ ተክሎችን እና እንስሳትን እና ለተወሰኑ አላማዎች ያሉትን የጥቃቅን ህዋሳት እድገት ለማሻሻል ህይወት ያላቸው ፍጥረታትን ወይም የፍጥረታቱን አካላት ለመቀየር የሚጠቅሙ የተለያዩ ስልቶች ላይ ያተኩራል። የተማሪ እንቅስቃሴዎች ከባዮፕሮሰሲንግ እስከ DNA ትንታኔ፣ እስከ ህክምና፣ ባዮሜካኒካል ስርአቶች እና አካባቢው ድረስ ይከልላል። ተማሪዎች ስለ ባዮቴክኖሎጂ የስራ አይነቶች ግንዛቤዎች እና መረዳትን ያገኛሉ። ተማሪዎች ከ George Washington University ጋር ለልዩ ፕሮጀክቶች በጋራ የመስራት እድል ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባዮሎጂ I

ኬሚስትሪ I

የኮሌጅ ባለሁለት ምዝገባ መስፈርቶችን ያሟሉ

### ባለሁለት ምዝገባ የምህንድስና መግቢያ

ይህ በ NOVA በኩል የሚሰጠው የመግቢያ የምህንድስና ኮርስ ቢያንስ 2 የኮሌጅ ክሬዲቶችን ለተማሪዎች ያቀርባል። የምህንድስና ሙያን፣ ሙያዊ ጽንሰ ሃሳቦችን፣ ስነምግባርን እና ሃላፊነትን ያስተዋውቃል። የእጅ ካልኩሌተሮች፣ የቁጥር ስርአቶች እና የአይነት መቀየሪያዎችን ይገመግማል። ርዕሶች የሚያካትቱት፤ ግየል ኮምፒውተር፣ ኦፕሬቲንግ ሲስተሞች እና ቅንብሮች፣ የምህንድስና ችግር ፈቺ እና ግራፊክ ቴክኒኮች። ተማሪዎች በኮሌጅ ደረጃ ያሉ የምህንድስናምደባዎችን እንዲያጠናቅቁ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በኮሌጅ ደረጃ ካልኩለስ እና እንግሊዝኛ 111 ውስጥ ምደባ

### የኤሌክትሮኒክስ ስርዓቶች I

በኮምፒውተር ቴክኖሎጂ በኤሌክትሮኒክ ምህንድስና ወይም የተገናኘ መስክ ስራዎች ለመቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች፣ ይህ ኮርስ የኤሌክትሮኒክ ቃላትን እና ክፍሎችን ያስተዋውቃል። አልጄብሪክ ስሌቶችን በመጠቀም፣ ተማሪዎች የኤሌክትሮኒክ ሰርኪዩት ችግሮችን ይፈታሉ። እነሱ የ AC ቮልቴጆችን ከ DC ቮልቴጆች እና በእያንዳንዱ ውስጥ ያለውን የክፍል እንቅስቃሴ ያነጻጽራሉ፣ የተለመደ የኤሌክትሪክ ሙከራ መሳሪያን ይጠቀማሉ እና የመበየድ ስልቶችን፣ የሰርኪዩት መስፈርቶችን እና የችግር ፈቺ ክህሎቶችን ይማራሉ። ተማሪዎች የናሙና ሰርኪዩቶችን በመገንባት እንዲሁም ከሰርኪዩት በርድ እስከ ማጠናቀቂያው በርካታ ፕሮጀክቶችን በመገንባት ያጎለብታሉ። ይህ ኮርስ ለኮምፒውተር ምህንድስና፣ ለኮምፒውተር ሳይንስ ወይም ለኮምፒውተር ቴክኖሎጂ ጥገና እንደ መግቢያ ሊያገለግል ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

### የኤሌክትሮኒክስ ስርዓቶች II

ይህ ኮርስ በ semiconductors/ solid state ክፍሎች ላይ የበለጠ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች የአምፐሊፋየሮችን (ትራንዚዝተሮችን)፣SCRs፣ የዲጂታል ሰርኪዮቶችን፣ የቮልቴጅ ማከፋፈያዎችን፣ የሃይል አቅራቢዎችን እና ሌላ በርካታ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ውጤቶች ይማራሉ። ተማሪዎች ለመደብር ቴክኒኮች እና ለሙከራ መሳሪያ ጥልቅ አጠቃቀም ይጋለጣሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በ coax፣ ምድብ 5 እና twisted pair block wire termination ሰልጥነዋል። የገመድ ማቋረጥ እና የሙከራ የምስክር ወረቀት በ Lucent Technology በኩል ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ አማራጭ ነው። ተማሪዎች የ NOCTI ኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ ፈተናን ይወስዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የኤሌክትሮኒክስ ስርዓቶች I

### የምህንድስና ትንታኔ እና መተግበሪያዎች II (ሮቦቲክስ)

ይህ ሊሆን ከሚችለው ባለአራት የኮርስ መንገድ ሁለተኛው በመሆን ተማሪዎች ስርዓቶችን እንዲመረምሩ፣ የቴክኖሎጂን እና የማህበረሰብን መስተጋብር፣ በንድፍ አለም አካባቢዎች ውስጥ የምህንድስና ንድፍ ሂደትን በመተግበር በቴክኖሎጂያዊ አለም እና በሞዴሊንግ መሰረታዊያን ውስጥ ያለ ስነምግባርን ይፈቅዳል። ተማሪዎች በላብራቶሪ አቀማመጥ መረጃን በቡድን ላይ በተመሰረቱ አቀራረቦች፣ ፕሮፖዛሎች እና የቴክኒካዊ ሪፖርቶች በሚገናኙበት ጊዜ በተግባራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ይሳተፋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የምህንድስና አሰሳዎች I

### የምህንድስና አሰሳዎች I

ተማሪዎች ቴክኖሎጂን እና የምህንድስና መሰረቶችን የገሃዱ አለም ችግሮች ከመፍታት ጋር አገናኝተው ይመረምራሉ። ተማሪዎች ዋና ዋና የምህንድስና ስኬቶችን ጨምሮ የምህንድስና ታሪክን ይመረምራሉ እንዲሁም ዋና የምህንድስና ስፔሻሊቲ መስኮችን መርህ እና ከእነሱ ጋር የተገናኙ ሙያዎችን ይመረምራሉ። ተማሪዎች የሂሳብ እና ሳይንሳዊ ጽንሰ ሃሳቦችን በመጠቀም የምህንድስና መሰረቶች ላይ ይለማመዳሉ እንዲሁም በተግባራዊ የምህንድስና ፕሮጀክቶች ውስጥ በመሳተፍ የምህንድስና ንድፍ ሂደት ላይ ያመለክታሉ። ተማሪዎች በቡድን ላይ በተመሰረቱ አቀራረቦች፣ ፕሮፖዛሎች እና ቴክኒካዊ ሪፖርቶች ከፕሮጀክት ጋር ከተገናኘ መረጃ ጋር ይገናኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11

### ዘላቂነት እና ታዳሽ ቴክኖሎጂዎች

ይህ ኮርስ አለም አቀፍ ዜጎችን በኢኮኖሚክስ፣ በባህል እና በአካባቢ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ይዳስሳል። ኮርሱ የአለም ማህበረሰብ እና ወደፊት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አካባቢያዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ያስተዋውቃል። ተማሪዎች የእኛን አካባቢ ጤና ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ እና በዘላቂ እርሻ፣ በጉልበት ቆጣቢ የህንጻ ንድፍ እና ታዳሽ የጉልበት ምንጮች የቀረቡትን መፍሂሄዎች ይዳስሳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቴክኒካል ስዕል እና ንድፍ I**

በዚህ የመሰረት ኮርስ፣ ተማሪዎች እውነተኛ የንድፍ ችግሮች ያሉባቸውን ቴክኒካዊ ስዕሎችን፣ምሳሌዎችን፣ ሞዴሎችን ወይም ፕሮቶታይፖችን እየነደፉ፣ እየሳሉ እና እየሰሩ መሰረታዊ የቴክኒካዊ ንድፍ ቋንቋን አውቶካድ በመጠቀም ይማራሉ። ተማሪዎች ለምስላዊ ውክልናዎች ሂሳባዊ ጽንሰ ሃሳቦችን ሲተገብሩ ቦታ የመያዝ ችሎታን ያዳብራሉ። ይህ ኮርስ በተለይ ለወደፊቶቹ የምህንድስና እና የአርክቴክቸር ተማሪዎች ይመከራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

# CTE: ንግድ እና የኢንዱስትሪ ትምህርት

ከኢኮኖሚክስ እና ከግል ፋይናንስ በስተቀር ሁሉም የ CTE ኮርሶች በተመረጠ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

የተማሪ የመምሪያ ክህሎቶች በት/ቤት በተመሰረተ ወይም በቨርቹዋል ኢንተርፕራይዞች፣ የሰራተኛን እንቅስቃሴዎች በመከታተል፣ በኢንተርንሺፖች እና/ወይም በ Skills USA ላይ በመሳተፍ ሊሻሻሉ ይችላል። ተማሪው ተጨማሪ ክሬዲት ለህብረት ስራ ትምህርት ተሞክሮው ሊቀበል ይችላል።

**አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ I**

በአውቶሞቢሎች ላይ ባለ የቅርብ ጊዜ የቴክኖሎጂያዊ ልህቀቶች፣ ቴክኒሻኖች ለዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና ስልጠና ዝግጁ መሆናቸው ወሳኝ ነገር ነው። ይህ ኮርስ ከ National Automotive Technician's Education Foundation's (CNATEF's) የማስተካከል እና የቀላል ጥገና እውቅና የተሰጠው ፕሮግራም ትልቁን የብቃቶች ናሙናን ያመለክታል ተማሪዎች ለ ASE (Automotive Service Excellence) የተማሪ ምስክር ወረቀት ለሆነው "በአውቶሞቲቭ ኢንስዱትሪ ውስጥ ሙያን እንደ አገልግሎት ባለሙያ ለመገንበት ያለ የመጀመሪያ ደረጃ" ሲዘጋጁ በሁሉም ስርዓቶች መመሪያ ይቀርብላቸዋል። እነዚህ ከኮርሱ ጋር የተገናኙ ክፍያዎች ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11

**የንግድ ፎቶግራፍ I**

የእይታዊ እውቀት መርሆዎችን የእይታዊ ይዘት ለማዘጋጀት ያለ የመተግበር ችሎታ ተማሪዎች በዛሬው የአለም አቀፍ፣ መልቲሚዲያ ማህበረሰብ ውስጥ ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋል። ተማውዎች በኢንዱስትሪው ላይ አግባብ የሆኑ የቴክኒክ ክህሎቶችን ይማራሉ እና የዲጂታል ካሜራዎች፣ የንድፍ ሶፍትዌር እና የኤዲቲንግ መሳሪያዎች መድረክ ላይ ለማቅረብ፣ ለማንሳት፣ ለማቀናበር፣ ለማተም እና የባለሙያ ደረጃ ምስሎችን ለማቅረብ ከተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ጋር የመስራት እድል አላቸው። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የፎቶግራፍ ስራን ይገመግማሉ እንዲሁም ይተቻሉ እና ስለፎቶግራፍ ታሪክ የፊልም እና የጨለማ ቤት እድገትን በማካተት (እንደ አማራጭ) ይመረምራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**የንግድ ፎቶግራፍ II**

የእይታዊ እውቀት መርሆዎችን የእይታዊ ይዘት ለማዘጋጀት ያለ የመተግበር ችሎታ ተማሪዎች በዛሬው የአለም አቀፍ፣ መልቲሚዲያ ማህበረሰብ ውስጥ ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋል። በዚህ የመጨረሻ አመት የንግድ ፎቶግራፍ፣ ተማሪዎች በኢንዱስትሪ አግባብ የሆኑ ቴክኒካዊ ክህሎቶችን ይማራሉ እንዲሁም ዲጂታል ካሜራዎችን፣ መብራትን፣ የዲዛይን ሶፍትዌር እና ግንኙነት ላላቸው ስራዎች

ፖርትፎሊዮዎችን ለማጎልበት የባለሙያ ደረጃ ምስሎችን ለማቅረብ፣ ለማንሳት፣ ለማስኬድ፣ ለማተም እና ለማቅረብ የሚያገለግሉ የኤዲቲንግ መሳሪያዎችን ጨምሮ ከተለያዩ የቴክኖሎጂ አይነቶች ጋር የመስራት እድል ያገኛሉ። ተማሪዎች ከጣቢያው ውጪ በሆኑ ስፍራዎች የተማሯቸውን ክህሎቶች ለመለማመድ እድል ሊኖራቸው ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የንግድ ፎቶግራፍ I

### ኮስሜቶሎጂ I

ይህ ከሁለት አመት ተከታታይ ፕሮግራም የመጀመሪያው አመት ነው። ተማሪዎች ስለጸጉር፣ ቆዳ እና ጥፍር እና ከእነዚህ ጋር የተገናኘ እንክብካቤን ይማራሉ። ተማሪዎች በክሊኒካል የላብ አቀማመጥ ወይም ክፍል ውስጥ ለተለዋዋጭ የክህሎት አተገባበር mannequins በመጠቀም ሂደቶችን ለመለማመድ ሲዘጋጁ በጽንሰ ሃሳቦች ላይ መሰረት ያደርጋሉ። ኮርሱ ግላዊ ደህንነት፣ ሙያዊነት እና የመሳሪያ እና የፋሲሊቲዎች የንፅህና አጠባበቅ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ጸጉር ላይ ሻምፖ ማድረግ፣ ኮንዲሽነር ማድረግ እንዲሁም ዘቢቤውዎችን እና የጸጉር አቆራረጥ ክህሎቶችን ያዳብራሉ። የእጅ እና የእግር ውበት አጠባበቅ ሂደቶች መግቢያን እንዲሁ ያገኛሉ። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 3

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11

### ኮስሜቶሎጂ II

ይህ ከሁለት አመት ተከታታይ ፕሮግራም ሁለተኛው አመት ነው። ተማሪዎች ክህሎታቸውን፣ እውቀት እና ተሞክሯቸውን ያጎለብታሉ እንዲሁም ለኮስሞቶሎጂ ፈቃድ ብቁ ለመሆን የሚያስፈልገውን የ 1080 የክፍል ውስጥ ተሞክሮ ሰአታት እንዲያሟሉ ይጠበቃል። ተማሪዎች ስለጸጉር፣ ቆዳ እና ጥፍር እና ከእነዚህ ጋር የተገናኘ እንክብካቤን ይማራሉ። ተማሪዎች በክሊኒካል የላብ አቀማመጥ ወይም ክፍል ውስጥ ለተለዋዋጭ የክህሎት አተገባበር mannequins በመጠቀም ሂደቶችን ለመለማመድ ሲዘጋጁ በጽንሰ ሃሳቦች ላይ መሰረት ያደርጋሉ። ኮርሱ ግላዊ ደህንነት፣ ሙያዊነት እና የመሳሪያ እና የፋሲሊቲዎች የንፅህና አጠባበቅ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ጸጉር ላይ ሻምፖ ማድረግ፣ ኮንዲሽነር ማድረግ እንዲሁም ዘቢቤውዎችን እና የጸጉር አቆራረጥ ክህሎቶችን ያዳብራሉ። ይህ ፕሮግራም ተማሪዎችን ለ Virginia State Board of Cosmetology Examination ያዘጋጃል። ክፍያዎች ከዚህ ኮርስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 3

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ኮስሜቶሎጂ I

### የወንጀል ፍትህ I

ይህ ኮርስ ተማሪዎችን ለመግቢያ ደረጃ ቅጥር በወንጀል ፍትህ ስርአት ውስጥ እንዲሁም በወንጀል ፍትህ፣ የፖለቲካ ሳይንስ እና ህግ የተገናኙ መስኮች ጋር ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመግባት ያዘጋጃቸዋል። ልዩ የሆኑ የስልጠና አካባቢዎች የሚያካትቱት ምርመራን፣ የደህንነት ስልጠናን፣ ግንኙነቶችን፣ የፍርድ ቤት ሂደቶችን እና ማስተካከያዎችን ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

### የወንጀል ፍትህ II

ሁለተኛው ደረጃ ኮርስ ተማሪዎች የህግ የበላይነትን እንዲረዱ፣ ህግ ማስከበርን እንዲዳስሱ፣ የወንጀል ክስተቶችን እንዲመረምሩ፣ የወንጀል ፍትህ የግንኙነት ክህሎቶችን እንዲተገብሩ እና የወንጀል ፍትህ አገልግሎቶች ስርአት የማረሚያ ክፍልን እንዲያስሱ ይፈቅዳል።

ተማሪዎች ሙያቸውን ለመቀጠል በወንጀል ፍትህ አገልግሎቶች ስርአት ውስጥ ያሉትን መርሆዎች፣ ስልቶች እና ልምዶች ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የወንጀል ፍትህ I

### ለሁለት ምዝገባ አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ II

ይህ ኮርስ ከ National Automotive Technician's Education Foundations (CNATEF's) ከማስተካከል እና የቀላል ጥገና እውቅና የተሰጠው ፕሮግራም ያለ ቅድሚያ ኮርስ ድግግሞሽ ያሉ የላቁ ብቃቶችን ያመለክታል። ተማሪዎች ለ ASE (Automotive Service Excellence) የተማሪ ምስክር ወረቀት ለሆነው "በአውቶሞቲቭ ኢንስዱትሪ ውስጥ ሙያን እንደ አገልግሎት ባለሙያ ለመገንባት ያለ የመጀመሪያ ደረጃ" ሲዘጋጁ በሁሉም ስርዓቶች መመሪያ ይቀርብላቸዋል። ይህን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀ የፕሮግራም መጠናቀቅን ያመጣል እና ተማሪዎች የ NATEF እኩል የተማሪ ፈተና የሆነውን እንዲያልፉ እና በመጨረሻም የምስክር ወረቀቱን እንዲቀበሉ ያዘጋጃቸዋል። እነዚህ ከኮርሱ ጋር የተገናኙ ክፍያዎች ናቸው። ተማሪዎች ባለ ሁለት ምዝገባ የ Northern Virginia Community College ጋር የኮሌጅ ክሬዲቶችን ሊያገኙ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ I

### ባለሁለት ምዝገባ አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ III

ይህ ኮርስ የመጀመሪያ ሁለት የአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ ኮርሶችን ላጠናቀቁ እና የተጠናቀቀ ፕሮግራም ሁኔታን ላገኙ ተማሪዎች ይገኛል። ለዚህ የመሰረት ኮርስ ያሉት ስራዎች የ National Automotive Technician's Education Foundation's (NATEF's) የመኪና አገልግሎት ቴክኖሎጂ እውቅና ያለው ፕሮግራም የመካከለኛ እርከን ደረጃዎችን ይወክላል። ተማሪዎች ለ ASE (Automotive Service Excellence) የተማሪ ምስክር ወረቀት ለሆነው "በአውቶሞቲቭ ኢንስዱትሪ ውስጥ ሙያን እንደ አገልግሎት ባለሙያ ለመገንባት ያለ የመጀመሪያ ደረጃ" ሲዘጋጁ በሁሉም ስርዓቶች መመሪያ ይቀርብላቸዋል። እነዚህ ከኮርሱ ጋር የተገናኙ ክፍያዎች ናቸው። ተማሪዎች ባለ ሁለት ምዝገባ የ Northern Virginia Community College ጋር የኮሌጅ ክሬዲቶችን ሊያገኙ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባለሁለት ምዝገባ አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ II

### ባለሁለት ምዝገባ የቴሌቪዥን እና የሚዲያ ፕሮዳክሽን II

ተማሪዎች የምርት ሂደት ደረጃዎች ማወቃቸውን ይቀጥላሉ እንዲሁም በቴሌቪዥን ስቱዲዮ እና በአዳዲስ የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ክህሎቶች የሚዲያ አተገባበሮች ላይ ያተኩራሉ። እነሱ የባለብዙ ካሜራ ስቱዲዮ ዝግጅትን ለቀጥታ ቀረጻ ፕሮዳክሽኖች ይማራሉ እንዲሁም በጣቢያው የቴሌቪዥን ስቱዲዮ ላይ በስቱዲዮ እና የቁጥጥር ክፍል መሳሪያ ክንውን ውስጥ ተሞክሮን ያገኛሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በቪዲዮ፣ በቴሌቪዥን እና በአዲስ ሚዲያ እንዲሁም በኢንተርንሺፖች፣ አፖረንትሺፖች እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ባሉ ተስፋዎች ባሉ አካባቢዎች ውስጥ የስራ እድሎችን ያስሳሉ። ተማሪዎች በኮሌጁ ሁለቴ እንዲመዘገቡ በዚህ ኮርስ C ወይም ከአማካይ የተሻለ ማግኘት አለባቸው። በሴሚስተሩ መጨረሻ ላይ C አማካይ ነጥብ ያላገኙ ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል። ተማሪዎች ከጣቢያው ውጪ በሆኑ ስፍራዎች የተማሯቸውን ክህሎቶች ለመለማመድ እድል ሊኖራቸው ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 2

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ቴሌቪዥን እና የሚዲያ ፕሮዳክሽን I እና ሁሉንም የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶች ያሟላል

### የኔትወርኪንግ ሃርድዌር ክንውኖች I እና II

ይህ የሁለት ሴሚስተር ኮርስ (0.5 ክሬዲቶች በሴሚስተር) አጠቃላይ የኔትወርኪንግ ጽንሰሃሳብ እና ከቤት እና አነስተኛ የቢሮ ኔትወርኮች እስከ ተጨማሪ ውስብስብ የኢንተርፕራይዝ ሞዴሎች ድረስ የአካባቢዎች አምድ ውስጥ ያሉ የራውቲንግ፣ ስዊቺንግ እና የላቁ ቴክኖሎጂዎች መሰረቶችን ይሸፍናል። ካሪኩለሙ ተማሪዎች ለኢንዱስትሪ ደረጃ የ Cisco Certified Network Associate (CCNA) የምስክር ወረቀት ፈተናዎች እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል። የአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመጀመሪያ ሁለት የ CCNA Discovery ኮርሶችን በማቅረብ ተማሪዎችን አማራጭ የመጀመሪያ ደረጃ የ CCNA የምስክር ወረቀት ማግኛ የሆነውን የ Cisco CCENT የምስክር ወረቀት ለጀመሪ የኔትወርክ ቴክኒሻኖች ያዘጋጃል። የ CCNA ግኝት ራሱን እንደቻለ የጥናት ኮርስ ተደርጎ ይቀርባል። ካሪኩለሙ ተራ በተራ የሚደርሱ ሁለት ኮርሶችን ይዟል። እያንዳንዱ ኮርስ የችግር መፍቻ ምዕራፍ እና የላቁ ቴክኖሎጂዎች (የድምጽ ቪዲዮ፣ ገመድ አልባ እና ደህንነት) በመያዝ በካሪኩለሙ በሙሉ ተዋውቋል። ተማሪዎች የ NOCTI የኮምፒውተር ኔትወርኪንግ ፈተናዎችን ሊወስዱ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የሳይበር ደህንነት መሰረታዊያን ወይም የሊሌክትሮኒክ ስርዓቶች I።

### ቴሌቪዥን እና የሚዲያ ፕሮዳክሽን I

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ቪዲዮ ቴክኖሎጂን ይዳስሳሉ እና ቴሌቪዥንን እንደ መረጃ ሚዲያ ይመረምሩታል። ተማሪዎች የቪዲዮ ፕሮዳክሽን መሰረታዊ መርሆዎችን፣ የሚዲያ እውቀት እና በክፍል ውስጥ ውይይቶች፣ በቪዲዮ ማሳያዎች እና በቦታው ባሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በኩል ያሉ ህጋዊ ገጽታዎችን ይማራሉ። በፕሮዳክሽን ሂደት (ቅድመ ፕሮዳክሽን፣ ፕሮዳክሽን እና ከፕሮዳክሽን በኋላ) ውስጥ ሲሰሩ፣ተማሪዎች በቪዲዮግራፊ፣ በኤዲቲንግ፣ በድምጽ ፕሮዳክሽን፣ በስክሪፕት ጽሁፍ እና በካሜራ ላይ አፈጻጸም ያሉ ቴክኒኮችን ይማራሉ። ተማሪዎች በኮምፒውተር ግራፊክስ፣ ልዩ ተጽዕኖ መተግበሪያዎች እና ሌላ ቴክኖኮች ውስጥ የተገናኘ የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ልምድን እንዲሁ ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11

### ቴሌቪዥን እና የሚዲያ ፕሮዳክሽን III

ይህ ኮርስ የቲቪ ፕሮዳክሽን ተርታ እንደ አንኳር ኮርስ በመሆን እና ተማሪዎች በ ACPS እና ትርፋማ ባልሆኑ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች የቀረቡትን የተለያዩ ፕሮግራሞች ተማሪዎች የሚጽፉበት፣ የሚያመርቱበት እና የሚያከፋፍሉበት እንደ ትንሽ የማምረቻ ክፍል ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚዘጋጁት ፕሮጀክቶች ለፖርትፎሊዮ ማጎልበቻ ይጠቅማሉ እናዲሁም በአሌክሳንድሪያ ወይም በ ACPS-TV በኩል በቴሌቪዥን ይሰራጫሉ። በግል እና በቡድን ላይ በተመሰረቱ ፕሮጀክቶች በኩል፣ ተማሪዎች የደንበኛ ትስስር፣ የፕሮጀክት ማጎልበት፣ የበጀት አመዳደብ፣ መርሃግብር የማውጣት፣ የምስል እና የድምጽ ድህረ-ፕሮዳክሽን እና በመጨረሻም አቀራረብ እና የምርት ስርጭትን ጨምሮ ሁሉንም አይነት የምርት ደረጃዎች ተሞክሮ ያገኛሉ። ተማሪዎች በኮሌጁ ሁለቴ እንዲመዘገቡ በዚህ ኮርስ C ወይም ከአማካይ የተሻለ ማግኘት አለባቸው። በሴሚስተሩ መጨረሻ ላይ C አማካይ ነጥብ ያላገኙ ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል። ተማሪዎች ከጣቢያው ውጪ በሆኑ ስፍራዎች የተማሯቸውን ክህሎቶች ለመለማመድ እድል ሊኖራቸው ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባለሁለት ምዝገባ እና የሚዲያ ፕሮዳክሽን II እናህይሉንም የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶች ያሟላሉ

# የእንግሊዝኛ ዋና ኮርሶች

በንባብ/በስነጽሁፍ እና በጽሁፍ ውስጥ የመማሪያ ደረጃዎች (SOL) ሙከራዎች ለሁሉም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጣሉ። በእነዚህ ሙከራዎች የማለፊያ ነጥቦች በእንግሊዝኛ ሁለት የተረጋገጡ ክሬዲቶችን ያመጣል።

### AP የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ቅንብር

የ AP እንግዝሊኛ ቋንቋ እና አወቃቀር ኮርስ ከኮሌጅ አጻጻፍ የመግቢያ ኮርስ ጋር የሚተካከል ነው። አላማው ውስብስብ ጽሁፎችን ተማሪዎች እንዲረዱ ለማስቻል እና ከበሰሉ አንባቢዎች ጋር በተሳካ ሁኔታ ለመገናኘት በበቂ ሁኔታ የበለጸገ እና ውስብስብ የሆነ ጽሁፍን ለመጻፍ ነው። ተማሪዎች በካሪኩለሙ በሙሉ ውጤታማ ሆነው ከአማካይ በላይ ስነጽሁፍ የመጻፍ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል። ገላጮ፣ ትንተናዊ እና አከራካሪ ጽሁፍ እንዲሁም ግላዊ እና አንጸባራቂ ጽሁፍ የተማሪዎችን የማቀናበር ሂደቶች ግንዛቤን እና ሃሳቦችን የሚገልጹበት መንገድ፣ ስትራቴጂዎችን ዳግም የሚያጤኑበትን እና ስራቸውን የሚከልሱበትን መንገድ ከፍ ማድረግን አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ምርምር የተደረገባቸውን የክርክር ወረቀቶች ጨምሮ በዋነኝነት ከአሜሪካዊ ስነጽሁፍ በመነሳት ከውስብስብ ኢ-ልብወለድ እና ልብወለድ የተቀናጀ መረጃን በመጠቀም በርካታ አይነት ወረቀቶችን ይጽፋሉ። የቃላት ስብስብ ጥናት፣ ጽሁፍ እና የሰዋሰው ጥናት እድገት ተማሪዎች ስታይል ያለውን ብስለት እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ወደዚህ ኮርስ ለመግባት የሚያስፈልጉትን ምደባዎች ለሚያጠናቅቅ ለማንኛዉም ተማሪ ይገኛል። ተማሪዎች የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ኦነርስ እንግሊዝኛን መውሰዳቸው እና B ወይም የተሻለ ነጥብ ማግኘታቸው በጥብቅ ይመከራል። በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

### AP የእንግሊዝኛ ስነጽሁፍ እና ቅንብር

ወደዚህ ኮርስ ለመግባት የሚያስፈልጉትን ምደባዎች ለሚያጠናቅቅ ለማንኛዉም ተማሪ ይገኛል። ተማሪዎች የ9ኛ፣ 10ኛ እና 11ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ኦነርስ ወይም DE ወይም AP እንግሊዝኛ እንደወሰዱ እና በእነዚህ ኮርሶች B ወይም ከዚያ የተሻለ ማግኘት እንዳለባቸው ይመከራል። በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል። የ AP እንግዝሊኛ ቋንቋ እና አወቃቀር ኮርስ ከኮሌጅ የእንግሊዝኛ የጀመሪ ደረጃ ኮርስ ጋር የሚተካከል ነው። ተማሪዎች ከአማካይ በላይ የስነጽሁፍ ንባብ እና ትርጉም ብቃት ሊኖራቸው እና ቀጣይነት ያለው እና ጥልቅ ንባቦችን የማጠናቀቅ መነቃቃት ሊኖራቸው ይገባል። ኮርሱ የስነጽሁፍ ክህሎቶችን ይገነባል፣ የቡድን ውይይት መለዋወጦችን ያጎለብታል እና ከልብወለድ፣ ከግጥም እና ድራማ የመጡ መረጃዎችን በመዋሃድ የተገኙ የምርምር ወረቀቶች በማካተት ከአለም የስነጽሁፍ ባህሎች በመነሳት የስነጽሁፍ ትንተና ላይ ያተኩራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

### ባለሁለት ምዝገባ የኮሌጅ ቅንብር 11

ይህ ሁለት ሴሚስተር ባለሁለት ምዝገባ ኮርስ ሲሆን የቀረበውም በ NOVA ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች

በእንግሊዝኛ ቅንብር ስድስት የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ተማሪዎች ለመማር፣ ለመስራት እና በተሞክሮ፣ በማስተዋል፣ በምርምር እና በተመረጠ ስነጽሁፍ ንባብ ላይ ለተመሰረቱ ሌላ የጽሁፍ አካባቢዎች የመጻፍ ክህሎትን ያዳብራሉ። ይህ ኮርስ ተማሪዎች አጻጻፍን እንደ ሂደት እንዲማሩ፣ ታዳሚውን እና አላማውን እንዲረዱ፣ ሃሳቦችን እና መረጃን እንዲያስሱ፣ እንዲያቀናብሩ፣ እንዲከልሱ እና አርትዕ እንዲያደርጉ ይመራል እንዲሁም በማሰብ፣ በማንበብ፣ በማዳመጥ እና በመናገር ውስጥ ልምዶችን በማዋሃድ አጻጻፍን ይደግፋል። ይህ ክፍል እንግሊዝኛ የ SOL ፈተናዎችን ለመውሰድ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው። ኮርሱ የ SOL ሙከራዎችን ለመደገፍ በተጨማሪነት ቀርቧል። ተማሪዎች በሁለተኛው ሴሚስተር ኮርስ ለመመዝገብ ሲ ወይም ከዛ የተሻለ ውጤት በመጀመሪያው ሴሚስተር መጨረሻ ላይ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። C ወይም ከዚያ የተሻለ ነጥብ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶችን ያሟላል

### ባለሁለት ምዝገባ የኮሌጅ ቅንብር 12

ይህ ሁለት ሴሚስተር ባለሁለት ምዝገባ ኮርስ ሲሆን የቀረበውም በ NOVA ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቅንብር ስድስት የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ተማሪዎች ለመማር፣ ለመስራት እና በተሞክሮ፣ በማስተዋል፣ በምርምር እና በተመረጠ ስነጽሁፍ ንባብ ላይ ለተመሰረቱ ሌላ የጽሁፍ አካባቢዎች የመጻፍ ክህሎትን ያዳብራሉ። ይህ ኮርስ ተማሪዎች አጻጻፍን እንደ ሂደት እንዲማሩ፣ ታዳሚውን እና አላማውን እንዲረዱ፣ ሃሳቦችን እና መረጃን እንዲያስሱ፣ እንዲያቀናብሩ፣ እንዲከልሱ እና አርትዕ እንዲያደርጉ ይመራል እንዲሁም በማሰብ፣ በማንበብ፣ በማዳመጥ እና በመናገር ውስጥ ልምዶችን በማዋሃድ አጻጻፍን ይደግፋል። ተማሪዎች በሁለተኛው ሴሚስተር ኮርስ ለመመዝገብ ሲ ወይም ከዛ የተሻለ ውጤት በመጀመሪያው ሴሚስተር መጨረሻ ላይ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። C ወይም ከዚያ የተሻለ ነጥብ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶችን ያሟላል

### ባለሁለት ምዝገባ የአለም ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት

ይህ ሁለት ሴሚስተር ባለሁለት ምዝገባ ኮርስ ሲሆን የቀረበውም በ NOVA ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ስነጽሁፍ ስድስት የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ኮርሱ የአለም ስነጽሁፎችን ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሚያመለክቱ ዋና ዋና የተመረጡ ስራዎችን ለተማሪዎች ያስተዋውቃል። በተጠኑት ስራዎች ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ወይም ተጽዕኖ የሚደረግባቸው ርዕሶች የሚያካትቱት የባህላዊ እንቅስቃሴዎች እውቅና (ፊሎሶፊያዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ.) ነው። ይህ ኮርስ የተማሪዎችን ችሎታዎች በወሳኝ ማንበብ እና መጻፍ ውስጥ ለመጨመር ይፈልጋል። ተማሪዎች በሁለተኛው ሴሚስተር ኮርስ ለመመዝገብ ሲ ወይም ከዛ የተሻለ ውጤት በመጀመሪያው ሴሚስተር መጨረሻ ላይ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። C ወይም ከዚያ የተሻለ ነጥብ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባለሁለት ምዝገባ የኮሌጅ ቅንብር 11

## እንግሊዝኛ 9

ይህ ኮርስ የአለም ታሪክን፣ የአለም ስነጽሁፍን እንዲሁም ተማሪዎች የጥልቅ አስተሳሰብ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ፣ ታሪካዊ እውቀት እና መረዳት ያገኛሉ፣ ከጥንት ጊዜያት እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ያለውን የአለም ስነጽሁፍ ይተነትናሉ እና ከዘመናዊ ስነጽሁፍ ጋር ያነጻጽራሉ እና ከተጠኑት ከእያንዳንዳቸው ዘመናት ያሉ የውክልና ስራዎችን ታሪካዊ ክስተቶች እና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እንዴት ተፅዕኖ እንደፈጠረ ይገልጻሉ። ተማሪዎች የተለዩ ትምህርቶችን እውቀት እና በማዋቀር ክህሎቶች ውስጥ ብቃትን ለማሳየት እንዲሁ የሚተረጎሙ ወረቀቶችን ይጽፋሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በሰዋስው፣ በምርምር (የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማካተት)፣ በቃላት ስብስብ፣ በህዝባዊ ንግግር እና በሙከራ አወሳሰድ ክህሎቶች ብቃትን ያጎለብታሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

## እንግሊዝኛ 10

ዘጠነኛ ክፍል የጀመረውን ሂደት በመቀጠል፣ ተማሪዎች በአለም ታሪክ እና በአለም ስነጽሁፍ መካከል ያለውን ትስስር በበለጠ ይዳስሳሉ። ተማሪዎች የታሪካዊ ክስተቶችን እና የዘመናትን ተጽዕኖ በስነጽሁፍ ውስጥ በመመርመር ከ 16ኛው ክፍለ ዘመን እስከ ዛሬ ያሉትን የስነጽሁፍ ስራዎች ያነባሉ እንዲሁም ይተነትናሉ። ተማሪዎች በክፍል ውይይቶች፣ በተለያዩ የአጻጻፍ አይነቶች እና ሌላ እንቅስቃሴዎች፣ የስነጽሁፍ አወቃቀሮችን ተመሳሳይነቶች እና ልዩነቶች በማሳየት፣ በምስሎች፣ በጭብጦች እና በበርካታ ታሪኮች እና ታሪካዊ ጊዜያት የነበሩ ጥንታዊ ቅርሶች በኩል ክህሎት ያካብታሉ። ተማሪዎች የስነጽሁፍ ቅንጭብጭቦችን እና ሙሉ ጽሁፎችን በጥልቀት ይነባሉ እና የቃል ቋንቋ ክህሎቶችን በግለሰብ እና በትናንሽ የቡድን እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ እና የጓደኛ ግምገማ በኩል ያጠናክራሉ። ለክፍል ውስጥ እና ከክልፍ ውጪ ለሆኑ የጽሁፍ ምደባዎች፣ ተማሪዎች ሃሳቦችን ያምነጫሉ እንዲሁም ያደራጃሉ፣ ረቂቆችን ያጎለብታሉ፣ የጽሁፍን ግልጽነት እና ትክክለኛነት ይገመግማሉ እንዲሁም ክለሳዎችን በተገቢው መንገድ ያደርጋሉ። ተማሪዎች በቀጥታ ትምህርት እና ተማሪዎች ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃን እንዲያገኙ በሚል የምርምር እንቅስቃሴዎችን እንዲያጠናቅቁ፣ የመረጃን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ፣ ለተወሰነ ርዕስ እና አላማ ተገቢነቱን እንዲያረጋገጡ እንዲሁም የምርምር ግኝቶቹን አቀራረብ ለማዘጋጀት መረጃዎቹን እንዲመርጡ የሚጠይቁ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10

## እንግሊዝኛ 11፦ የአሜሪካ ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት

ተማሪዎች ከዚህ ሃገር ምስረታ እስከ አሁን ያሉትን የአሜሪካ ገጣሚዎች፣ ጸሃፊዎች እና የፕሮዝ ጸሃፊዎች ጭብጦች፣ የእይታ ነጥቦች እና ስልቶች ይመረምራሉ እንዲሁም ያነጻጽራሉ። ከስነጽሁፍ ትምህርት በቀጠሉ ጽሁፎች እና ፕሮጀክቶች በኩል፣ ተማሪዎች የማዋቀር ክህሎቶችን፣ የቃላት ስብስብን፣ የምርምር ስትራቴጂዎችን እና የቃል ዝግጅት ችሎታን ያጎለብታሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

## እንግሊዝኛ 12፦ ብሪትሽ እና የአለም ስነጽሁፍ

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ሁሉንም የብሪትሽ እና የአለም ስነጽሁፍ እድገት ሁሉንም አይነት ዘውጎች ይመረምራሉ፣ እንዲሁም ከአንግሎ-ሳክሰን ዘመን እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ዘውጎቹን ስለፈጠሯቸው ጸሃፊዎች ይመረምራሉ። ትምህርቱ በብሪትሽ ስነጽሁፍ ላይ ያተኩራል ነገር ግን በርካታ ብዙ የባህል ጽሁፎችን

ያካትታል። ኮርሱ አጽንዖት የሚሰጠው ከተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀር ጋር ያሉ የቃላት ስብስብ እድገቶች እና ተሞክሮዎች ላይ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

### ኦነርስ እንግሊዝኛ 9

ይህ የክፍት ምዝገባ ኦነርስ የእንግዝሊኛ ኮርስ ተማሪዎች የላቁ የጽሁፍ እና የንግግር ግንኙነቶችን እንዲሁም ለኮሌጅ የዝግጅት ስራ የሚያስፈልጉ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የንግግር ስትራቴጂዎች ላይ እንዲያመለክቱ ይጠይቃል። ይህ ኮርስ ስነጽሁፍን ከቀድሞ ስልጣኔዎች እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የክላሲካል ጽሁፎችን ከዘመናዊ የአለም ስነጽሁፍ ምሳሌ ጋር በማነጻጸር ይተነትናል። ተማሪዎች በዋና ዋና የተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች ጸሃፊዎች ምሳሌ እንደተሰጠባቸው እንዴት ታሪካዊ ክስተቶች እና የፖለቲካ አስተሳሰቦች ስነጽሁፍ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳረፉ ይማራሉ። ተማሪዎች ለህትመት አመቺ የሆነ አጻጻፍ ላይ አጽንዖት በመስጠት የድርሰት አይነቶችን (ተራኪ፣ ገላጭ፣ አሳማኝ) ያጎለብታሉ። እነሱ ስታይል፣ ሙድ እና በስነጽሁፍ ውስጥ ያለ የጭብጥ አስፈላጊነትን ጨምሮ በርካታ የስነጽሁፍ ስራዎችን ጥቅሞች የሚገመግሙ ድርሰቶችን ይጽፋሉ። አመቱን በሙሉ ያለ ዋና ትኩረት የንፅፅር ትንታኔ፣ የተመሳሳይ እና የልዩነት እንዲሁም በአለም ስነጽሁፍ ውስጥ ያሉ አለም አቀፍ አካሄዶች አካባቢን ማስተዋል ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

### ኦነርስ እንግሊዝኛ 10

በዚህ የኦነርስ ኮርስ ውስጥ የሚመዘገቡ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ 9 ኮርስን እንዲወስዱ እና የመጨረሻ ውጤት የሆነውን B ወይም ከዚያ የተሻለ እንዲያገኙ ይመከራል። በእንግሊዝኛ 10 እንዳለው የመደበኛ ማቅረብ፣ በኦነርስ ኮርስ ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች ከ16ኛው ክፍለዘመን እስከአሁን ድረስ የስነጽሁፍ ስራዎችን በማንበብ እና በመተንተን ባለፉት አራት ክፍለ ዘመናት ውስጥ በነበሩት ታሪካዊ ክስተቶች እና ዘመናት ተጽእኖዎች የደረሱባቸውን የአለም ስነጽሁፍ ጥናት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። በተጨማሪም፣ በኦነርስ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የሚፈለጉትን ንባቦች በሰፊ ስፋት እና ጥልቀት ያገኛሉ። ተማሪዎች ተጨማሪ ሙሉ የስነጽሁፍ ስራዎችን በማንበብ፣ ተጨማሪ የረዘመ አጻጻፍን እና የቃል ወሳኝ ትንታኔዎችን በመተግበር እና አጻጻፍን በተጠኑ ደራሲያን ቅርጾች እና ስታይሎች አይነት አጻጻፍን እንዲሁ ይለማመዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10

### ኦነርስ እንግሊዝኛ 11፡- የአሜሪካ ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት

ወደዚህ የኦነርስ-ደረጃ ኮርስ ለመግባት የሚያስፈልጉትን ምደባዎች ለሚያጠናቅቅ ለማንኛዉም ተማሪ ክፍት ነው። ተማሪዎች እንግሊዝኛ 10 እንዲወስዱ እና B ወይም ከዚያ የተሻለ እንዲያገኙ ይመከራሉ። የአሜሪካ ስነጽሁፍ የጊዜ ቅደም ተከተል ጥናት ላይ በማተኮር፣ ይህ ኮርስ ተማሪዎች በአሜሪካን ስልጣኔ እና የእዉቀት ታሪክ ውስጥ በስነጽሁፍ ስራዎች እና ወጎችእንዲሁም ፋሽን መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲገነዘቡ ይጥራል። የጽሁፍ ክህሎቶች፣ ጥልቅ የአስተሳሰብ ክህሎቶች እና የቃላት ስብስብ በትንተናዊ ድርሰቶች እድገት ውስጥ ተለጥጠው ይታያሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

### ኦነርስ እንግሊዝኛ 12

ወደዚህ የኦነርስ ደረጃ ኮርስ መግቢያ የተጠየቁትን ምደባዎች ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ ለሆነ ለማንኛዉም ተማሪ ክፍት ነው።

ተማሪዎች እንግሊዝኛ 11 ይመከራሉ፤ የአሜሪካ ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት እና B ወይም ከዚያ በላይ ማግኘት። በዚህ ኦነርስ ኮርስ ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች ልብ ወለድ፣ ልብወለድ ያልሆነ፣ ግጥም፣ ድራማ እና የፈጠራ ልብወለድ ያልሆኑ ስራዎችን ከዘመናዉ ብሪትሽ፣ አሜሪካን እና የአለም ስነጽሁፍ አጽንዖት ጋር ያነባሉ እንዲሁም ይተነትናሉ። ይህ የኮሌጅ የዝግጅት ኮርስ ከስነጽሁፍ ምርምር የሴሚናር ፕሮጀክት እና ለኮሌጅ ስኬት አስፈላጊ የሆነውን ራስን የቻለ ጥልቅ ንባብ፣ ጽሁፍ እና ክህሎቶችን መጠየቅ ላይ አጽንዖት የሚሰጥ ለተመልካች ከሚሆን አቀራረብ ጋር ይጠናቀቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

# የእንግሊዝኛ ተመራጮች

በንባብ/በስነጽሁፍ እና በጽሁፍ ውስጥ የመማሪያ ደረጃዎች (SOL) ሙከራዎች ለሁሉም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጣሉ። በእነዚህ ሙከራዎች የማለፊያ ነጥቦች በእንግሊዝኛ ሁለት የተረጋገጡ ክሬዲቶችን ያመጣል።

### የላቀ የመማር ስትራቴጂዎች A (ሴሚስተር 1)

በምርምር ላይ የተደገፉ ፕሮግራሞችን በመጠቀም፣ ይህ ኮርስ በንባብ፣ በጽሁፍ፣ በንግግር፣ በማዳመጥ እና በማሰብ ላይ ያሉ ክህሎቶችን ያጠነክራል። ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን ለማሳደግ፣ ብቃትን ለመጨመር እና የንባብ ግንዛቤን እና የመጻፍ ክህሎቶችን በሁሉም የካሪኩለም አካባቢዎች ለማሻሻል ያሉትን ስትራቴጂዎች ይማራሉ። የዚህ ኮርስ አስፈላጊ አላማው ተማሪዎች ለመዝናናት ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ ለማበረታታት ነው። የኮርስ ስራ የእያንዳንዱን እተማሪ ፍላጎቶች ለማሟላት በሚል ይለያያል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### የላቀ የመማር ስትራቴጂዎች B (ሴሚስተር 2)

በምርምር ላይ የተደገፉ ፕሮግራሞችን በመጠቀም፣ ይህ ኮርስ በንባብ፣ በጽሁፍ፣ በንግግር፣ በማዳመጥ እና በማሰብ ላይ ያሉ ክህሎቶችን ያጠነክራል። ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን ለማሳደግ፣ ብቃትን ለመጨመር እና የንባብ ግንዛቤን እና የመጻፍ ክህሎቶችን በሁሉም የካሪኩለም አካባቢዎች ለማሻሻል ያሉትን ስትራቴጂዎች ይማራሉ። የዚህ ኮርስ አስፈላጊ አላማው ተማሪዎች ለመዝናናት ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ ለማበረታታት ነው። የኮርስ ስራ የእያንዳንዱን እተማሪ ፍላጎቶች ለማሟላት በሚል ይለያያል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### አገናኞች

**ሲቪክስ አገናኝ**

**እንግሊዝኛ አገናኝ**

**ታሪክ አገናኝ**

**ሳይንስ አገናኝ**

የአገናኝ ኮርሶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ የእድገት ክፍሎች ሲሆኑ በተለየ ሁኔታ የረዥም ጊዜ እረፍቶችን ወይም መቆራረጦችን በመደበኛው የእንግሊዝኛ ትምህርታቸው (SLIFE) የነበራቸው እና በመጀመሪያ ቋንቋ እውቀታቸው ዝቅተኛ የውጤት ደረጃ በጉልህ ደረጃ ያስመዘገቡ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተነደፉ ናቸው። የ Bridges ፕሮግራም ለ SLIFE ተማሪዎች የተጠናከረ እና ግለሰባዊ የሆነ ጣልቃ ገብነት ያለበት በአለም ውስጥ ጭብጣዊ በሆነ አካሄድ የሚቆይ የእንግሊዝኛ ስነጽሁፍ ክህሎቶችን ለመገንባት ትርጉምን የሚጠቀሙ የተበጁ የክፍሎች ስብስብን ያቀርባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

### ለ 21ኛው ክፍለዘመን የኮሌጅ ብቃቶች ሀ

በዚህ ተግባራዊ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች በት/ቤት እና በስራ ቦታ ላይ ለስኬት ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ 9-12 መስፈርቶች የይዘት አካባቢ ክፍሎች ኮርስ ተማሪዎች የንባብ፣ የጽሁፍ፣ የንግግር እና የማዳመጥ ክህሎቶችን ያመለክታሉ። ተማሪዎች ለተለያዩ አላማዎች ያነባሉ፣ ያጠቃልላሉ፣ ገለጻ ያደርጋሉ፣ ንፅፅር እና ተቃርኖ ያደርጋሉ እንዲሁም በጥልቀት ያነባሉ። እነሱ የጽሁፍ ክህሎቶችን እና የጽሁፍ ሂደትን በመተግበር ልምዶችን እና የምርምር ፕሮጀክቶችን ለማጥናት፣ እና በዝግጅቶች እና ማሳያዎች በኩል ውጤታማ የሆኑ የቃል ግንኙነት ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። በተጨማሪም፣ ከፍ ያለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተማሪዎች መረጃ እንዲያገኙ እና በግልጽ የተጻፈ ግንኙነት እንዲያዘጋጁ ይረዳቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### ለ 21ኛው ክፍለዘመን የኮሌጅ ብቃቶች ለ

በዚህ ተግባራዊ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች በት/ቤት እና በስራ ቦታ ላይ ለስኬት ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። ለይዘት አካባቢ ክፍሎች የኮርስ መስፈርቶች ተማሪዎች የንባብ፣ የጽሁፍ፣ የንግግር እና የማዳመጥ ክህሎቶችን ያመለክታሉ። ተማሪዎች ለተለያዩ አላማዎች ያነባሉ፣ ያጠቃልላሉ፣ ገለጻ ያደርጋሉ፣ ንፅፅር እና ተቃርኖ ያደርጋሉ እንዲሁም በጥልቀት ያነባሉ። እነሱ የጽሁፍ ክህሎቶችን እና የጽሁፍ ሂደትን በመተግበር ልምዶችን እና የምርምር ፕሮጀክቶችን ለማጥናት፣ እና በዝግጅቶች እና ማሳያዎች በኩል ውጤታማ የሆኑ የቃል ግንኙነት ክህሎቶችን ያጎለብታሉ። በተጨማሪም፣ ከፍ ያለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተማሪዎች መረጃ እንዲያገኙ እና በግልጽ የተጻፈ ግንኙነት እንዲያዘጋጁ ይረዳቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የፈጠራ ጽሁፍ

ይህ ክፍል ለግጥም እና ፕሮዝ መጻፍ የተለየ ችሎታ ለሚያሳዩ ተማሪዎች የታለመ ነው። ተሳታፊዎች የጽሁፍ እና የህትመት ሂደቶች፣ የግጥም ዝግጅት፣ የአጫጭር ልብወለድ እና ድራማጥልቅ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ። የተማሪ ጽሁፍ ቡድኖች የጓደኛ ትችትን እና ልዩ የጽሁፍ አይነቶችን መሻሻል ይደግፋል። ተሳታፊዎች ባህሪያትን ለመሳል፣ ቅንብሮችን ለመመስረት፣ ትረካ ላይ ለማተኮር እና ምልክቶችን ለመጠቀም መሰረታዊ ቴክኒኮችን ይካናሉ። የጽሁፍ ስራ ግላዊ ፖርትፎሊዮዎችን ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ክፍሉ የተማሪ ጽሁፎችን የህትመት ስራ ያዘጋጃል። ተማሪዎች የታዳጊ ጸሃፊያንን ስራዎች በሚያጎሉ ውድድሮች እና መጽሄቶች የተመረጡ ስራዎችን እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ናሙና መጻፍ

### ክርክር I

ይህ ክፍል ከፖሊሲ ክርክር ጋር የተሳሰረ መዋቅር  እና ስትራቴጂዎች ላይ ፍላጎት  ተሳታፊዎች በየአመቱ ላለው የተለየ የክርክር ርዕስ፣ በክርክር እና በምርምር ላይ ያሉትን ሁለቱንም የቴክኒኮች ጥልቅ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ። የተማሪ የክርክር ቡድኖች ምርምር ለማድረግ፣ ስትራቴጂዎችን ለመቅረጽ እና ክርክሮችን ለማዘጋጀት ትብብርን ያበረታታሉ። ተሳታፊዎች መሰረታዊ ንግግር እና የምርምር ክህሎቶችን እንዲሁም ሎጂክ እና ምክንያታዊነትን ይካናሉ። የፖሊሲ ክርክርን ከማጥናት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች የክርክር ታሪክን እና ዘመናዊ መተግበሪያዎችን እንዲሁ ይማራሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### ክርክር II

ይህ ኮርስ በክርክር ክህሎቶቻቸው አንድ እውቀታቸው ላይ መገንባት ለሚቀጥሉ ተማሪዎች ነው። ይህ ኮርስ ተማሪዎች ሃገራዊ የፖሊሲ ክርክር ርዕስን እንዲመረምሩ እና እንዲከራከሩ ይፈቅዳል። በክርክር II ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው መስራት ይጠበቅባቸዋል እና በኮርስ ውሳኔዎች ውስጥ በንቃት መሳተፍ ይገባቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ክርክር I

### እንግሊዝኛ ለአካዳሚክ አላማዎች (EAP)

- EAP አልጄብራ I
- EAP አልጄብራ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንተና
- EAP አልጄብራ II
- EAP ባዮሎጂ
- EAP የመሬት ሳይንስ
- EAP ኢኮሎጂ
- EAP እንግሊዝኛ
- EAP ጂኦሜትሪ
- EAP ቴክኖሎጂ*
- EAP የ U.S./ቨርጂኒያ ታሪክ
- EAP የአለም ስልጣኔዎች I
- EAP የአለም ስልጣኔዎች II

እንግሊዝኛ ለአካዳሚ አላማ (EAP) ኮርሶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ክፍሎች ሲሆኑ የተነደፉት በተለይ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሲሆን ከዋና የይዘት ኮርሶች ጋር ጎን ለጎን ይተገበራሉ። በ EAP ውስጥ፣ በይዘት አካባቢው ውስጥ በተለያዩ ዘውጎች ያሉ ጽሁፎችን በማዘጋጀት እና በመረዳት እንዲሁም በአምስት የቋንቋ ብቃቶች አካባቢ ብቁ ለመሆን ተማውዎች የቀጥታ ቋንቋ መመሪያን ይቀበላሉ። ተማሪዎች በማዛመድ የ SOL ወይም ዋና ክፍል የ EAP ክፍል ብቻ ማስገባት አለባቸው እንዲሁም በማስረጃ አካል ምርመራ ላይ በመመስረት ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ይታወቃል (ለምሳሌ፣ የት/ቤት ታሪክ፣ ውጤቶች፣ የአስተማሪ ድጋፍ፣ ለ ELLs ደረጃዎች መዳረሻ፣ የ SRI ነጥብ እና የጽሁፍ ናሙናዎች)።

EAP ቴክኖሎጂ የሚዛመድ የ SOL ኮርስን አይደግፍም። ከኮምፒውተር ፕሮግራሞች ጋር የተወሰነ ልምድ ላላቸው ጀማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተግባር ኮርስ ነው።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የማንበብና መጻፍ መሰረቶች

ይህ ኮርስ ተማሪዎች የተግባራዊ የንባብ ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ እና አዳዲስ ስትራቴጂዎችን በማዳበር በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክፍሎቻቸው የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ካሪኩለሙ ሙያዊ እና አካዳሚያዊ መማርን ያሰፋል እና መሰረታዊ የንባብ ብቃትን በማጎልበት ግላዊ ደህንነትን ያስተዋውቃል። ትምህርቱ ንቁ በሆነ መጻፍና ማንበብ በምርምር ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን ይጠቀማል። ተማሪዎች በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በመናገር፣ በመስማት እና በማሰብ ውስጥ ያሉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ እንዲሁም ይተገብራሉ። የዚህ ኮርስ አስፈላጊ አላማው ተማሪዎች ለመዝናናት ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ ለማበረታታት ነው።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

### ጋዜጠኝነት I

ተማሪዎች ትክክለኛ መረጃን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የጋዜጠኝነት ክህሎቶችን ያገኛሉ እና በትክክል እና በአጭሩ ይጽፋሉ። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ በርካታ የሚዲያ አይነቶችን ይመረምራሉ። ተማሪዎች የቃለመጠይቅ፣ የጽሁፍ እና ለጋዜጦች ወይም አመታዊ መጻህፍት መሰረታዊ ክህሎቶች አቀማመጥ እንዲሁ ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### ጋዜጠኝነት II፦ መጽሄት

ተማሪዎች የት/ቤቱን ስነጽሁፍ እና የስነጥበባት መጽሄት የሆነውን Labyrinth የመፍጠር ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች ሁሉንም አይነት የመጽሄት ፈጠራ እና ህትመት አይነቶች ያስተዳድራሉ፣ ይህም የሚያካትተው ከ A.C.ተማሪዎች የጽሁፍ እና የእይታ ማስገባቶችን መሰብሰብ፣ ስራን ለህትመት መምረጥ፣ መጽሄቶችን መንደፍ እና ወደ ህዝቡ ማውጣት እና የገንዘብ ማሰባሰቢያ ማዘጋጀት ናቸው፦፤ የሰራተኛ አባላት ስርአት ያላቸው፣ በራሳቸው የተነቃቁ፣ ቡድን አቀፍ፣ ለማወቅ የሚጓጉ እና ወደፈጠራ ያደሉ መሆን አለባቸው። ጸሃፊዎች፣ አርቲስቶች፣ ፎቶ አንሺዎች እና ሌላ የፈጠራ ግለሰቦች የእኛ ሰራተኞች ጋር ለመቀላቀል ይበረታታሉ። ግራፊክ ዲዛይን የኮርሱ አንድ አስፈላጊ አካል ነው። Adobe InDesign እና Photoshop ጥቅም ላይ ውለዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

### ጋዜጠኝነት II፦ ጋዜጣ

ተማሪዎች የት/ቤቱ ጋዜጣ የሆነውን Theogony የማተም ሃላፊነት አለባቸው። ጋዜጣው በየአመቱ በወረቀት እና በኦንላይን ይታተማል። ጋዜጣው ሙሉ በሙሉ በተማሪ ይንቀሳቀሳል። በዚህ ኮርስ ውስጥ ያሉ አስፈላጊ ክህሎቶች የሚያካትቱት ግልጽ፣ አጭር ታሪኮችን ቃለመጠይቅ ማድረግ እና መጻፍ ናቸው። ተማሪዎች በመጻፍ እና በሰዋሰው በሁለቱም ያላቸውን ብቃት ማሳየት አለባቸው። በእንግሊዝኛ ኮርሶች ከፍተኛ ውጤቶች ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። የጋዜጠኝነት I ያልወሰዱ ለዚህ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች የጽሁፍ ፈተናን እንዲወስዱ እና እንዲያልፉ ሊጠየቁ ይችላሉ። የሰራተኛ ጽሁፎች ወርሃዊ ቀነ-ገደቦችን ማክበር አለባቸው እና አርትዕ የተደረገባቸውን ስራ ለማስተካከል ዝግጁ መሆን አለባቸው። ፎቶ አንሺዎች ተመሳሳይ የጊዜ ገደቦች ላይ መድረስ አለባቸው። ግራፊክ ዲዛይን የዚህ ኮርስ አንድ አስፈላጊ አካል ነው። ፎቶሾፕ እና ኢንዲዛይን ጥቅም ላይ ይውላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

### ጋዜጠኝነት II፦ አመታዊ መጽሃፍ

ተማሪዎች የት/ቤቱ ጋዜጣ የሆነውንና ሙሉ በሙሉ በተማሪዎች የሚንቀሳቀሰውን የማተም ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በመጻፍ እና በሰዋሰው በሁለቱም ያላቸውን ብቃት ማሳየት አለባቸው። በእንግሊዝኛ ኮርሶች ከፍተኛ ውጤቶች ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። የሰራተኛ ጽሁፎች እንዲሁ ቀነ-ገደቦችን ማክበር አለባቸው እና አርትዕ የተደረገባቸውን ስራ ለማስተካከል ዝግጁ መሆን አለባቸው። ፎቶ አንሺዎች የጊዜ ገደቦቹን ላይ ማድረስ አለባቸው እና የራሳቸው ካሜራዎች ሊኖራቸው ይገባል። ግራፊክ ዲዛይን የዚህ ኮርስ አንድ አስፈላጊ አካልም ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

### ማንበብና መጻፍ

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች መሰረታዊ ክህሎቶችን የሚከተሉትን በማካተት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ይማራሉ፤ የደብቢቤ መለየት፣ የቃል ማጥቃት ክህሎቶች፣ የእይታ ስራ መለየት፣ የቁንቋ እድገት እና የአርፍተ ነገር አወቃቀር ናቸው። እነዚህ የስነጽሁፍ ክህሎቶች ህዝባዊ ትራንስፖርቶችን ለማግኘት፣ የቅጥር እድሎችን ለማግኘት እና ራስን ችሎ ለመኖር ያስፈልጋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

### ማንበብና መጻፍ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች

ይህ ኮርስ ፈጣን የመማር እና የቋንቋ መቅሰምን ኢላማ ውስጥ ለሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ላሉ የ EL ተማሪዎች ያስተዋውቃል። እንደ MTSS፣ ይህ የ Tier III ጣልቃ ገብነት ኮርስ ነው። ኮርሱ ታዳጊ ሆነው እየተነሱ ለሆኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀት የጀማሪ ደረጃ ላይ ያሉ እና የንባብ ግንዛቤ እና ትርጉም፣ ጽሁፍ፣ ንግግር እና ማዳመጥን ለማዳበር ለሚፈልጉ አንባቢዎች የተነደፈ ነው። ኮርሱ የተማሪ እንቅስቃሴ የስነጽሁፍ ተከታታይነትን ከመነሻ መሰረታዊ የቋንቋ ማግኛ እስከ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ውስጥ ያሉትን የሚመራ እና ራሱን የቻለ መተላለፍ ደረጃን ጨምሮ ይደግፋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ደረጃ III ጣልቃ ገብነትን የሚጠይቁ የ EL ተማሪዎችን ኢላማ ማድረግ

### የህዝብ ንግግር I

ይህ ኮርስ የተማሪዎችን በራስ መተማመን፣ ሃሳቦችን የማደራጀት ችሎታ እና ለሌሎች ሰዎች ያለው ስሱነትን ይገለብታል። ተማሪዎች ከጓደኞች፣ ከወላጆች እና ከአስተማሪዎች ጋር እንዲያወሩ የሚረዳቸውን ክህሎቶች ሲማሩ የእርስ በእርስ ግንኙነት ላይ ይሰራሉ፤ በስራ እና በኮሌጅ ቃለ መጠይቆች ላይ ይሳተፋሉ፤ እንዲሁም በቡድኖች ፊት ሆነው ያወራሉ። ተማሪዎች ርዕስ እንዲመርጡ ይማራሉ፤ ሃሳቦችን መቅረጽ፣ ማደራጀት እና መደገፍ፤ እና እነዚህን ስኬታማ ንግግር እንዲሆኑ መፍጠር።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### የህዝብ ንግግር II

ይህ ኮርስ የሚተረጎም አነጋገር ላይ ይዞራል እንዲሁም ከመግለጫ እና ድራማዊ ዱዎ፣ ወደ ድራማዊ ትርጓሜ እና የመጀመሪያ ስራዎች ያሉ በርካታ የትርጓሜ አካባቢዎችን ያስተምራል። ያለጊዜ መናገር እና ያለጊዜ መሥራትም እንዲሁ ተካትቷል። የህዝብ ንግግር I ለዚህ ኮርስ ቅድመ-ሁኔታ አይደለም።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### የጽሁፍ ማዕከል የጓደኛ ማጠናከሪያ ትምህርት

ይህ ኮርስ ተማሪ ጸሃፊዎች ጉዳደኛ ስተማሪዎች እንዲሆኑ ያግዛቸዋል። የኮርሱ መጀመሪያ የማዕከል ጽንሰ ሃሳብ እና መሰረታዊ የትምህርት አካሄዶችን ይሸፍናል። ከስልጠና ጊዜው በኋላ፣ አስተማሪዎች የቀረውን ኮርስ በማስተማር፣ የጽሁፍ ማዕከልን ለማሻሻል በግላዊ ፕሮጀክቶች ላይ መስራት፣ እና የራሳቸውን አጻጻፍ በማጎልበት ያሳልፋሉ። በተጨማሪም አስተማሪዎች በመጻፊያ ማዕከል ኮንፈረንሶች ላይ የማቅረብ፣ ከአስተማሪዎች ጋር ክፍል ውስጥ መስራት እና ጽሁፋቸውን ለጽሁፍ ማዕከል ህትመቶችን የማስገባት እድሎች አሏቸው። አስተማሪዎች የእርስ በእርስ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ፣ የጽሁፍ ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ፣ የመሪነት ክህሎትን ያገኛሉ እና የጽሁፍ ማዕከል ማህበረሰብ አካል የመሆን እድሎችን ይኖራቸዋል። ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ለጽሁፍ ማዕከል ዳይሬክተሩ ማመልከቻ (ከእንግሊዝኛ አስተማሪ ፈቃድ መስጠት ጋር) ማስገባት ያስፈልጋቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ማመልከቻ እና ለማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራሙ ያለ ተቀባይነት

# የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

ሁሉም የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ኮርሶች በተመራጭ ክሬዲት ላይ ይተገበራል።

**25ኛው ሰአት የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**

25ኛው ሰአት የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት የ9ኛ ወይም 10ኛ ክፍል የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት መስፈርት። በዚህ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ ባሉ ሰአታት ራሳቸውን ችለው የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ይተነትናሉ እንዲሁም ይመዘግባሉ። ተማሪዎች የልብ ምት መቆጣጠሪያዎችን በመጠቀም ወይም በ ACPS በጸደቁ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንዲሳተፉ አማራጭ አላቸው።

ሁሉም ተማሪዎች የግላዊ አካል ብቃት ደረጃቸውን ለማወቅ እና የግላዊ አካል ብቃት እቅድ በማጎልበት የግለሰባዊ ማሻሻያን ለመለካት እንደ ምክንያት ለመውሰድ በአመቱ ውስጥ የቨርጂኒያ ከጤንነት ጋር የተገናኘ የአካል ብቃት ምርመራዎች ይሰጧቸዋል። በግለሰብ ስብሰባዎች እና በሽራ ጊዜ ከአስተማሪው ጋር ያለ ግንኙነት ይካሄዳል።

**ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ**ክፍሉ የ CPR እና የካሪኩለሙ የመጀመሪያ እርዳታ ክፍልን ለመሸፈን እንዲሁም ለአካል ብቃት ሙከራ መርሃግብር እንደተያዘለት በመጀመሪያው ሩብ አመት ይሰበሰባል። በአንድ ሩብ አመት ወቅት የቨርጂኒያ ጤና የመማር ደረጃዎች በ Canvas በኩል ትምህርት ይሰጣል።

**ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ**ክፍሉ የአሽከርካሪ ትምህርትን ለመሸፈን እንዲሁም እንደ አካል ብቃት ሙከራ መርሃግብር ለአንድ ሩብ አመት ይሰበሰባል። የቨርጂኒያ ጤና የመማር ደረጃዎች በ Canvas በኩል ትምህርት ይሰጣል

ለ § 22.1-205 የመሪ ትምህርት ፕሮግራሞች ያለ ማሻሻያ የሆነውና በአጠቃላይ የቨርጂኒያ ጉባኤ የተደነገገው House Bill 1782 የመሪ ትምህርት ካሪኩለም የክፍል ውስጥ አካል በመሆን ለተጨማሪ የወላጅ/ተማሪ መሪ የትምህርት አካል አካታችነትን ይፈልጋል። ከአዲሱ ህግ ጋር ተገዢ በመሆን፣ ACPS የ 90 ደቂቃ የወላጅ/ ተማሪ የትራፊክ ደህንነት አቀራረብን ይፈልጋል፣ ይህም ማከተት የሚያስፈልገው ሀ) ታዳጊ የነጂ ባህሪን በተመለከተ የወላጅ ሃላፊነቶች፣ ለ) በቨርጂኒያ ኮድ መሰረት የታዳጊ አነዳድ ገደቦች እና ሐ) ጠጥቶ መንዳት እና ከመጠጫ እድሜ በታች ሆኖ አልኮል መጠቀም ያላቸው ጉዳቶች።

በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ለእድሜ የሚመጥን የቤተሰብ የህይወት መመሪያ በዚህ ኮርስ ውስጥ ያገኛሉ። ይዘት በስቴት የመማሪያ ደረጃዎች ላይ ይመሰረታል፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ከመመሪያው የማስወጣት እድል ይኖራቸዋል።

ተማሪ ከዚህ ኮርስ ጋር የተገናኙ ክፍያዎችን የመክፈል ሃላፊነት አለበት። Fitbits ዝቅተኛ በሆነ የኪራይ ዋጋ ይገኛል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10

**ርዝመት፦** አንድ ሴሚስተር

**ተስማሚ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**

ይህ ኮርስ ለአጠቃላይ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ተጨማሪ ነው። በመደበኛ የሰውነት ማጎልመሻ የትምህርት ክፍሎች ለመሳተፍ የማይችሉ ተማሪዎች የእድገት እንቅስቃሴዎች፣ ጨዋታዎች፣

ስፖርቶች እና ሪትሞች ኮርስ ሊቀርብላቸው ይችላል። ንቁ ተሳትፎ በበርካታ የመዝናኛ ስፖርቶች ውስጥ ይበረታታል።

ተማሪዎች ለተሳታፊው የተወሰኑ ሁኔታዎች የሚስማሙ ደንቦችን እና ቴክኒኮችን ለስፖርቶች ይማራሉ። በዚህ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች መደበኛ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና/ወይም አስፈላጊ ሲሆን የጤና ትምህርት ክፍሎችን ሊቀላቀሉ ይችላሉ። ግቡ ተማሪዎች ችሎታቸውን ከዕለት ተዕለት አኗኗር ጋር እንዲያለማምዱ ለመርዳት ነው።

**ማስታወሻ:**

ሙሉ አመት

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የአካል ብቃት I

ይህ ተመራጭ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ሲሆን በአካል ብቃት፣ በጥንካሬ ስልጠና፣  በአካላዊ ማመቻቸት እንዲሁም ጤና እና ደህንነትን ለማስተዋወቅ በህይወት ዘመን የጤና ጽንሰሃሳቦች፣ እንቅስቃሴዎች እና እውቀት ላይ ያተኩራል። ይህ ኮርስ ለጀማሪ እና ለከፍተኛ ተማሪ ግለሰባዊ የክብደት ስልጠና እና የአካል ብቃት ማመቻቸትን ለማጎልበት የተዋቀረ ነው። ኮርሱ የስልጠና መርሆዎችን በደንብ ማወቅ እና ከምዘና ክፍል ላብራቶሪ ተሞክሮዎች ተሳትፎ አስቀድሞ የአካል ብቃት ማዕከል የደህንነት ህጎችን በደንብ መረዳት ይጠይቃል። ተማሪዎች ጤናን የሚያሻሽል የአካል ብቃትን ለህይወት ዘመን ሙሉ ለማግኘት እና ለመጠበቅ ያሉ የክህሎት እና ከጤና ጋር የተገናኘ የብቃት ክፍሎችን ያካተተ የግል የአካል ብቃት እና የማመቻቸት ፕሮግራም ለማቀድ እና ለማስፈጸም የሚሆን አስፈላጊ መረጃን እና ክህሎቶችን ያገኛሉ።

ይህ ኮርስ ለጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 ወይም  የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ምትክ ወይም ወይም እኩሌታ አይደለም።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### የአካል ብቃት II

ይህ ተመራጭ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ኮርስ ነው። የዚህ ኮርስ አላማ ተማሪዎች የአካል ብቃት ጽንሰሃሳቦችን፣ መርሆዎችን እና ስትራቴጂዎችን እውቀት በማሳየት ከፍተኛ የሆነ የአካል ብቃት ደረጃን እንዴት ማሳካት እና መጠበቅ እንደሚቻል ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማስቻል ነው። የእያንዳንዱ ተማሪ የአካል ብቃት ደረጃዎች ይገመገማሉ እንዲሁም ተማሪው የግል ግቦችን ይቀርጻል እና ግላዊ የአካል ብቃት ፕሮግራሞችን ያጎለብታል። ተማሪዎች የለብና የመተንፈሻ መቋቋምን፣ መተጣጠፍን፣ የጡንቻ ጥንካሬን እና ስናትን እንዲሁም የአካል መዋቅርን ለማሻሻል እነዚህን ግላዊ የአካል ብቃት ፕሮግራሞች ያጎለብታሉ እንዲሁም ይሳተፋሉ። ተማሪዎች የግላቸውን የአካል ብቃት እቅድ ለመገምገም፣ ለማቀድ፣ ለመቆጣጠር እና ለመለወጥ ጽንሰ ሃሳቦችን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በመማር እና በሰውነት ብቃት ስልጠና አፈጻጸም ላይ የሚተገበሩ የሳይኮሎጂያዊ እና ማህበራዊ ጽንሰ ሃሳቦችን፣ መርሆዎችን እና ስትራቴጂዎችን ያሳያሉ። የይዘት ደረጃዎች የሚያካትቱት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደቡት፤ ለደህንነት፣ ለህጎች እና ደንቦች፣ ለቃላት፣ ለሰርኪዩት ስልጠና፣ ለክሮስፊት ስልጠና፣ ለክብደት ስልጠና፣ ለመለጠጥ እንዲሁም ለአይሶሜትሪክ እና ፕላዮሜትሪክ እንቅስቃሴዎች ነው።

ይህ ኮርስ ለጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 ወይም  የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ምትክ ወይም ወይም እኩሌታ አይደለም።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የአካል ብቃት I

### የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9

ዘጠነኛ ክፍል ያለው የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ለምርቃት ያስፈልጋል እና ለአካላዊ ግንባታ የምርጫ አካሄድን ለተማሪዎች ይሰጣል እንዲሁም ንቁ የሆነ ህይወትን ለመምራት የመሰረት ስራውን ይሰራል። በግምት በየሁለት ሳምንቱ ተማሪዎች ለእንቅስቃሴ ምሪት ይመዘገባሉ (የቡድን ስፖርቶች፣ የግለሰብ ስፖርቶች፣ ከቤት ውጪ መዝናኛ ወይም የማሰስ እንቅስቃሴዎች) ሁሉም ተማሪዎች የግላዊ አካል ብቃት ደረጃቸውን ለማወቅ እና የግለሰባዊ ማሻሻያን ለመለካት እንደ ምክንያት ለመውሰድ በአመቱ ውስጥ የቨርጂኒያ ከጤንነት ጋር የተገናኘ የአካል ብቃት ምርመራዎች ይሰጧቸዋል። የጤና ትምህርት መመሪያ አመቱን ሙሉ በዙር የሚከናወን ነው እና ትኩረቱም በአመጋገብ ትምህርት፣ የሸማች ጤና፣ የአእምሮ ጤና፣ የመድሃኒት አጠቃቀም፣ የማህበረሰብ ጤና፣ የአካል ብቃት መርሆዎች እና AED፣ CPR እና የመጀመሪያ እርዳታ መመሪያ ላይ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ለእድሜ የሚመጥን የቤተሰብ የህይወት መመሪያ በዚህ ኮርስ ውስጥ ያገኛሉ። ይዘት በስቴት የመማሪያ ደረጃዎች ላይ ይመሰረታል፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ከመመሪያው የማስወጣት እድል ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

### የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10

አስርኛ ክፍል ያለው የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ለምርቃት ያስፈልጋል እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት የምርጫ አካሄድን ለተማሪዎች ይሰጣል። በእያንዳንዱ ሩብ አመት መጀመሪያ ላይ፣ ተማሪዎች ለእንቅስቃሴ ጥምረት (የቡድን ስፖርቶች፣ የግል ስፖርቶች፣ የውጪ መዝናኛ ወይም የአሰሳ እንቅስቃሴዎች) ይመዘገባሉ። በሳምንት አንዴ፣ ተማሪዎች የቨርጂኒያ የትምህርት ጤና ደረጃዎችን እና የቨርጂኒያ ከጤና ጋር የተገናኙ የአካል ብቃት ሙከራዎችን ያካትታሉ። ተማሪዎች የግል አካል ብቃት እቅዶችን ያጎለብታሉ፣ እንቅስቃሴን ለመለካት ፔዶሜትሮችን ይጠቀማሉ እና የአካላዊ እንቅስቃሴ መጠንን ለመለካት የልብ ምት መቆጣጠሪያዎችን ይጠቀማሉ። የመንዳት ትምህርት በሁለተኛው እና በሶስተኛው ሩብ አመት ብቻ የሚሰጥ ይሆናል እና ለክፍል ትምህርት የሚያስፈልገውን የ 36-ሰአት የማስተማሪያ ጊዜን ያሟላል። የ CPR መመሪያ በመደበኛነት በአራተኛው ሩብ አመት ወቅት ይከናወናል።

ACPS ከሚያቀርባቸው 36 የክፍል ውስጥ ሰአታት በተጨማሪ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉ ግለሰቦች በግል በተቀጠረ አስተማሪ 14 የመኪና ውስጥ ስልጠና ክፍለ ጊዜን እና የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር በመሆን 45 ሰአታትየተመሰከረለት አነዳድ ማጠናቀቅ አለበት። ለበለጠ መረጃ ወደ ቨርጂኒያ DMV ድረገጽ ይሂዱ።

ለ § 22.1-205 የመሪ ትምህርት ፕሮግራሞች ያለ ማሻሻያ የሆነውና በአጠቃላይ የቨርጂኒያ ጉባኤ የተደነገገው House Bill 1782 የመሪ ትምህርት ካሪኩለም የክፍል ውስጥ አካል በመሆን ለተጨማሪ የወላጅ/ተማሪ መሪ የትምህርት አካል አካታችነትን ይፈልጋል። ከአዲሱ ህግ ጋር ተገዢ በመሆን፣ ACPS የ 90 ደቂቃ የወላጅ/ ተማሪ የትራፊክ ደህንነት አቀራረብን ይፈልጋል፣ ይህም ማካተት

የሚያስፈልገው ሀ) ታዳጊ የነጂ ባህሪን በተመለከተ የወላጅ ሃላፊነቶች፣ ለ) በቨርጂኒያ ኮድ መሰረት የታዳጊ አነዳድ ገደቦች እና ሐ) ጠጥቶ መንዳት እና ከመጠጫ እድሜ በታች ሆኖ አልኮል መጠቀም ያላቸው ጉዳቶች።

በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ለእድሜ የሚመጥን የቤተሰብ የህይወት መመሪያ በዚህ ኮርስ ውስጥ ያገኛሉ። ይዘት በስቴት የመማሪያ ደረጃዎች ላይ ይመሰረታል፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ከመመሪያው የማስወጣት እድል ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9

### የዛሬዎቹን ታዳጊዎች የገጠሟቸው ጉዳዮች

አጠቃላይ የሰው ልጅ እድገት እና የማጎልበት ኮርስ ለቁም ነገር ግምት እና የቤተሰብ፣ የግንኙነቶች፣ የእጮኝነት ጥሰት፣ የሰው ልጅ ወሲባዊነት፣ የወላጅነት፣ የልጅ እድገት እና ከጉርምስና እስከ ጉልምስና የተለየ እድል ያቀርባል። ይዘት እና እንቅስቃሴዎች ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የታለመ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ ኮርሱ ከ 9-12ኛ ክፍል ውስጥ እንዲሁም ከ 9-12ኛ ክፍሎች አስቀድሞ በበጋ ት/ቤት ሊወሰድ ይችላል። ይህንን ኮርስ 9ኛ ክፍል ለመውሰድ ለሚፈልጉ ነገር ግን ኮርሱን መርሃ ግብር ለማስያዝ አስቸጋሪ የሆነባቸው ተማሪዎች በክረምት ትምህርት ወይም ቅደም ያለ ክፍል ከሆነ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 በመውሰድ ክፍል ሊፈጥሩ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### የአለም ዳንስ

ተማሪዎች የተለያዩ የምት እንቅስቃሴዎችን እና የዳንስ ዘውጎችን ያስሳሉ እንዲሁም ይመረምራሉ። ኮርሱ ላቲን፣ ሂፕሆፕ እና ማህበራዊ ዳንስ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች በቴክኒክ፣ በብቃት እና በኮርዮግራፊ ውስጥ ያለ ብቃትን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች በአለም ዙሪያ ላይ ዳንስ ያለውን ታሪካዊ እና ባህላዊ እንድምታ ላይ እንዲሁ ያተኩራሉ። አግባብ የሆነ የመደነሻ ጫማ ያስፈልጋል።

ይህ ኮርስ ለጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 ወይም  የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ምትክ ወይም ወይም እኩሌታ አይደለም።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

# አመራር

### የላቀ የመሪነት እድገት III

ይህ በመሪነት ተርታ ውስጥ የመጨረሻው ኮርስ ነው። ተማሪዎች በአዲሱ ፕሮግራም ውስጥ አዳዲስ ተማሪዎችን ሊያሰለጥኑ እና እንደ ምሳሌ ሞዴሎች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ተማሪዎች የት/ቤት ፕሮግራሞችን እና ዝግጅቶችን ማቀድ እና ማዘጋጀትን በቀዳሚነት ይመራሉ። ተማሪዎች አዳዲስ ፕሮግራሞችን ሊጀምሩ እና ሃሳቦች እንዴት እንደሚተገበሩ ሊማሩ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የአመራር ክህሎት እድገት

**የአመራር ክህሎት እድገት I**

ይህ ኮርስ በት/ቤት እና በድርጅቶች ውስጥ ንቁ ለሆኑ እና የመሪነት ክህሎቶችን ለመለየት እና ለመተግበር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የተነደፈ ነው። ወደመሪነት ፕሮግራሙ ተቀባይነትን ያገኙ ተማሪዎች በአካዳሚክ፣ አትሌቲክ፣ ማህበራዊ እና ሙያዊ (የስራ) አካባቢዎች በውጤታማነት እንዲንቀሳቀሱ የሚረዳቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ይማራሉ። ይህ ኮርስ ተማሪዎች በመሪነት በታዎች ላይ ሃላፊነት የሚሰማቸው እና የስነምግባር ባህሪን የተላበሱ ሆነው እንዲያስተዋውቁ ይረዳቸዋል። ተማሪዎች በርካታ የማርኬቲንግ እንቅስቃሴን ያሳድጋሉ እንዲሁም ይተገብራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11

**የአመራር ክህሎት እድገት II**

ተማሪዎች ከውጤታማ የመሪነት ክህሎቶች፣ ድርጅታዊ ባህሪን ከመረዳት፣ በስራ ቦታ ውጤታማ የሆነ ግንኙነት ከመጠቀም፣ የሰው ሃይልን እና የድርጅት ችግሮችን ከመቆጣጠር፣ ሰራተኞችን ከማማከር እና ከማሰልጠን፣ ግጭቶችን ከመፍታት እና ለወደፊቱ እቅድ ከማውጣት ጋር የተገናኙትን የግለሰብ ብቃቶችን በመለየት ያጎለብታሉ። በመሪነት ውስጥ ትምህርትን መቀጠል እንዲሁም ከት/ቤት እና ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር በጋራ በመሆን ተግባራዊ የመሪነት ክህሎቶች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የአመራር ክህሎት እድገት I

# የሂሳብ ትምህርት ዋና ኮርሶች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ ለአልጄብራ I፣ ለጂኦሜትሪ እና ለአልጄብራ II የ SOL የሂሳብ ሙከራዎች አሉ።

**AP ካልኩለስ AB**

ይህ ኮርስ ሊሚትስ፣ ዴሪቬቲቭስ እና ኢንቲግራልስ እንዲሁም አተገባበራቸውን ጨምሮ በካልኩለስ ውስጥ ስላሉ ርዕሶች ያስተምራል። በ AP ፈተና ጥሩ ነጥብ ላስመዘገቡ ተማሪዎች ኮሌጆች ከፍ ያለ ምደባ ወይም ክሬዲት ሊያበረክቱ ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ቅድመ-ካልኩለስ

**AP ካልኩለስ BC**

ይህ የ AP ኮርስ የነጠላ ተለዋዋጭ ፈንክሽኖች ካልኩለስ ጥልቅ የሆነ ማስተማርን ይሰጣል። የኮርስ ይዘቱ በኢንፋናይት ሲሪስ እና ፖላር እና ፓራሜትሪክ እኩልታዎች እንዲሁም በ AP ካልኩለስ AB ላይ ሽፋን የተሰጣቸው ርዕሶችን አካትቷል። ኮርሱ ኮሌጆች ከፍተኛ የሆነ ምደባ ወይም ክሬዲት በ AP ፈተና ላይ አሪፍ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች የሚሰጡት የኮሌጅ-ደረጃ ሂሳብ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ቅድመ-ካልኩለስ

በፕሪ ካልኩለስ C ወይም ከዚያ በላይ ውጤት ያግኙ።

## AP ኮምፒውተር ሳይንስ A

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የተወሳሰቡ ፕሮግራሞችን ጃቫን በመጠቀም ይነድፋሉ እንዲሁ ይጽፋሉ። በፕሮግራም ንድፍ፣ ዘዴዎች፣ የውሂብ አይነቶች እና አወቃቀሮች፣ ክፍሎች፣ አልጎሪዝሞች፣ የኮምፒውተር ስርዓቶች እና በኮምፒውቲንግ መስክ ጥቅም ላይ የሚውሉ እንደ መለየት እና ቴክኒኮችን መፈለግ የመሳሰሉ መተግበሪያዎች ላይ አጽንዖት ተሰጥቷል። ተማሪዎች ክላሶችን እና ፖይንተሮችን በመጠቀም እንዲሁም እነዚያን የውሂብ አይነቶች በገሃዱ አለም ማስመሰያዎች ውስጥ በመተግበር በርካታ የላቁ የውሂብ አይነቶችን ያጎለብታሉ። የኮርስ ይዘቱ የላቀ አመዳደብ የኮምፒውተር ሳይንስ ካሪኩለምን በቅርበት ይከታተላል እና ተማሪው የ AP ኮምፒውተር ሳይንስ A ፈተናን እንዲወስድ ያዘጋጀዋል።

ይህ ኮርስ በኦንላይን ብቻ ሊቀርብ ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ II

## AP ስታትስቲክስ

ተማሪዎች ውሂብን ለመተንተን፣ አግባብነት ያላቸው የውሁብ አሰባሰብ እና ትንተና ዘዴዎችን ለማወቅ፣ የውሂብ ስርጭት ምን መምሰል እንደሚገባው ለመገመት መማር እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሞዴሎችን ምርጫ ለመምራት ስታትስቲካዊ ማመዛዘንን ለመጠቀም ግራፊካል እና የአሃዝ ስልቶችን ይጠቀማሉ። የኮርስ ይዘት የላቀ ምደባ ፕሮባቢሊቲ እና ስታቲስቲክስ ፈተናን በቅርበት ይከታተላል። ተማሪዎች የፕሮባቢሊቲ እና ስታቲስቲክስ እውቀት ቁጥራቸው ለበዛ የኮሌጅ ዋና ትምህርቶች አስፈላጊነቱ እየጨመረ እንደመጣ ሊገነዘቡት ያስፈልጋል። ተማሪዎች የ TI-83 ወይም TI-84 ማስያዎችን በዚህ ኮርስ ውስጥ ይጠቀማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ከአልጄብራ II ያለፈ የአንድ አመት ሂሳብ

## አልጄብራ፣ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንተና

በሂሳባዊ ሞዴሊንግ እና የውሂብ ትንተና አውድ ውስጥ፣ ተማሪዎች ፈንክሽኖችን እና ባህሪያቸውን፣ የኢ-እኩልታዎችን ስርዓቶች፣ ፕሮባቢሊቲ እና የሙከራ ንድፍ እና አፈጻጸምን ይማራሉ። ውሂብ ከሳይንስ፣ ቢዝነስ እና ፋይናንስ ከሚመጡ ተግባራዊ መተግበሪያዎች ይፈጠራሉ። ተማሪዎች የሊኒየር፣ ኳድራቲክ፣ ኤክስፖኔንሻል ወይም ሎጋሪዝሚክ እኩልታዎችን ወይም የእኩልታዎች ስርዓትን አሰላል የሚጠይቁ ችግሮችን ይፈታሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ I እና ጂኦሜትሪ

**አልጄብራ II**

የላቀ የአልጄብራይክ ጽንሰ ሃሳቦች ዝርዝር አያያዝ በፈንክሽኖች፣ “በፈንክሽኖች ቤተሰብ፣ ”እኩሌታዎች፣ ኢ-እኩሌታዎች፣ የእኩሌታዎች እና ኢ-እኩሌታዎች ስርአቶች፣ ፖሊኖሚያልስ፣ ራሽናል እና ራዲካል እኩሌታዎች፣ ኮምፕሌክስ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተሎች እና ተከታታዮች በኩል ቀርቧል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ I ጂኦሜትሪ

**ዲስክሪት ሂሳብ**

ይህ ኮርስ የሚቆጠር (የተለየ) አካላት ቁጥር ያለው የሂሳብ ስብስብ እና ስርዓቶች ባህርያት ጥናት ነው። በኮርሱ ውስጥ ያሉ ርዕሶች የሚያካትቱት የምርጫ ጽንሰ ሃሳብ፣ ፍትሃዊ ውሳኔ፣ ክፍፍል፣ የግራፍ ጽንሰ ሃሳብ እና መደጋገም ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ II ወይም አልጄብራ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንታኔ

**ባለሁለት ምዝገባ ካልኩለስ II**

ይህ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አመት የተበተነ የኮሌጅ ሴሚስተር ኮርስ ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች 4 የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ይህ ኮርስ ሬክታንጉላር፣ ፖላር እና ፓራሜትሪክ ትግበራዎችን በማካተት የአልጄብሪክ እና ትራንስደንታል ፈንክሽኖች ካልኩለስ ትምህርትን ይቀጥላል። ትምህርቱ የሂሳብ፣ የአካላዊ እና የምህንድስና ሳይንስ ፕሮግራሞችን ይዟል። ይህንን ኮርስ የሚወስዱ ተማሪዎች የ AP ካልኩለስ BC ፈተናን መውሰድ ይችላሉ። ይህ ኮርስ በኦንላይን ላይ በገለልተኛ ትምህርት በኩል ብቻ ሊሰጥ ይችላል እና የ Virginia Community College የሴሚስተር መርሃግብርን ይከተላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

አንድ ሴሚስተር

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በ AP ካልኩለስ AB ፈተና 4 ወይም የተሻለ ማምጣት እና ሁሉንም የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶች ማሟላት

**ባለሁለት ምዝገባ ካልኩለስ III እና ዲፈረንሻል እኩልታዎች**

ይህ ሁለት ሴሚስተር ባለሁለት ምዝገባ ኮርስ ሲሆን የቀረበውም በ NOVA ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች 7 የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። የኮርሱ የመጀመሪያ ሴሚስተር የሚያተኩረው የፈንክሽን፣ የሊሚት፣ የኮንቲኒዩቲ፣ የዴሪቬቲቭ፣ የኢንቲግራል እና የቬክተር ቅርጽ ወደ ሁለት እና ሶስት አቅጣጫ ቦታ ጽንሰ ሃሳቦችን ያሰፋል። ርዕሶች የሚያካትቱት፤ የቬክተር ፈንክሽኖች፣ መልቲቫሪዬት ፈንክሽኖች፣ ፓርሻል ዴሪቬቲቭስ፣ መልቲፕል ኢንቲግራል እና የቬክተር ካልኩለስ መግቢያን ነው። ሁለተኛ ሴሚስተር ኦርዲናሪ ዲፈረንሻል እኩሌታዎችን ያስተዋውቃል። ርዕሶች የሚያካትቱት፤ የመጀመሪያ ደረጃ ዲፈረንሻል እኩሌታዎች፣ ሁለተኛ እና ከዚያ በላይ ደረጃ መደበኛ የዲፈረንሻል እኩሌታዎች ከመተግበሪያቸው እና የአሃዝ ዘዴዎች ጋር። ይህ ኮርስ በኦንላይን ላይ በገለልተኛ ትምህርት በኩል ብቻ ሊሰጥ ይችላል እና የ Virginia Community College የሴሚስተር መርሃግብርን ይከተላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

አንድ ሴሚስተር

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በ AP ካልኩለስ BC ፈተና 4 ወይም የተሻለ ማምጣት እና ሁሉንም የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶች ማሟላት

ሂሳብ

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች መሰረታዊ ክህሎቶችን የሚከተሉትን በማካተት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ይማራሉ፤ የሂሳብ ስሌቶች፣ ገንዘብ መቁጠር እና አስተዳደር ናቸው። እነዚህ ተግባራዊ የሂሳብ ክህሎቶች ህዝባዊ ትራንስፖርቶችን ለማግኘት፣ የቅጥር እድሎችን ለማግኘት እና ራስን ችሎ ለመኖር ያስፈልጋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ተማሪው ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው።

**ቅድመ-ካልኩለስ**

ስለፈንክሽኖች፣ ስለአናሊቲክ ጂኦሜትሪ እና ትሪጎኖሜትሪ መደበኛ የሆነ የካልኩለስ ትምህርትን ይቀድማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ II

**ፕሮባቢሊቲ እና ስታትስቲክስ**

ይህ የመግቢያ ስታቲስቲክስ እና ፕሮባቢሊቲ ኮርስ ውሂብን መሰብሰብ እና መተንተን፣ ግምቶችን ማድረግ እና ትርጉም ባላቸው መንገዶች ውሂብን በማደራጀት ግራፍ ማድረግ ላይ ያተኩራል። ርዕሶች የሚያካትቱት የተቆጣሪ ህጎች permutations and combinations የ univariate እና bivariate ውሂብ፣ መደበኛ ስርጭት እና የዳሰሳ ጥናት ትንታኔ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጄብራ II ወይም አልጄብራ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንታኔ

# የሂሳብ ተመራጮች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ ለአልጄብራ I፣ ለጂኦሜትሪ እና ለአልጄብራ II የ SOL የሂሳብ ሙከራዎች አሉ።

**AP የኮምፒውተር ሳይንስ መርሆዎች**

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ለኮምፒውተር ሳይንስ መግቢያ በማስተዋወቅ ለፕሮግራሚንግ እና በአሁኑ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን የኮምፒውተሮችን ተጽዕኖ ያሳያሉ። ኮርሱ ችግር መፍታት እና የገሃዱ አለም ትግበራዎች ላይ ያተኩራል። የትምህርቱ ክፍሎች የሚያካትቱት፤ የመረጃ እና የውሂብ ማውጣጣት የዲጂታል ውክልና፣ አልጎሪዝሞች፣ ኢንተርኔት እና ፕሮግራሚንግ እንዲሁም የክንውን ስራዎች ከብዙዎቹ ውስጥ ናቸው። ይህ ኮርስ በኮምፒውተር ሳይንስ እና በ STEM መስኮች ያለውን ተሳትፎ ለማስፋት የተነደፈ ነው እንዲሁም በሃገራዊ የሳይንስ ፋውንዴሽን በከፍተኛ ደረጃ ይደገፋል።

ኮርሱ ለ AP ኮምፒውርተ ሳይንስ A ቅድሚያ የሚወሰድ ሆኖ ያገለግላል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

አልጀብራ I

### የአልጀብራ ዝግጁነት I

የዚህ ኮርስ የትምህርት ግብ የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) ከተቋረጠ ትምህርት ጋር ያሉ ተማሪዎችን በአልጀብራ I ውጤታማ እንዲሆኑ ነው። ተማሪዎች በ Office of English Learner Services በሚሰጠው የሂሳብ ትምህርት ምዘና በኩል ለዚህ ኮርስ ሙከራ ያደርጋሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የአልጀብራ ዝግጁነት II

የዚህ ኮርስ የትምህርት ግብ የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) ከተቋረጠ ትምህርት ጋር ያሉ ተማሪዎችን በአልጀብራ I ውጤታማ እንዲሆኑ ነው። ተማሪዎች በ Office of English Learner Services በሚሰጠው የሂሳብ ትምህርት ምዘና በኩል ለዚህ ኮርስ ሙከራ ያደርጋሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የኮምፒውተር ሳይንስ መግቢያ

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የኮምፒውርተ ሳይንስን የተለያዩ ዘርፎች በፕሮግራሚንግ ላይ ትኩረት በማድረግ ግንዛቤን ይጨብጣሉ። ኮምፒውተር ሳይንስ የኮምፒውተሮች ጽንሰሃሳብ እና አተገባበር እንደ የማስያ መሳሪያዎች በመሆን በእውነታው አለም ያል ችግሮችን መፍታት ላይ ትኩረት ያደረገ የጥናት መስክ ነው። ይህ ኮርስ የፕሮግራሞችን ንድፍ እና እድገት በመመርመር የኮምፒውተሮችን አጠቃቀም እና አፈጻጸም ላይ ተማሪዎች ያላቸውን ትኩረት ያጠባል። በተለይ፣ ተማሪዎች የራሳቸውን ፕሮግራሞች እና መተግበሪያዎች በበርካታ ቋንቋዎች ለመፍጠር ይማራሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

### የሂሳብ ማዕከል የጓደኛ አጋዥ ስልጠና

የ ACHS የሂሳብ ማዕከል የጓደኛ አስተማሪ እድል በሂሳብ ኮርሶች ውስጥ ያለውን የተማሪ ራሱን የቻለ የመማር እና የአካዳሚያዊ ስኬት ያበረታታል፣ ያስተዋውቃል እንዲሁም ያጠናክራል። የሂሳብ ማዕከል አስተማሪ መደበኛ ግዴታዎች የሚያካትቱት፡-

- በስልጠና ክፍለጊዜያት ውስጥ መሳተፍ ተማሪዎች የአጋዥ ስልጠናዎችን ለሚማሩ ስለሂሳብ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን እንዲያዳብሩ እንዲሁም በመማር ውስጥ ክፍተቶች ሊኖርባቸው ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር አብሮ የመስራት ቴክኒኮችን ለመርዳት የጓደኛ አስተማሪዎች የስልጠና ክፍለ ጊዜ ላይ ይሳተፋሉ።
- ለውድ ተማሪዎች የአካዳሚክ ድጋፍ ማቅረብ እና ለሂሳብ በፍላጎት ማሳተፍ።
- በክፍል ስራ/የቤት ስራ ችግሮች፣በኮርስ ይዘት፣ በሚተላለፉ እና ለንጥል ስራዎች ጥናት ስራዎች ላይ በትብብር ለመስራት ከግለሰቦች እና ከትናንሽ ቡድኖች ጋር በመደበኛነት መገናኘት።

- ተማሪ የ ACHS ሂሳብ ማዕከልን እንዲጠቀም ለማስተዋወቅ ከት/ቤት አካባቢ ጋር በመሆን የማስተዋወቅ ስራን መስራት።

ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከሂሳብ አስተማሪ ድጋፍ እስከ የ ACHS የሂሳብ ማዕከል አስተባባሪ አስተማሪ ጋር በማድረግ ማመልከቻ ማስገባት ያስፈልጋቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5-1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ማመልከቻ እና ለማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራሙ ያለ ተቀባይነት

**የጋራ መስፈርቶች፡-**

ቅድመ-ካልኩለስ፣ AP ስታትስቲክስ ወይም AP ካልኩለስ AB ወይም AP ካልኩለስ BC

# ሙዚቃ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

### AP የሙዚቃ ጽንሰ ሐሳብ

ይህ ኮርስ የሙዚቃ ቲዎሪ I ለተጠናቀቁ የከፍተኛ የሙዚቃ ተማሪዎች የታለመ ነው። በዚህ ኮርስ ውስጥ የስኬት መሰረት የሚባለው ተማሪው የሙዚቃዊ ማስታወሻን የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታው ነው። መዝገበ ቃላት፣ በአይን መዘመር እና የሙዚቃ ትንታኔን የመሳሰሉ የሙዚቀኛነት ክህሎቶች የበለጠ ይዳብራሉ። በዋና መዋቅር ውስጥ ያሉ ክህሎቶች፣ የድምጽ/የመሳሪያ አቀማመጥ ቴክኒኮች፣ የላቀ ክፍል አጻጻፍ፣የመሳሪያ መሻገሪያዎች እና የውጤት ትንተና አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። ተማሪዎች የሙዚቃ መጻፊያ የኮምፒውተር ሶፍትዌር እና ከ MIDI/ synthesizer ጋር ይተዋወቃሉ። ይህ ኮርስ የሙዚቃ ጽንሰ ሃሳብ II ን ይተካል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

### የላቀ ኳየር

የቨርጂኒያ የሁለተኛ ደረጃ የድምጽ/የዜማ ሙዚቃ፣ የአርቲስቶች ደረጃ በግለሰብ እና በስብስብ አፈጻጸም ውስጥ ተማውዎች የሙዚቀኝነት ክህሎቶችን ማጣራት እንዲችሉ ያደርጋል። ተማሪዎች የሙዚቃዊ ክንውኖችን የማጎልበት ችሎታን ይቀጥላሉ እና በእውቀት ክህሎቶች እና የትንተና አስተሳሰብ በመጠቀም ምርጫዎችን እና የሚሻላቸውን ይገልጻሉ። በማህበረሰቡ እና በአለም ውስጥ ላለ ሙዚቃ ያላቸውን ግንኙነቶች ያሰፋሉ እንዲሁም ግለሰባዊ የክንውን ፖርትፎሊዮዎችን ያጎለብታሉ። በግል እና  በስብስብ ዝማሬ ጥልቅ የሆነ ተሞክሮ እና ተማሪውን ለወደፊት የሙዚቃ እና የድምጽ እድገት እና የስራ እድሎች እንዲዘጋጅ ለመርዳት የውጪ ቋንቋዎችን መጠቀም።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የተሳካ አዲሽን

### የላቀ ኦርኬስትራ

ይህ ኮርስ በክፍል IV እና V ያሉ የ VBODA የደረጃ ስርአት ላይ በተሳካ ሁኔታ ለሚጫወቱ ከ 9-12ኛ ክፍል ለሆኑ ተማሪዎች ቀርቧል። የላቀ የአጨዋወት ተሞክሮ ያላቸው ተማሪዎች ዝቅ በማለት፣ ጣቶችን በመጠቀም እና ከጥሩ ኢንቶኔሽን፣ ሪትም እና ሙዚቀኛነት ጋር ክህሎቶችን ማጎልበት ይቀጥላሉ። በዚህ ኮርስ

ውስጥ ያለው ስኬት በ ስትሪንግ ኦርኬስትራ II ወይም ቻምበር ኦርኬስትራወደመሳተፍ ሊመራ ይገባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በኦርኬስትራ ኮርስ ውስ ቀደም ያለ ተሳትፎ

### የላቀ የትርኢት ስብስብ

በዚህ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የእጅ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ክህሎቶቻቸውን የበለጠ ያሳድጋሉ። ጉልህ አስተዋጽዖ በሙዚቃ ትምህርት እና የእጅ ሙዚቃ መሳሪያ መሰረታዊ እውቀት ላይ ይደረጋል። የዚህ ኮርስ አባላት የላቁ የምት ቴክኒኮችን ይማራሉ እና ከመካከለኛ እስከ ላቀ የሙዚቃ ሪፐርቶር ያከናውናሉ። ይህ ኮርስ እንደ ክንውን ስብስብ ሆኖ ይንቀሳቀሳል እና በትምህርት አመቱ ቢያንስ ሁለት ኮንሰርቶችን ያከናውናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የ Wind ስብስብእና/ወይም የሲምፎኒክ ባንድ እንደ እጅ መሳሪያ ክፍል ሆነው ያገለግላሉ። በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሚደረገው ባንድ ውስጥ እንዲሳተፉ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የትርኢት ስብስብ ወይም የዳይሬክተር ፈቃድ።

### ቻምበር ሙዚቃ - ስምንተኛው ክፍለ ጊዜ

ይህ ኮርስ ከት/ቤት በኋላ በስምንተኛው ክፍለ ጊዜ የሚቀርብ ነው። የቻምበር ሙዚቃ ተማሪዎች በትንሽ የስብስብ ሪፐርቶር ውስጥ የአፈጻጸም እድል እንዲያገኙ የተነደፈ ነው። በርካታ ስብስቦች ባለው የግላዊ ስትሪንግ ትሪዮ፣ ቋርቴትስ እና በተመረጠው ሪፔርቶሪ መሰረት ባሉ ሌሎች ስብስቦች በመጠቀም ቅርጽ ይይዛሉ። ይህ ክፍል ለውጤት ወይም ለማለፍ/መውደቅ ሊወሰድ ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በኦርኬስትራ ኮርስ ውስ ቀደም ያለ ተሳትፎ

### ቻምበር ኦርኬስትራ

በዚህ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለት/ቤቱ ወካይ አከናዋኝ የስትሪንግ ኦርኬስትራ ይፈጥራሉ። የላቁ ቴክኒካዊ ክህሎቶች ተከታታይ እድገት ላይ እና የተገናኘ ስነጽሁፍ ጥናት ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች ለኮርሱ ክሬዲት ለመቀበል ሁለቱንም የት/ቤት ቀን እና ከት/ቤት ቀን ውጪ የተሳትፎ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። የቨርጂኒያ የሁለተኛ ደረጃ የመሳሪያ ሙዚቃ ደረጃዎች፣ የላቀ እና የአርቲስት ደረጃ ተማሪዎች የቴክኒካዊ እና ገላጭ ክህሎቶችን በአርቲስት የሙዚቀኛነት ደረጃን እንዲያገኙ ያስችላል። ተማሪዎች በአካባቢ፣ በዲስትሪክት፣ በክልል እና በስቴት ክስተቶች ላይ ለመሳተፍ እድሎች ይቀርቡላቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የተሳካ ኦዲሽን።

### የኮንሰርት ባንድ

የኮንሰርት ባንድ ደረጃ II - IV ስነጽሁፍን ያከናውናል። ተማሪዎች በድምጽ ፕሮዳክሽን፣ ኢንቶኔሽን፣ ስልት፣ ሪትም፣ ማመጣጠን እና ሙዚቀኛነት ውስጥ ያሉ ክህሎቶችን ለማዳበር ይሰራሉ። የኮንሰርት ባንድ ቢያንስ ሁለት ኮንሰርቶችን በአመት ያቀርባል፣ በስቴት ኮንሰርት ምዘና ውስጥ ይሳተፋል (አግባብ ሲሆን) በዚህ ኮርስ ውስጥ በተሳካ

ሁኔታ መሳተፍ ተማሪዎችን ለሲምፎኒክ ባንድ እና/ወይም ለዊንድ ስብሰባ ያዘጋጃቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### የኮንሰርት ኳየር

ኮንሰርት ኳየር ሁሉም የዝማሬ ዘርፎች ለትላልቅ ኮንሰርቶች እና የማህበረሰብ ዝግጅቶች ሊያጠኑ እና በጋራ ሊተገብሩ የሚችሉበትን መካከለኛ ያቀርባል። በመርሃ ግብሩ ምክንያት ለማንኛዉም የዜማ ኮርሶች ላልተመዘገቡ ተማሪዎችም እንዲሁ ክፍት ነው። በኮንሰርት ኳየር ውስጥ ያሉ የዜማ ተማሪዎች ከምእራብ አውሮፓዊያን ክላሲካል እስከ Broadway እና ወንጌል ያሉ እያንዳንዱ የሙዚቃ ዘይቤን ይዳስሳሉ። ተማሪዎች የብዛት ስብስብ ድምጽ ላይ ብቁ ሆነውየሚማሩት በዚህ ኮርስ ውስጥ ነው። መገኘት ግዴታ ነው። የኳየር አባላት በመኸር፣በክረምት እና በጸደይ ኮንሰርቶች ውስጥ እንዲያከናውኑ ይጠበቃል እና ለሙዚቀኞች ኦዲሽን፣ በዋሽንግተን/ኬኔዲ ማዕከል ኦነርስ በቴሌቪዥን የተላለፉ ፕሮዳክሽኖች ውስጥ ለክሪስማስ፣ ለዲስትሪክት ዝማሬ እና ለ VMEA ኦነር ኳየር ይበረታታሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የቀድሞ የመዝመር መመሪያ

### የ Jazz ስብስብ

ይህ ቡድን ስዊንግ፣ ጃዝ እና ሮክን በማካተት በርካታ ስነጽሁፍን ያጠናል እንዲሁም ይከውናል። በየአመቱ፣ ቡድኑ በኮንሰሮች፣ በተወሰነባቸው ፌስቲቫሎች፣ እና በበርካታ የሲቪክ አጋጣሚዎች ላይ ያከናውናል። የተሻሉ ክህሎቶችን ለማሳደግ እና ጨዋታን ለመሰብሰብ የተለየ አጽንዖት ተቀምጧል። አባልነት ከፍተኛ የሆነ የሙዚቃ ክህሎት እና ግላዊ ስነ-ስርአት ይጠይቃል። ይህ ክፍል ለውጤት ወይም ለማለፍ/መውደቅ ሊወሰድ ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፦**

የኮንሰርት ባንድ፣ ሲምፎኒክ ባንድ ወይም የንፋስ ስብስብ

### የተደባለቀ ኳየር

ይህ በኮንሰርት ኳየር ኮርስ በማስተማሪያ ደረጃ የሚሰጥ ጀማሪ የመዝሙር ኮርስ ነው። የኳየር ተማሪዎች ለሚጠናው ለእያንዳንዱ ሪፐርቶር ክፍል ለተለያየ የድምጽ ቴክኒክ ተለዋዋጭ ፍላጎቶች ትኩረት እንዲያደርጉ እድሉ ተዘጋጅቷል። የተከናወነ ሙዚቃ የታሪካዊ ጊዜያትን እና ዘይቤዎችን ይሸፍናል። ክብደቱ የ Virginia Choral Directors' Association (VCDA) ከ II እስከ IV ክፍሎች ድረስ የመመደቢያ ስርአት ይወሰናል። የኳየር አባላት በመኸር፣በክረምት እና በጸደይ ኮንሰርቶች ውስጥ እንዲያከናውኑ እና በዳይሬክተሩ እንደሚወሰነው በአካባቢ/ዲስትሪክት ፌስቲቫሎች እንዲሳተፉ ይጠበቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የቀድሞ የመዝመር መመሪያ

### የሙዚቃ ላብራቶሪ/ጊታር

ይህ ኮርስ ጊታር ተጫውተው የማያውቁ ተማሪዎችን ለመድረስ የተነደፈ ነው። ዜማዎችን እና ጥቂት ኮርዶችን መጫወት ለመማር አጽንዖት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች እንደ ኖት ማንበብ፣ የኖት ጽንሰ ሐሳብ እና የተገናኙ የሙዚቃ እውቀቶች አይነት የሙዚቃ መሰረቶችን ይማራሉ። ኮርሱ ባህላዊ፣ ክላሲካል፣ ጃዝ እና ሮክ ሙዚቃዎችን ጨምሮ ተማሪዎች በበርካታ የሙዚቃ ስታይሎች እንዲተዋወቁ

ያደርጋል፤ ለቡድን ጨዋታ እድሎችን ያቀርባል፤ እና ምንም እንኳን መሰረታዊ የሆኑ አንዳንድ ዝቅተኛ የሚጠበቁ ነገሮች ቢኖሩም፣ ተማሪዎች በራሳቸው ዋጋ እየላቁ ይሄዱ። ለተማሪዎች የራሳቸውን መሳሪያዎች ያቀርባሉ። ይህ ኮርስ የግማሽ አመት ኮርሶችን ለሚወስዱ ተማሪዎች ተጨማሪ አማራጭን በበለጠ ክንውናዊ ባልሆኑ እንቅስቃሴዎች ለሚያደርጉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች የሙዚቃ ክፍሉ የማዳረስ እድል እንዲኖረው ሆኖ ይሰጣል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**የሙዚቃ**

የሙዚቃ ጽንሰ ሃሳብ ለተማሪዎች አስፈላጊ የስራ መሳሪያዎችን ከፈጠራዊ እና የክንውን እይታዎች ያቀርባል። ኮርሱ በስፋቶች፣ በመዝለሎች፣ በኮርዶች፣ በባለአራት ክፍል ጽሁፍ እና ቅጽ ላይ አጽንዖት በመስጠት የሙዚቃ ንባብ መሰረታዊያን ላይ አስፋፍቶ ያያል። እያንዳንዱ ስልጠና የኮርሱ አስፈላጊ ክፍል ነው። የሙዚቃ ጽንሰ ሃሳብ በኮሌጅ ውስጥ በሙዚቃ ዋና ትምህርታቸውን ለማድረግ ላቀዱ ወይም በክንውን/ አወቃቀር ላይ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**የትርኢት ስብስብ**

ይህ ኮርስ ሁለቱንም የኮንሰርት እና ሰልፍ የማድረግ የእጅ ሬፔርቶሬን በተሳካ ሁኔታ ለመከወን መሰረታዊ ክህሎቶች እና እውቀት ለመስጠት የቀረበ ነው። እንደዚህ ኮርስ አባላት፣ ተማሪዎች ሰፊ የእጅ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የመማር እና የመተግበር እድል ያገኛሉ። እነዚህ መሳሪያዎች የሚያካትቱት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደቡት የስኔር ከበሮ፣ የባስ ከበሮ፣ ሲምባሎች፣ ማሪምባ፣ ግሎንስፒል፣ ኮንጋስ እና ቦንጎስ ናቸው። በተጨማሪም፣ በሁሉም ትርዒት አቅራቢዎች የሚፈለጉ የሙዚቃ እውቀት ክህሎቶች እድገትን የትኩረት አጽንዖት ይህ ኮርስ ያሳያል። ይህ ኮርስ ለትምህርት አመቱ በተሰጠው ምዝገባ ላይ በመመስረት እንደ ክንውን ስብስብ ሆኖ ይንቀሳቀሳል። በተጨማሪም፣ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የኮንሰርት ባንድ፣ የሲምፎኒክ ባንድ ወይም የ Wind ስብስብ አባላትም ናቸው እንዲሁም ለእነዚያ ስብስቦች ባሉ ህጎች እና ፖሊሲዎች ይገዛሉ። የትርኢት ስብስብ ተማሪዎች በኮንሰርቶች ላይ ከባንድ ክፍሎች ጋር ያከናውናሉ። በተጨማሪም፣ የትርኢት ስብስቦች አልፎ አልፎ የራሳቸው አፈጻጸም ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**የክንውን ትርኢት/የማሳያ ኳየር - ስምንተኛው ፔሬድ**

ዘፋኞች/ የማሳያ ኳየር በት/ቤቱ እና በማህበረሰቡ ውስጥ የበለጠ ፈታኝ ከባድ የዜማ ሙዚቃን የማሳያ መድረክ ያገኛሉ። የኳየር ተማሪዎች የሙዚቃ ሌላ አይነት ዘይቤዎችን እንዲያስሱ እድል ተሰጥቷቸዋል ይህም የሚያካትተው ነገር ግን ለ Broadway እይታ ድምጸች እና በርካታ በወንጌል አለም ውስጥ ላሉ ስታይሎች ብቻ ያልተወሰ ነው። የኳየር ተማሪዎች የሚተገብሯቸው በርካታ ክፍሎች የተዘጋጁ ብዙ አይነት ኬሮዮግራፊ እንዲማሩ እንዲሁ እድሉን ያገኛሉ። የኳየር አባላት በመኸር፣ በክረምት እና በጸደይ ኮንሰርቶች ውስጥ እንዲያከናውኑ ይጠበቃል እና ለሙዚቀኞች ኦዲሽን፣ በዋሽንግተን/ኬኔዲ ማዕከል ኦነርስ በቴሌቪዥን የተላለፉ ፕሮዳክሽኖች ውስጥ ለክሪስማስ፣ ለዲስትሪክት ዝማሬ እና ለ VMEA ኦነር ኳየር ይበረታታሉ። ይህ ክፍል ለውጤት ወይም ለማለፍ/መውደቅ ሊወሰድ ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፡-**

የኮንሰርት ኳየር

### ስትሪንግ ኦርኬስትራ I

ይህ ኮርስ በኦርኬስትራዊ ሙዚቃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል እና በጥሩ ቅላጼ እና ሪትም ዝቅ በማድረግ፣ ጣቶችን በመጠቀም እና ሙዚቃን በማንበብ የክንውን ክህሎታቸውን ለማላቅ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ቀርቧል። ይህ ኮርስ በ VBODA የደረጃ ስርአት በክፍል III እና IV ላይ በተሳካ ሁኔታ ለሚጫወቱ ተማሪዎች ቀርቧል። በዚህ ኮርስ ውስጥ ያለው ስኬት በ ስትሪንግ ኦርኬስትራ II ፣ የላቀ ኦርኬስትራ ወይም ቻምበር ኦርኬስትራወደመሳተፍ ሊመራ ይገባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በኦርኬስትራ ኮርስ ውስ ቀደም ያለ ተሳትፎ

### ስትሪንግ ኦርኬስትራ II

ተማሪዎች ዝቅ በማለት፣ ጣቶችን በመጠቀም እና ሙዚቃን በማንበብ ከጥሩ ኢንቶኔሽን እና ሪትም ጋር ማጎልበታቸውን ይቀጥላሉ። ይህ ኮርስ በ VBODA የደረጃ ስርአት በክፍል IV ላይ በተሳካ ሁኔታ ለሚጫወቱ ተማሪዎች ቀርቧል። በዚህ ኮርስ ውስጥ ያለው ስኬት በ ላቀ ኦርኬስትራወይም ቻምበር ኦርኬስትራወደመሳተፍ ሊመራ ይገባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የተሳካ ኦዲሽን።

### የስትሪንግስ ግኝት

ይህ ኮርስ ቫዮሊን፣ ቪዮላ፣ ሴሎ ወይም ባለሁለት ባስ ለመጫወት ለሚፈልግ ለማንኛዉም ተማሪ ክፍት ነው። የቀድሞ የመጫወት ተሞክሮ (የመጀመሪያ፣ የመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት) ያላቸው ተማሪዎች ለመመዝገብ መበረታታት አለባቸው። ተማሪዎች የመረጡትን የስትሪንግ መሳሪያ መሰረታዊ አጨዋወቶች ይማራሉ፣ ከእነዚህም ውስጥ፤ መሳሪያው እንዴት እንደሚያዝ እና ዝቅ እንደሚል፣ የኖት ማንበብ እና ሪትሞች። መሳሪያን ከመማር ልምድ ውጪ፣ የማስተላለፊያ ግቦች የሚያካትቱት በ ስትሪንግ ኦርኬስትራ II በሚቀጥለው የትምህርት አመት ውስጥ ለመሳተፍ ያለ ዝግጁነትን ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

### ሲምፎኒክ ባንድ

የሲምፎኒክ ባንድ በ VBODA ደረጃ III-V ላይ ሙዚቃን ይከውናሉ። በተከታታይ የላቁ ቴክኒካዊ ክህሎቶች እና በተገናኘ ስነጽሁፍ ላይ ያለ ጥናት አጽንዖት ይሰጥበታል። ለእያንዳንዱ ደረጃ ስኬታማ የሆኑ ተከታታይ ጽንሰ ሃሳቦች ማጠናቀቅ ላይ በመመስረት፣ ተማሪዎች በኮርስ ደረጃው እንደተገለጸው ይቀጥላሉ። በዚህ ኮርስ ውስጥ የማርሽ ባንድ ቴክኒኮች፣ ልምምዶች፣ እና አፈጻጸሞች ያስፈልጋሉ። ተማሪዎች ለኮርሱ ክሬዲት ለመቀበል ሁለቱንም የት/ቤት ቀን እና ከት/ቤት ቀን ውጪ የተሳትፎ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። የቨርጂኒያ የሁለተኛ ደረጃ የመሳሪያ ሙዚቃ ደረጃ፣ የላቀ ደረጃ ተማሪዎች የበለጠ የላቀቲቴክኒካዊ እና ገላጭ ክህሎቶችን እንዲያገኙ እና የሙዚቀኛነት የበሰለ ደረጃን ለማሳየት ያስችላል። ተማሪዎች

በአካባቢ፣ በዲስትሪክት፣ በክልል እና በስቴት ክስተቶች ላይ ለመሳተፍ እድሎች ይቀርቡላቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የተሳካ ኦዲሽን

**የንፋስ ስብስብ**

በዚህ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለት/ቤቱ ወካይ አከናዋኝ ባንድ ይፈጥራሉ። የላቁ ቴክኒካዊ ክህሎቶች ተከታታይ እድገት ላይ እና የተገናኘ ስነጽሁፍ ጥናት ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። በዚህ ኮርስ ውስጥ የማርሽ ባንድ ቴክኒኮች፣ ልምምዶች፣ እና አፈጻጸሞች ያስፈልጋሉ። ተማሪዎች ለኮርሱ ክሬዲት ለመቀበል ሁለቱንም የት/ቤት ቀን እና ከት/ቤት ቀን ውጪ የተሳትፎ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። የቨርጂኒያ የሁለተኛ ደረጃ የመሳሪያ ሙዚቃ ደረጃዎች፣ የአርቲስት ደረጃ ተማሪዎች የቴክኒካዊ እና ገላጭ ክህሎቶችን በአርቲስት የሙዚቀኛነት ደረጃ እንዲያገኙ ያስችላል። ተማሪዎች በአካባቢ፣ በዲስትሪክት፣ በክልል እና በስቴት ክስተቶች ላይ ለመሳተፍ እድሎች ይቀርቡላቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የተሳካ ኦዲሽን

# የኦንላይን እና የሳተላይት ካምፓስ ኮርሶች

የ ACPS Online Learning Program (ACPS-OLP) ለተማሪዎች፣ የላቀ ምደባ (AP)፣ የተመራጭ እና ዋና (ለመጀመሪያ ጊዜ) የክሬዲት ኮርሶችን እንዲወስዱ የክሬዲት መመለሻ እድሎችን አቅርቧል። በ 2013-14 ዘጠነኛ ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ የገቡ ተማሪዎች መደበኛ እና የላቀ ትምህርቶች ዲፕሎማን ለማግኘት የሚያስፈልገው የቨርቹዋል ኮርስ ተሞክሮ አላቸው። የ ACPS ተማሪዎች በ ACPS-OLP በኩል ይህንን መስፈርት ለማሟላት እዚህ ጋር የተዘረዘረውን ኮርስ ሊወስዱ ይችላሉ።

የኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ ኮርስ በተደባለቀ አካባቢ ውስጥ ለመስጠት የተነደፈ ሲሆን የኦንላይን ኮርስ መስፈርትን በማሟላት በ ACPS ቦርድ የጸደቀ ትርጉምን በዚህ ያሟላል።

በ ACPS- OLP በኩል የሚቀርቡ ሁሉም ኮርሶች ግለሰባዊ፣ በራስ በሚለዋወጥ መመሪያ በኩል ይቀርባል እንዲሁም በመማር የማኔጅመንት ስርዓት (እንደ ጥቁር ሰሌዳ) ላይ ይከናወናል። በምዝገባ ጊዜ፣ ተማሪዎች የኮርስ ምዝገባቸውን ለመደገፍ በጣቢያ ላይ የተመሰረተ አማካሪ እንዲሁም ይዘቱን እንዲደግፍ የኦንላይን አስተማሪን ይመድባሉ። ኮርሶች ከ 9-12ኛ እና ከ 6-8ኛ (በት/ቤቱ አስተዳደር ተገቢ ነው ተብሎ ሲቆርጠ) ለሆኑ ተማሪዎች ይገኛሉ። በተመሳሳይ፣ የ AP ኮርሶች ከ 10-12 ላሉ ተማሪዎች እና በትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተገቢ ነው ተብሎ እንደተቆጠረው ይገኛል።

የኮርስ ክሬዲት ይለያያል እና በኮርሱ ላይ የተመሰረተ ነው፣ ይሁን እንጂ ተመራጮች በተለምዶ 0.5 ክሬዲቶች እንዲሁም ዋና ኮርሶች 1.0 ክሬዲት ዋጋ አላቸው። ብዙዎቹ ኮርሶች በተከፋፈሉ ምዝገባዎች

ቀርበዋል (ተማሪዎች አመቱን በሙሉ በማንኛዉም ጊዜ መመዝገብ ይችላሉ)። የኮርስ አቅርቦቶቹ እና መገኛው በቨርጂኒያ ህግ መሰረት አመቱን ሙሉ ከፍ ዝቅ ይላል። የኦንላይን ኮርሶች ተማሪዎች የኮርስ ስራቸውን እንዲያጠናቅቁ አስደናቂ ተለዋዋጭነት እንዲኖር ቢያደርግም፣ ተማሪዎች ኮርሱን በጊዜው ለመጨረስ እኩል መራመድ ይገባቸዋል። ስለዚህ፣ የተማሪው የሩብ አመት ውጤት (በእሱ ወይም በእሷ የሩብ አመት ሪፖርት ካርድ ላይ የሚታየው) ሁለቱንም እርምጃን እና አፈጻጸምን ካካተተ ስሌት የመጣ ነው። ለኦንላይን ኮርሶች በእያንዳንዱ ሴሚስተር የተወሰነ ቅጥር ያላቸው ቦታዎች ሊገኙ ይችላሉ፣ እና ለደረሱ ተመራቂዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

የኦንላይን ኮርሶች የአቅራቢ መገኘት እና የ VDOE መጽደቅ ሁኔታ ስር ይገዛሉ። ከስር የተዘረዘሩት ሁሉም ኮርሶች በቀደሙት ምክንያቶች ላይገኙ እንደሚችሉ እባክዎ ያስታውሱ። የኦንላይን መማሪያ ዳይሬክተር የሆኑትን Izora Everson ስለ ኮርስ መገኘት እባክዎ ያረጋግጡ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የ ACPS የኦንላይን ትምህርት ዳይሬክት የሆነውን Izora Everson በ izora.everson@acps.k12.va.us ላይ ወይም 703-619-8400 ላይ ያግኙ።

ለሁሉም ኮርሶች ሙሉ ገለጻ፣ እባክዎ ወደ www.acps.k12.va.us/onlinelearningይሂዱ

# ስኬታማ የሆነ የኦንላይን ተማሪ መገለጫ

በኦንላይን ኮርሶች ላይ ለመሳተፍ የመረጡ ተማሪዎች ግላዊ ክህሎታቸውን እና ግንዛቤያቸውን ትምህርቱን በኦንላይን ስለወሰዱ መመርመር ያስፈልጋቸዋል። የሚከተሉት ባህሪያት የተማሪው ስኬት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ ያደርጋሉ፡-

**ብቃት ያለን የማንበብ ደረጃ** – ተማርዎች 900 ወይም ከዚያ በላይ በስኮላስቲክ የማንበብ ቆጠራ ላይ የተገመገመ የመዝገብ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል።

**የራስ መነቃቃት –** ተማሪዎች የራሳቸውን የትምህርት አካባቢዎች እና ዘዴዎች የኮርስ መስፈርቶችን ለማሟላት እና ግለሰባዊ የአካዳሚክ ስኬትን ለመቀዳጀት አቅጣጫ ሊያሲዙ ይችላል።

**ራሱን የቻለ ተማሪ –** የኦንላይን አካባቢ ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እንዲማሩ በማስቻል፣ የመቸኮል ወይም የመገፋት የጭንቀት ስሜትን ለመቀነስ እና በመማር ሂደት ውስጥ ደስታን ለመስጠት ያስችላል።

**ኮምፒውተር የተማረ –** ምንም እንኳ ከፍተኛ የሆነ የኮምፒውተር ክህሎቶች እንዲኖራቸው ባያስፈልጋቸውም፣ ተማሪዎች ኢሜይል እና ኢንተርኔትን እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ የኪቦርዲንግ ክህሎቶች መሰረታዊ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል።

**የጊዜ አጠቃቀም –** ተማሪዎች ለመማር የራሳቸውን ምርጥ ጊዜ ማደራጀት እና ማቀድ መቻል አለባቸው። ለሁሉም ሰው ምርጥ የሚባል ጊዜ የለም ነገር ግን ለመማር ያለው ቁልፍ ነገር ለመማር ጊዜ መስጠት ነው።

**ውጤታማ የጽሁፍ ግንኙነት ክህሎቶች –** ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው እንዲሁም ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘት ኢሜይል እና የውይይት ፎረሞችን መጠቀም አለባቸው። ሃሳቦችን እና ምደባዎች ጋር ለመገናኘት በግልጽ የመጻፍ ችሎታ ወሳኝ ነው። ይህ ዘዴ ለተማሪው ፈጣን የሆነ ግብረመልስ እንዲሁም ሊያጋጥመው ወይም ሊያጋጥማት የሚችለውን ማንኛዉም አሳሳቢ ጉዳዮች ወይም ችግሮች ለአስተማሪው የመግለጽ ዘዴን ይሰጣል።

**ግላዊ ቁርጠኝነት –** ክፍል ለማስጀመር እና ለማስጨረስ ምንም ደወሎች ስለሌሉ፣ ተማሪዎች በኦንላይን ኮርሶች ጠንካራ የሆነ የመማር እና እውቀቶችን እና ክህሎቶችን የማግኘት ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። በዚህ አይነት ለመማር ቃል መግባት በጣም ሙያዊ የሆነ ውሳኔ ነው እና አካዳሚያዊ ስኬትን ለማምጣት ጠንካራ የሆነ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።

**የመጨረሻ ግን ዝቅተኛ ያልሆነው፣** ስኬታማ የኦንላይን ተማሪዎች ማለት የኦንላይን ትምህርት እምረጥ የሚፈልጉት ምርጫ እንደሆነ ለራሳቸው የሚወስኑ ተማሪዎች ናቸው።

ልዩ ማስታወሻ: ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ክህሎቶች ኦንላይን ኮርስ በመውሰድ በእርግጥም ይመራሉ እንዲሁም የበለጠ ያውቃሉ። ተማሪዎ ከላይ ባሉት ሁሉም ክህሎቶች በደንብ ውጤታማ ባለመሆኑ ምክንያት ብቻ እሱን/እሷን በኦንላይን ትምህርት ላይ የጠየቀችውን ጥያቄ እንዳይከለክሉ ጥንቃቄ ያድርጉ። እነዚህ ከግምት ውስጥ ብቻ የገቡ ናቸው።

### *በኦንላይን ኦርስ ላይ ለመመዝገብ ተማሪው የተሻለ ፍላጎት የሚኖረው መቼ ሊሆን ይችላል?*

- በት/ቤት ያሉትን የመርሃግብር ግጭቶች ለመፍታት ወይም የተለያየ የመርሃግብር መዋቅሮችን ፍላጎቶች ለማሟላት
- ተማሪ ሌላ የት/ቤት/ቤተሰብ/ስራ ሃላፊነቶችን ለማሟላት የጊዜ አጠቃቀሙን ተለዋዋጭ አድርጎ ለመፍቀድ
- በተማሪው የቤት ት/ቤት የማይገኙ ኮርሶችን ለመውሰድ
- ክሬዲት ለማዘጋጀት
- ኦንላይን የተሻለ ተስማሚ የመማር አካባቢ ሊሆን ይችላል
- ተማሪ የርቀት ትምህርት ኮርስ የመውሰድ ተሞክሮን ይፈልጋል
- ኮርስን(ኮርሶችን) በፈጣን እርምጃ እንዲያጠናቅቅ ለተማሪ እድልን ለማቅረብ
- ተጨማሪ ጊዜ ለሚፈልጉ ተማሪዎች የኮርስ ስራን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜን ለመስጠት
- የተላከ ተማሪ ፍላጎቶችን ለማሟላት
- ሙሉ ቀን ለመቆየት የማያስችላቸው የህክምና ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት

### *በኦንላይን ኦርስ ላይ ለመመዝገብ ተማሪው የተሻለ ፍላጎት የሚኖረው መቼ ሊሆን ይችላል?*

- ተማሪው የስኬታማ የኦንላይን ተማሪን መገለጫ አያሟላም
- ተማሪው አጠቃላይ ኮርስ ሳይሆን የማሻሻያ ፕሮግራም ይፈልጋል
- ተማሪው ተገቢ ለሆነ የኮምፒውተር ሃርድዌር አስተማማኝ መዳረሻ አይኖረውም
- የኦንላይን ኮርስ መውሰድ የተማውሪ ምርጫ አይደለም። ተማሪዎች ኮርሱን(ኮርሶቹን) ጉልህ ቁጥር ባላቸው ወጣቶች የኦንላይን ኮርሶቹን ለተማሪዎቹ ከሚመርጡ በኦንላይን ለመውሰድ መፈለግ አለባቸው

**የኦንላይን እና የሳተላይት ካምፓስ ኮርሶች**

## የላቁ የአመዳደብ ኮርሶች

**የማህበራዊ ትምህርቶች፡-**

- AP የስነጥበብ ታሪክ
- AP ሰብአዊ ጂኦግራፊ
- AP ማክሮኢኮኖሚክስ
- AP ማይክሮኢኮኖሚክስ
- AP ሳይኮሎጂ
- AP የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት እና ፖለቲካ
- AP የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ
- AP የአለም ታሪክ፡- ዘመናዊ

**ሳይንስ፡-**

- AP ባዮሎጂ
- AP አካባቢያዊ ሳይንስ

**ሂሳብ፦**

- AP ካልኩለስ AB
- AP ካልኩለስ BC
- AP ስታትስቲክስ

**ቴክኖሎጂ፦**

- AP ኮምፒውተር ሳይንስ A

**የቋንቋ ስነጥበባት፦**

- AP የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ቅንብር
- AP የእንግሊዝኛ ስነጽሁፍ እና ቅንብር

**የአለም ቋንቋ፦**

- AP የፈረንሳይ ቋንቋ እና ባህል

## ዋናው ክሬዲት/መሰረታዊ የክሬዲት ኮርሶች

**ሂሳብ፦**

- አልጄብራ I፣ አልጄብራ I ኦነርስ
- አልጄብራ II፣ አልጄብራ II ኦነርስ
- አልጄብራ II እና ትሪጎኖሜትሪ
- አልጄብራ፣ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንታኔ
- ካልኩለስ
- ጂኦሜትሪ
- ቅድመ-አልጄብራ
- ቅድመ-ካልኩለስ
- ፕሮባቢሊቲ እና ስታትስቲክስ

**የቋንቋ ስነጥበባት፦**

- እንግሊዝኛ 9፣ ኦነርስ እንግሊዝኛ 9
- እንግሊዝኛ 10፣ ኦነርስ እንግሊዝኛ 10
- እንግሊዝኛ 11፦ የአሜሪካ ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት፣ ኦነርስእንግሊዝኛ 11፦ የአሜሪካ ስነጽሁፍ የዳሰሳ ጥናት
- እንግሊዝኛ 12፦ ብሪትሽ እና የአለም ስነጽሁፍ፣ ኦነርስ እንግሊዝኛ 12
- ጋዜጠኝነት

**ሳይንስ፦**

- ባዮሎጂ I፣ ኦነርስ ባዮሎጂ I
- ኬሚስትሪ I፣ ኦነርስ ኬሚስትሪ I
- የመሬት ሳይንስ I
- ኢኮሎጂ
- አካባቢያዊ ሳይንስ
- አካላዊ ሳይንስ
- ፊዚክስ I

**የማህበራዊ ትምህርቶች፦**

- ቨርጂኒያ እና የ U.S. መንግስት፣ ኦነርስ የቨርጂኒያ እና የ U.S. መንግስት-እኛ ሰዎች
- ቨርጂኒያ እና የ U.S. ታሪክ፣ ኦነርስ ቨርጂኒያ እና የ U.S. ታሪክ
- ሲቪክስ
- ኢኮኖሚክስ
- ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ
- ሳይኮሎጂ
- ሶሲዮሎጂ
- የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል I፣ ኦነርስ የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል I
- የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል II፣ ኦነርስ የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል II

**የአለም ቋንቋዎች፦**

- ፈረንሳይኛ I
- ፈረንሳይኛ II
- ፈረንሳይኛ III
- ጀርመንኛ I
- ጀርመንኛ II
- ላቲን I
- ላቲን II

- ላቲን III
- ማንድሪያን (ቻይንኛ) I
- ማንድሪያን (ቻይንኛ) II
- ማንድሪያን (ቻይንኛ) III
- ስፓኒሽ I
- ስፓኒሽ II
- ስፓኒሽ III

## ተመራጮች

- አንትሮፖሎጂ (0.5 ክሬዲት)
- የስነጥበብ አድናቆት (0.5 ክሬዲት)
- የስነጥበብ ታሪክ (0.5 ክሬዲት)
- አስትሮኖሚ፦ አጽናፈ ሰማይን ማሰስ (0.5 ክሬዲት)
- አናቶሚ (0.5 ክሬዲት)
- ባዮቴክኖሎጂ (0.5 ክሬዲት)
- ባዮቴክኖሎጂ፦ የተፈጥሮ ሚስጥሮችን መፍታት (0.5 ክሬዲት)
- ስራዎች በወንጀል ፍትህ ውስጥ (0.5 ክሬዲት)
- የስራ እቅድ ማውጣት (0.5 ክሬዲቶች)
- የኮምፒውተር መተግበሪያዎች - Office 2010
- በአካል ብቃት ውስጥ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦች (0.5 ክሬዲት)
- የኮስሜቶሎጂ የቅርብ ጊዜ ስታይሎች (0.5 ክሬዲት)
- የሳይበር ደህንነት I (0.5 ክሬዲት)
- የሳይበር ደህንነት II (0.5 ክሬዲት)
- መድሃኒቶች እና አልኮል (0.5 ክሬዲት)
- ቤተሰብ እና የሸማች ሳይንስ (0.5 ክሬዲት)
- የቤተሰብ አኗኗር እና ግንኙነቶች (0.5 ክሬዲት)
- ፎረንሲክ ሳይንስ I፦ የሙታን ሚስጢሮች (0.5 ክሬዲት)
- ፎረንሲክ ሳይንስ II፦ የሟቾች ተጨማሪ ሚስጥሮች (0.5 credit)
- የጎቲክ ስነጽሁፍ፦ የጨራቅ ታሪኮች (0.5 credit)
- የጤና ውጤት 9 (0.5 ክሬዲት) — ከሰውነት ማጎልመሻ 9 ጋር የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ 9ለማካተት በጋራ ይወሰዳል
- የጤና ውጤት 10 (0.5 ክሬዲት) — ከሰውነት ማጎልመሻ 10 ጋር የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ 10ለማካተት በጋራ ይወሰዳል
- ጤና እና ግላዊ ጤንነት (0.5 ክሬዲት)
- የሆሎካስት ታሪክ (0.5 ክሬዲት)
- በቤት የተወሰነ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና ጤና (0.5 ክሬዲት)
- አለም አቀፍ ቢዝነስ፦ በ 21ኛው ክፍለ ጊዜ አለም አቀፍ ኮሜርስ (0.5 ክሬዲት)
- የነርሲንግ መግቢያ I (0.5 ክሬዲት)
- የነርሲንግ መግቢያ II (0.5 ክሬዲት)
- የኮዲንግ መግቢያ (0.5 ክሬዲት)
- ግንኙነቶች እና ንግግር መግቢያ (0.5 ክሬዲት)
- የሴቶች ትምህርቶች መግቢያ በፊልም ግላዊ ጉዞ (0.5 ክሬዲት)
- ህግ እና ትዕዛዝ፦ የህግ ትምህርቶች መግቢያ (0.5 ክሬዲት)
- የህግ ትምህርቶች (0.5 ክሬዲቶች)
- ማንበብና መጻፍ እና ግንዛቤ 1 (0.5 ክሬዲት)
- ማንበብና መጻፍ እና ግንዛቤ 2 (0.5 ክሬዲት)
- የባህር ሳይንስ I (0.5 ክሬዲት)
- የባህር ሳይንስ II (0.5 ክሬዲት)
- የሜዲካል ቃላት I (0.5 ክሬዲት)
- አፈታሪክ እና ተረት የአፈታሪክ ተረቶች (0.5 ክሬዲት)
- የኦንላይን ትምህርት እና የዲጂታል ዜግነት (0.5 ክሬዲት)
- የጓደኛ ማማከር (0.5 ክሬዲት)
- የግል ፋይናንስ (0.5 ክሬዲት)
- የግል አሰልጣኝ (0.5 ክሬዲት)
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 (5 ክሬዲት) — ከጤና 9 ጋር አብሮ በመወሰድ የ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9ንማካተት

- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10 (0.5 ክሬዲት) — ከጤና 10 ጋር አብሮ በመወሰድ የ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ን ማካተት
- ፊዚዮሎጂ (0.5 ክሬዲት)
- ለኮሌጅ ስኬት ንባብ (0.5 ክሬዲት)
- ታዳሽ ቴክኖሎጂዎች (0.5 ክሬዲት)
- ማህበራዊ ችግሮች I:- ቀውስ፣ ግጭቶች፣ እና ተግዳሮቶች (0.5 ክሬዲት)
- ማህበራዊ ችግሮች II:- ቀውስ፣ ግጭቶች፣ እና ተግዳሮቶች (0.5 ክሬዲት)
- ስፖርት እና የመዝናኛ ማርኬቲንግ (0.5 ክሬዲት)
- ለአካዳሚያዊ ስኬት ያሉ ስትራቴጂዎች (0.5 ክሬዲት)
- ቲያትር፣ ሲኒማ እና የፊልም ፕሮዳክሽን
- የአለም ሃይማኖቶች፡- ብዝሀነትን ማሰስ (0.5 ክሬዲት)

## የክሬዲት ማገገሚያ ኮርሶች

- የክሬዲት ማገገሚያ አልጄብራ I
- የክሬዲት ማገገሚያ አልጄብራ II
- የክሬዲት ማገገሚያ አልጄብራ II እና ትሪጎኖሜትሪ
- የክሬዲት ማገገሚያ አልጄብራ፣ ፈንክሽኖች እና የውሂብ ትንተና
- የክሬዲት ማገገሚያ ጂኦሜትሪ
- የክሬዲት ማገገሚያ ፕሮባቢሊቲ እና ስታትስቲክስ
- የክሬዲት ማገገሚያ የአሜሪካ መንግስት
- የክሬዲት ማገገሚያ የአሜሪካ ታሪክ
- የክሬዲት ማገገሚያ ኢኮኖሚክ እና የግል ፋይናንስ
- የክሬዲት ማገገሚያ ጂኦግራፊ
- የክሬዲት ማገገሚያ የአለም ታሪክ
- የክሬዲት ማገገሚያ ባዮሎጂ
- የክሬዲት ማገገሚያ ኬሚስትሪ
- የክሬዲት ማገገሚያ የመሬት ሳይንስ
- የክሬዲት ማገገሚያ ኢኮሎጂ
- የክሬዲት ማገገሚያ የአካላዊ ሳይንስ
- የክሬዲት ማገገሚያ ፊዚክስ
- የክሬዲት ማገገሚያ እንግሊዝኛ 9
- የክሬዲት ማገገሚያ የጤና ውጤት 9 (0.5 ክሬዲት) — የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9ን ለማካተት ከክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9 ጋር በጋራ ይወሰዳል።
- የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ 9 (0.5 ክሬዲት) — የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 9ን ለማካተት ከክሬዲት ማገገሚያ ጤና 9 ጋር በጋራ ይወሰዳል።
- የክሬዲት ማገገሚያ እንግሊዝኛ 10
- የክሬዲት ማገገሚያ እንግሊዝኛ 11
- የክሬዲት ማገገሚያ እንግሊዝኛ 12
- የክሬዲት ማገገሚያ ጤና 10 (0.5 ክሬዲት) — የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ን ለማካተት ከክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10 ጋር በጋራ ይወሰዳል።
- የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10 (0.5 ክሬዲት) — የክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10ን ለማካተት ከክሬዲት ማገገሚያ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት 10 ጋር በጋራ ይወሰዳል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

# ሳይንስ

## አጠቃላይ ሳይንስ

የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ ፕሮግራም የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ለማሟላት የተነደፈ ነው። መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እና የላቀ (ኦነርስ) የትምህርት ፕሮግራም በማህበራዊ ትምህርቶች ውስጥ ይሰጣል። 6ኛ ክፍል ላይ ያለው ትኩረት በአከባቢ፣ በውሃ፣ በመሬት እና በህዋ ሳይንስ ላይ ነው። 7ኛ ክፍል ላይ፣ ተማሪዎች ከህይወት ሳይንስ ጋር በሚገናኙ ጥናቶች ላይ

በህያው አለም ውስጥ ባለው ለውጥ፣ ዑደቶች፣ አካሄዶች እና ግንኙነቶች አጽንዖቶች ጋር በመሆን ይሳተፋሉ። 8ኛ ክፍል ላይ፣ የቁስ አካል፣ ፊዚክስ እና ሃይል ተፈጥሮ እና አወቃቀር ላይ ጥናት ይደረጋል። ተማሪዎች ከ 6፣ 7 እና 8ኛ ክፍል የሳይንስ ይዘትን ያካተተ አጠቃላይ የ SOL ፈተናን 8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ ይወስዳሉ።

# የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኦነርስ ፕሮግራም

ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ የመደበኛ የትምህርቶች ፕሮግራም እንደ አማራጭ፣ የላቀ ወይም ኦነርስ አማራጮች ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ይገኛል። እነዚህ ኮርሶች የታዘዙትን የ ACPS ካሪኩለም እና የቨርጂኒያ ሳይንስ SOL ይከተላሉ። እነሱ በከፍተኛ ደረጃ ለተነቃቁ ተማሪዎች ይመከራሉ። ተማሪዎች ከገሃዱ አለም ችግሮች ጋር የተገናኙ የትንሽ-ቡድን እና የግለሰብ ምርምር ፕሮጀክቶችን ለማድረግ የሙከራ ንድፍ ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የሳይንስን ሚና በህይወታቸው ላይ መገንዘባቸውን ያሳድጋሉ። እያንዳንዱ ተማሪ ወደ ት/ቤት ሳይንስ ዝግጅት እና የ ACPS የሳይንስ ዝግጅት ውስጥ ለመግባት እንዲችል የሳይንስ ፕሮጀክት ማቅረብ እና መተግበር ይጠበቅበታል።

የ Talented and Gifted (TAG) አገልግሎቶችን በሳይንስ ለመቀበል የተለዩ ተማሪዎች በአጠቃላይ ሳይንስ፣ በህይወት ሳይንስ ወይም በአካላዊ ሳይንስ የኦነርስ ክፍሎች መርሃግብር ተይዞላቸዋል። ለናሙና የሁለተኛ ደረጃ ሳይንስ የኮርስ ተከታታዮች፣ እዚህ ጋር ይመልከቱ።

### የሳይንስ ማዕከል የጓደኛ አስተማሪ

የ A.C.H.S. የሳይንስ ማዕከል የጓደኛ አስተማሪ እድል በሳይንስ ኮርሶች ውስጥ ያለውን የተማሪ ራሱን የቻለ የመማር እና የአካዳሚያዊ ስኬት ያበረታታል፣ ያስተዋውቃል እንዲሁም ያጠናክራል። የሳይንስ ማዕከል አስተማሪ tመደበኛ ግዴታዎች የሚያካትቱት፦

- በስልጠና ክፍለጊዜያት ውስጥ መሳተፍ ተማሪዎች የአጋዥ ስልጠናዎችን ለሚማሩ ስለሳይንሶች ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን እንዲያዳብሩ እንዲሁም በመማር ውስጥ ክፍተቶች ሊኖርባቸው ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር አብሮ የመስራት ቴክኒኮችን ለመርዳት የጓደኛ አስተማሪዎች የስድስት ሳምንት የስልጠና ክፍለ ጊዜያት ላይ ይሳተፋሉ።
- ለውድ ተማሪዎች የአካዳሚክ ድጋፍ ማቅረብ እና ለሳይንስ በፍላጎት ማሳተፍ።
- በክፍል ስራ/የቤት ስራ ችግሮች፣በኮርስ ይዘት፣ በላብራቶሪ ሪፖርቶች፣ ጊዝሞዎች እና ለንጥል ፈተናዎች በማጥናት ላይ በትብብር ለመስራት ከግለሰቦች እና ከትናንሽ ቡድኖች ጋር በመደበኛነት መገናኘት።
- ተማሪ የ A.C. ሳይንስ ማዕከልን እንዲጠቀም ለማስተዋወቅ ከት/ቤት አካባቢ ጋር በመሆን የማስተዋወቅ ስራን መስራት።
- የሳይንስ ማዕከል የጓደኛ አስተማሪዎች በግለሰቦች መካከል ያሉ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ፣ የእነሱን ሳይንሳዊ የክህሎቶች ምክንያት ያሻሽላሉ፣ የመሪነት ክህሎትን ያስገኛሉ እንዲሁም የሳይንስ ማዕከል ማህበረሰብ አካል የመሆን እድሎች ይኖራቸዋል።

ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከሳይንስ አስተማሪ ድጋፍ እስከ ሳይንስ ማዕከል አስተባባሪ አስተማሪ ጋር በማድረግ ማመልከቻ ማስገባት ያስፈልጋቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

# የሳይንስ ዋና ኮርሶች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ (EOC) የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ ለመሬት ሳይንስ፣ ባዮሎጂ እና ኬሚስትሪ የ EOC SOL ሳይንስ ሙከራዎች አሉ። በሳይንስ ውስጥ ላለው ለናሙና ኮርስ ተከታታዮች ገጽ 19 ላይ ይመልከቱ። በ AP ሳይንስ ኮርሶች

ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች ከ AP የሳይንስ ኮርስ ጋር አብሮ የሚሄደውን ባለ 1.0 ክሬዲት የ AP ሳይንስ ላብ ሴሚናር አንድ ላይ መመዝገብ ይገባቸዋል። በማንኛዉም የሳይንስ ኮርስ፣ ሃሳቦችን የሚያረጋግጥ ወይም የሚገዳደር ሳይንሳዊ ምርምር ትኩረት ተሰጥቶታል። ስለዚህ፣ ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን ለከተማው የሳይንስ ዝግጅት ውድድር መግቢያ እንዲያዘጋጁ ይበረታታሉ።

**AP ባዮሎጂ**

በዚህ የኮሌጅ እኩሌት ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች መሰረታዊ የፊዚዮሎጂካል ስራዎችን የፊሎጄኔቲክ የዳሰሳ ጥናት፣ ዘመናዊ የሞሎኪውላር ጄኔቲክስ፣ የዴቨሎፐመንታል ባዮሎጂ እና ህይወት ያላቸው ስርዓቶች ባዮኬሚስትሪን በጥልቀት ይመረምራሉ። ተማሪዎች በሳይቶሎጂ፣ የሴል መተንፈስ እና ፎቶሲንተሲስ፣ ኢንዛይሞሎጂ፣ ቨርተብሬ አናቶሚ እና ፊዚዎሎጂ እንዲሁም ኢኮሎጂ ላይ አጽንዖት በመስጠት የባይሎጂ ግንዛቤያቸውን ያሰፋሉ። በተጨማሪ የላብራቶሪ ስራ ውስጥ፣ ተማሪዎች አስፈላጊ የላብራቶሪ ክህሎቶችን፣ ችግር ፈቺ ቴክኒኮችን፣ የምርምር ቴክኒኮችን እና የከፍተኛ ደረጃ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ያጎለብታሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ኬሚስትሪ I እና ባዮሎጂ I

**የጋራ መስፈርቶች፦**

AP ሳይንስ የላብ ሴሚናር

**AP ኬሚስትሪ**

ይህ ከኮሌጅ ጋር እኩል የሆነ ኮርስ ተማሪዎች የኬሚስትሪ I ጽንሰ ሃሳቦችን እና ጉልህ ቁጥሮችን፣ አቶሞችን፣ ሞሎችን፣ የኬሚካል ምላሾችን እና ጋዞችን ያሉ ክንውኖችን ጨምሮ መረዳታቸውን በማስፋት እንዲጀምሩ ይፈቅዳል።  የአሙቱ ቀሪ ጊዜ ቴርሞኬሚስትሪ፣ በንዲንግ፣ ካይኔቲክስ፣ ኢኩሊብረም እና ኤሌክትሮኬሚስትሪን ጨምሮ ያሉ የኬሚካል ርዕሶች ጥልቅ ምርምር እንዲደረግ ይፈቅዳል። በሂሳባዊ ስሌቶች እና የቅንጣት ሞዴሊንግ በኩል ኬሚስትሪን መረዳት አጽንዖት ተሰጥቶታል። በተራዘመ የላብራቶሪ ስራ እና በሂሳብ ትንታኔ፣ ተማሪዎች የበለጠ አስፈላጊ የሆኑ የላብራቶሪ ክህሎቶችን፣ ችግር መፍቻ ዘዴዎችን፣ የምርምር ዘዴዎችን እና የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎቶችን ያዳብራሉ።

**[g2]የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦ [/g2]**1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አልጄብራ II እና ኬሚስትሪ I

**የጋራ መስፈርቶች፦**

AP ሳይንስ የላብ ሴሚናር

**AP አካባቢያዊ ሳይንስ**

ይህ ከኮሌጅ ጋር እኩል የሆነ ኮርስ ተማሪዎች የተፈጥሮ አለምን የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ለመረዳት የሚያስፈልጉትን የሳይንሳዊ መርሆዎች፣ ጽንሰ ሃሳቦች እና ዘዴዎችን በጥልቀት የመማር እድል ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች የአካባቢ ችግሮችን በተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ሁለቱንም በመለየት እና በመተንተን፣ ከእነዚህ ችግሮች ጋር ያሉትን አንጻራዊ

አደጋዎች በመግምገም እንዲሁም እነሱን ለመፍታት እና/ወይም ለመከላከል አማራጭ መፍትሄዎችን በመመርመር ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ። በተራዘመ የላብራቶሪ ስራ እና በሂሳብ ትንታኔ፣ ተማሪዎች የበለጠ አስፈላጊ የሆኑ የላብራቶሪ ክህሎቶችን፣ ችግር መፍቻ ዘዴዎችን፣ የምርምር ዘዴዎችን እና የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎቶችን ያዳብራሉ። ከ 10-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይህ ኮርስ ክፍት ሆኖ ሳለ፣ 10ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ኮርሱን ከመውሰዳቸው በፊት ከሳይንስ ክፍል አለቃ ወይም የክፍል አስተማሪ የድጋፍ ደብዳቤ ማስገባት አለባቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ባዮሎጂ I፣ አልጄብራ I እና ጂኦሜትሪ

**የጋራ መስፈርቶች፦**

AP ሳይንስ የላብ ሴሚናር

### AP ፊዚክስ 1

ይህ በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የላብራቶሪ ኮርስ የመጀመሪያ አመት ፊዚክስን በፈጠነ መንገድ ለመማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ነው። ተማሪዎችን ለኮሌጅ ደረጃ ፊዚክስ ለማዘጋጀት ተነድፏል። ተማሪዎች ስለ እንቅስቃሴ፣ ሃይላት እና ጉልበት ገለጻ፣ ትንታኔ እና ውይይት ያደርጋሉ። እንደ አልጄብራ እና ትሪጎኖሜትሪ ባለ የሂሳብ ትምህርት በዚህ ኮርስ ውስጥ ችግር መፍታት አጽንዖት ይሰጥበታል። ተማሪዎች ዲያግራሞችን፣ ግራፎችን እና የጽሁፍ መግለጫዎችን ያሉ በርካታ መወከያዎችን በመጠቀም የፊዚክስ ጽንሰ ሃሳቦችን ሞዴል ያደርጋሉ። የትምህርት ምዕራፎች የሚያካትቱት ካይኔማቲክስ፣ የኒውተን ዳይናሚክስ፣ ጉልበት እና ሞመንተም፣ የመዞር እንቅስቃሴ፣ ሜካኒካል እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ዌቮች እና የኤሌክትሪክ ሰርኪዩቶች ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ የግራፊንግ ማስያዎች፣ የኮምፒዩተር ማስመሰያዎች እና ፕሮብ ዌርን ያካተት ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ። ከዚህ ቀደም የ AP ፊዚክስ C የወሰዱ ተማሪዎች ይህንን ኮርስ ላይወስዱ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አልጄብራ II

**የጋራ መስፈርቶች፦**

ቅድመ-ካልኩለስ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የሂሳብ ክፍል

### AP ፊዚክስ 2

ይህ በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የላብራቶሪ ኮርስ ፊዚክስን በፈጠነ መንገድ ለመማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ነው። ተማሪዎችን ለኮሌጅ ደረጃ ፊዚክስ ለማዘጋጀት ተነድፏል። ይህ የሁለተኛ አመት የፊዚክስ ኮርስ ነው እና መወሰድ ያለበት ተማሪዎች የ AP ፊዚክስ I ን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ ነው። ምንም እንኳን እንደ አልጄብራ እና ትሪጎኖሜትሪ ያለ ሂሳብ በዚህ ኮርስ ውስጥ በችግር መፍታት በኩል አጽንዖት የተሰጠው ቢሆንም፣ ተማሪዎች ዲያግራሞችን፣ ግራፎችን እና የጽሁፍ ገለጻዎችን በማካተት የፊዚክስ ጽንሰ ሃሳቦችን ሞዴል ለማድረግ በርካታ ውክልናዎችን ይጠቀማሉ። የትምህርት ምዕራፎች የሚያካትቱት የፈሳሽ ሜካኒክስ፣ ቴርሞዳይናሚክስ፣ ኤሌክትሪሲቲ እና ማግኔቲዝም ፣ ኦፕቲክስ፣ አቶሚክ ፊዚክስ እና ኑክሌር ፊዚክስ ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ

የግራፊንግ ማስመሰያዎች፣ የኮምፒውተር ማስመሰያዎች እና ፕሮብ ዌርን ያካተት ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ቅድመ-ካልኩለስ እና AP ፊዚክስ 1

### AP ፊዚክስ C: ኤሌክትሪሲቲ እና ማግኔቲዝም፤ ሜካኒክስ

ይህ ከኮሌጅ ጋር እኩል የሆነ ኮርስ ተማሪዎች በፊዚክስ የመጀመሪያ ኮርስ ያገኙትን የራሳቸውን ግንዛቤ እንዲገነቡ በመፍቀድ ይጀምራል። ስለዚህ ፊዚክስ C እንደ በሁለተኛ አመት የፊዚክስ ኮርስ ሆኖ እንዲወሰድ አጥብቆ ይመከራል። በሁለተኛው ሴሚስተር ውስጥ፣ ተማሪዎች የኮሌጅ ደረጃ የሌክትሪሲቲ እና ማግኔቲዝም ትምህርትን ያጠናቅቃሉ። በግንቦት ውስጥ፣ ተማሪዎች ባለሁለት የ AP የኮርስ መጨረሻ ፈተናዎችን ያጠናቅቃሉ ይህም እያንዳንዱ በግምት አንድ የኮሌጅ ስራ ሴሚስተር ጋር ይዛመዳል። ይህ ኮርስ ጥብቅ፣ ሂሳብ የበዛበት እና በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ምናባዊ ነው። የአካላዊ መርሆዎች በሚዘጋጁበት ጊዜያት ሁሉ እና እነሱን ለአካላዊ ችግሮች ሲተገበሩ ካልኩለስ ጥቅም ላይ ይውላል። ልዩ የሆኑ የተለያዩ ፈታኝ ችግሮችን ለመፍታት ጠንካራ አጽንዖት ተቀምጧል። በ AP ካልኩለስ BC በጋራ የተመዘገቡ ተማሪዎች ወይም የፊዚክስ ኮርስን ከዚህ በፊት ፈጽሞ ወስደው የማያውቁ ተማሪዎች በአስተማሪው ፈቃድ ኮርስ ሊወስዱ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

AP ካልኩለስ AB ወይም AP ካልኩለስ BC

**የጋራ መስፈርቶች፡-**

AP ሳይንስ የላብ ሴሚናር

### ባዮሎጂ I

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለሳይንሳዊ ክስተት እና ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች የሳይንሳዊ አስተሳሰብ ታሪክን እንዲሁም ባዮሞሎኪውሎችን፣ ሴሎችን፣ ዝግመተ ለውጥን እና ኢኮሎጂን በመመርመር የሚደግፉትን መረጃዎችን እንዲሁ ያስሳሉ። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Biology Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### ባዮሎጂ I (IA)

በአለም አቀፍ አካዳሚ (IA) ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ይህንን ኮርስ ከ 9ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ (IA) ጋር ባለ ተከታታይ በ 2 አመት ውስጥ ያጠናቅቃሉ። በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለሳይንሳዊ ክስተት እና ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች የሳይንሳዊ አስተሳሰብ ታሪክን እንዲሁም ባዮሞሎኪውሎችን፣ ሴሎችን፣

ዝግመተ ለውጥን እና ኢኮሎጂን በመመርመር የሚደግፉትን መረጃዎችን እንዲሁ ያስሳሉ። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ VA biology Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

## ባዮሎጂ II፦ ኢኮሎጂ

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለአካባቢያዊ አሳሳቢ ጉዳዮች ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች ከአየር ንብረት ለውጥ፣ ከህዝብ ቁጥር እና ከተፈጥሮ አለም ጋር ጋር የተገናኘ ሳይንሳዊ ውሂብን በመተንተን የሰው ልጅ ተጽዕኖን በምድር ላይ ይማራሉ። ተማሪዎች ታሪካዊ እይታዎችን እና ከአካባቢያዊ ሳይንስ ጋር የተገናኙ አዳዲስ ርዕሶች ያሏቸው የወቅቱ ዜናዎችን በመፈተሽ ተለዋዋጭ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የማህበረሰብ ግንኙነትን እንዲሁ ይመረምራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

> ማስታወሻ: ለባዮሎጂ EOC SOL ሳያልፉ የቀሩ ተማሪዎች በኮርሱ መጨረሻ ላይ ፈተናውን ዳግም የመውሰድ እድል ይኖራቸዋል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

1 የሳይንስ ክሬዲት

## ባዮሎጂ II፦ የሰው አናቶሚ እና ፊዚዮሎጂ

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለሰው አወቃቀሮች እና ስራዎች ጥልቅ የአናቶሚካል ጽንሰሃሳቦችን በመጠቀም ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ኮርሶ የሚያካትተው የተለያዩ አጥቢ እንስሳትን ክፍሎች እና አካሎቻቸውን ሲሆን ይህም ኢንተርጉሜንታሪ፣ የጡንቻ፣ የነርቭ፣ የእህል መፍጫ፣ የመተንፈሻ፣ የመዘዋወሪያ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የኢንዶክሪን እና የመራቢያ ስርአቶች የያዙ ርዕሶችን እንደ ተጨማሪ ትምህርት ይዘዋል። ተማሪዎች ታሪካዊ እይታዎችን እና ከሰው ልጅ አካል ጋር የተገናኙ አዳዲስ ርዕሶች ያሏቸው የወቅቱ ዜናዎችን በመፈተሽ ተለዋዋጭ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የማህበረሰብ ግንኙነትን እንዲሁ ይመረምራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

2 የሳይንስ ክሬዲቶች

## ኬሚስትሪ I

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለሳይንሳዊ ክስተት፣ ቁስ አካል እና ጉልበት ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። የሂሳብ ትምህርት በዚህ ኮርስ ውስጥ አጽንዖት ተሰጥቶታል እና የኬሚካል መጠኖችን እና ቀመሮችን በመለዋወጥ፣ ተማሪዎች ስለ ላብራቶሪ ደህንነት እና መሳሪያ፣ አቶሞች፣ ግንኙነቶች፣ ኬሚካል ምላሾች፣ ሞሎች እና ጋዞች ይማራሉ። ተማሪዎች እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ የግራፊንግ ማስመሰያዎች፣ የኮምፒውተር ማስመሰያዎች እና ፕሮብ ዌርን ያካተት ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Chemistry Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፦**

ጂኦሜትሪ፣ ይሁን እንጂ አልጄብራ II በደንብ ይበረታታል።

**የመሬት ሳይንስ I**

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለመሬት ጥንቅሮች፣አወቃቀር፣ ሂደቶች እና ታሪክ ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ርዕሶች በስርአት በተመሰረተ አካሄድ ይጠናሉ እና የሚያካትቱትም አስትሮኖሚ፣ ሜትሮሎጂ፣ ጂኦሎጂ፣ ኦሽኖግራፊ እና አካባቢያዊ ሳይንስ ናቸው። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Earth Science Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**የመሬት ሳይንስ II፦ አስትሮኖሚ**

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ከፕላኔት መሬት ጀምሮ እስከ አጽናፈ ሰማይ ጥግ ድረስ ያለ ስለተፈጥሮ አለምን ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። የሂሳብ ትምህርት በዚህ ኮርስ ውስጥ አጽንዖት የተሰጠው ከአስትሮኖሚያዊ አካሄድ ያለ የመሬት ሳይንስ ትምህርት፣ የክዋክብት ስብስቦች፣ ጸሃይ እና ጨረቃ፣ ፕላኔቶች፣ አስትሮይዶች፣ ኮሜቶች፣ የክዋክብት አወቃቀር እና ዝግመታቸው፣ ፐልሳሮች፣ ብላክ ሆልስ፣ ጋዛማው ኔቡላ፣ የከዋክብት ክምችቶች፣ ጋላክሲዎች እና ቋሳርስን በማሰስ ላይ ነው። ተጨማሪ የላብራቶሪ ስራ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕላኔታሪየም ውስጥ የሂሳብ መርሆዎች መዋሃድ እና ምስላዊ የአስትሮኖሚያዊ ቁሶች መታየትን ያካትታል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

ማስታወሻ: የመሬት ሳይንስ I ያላጠናቀቁ ተማሪዎች የ SOL ፈተና መሬት ሳይንስ የመውሰድ እና የተረጋገጠ የሳይንስ ክሬዲት የማግኘት አማራጭ አላቸው። ይህ ኮርስ የሂሳብ ብቃት ባላቸው ተማሪዎች ከግምት ውስጥ የሚገባ ከፍተኛ ደረጃ ሳይንስ ነው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

2 የሳይንስ ክሬዲቶች

**የመሬት ሳይንስ II፦ ኦሽኖግራፊ**

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች በሰዎች እና በውቂያኖሶች መካከል ያለውን አካባቢያዊ መስተጋብሮች ሲዳስሱ፣ ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች ከመሬት ሳይንስ እይታ ኦሽኖግራፊን ይማራሉ፣ ብዝሃ ህይወትን፣ የባህር ወለልን ጂኦሎጂ እና የባህል ወለልን መስፋፋት፣ አህጎራዊ መንሸራተት እና በባህሮች ውስጥ ያሉትን የተክል እና እንስሳ ማህበረሰቦች ባዮሎጂን ያስሳሉ። ከመሬት ውቅያኖስ ጋር ያሉ የአሁን የዜና ርዕሶችን ማሰስ አካትቶ የላብራቶሪ ስራ በፕሮጀክት ላይ በተመሰረተ መማር የተጨመረ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

2 የሳይንስ ክሬዲቶች

**አካባቢያዊ ሳይንስ (IA)**

በአለም አቀፍ አካዳሚ (IA) ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ይህንን ኮርስ ከ 9-12ኛ ክፍሎች ባዮሎጂ ጋር ባለ ተከታታይ በ 2 አመት ውስጥ ያጠናቅቃሉ። በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ከ K-8 ድረስ የላብራቶሪ ክህሎቶቻቸውን ያሰድጋሉ እና ይቀጥላሉ። ይህ ኮርስ የሰው ልጅ ተጽእኖ በፕላኔታችን ላይ ያለውን ጨምሮ የአካባቢያችንን በርካታ ክፍሎች አጣምሮ ይዟል። በዚህ ኮርስ ውስጥ ተማሪዎች ያገኟቸው ክህሎቶች የባዮሎጂ ወይም የመሬት ሳይንስ መማሪያ ደረጃዎችን እንዲወስዱ በማዘጋጀት በአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ ባሉ የላብራቶሪ ተሞክሮዎች እና የመስክ ምርመራዎች ላይ ያተኩራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

**ኦነርስ ባዮሎጂ I**

ይህ በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የላብራቶሪ ኮርስ ባዮሎጂን በፈጠነ መንገድ ለመማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ይህም ለተጨማሪ የላብራቶሪ ምርምሮች እና በምርምር ላይ የተደገፉ ፕሮጀክቶች ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል። ተማሪዎችን ለ AP ባዮሎጂ ወይም በባዮሎጂ የመጀመሪያ አመት የኮሌጅ ኮርስ ለማዘጋጀት ተነድፏል። ተማሪዎች የሳይንሳዊ አስተሳሰብ ታሪክን እንዲሁም ባዮሞሎኪውሎችን፣ ሴሎችን፣ ዝግመተ ለውጥን እና ኢኮሎጂን በመመርመር የሚደግፉትን መረጃዎችን እንዲሁ ያስሳሉ። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Biology Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል። ተማሪዎች የሳይንስ፣ቴክኖሎጂ እና ማህበረሰቡን ተለዋዋጭ ግንኙነት ታሪካዊ እይታዎችን እና የአሁኑን የዜና ርዕሶች በማጤን እንዲሁ ምርምር ያደርጋሉ። የ Intel ISEF መመሪያዎችን ለውድድር ወደ ከተማው የሳይንስ ዝግጅት ለመግባት ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

**ኦነርስ ኬሚስትሪ I**

ይህ በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የላብራቶሪ ኮርስ ኬሚስትሪን በፈጠነ መንገድ ለመማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ይህም ለተጨማሪ የላብራቶሪ ምርምሮች እና በምርምር ላይ የተደገፉ ፕሮጀክቶች ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል። ተማሪዎችን ለ AP ኬሚስትሪ ወይም በኬሚስትሪ የመጀመሪያ አመት የኮሌጅ ኮርስ ለማዘጋጀት ተነድፏል። የሂሳብ ትምህርት በዚህ ኮርስ ውስጥ አጽንዖት ተሰጥቶታል እና የኬሚካል መጠኖችን እና ቀመሮችን በመለዋወጥ፣ ተማሪዎች ስለ ላብራቶሪ ደህንነት እና መሳሪያ፣ አቶሞች፣ ግንኙነቶች፣ ኬሚካል ምላሾች፣ ሞሎች እና ጋዞች ይማራሉ። ተማሪዎች እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ የግራፊንግ ማስያዎች፣ የኮምፒውተር ማስመሰያዎች እና ፕሮብ ዌርን ያካተት ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Chemistry Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል። ተማሪዎች የሳይንስ፣ቴክኖሎጂ እና ማህበረሰቡን ተለዋዋጭ ግንኙነት ታሪካዊ እይታዎችን እና የአሁኑን የዜና ርዕሶች በማጤን እንዲሁ ምርምር ያደርጋሉ። የ Intel ISEF መመሪያዎችን ለውድድር ወደ ከተማው የሳይንስ ዝግጅት ለመግባት ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፦**

አልጄብራ II

**ኦነርስ የመሬት ሳይንስ I**

ይህ በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የላብራቶሪ ኮርስ የመሬት ሳይንስን በፈጠነ መንገድ ለመማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ይህም ለተጨማሪ የላብራቶሪ ምርምሮች እና በምርምር ላይ የተደገፉ ፕሮጀክቶች ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል። ለ AP የአካባቢያዊ ሳይንስ ወይም በመሬት ሳይንስ ውስጥ ለመጀመሪያ አመት የኮሌጅ ኮርስ ተማሪዎችን ለማዘጋጀት ተነድፏል። ርዕሶች በስርአት በተመሰረተ አካሄድ ይጠናሉ እና የሚያካትቱትም አስትሮኖሚ፣ ሜትሮሎጂ፣ ጂኦሎጂ፣ ኦሽኖግራፊ እና አካባቢያዊ ሳይንስ ናቸው። ይህ ካሪኩለም በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በመቅረጽ ከ Virginia Earth Science Standards of Learning ጋር አብሮ ይሄዳል። ተማሪዎች ታሪካዊ እይታዎችን እና እንደ አየር ንብረት ለውጥ፣ እንቅክባኬ፣ የህዋ እድሜ እና የ GPS ጥቅም የመሳሰሉ አዳዲስ ርዕሶች ያሏቸው የወቅቱ ዜናዎችን በመፈተሽ ተለዋዋጭ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የማህበረሰብ ግንኙነትን እንዲሁ ይመረምራሉ። የ Intel ISEF መመሪያዎችን ለውድድር ወደ ከተማው የሳይንስ ዝግጅት ለመግባት ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

**ፊዚክስ I**

በዚህ በላብራቶሪ ላይ በተመሰረተ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ስለሃይል እና እንቅስቃሴ፣ ሃይሎች እና ጉልበት ለመረዳት፣ ለማስረዳት፣ ለመተንተን እና ለመነጋገር የሚያስፈልጉ ከፍተኛ ደረጃ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች ዲያግራሞችን፣ ግራፍን፣ አልጄብራን እና የጽሁፍ መግለጫዎችን ጨምሮ የሚገኙ በርካታ መግለጫዎችን በመጠቀም የመጀመሪያ አመት የፊዚክስ ጽንሰ ሃሳቦችን ሞዴል ያደርጋሉ። የትምህርት ምዕራፎች የሚያካትቱት እንቅስቃሴ፣ ሃይል፣ ጉልበት እና ሞመንተም፣ ሜካኒካል እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ዌቮች እና የኤሌክትሪክ ሰርኪዩቶች ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ የግራፊንግ ማስመሰያዎች፣ የኮምፒውተር ማስመሰያዎች እና ፕሮብ ዌርን ያካተት ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ። ይህ ካሪኩለም ከቨርጂኒያ የፊዚክስ የመማር ደረጃዎች ጋር አንድ ላይ በመሄድ በማስተዋል፣ ሙከራ በማድረግ እና ሞዴል በማድረግ ላይ ያተኩራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አልጄብራ I እና ጂኦሜትሪ

**የጋራ መስፈርቶች፦**

አልጄብራ II እና ከፍተኛ ደረጃ የሂሳብ ትምህርት

**የሳይንስ ምርምር**

ይህ ኮርስ ተማሪዎች ያራሳቸውን ሳይንሳዊ ጥያቄዎች እና ክህሎቶች በሳይንስ ውስጥ ባለው እውነተኛ ምርምር በኩል እንዲፈልጉ እድል ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች የራሳቸውን ፕሮጀክቶች እንዲያጎለብቱ እና በከተማ የሳይንስ ዝግጅት እና VJAS ላይ ለአቀራረብ የሚመቹ የሳይንሳዊ ወረቀቶችን እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ውይይቶችን፣ ኢንተርንሺፖችን እና/ወይም በመረጧቸው የትምህርት አይነቶች ተፈጥሮ ላይ ከሳይንስቲቶች እና ባለሙያዎች ጋር ሆነው ምክሮችን እንዲከታተሉ ይበረታታሉ። ተማሪዎች ለበርካታ አመታት ሊሳተፉ ይችላሉ፤ 10ኛ እና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ይበረታታሉ፤ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአስተማሪ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ኮርስ የሚያካትተው ተማሪዎች ለትምህርቱ ርዕስን የሚያጎለብቱበትን የበጋ ምደባ በታን ያካትታል። ተማሪዎች ለዚህ ምደባ አስተማሪያቸውን ማግኘት አለባቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

አንድ የኦነርስ ወይም የ AP ሳይንስ ኮርስ

# የሳይንስ ተመራጮች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ (EOC) የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ ለመሬት ሳይንስ፣ ለባዮሎጂ እና ለኬሚስትሪ የ EOC SOL ሳይንስ ሙከራዎች አሉ። በሳይንስ ውስጥ ላለው ለናሙና ኮርስ ተከታታዮች ገጽ 19 ላይ ይመልከቱ። በ AP ሳይንስ ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች ከ AP የሳይንስ ኮርስ ጋር አብሮ የሚሄደውን ባለ 1.0 ክሬዲት የ AP ሳይንስ ላብ ሴሚናር አንድ ላይ መመዝገብ ይገባቸዋል። በማንኛዉም የሳይንስ ኮርስ፣ ሃሳቦችን የሚያረጋግጥ ወይም የሚገዳደር ሳይንሳዊ ምርምር ትኩረት ተሰጥቶታል። ስለዚህ፣ ተማሪዎች የምርምር ፕሮጀክቶችን ለከተማው የሳይንስ ዝግጅት ውድድር መግቢያ እንዲያዘጋጁ ይበረታታሉ።

**AP ሳይንስ የላብ ሴሚናር**

ተማሪዎች የ AP ባዮሎጂ፣ AP ኬሚስትሪ፣ AP ፊዚክስ C አካል እንደ አንድ ክሬዲት የላብራቶሪ ኮርስ አድርገው እንዲወስዱት ይጠየቃሉ፦ ኤሌክትሪሲቲ እና ማግኔቲዝም፤ ሜካኒክስ እና AP አካባቢያዊ ሳይንስ። ከክፍል እና ከላብራቶሪ የሚመጡ ውጤቶች ለኮርሱ ሁለቱም ክፍሎች አማካይ ይወሰድባቸዋል እና ምደባ ይደረግባቸዋል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**የጋራ መስፈርቶች፦**

AP ባዮሎጂ፣ AP ኬሚስትሪ፣ AP አካባቢያዊ ሳይንስ እና/ወይም AP ፊዚክስ C፦ ኤሌክትሪሲቲ እና ማግኔቲዝም፤ ሜካኒክስ)

# የማህበራዊ ትምህርቶች ዋና ኮርሶች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ የ SOL ታሪክ እና ለ U.S. ታሪክ፣ የአለም ታሪክ ክፍል I እና የአለም ታሪክ ክፍል II የ  ማህበራዊ ሳይንሶች ሙከራዎች ይገኛሉ። የሚያስፈልጉ የተረጋገጡ ክሬዲቶች ቁጥር በምረቃ አመት እና በዲፕሎማው አይነት ላይ ይወሰናል። ይህንን ገጽ ይመልከቱ።

**AP የተነጻጻሪ መንግስት እና ፖለቲካ**

የንፅፅር መንግስት እና ፖለቲካ በእኛ ዘመናዊ የተገናኘ አለም ውስጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነ የጥናት መስክ ነው። ባለፉት በርካታ አስርት አመታት የታዩ የግሎባላይዜሽን እና የሌሎች ክስተቶች በሌላ በማንኛዉም የታሪክ ጊዜ ይልቅ የአለምን ሃገራት ወደ አንድ አቅርቧል። በአለም ላይ ያሉ ክስተቶች አሁን በቀጥታ በህይወታችን ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ይገኛሉ እና የወደፊት መሪዎቻችን የሆኑት ተማሪዎች የእነዚህን ሃገራት ተመሳሳይነቶች እና ልዩነቶች የመገንዘብ ስራቸው ነው። በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች መንግስትን እና የእያንዳንዳቸውን ሃገራት ፖለቲካ ውድድር እና ንፅፅር ልዩነት ያጠናሉ እንዲሁም በአለም ላይ በዘመናዊ የፖለቲካዊ ስርዓቶች መካከል ያሉትን የሚመሳሰሉ እና የሚለያዩ ነገሮች ይተነትናሉ። የሚጠኑ ስድስት ሃገራት ታላቋ ብሪቴን፣ ኢራን፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ ሜክሲኮ እና ናይጄሪያ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**AP ሰብአዊ ጂኦግራፊ**

ይህ የኮሌጅ ደረጃ ኮርስ ተማሪዎችን የሰው ልጅን ግንዛቤ፣ ጥቅም እና የመሬት ወለልን መቀየሮች የቀረጹ ስልታዊ አካሄዶች እና ሂደቶች ጥናት ለማስተዋወቅ የተነደፈ ነው። ተማሪዎች የቦታ ጽንሰ ሃሳቦን እና የአቀማመጥ ትንተናን በማስገባት የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ድርጅትን እና የእሱን አካባቢያዊ መዘዞች ይመረምራሉ። እንዲሁም እነሱ ጂኦግራፈሮች በምርምር እና ትግበራቸው ላይ ስለሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች እና መሳሪያዎች ይማራሉ። ካሪኩለሙ የሃገራዊ የጂኦግራፊያዊ ደረጃዎችን (2012) ግቦች ያንጸባርቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የቨርጂኒያ የትምህርት ዲፓርትመንት የጂኦግራፊ የኮርስ መጨረሻ SOL ይወስዳሉ።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

**AP የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት እና ፖለቲካ**

ተማሪዎች በተለይ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስትን በሃገራዊ፣ በስቴት እና በአካባቢ ደረጃዎች ላይ የመንግስትን መርሆዎች እና ሂደቶች ይመረምራሉ። ርዕሶች የሚያካትቱት ፖለቲካዊ ቅርስ፣ ህገመንግስት፣ ፖለቲካ፣ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊ  ነጻነቶች፣ የመንግስት፣ የህግ እና የፍትህ ስርአት ተቋማት፣ መሰረታዊ ኢኮኖሚክስ እና የወቅቱ የውስጥ እና የውጪ ፖሊሲ ነው። በከፍተኛ ሁኔታ ለተነቃቁ ተማሪዎች ታልሞ፣ ይህ ኮርስ የኮሌጅ ደረጃ ቁሳቁሶችን ይጠቀማል እና የበጋ ማንበቢያ መስፈርትን ያካትታል። ተማሪዎች ለ AP ሙከራ ዝግጅት ንባብ፣ ትንታኔ፣ ጽሁፍ እና ንግግር ላይ ያተኮሩ ምደባዎችን ያጠናቅቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

**AP የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ**

የኮሌጅ ደረጃ ጽሁፍን በመጠቀም፣ተማሪዎች የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክን የቀረጹ ዋና ዋና ጭብጦችን፣ ክስተቶችን እና ሃሳቦችን ይማራሉ። ተማሪዎች የአሜሪካዊያንን የፖለቲካ እና ዲፕሎማሲያዊ ውሳኔ አደራረጎች፣ ሃገራዊ እና የክፍል ፍላጎቶች እንዲሁም ሃገራዊ የታሪክ እድገት ጋር የተገናኙ የተለያዩ ማንነቶች እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በጥልቀት ይመረምራሉ። የአሜሪካ ታሪክ ጭብጦች፣ ከወቅታዊ ክስተቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት እና ለ AP ዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ ሙከራ የሚያስፈልጉ ሙከራዎች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

## AP የአለም ታሪክ፦ ዘመናዊ

ሞደርን ማለት በኮሌጅ ደረጃ የሚሰጥ ዘመናዊ የአለም ታሪክ ኮርስ መግቢያ ነው። ተማሪዎች የአለም ታሪክ ግንዛቤያቸውን ከ c ተነስተው ያበለጽጋሉ። ከ 1200 CE እስከ አሁን ድረስ ያሉ የታሪካዊ ምንጮችን ሲተነትኑ እና ግንኙነቶችን ለመፍጠር ይማራሉ እንዲሁም የሰው ልጆች እና አካባቢው፣ ባህላዊ እድገቶች እና መስተጋብሮች፣ አገዛዝ፣ የኢኮኖሚ ስርአቶች፣ ማህበራዊ መስተጋብሮች እና ድርጅት እንዲሁም ቴክኖሎጂ እና ፈጠራን የመሳሰሉ ጽንሰ ሃሳቦችን ሲዳስሱ ታሪካዊ ክርክሮችን ይቀርጻሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

## ባለሁለት ምዝገባ የኮሌጅ U.S. ታሪክ

ይህ ሁለት ሴሚስተር ባለሁለት ምዝገባ ኮርስ ሲሆን የቀረበውም በ NOVA ነው። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በታሪክ ስድስት የኮሌጅ ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ይህ ኮርስ የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክን ከጅማሮ እስከ አሁን ይዳስሳል። HIS 121 በቅድመ ኮሎምቢያዊያን ዘመን ይጀምራል እና በዳግም ግንባታ ዘመን ላይ ያበቃል። HIS-I22 በወርቃማ ዘመን ይጀምራል እና በአሁኑ ጊዜ ላይ ያበቃል። ተማሪዎች የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክን የቀረጹ ጭብጦችን፣ ክስተቶችን እና ሃሳቦችን ለማጥናት የኮሌጅ ደረጃ ጸሁፎችን እና ታሪካዊ ሰነዶችን ይጠቀማሉ። ድርሰቶች እና የምርምር ወረቀቶች እንዲሁም ለ AP የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ ፈተና የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ጨምሮ በኮሌጅ ደረጃ የንባብ እና የጽሁፍ ምደባዎች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። ተማሪዎች በሁለተኛው ሴሚስተር ኮርስ ለመመዝገብ ሲ ወይም ከዛ የተሻለ ውጤት በመጀመሪያው ሴሚስተር መጨረሻ ላይ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። C ወይም ከዚያ የተሻለ ነጥብ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ-ያልሆነ-የደረጃ ኮርስ እንዲዘዋወሩ ይደረጋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

የኮሌጅ መግቢያ መስፈርቶችን ያሟላል

## ኦነርስ የቨርጂኒያ እና የ U.S. መንግስት - እኛ ህዝቦች

በክርክር እና በህዝባዊ ንግግር ላይ ክህሎታቸውን ማሳየት ለሚፈልጉ እና ለህግ፣ ለህዝባዊ ፖሊሲ የ U.S ህገመንግስት እና መንግስት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ይህ ኮርስ ይስባቸዋል። ተማሪዎች በሚከተሉት ግቦች ላይ እየሰሩ የእኛን ህገመንግስት እና ፖለቲካዊ ስርአት ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን ያገኛሉ፤

1. በዲስትሪክት እና በስቴት ደረጃ “እኛ ህዝቦች” በሚሉ ውድድሮች እና/ወይም ማሳያ ላይ ለመሳተፍ ይዘጋጁ።

2. ተማሪዎች ስለሚኖሩበት አለም እንዲያስቡ ማጎልበት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለውጥ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርገው ላይ በማተኮር የተወሰኑ ህዝባዊ ችግሮች ላይ ጥናት ማድረግ። ተማሪዎች ለውጥ ያስፈልገዋል ብለው የሚያምኑበትን ጉዳይ ይመርጣሉ። ከዚያም ለአሁኑ ሁኔታ ያሉ አማራጮችን ለማወቅ፣ የለውጥ ዋጋዎቹን እና የትኞቹ መኮንኖች ውሳኔውን ለመወሰን ሃላፊነት እንደሚወስዱ ርዕስ በጥልቀት ይመርምሩ፣ ከዛ ለውጥ ለማምጣት የተነደፈ የተግባር እቅድን ይገንቡ። ተማሪዎች የመንግስት ባለስልጣናትን ለማግኘት፣ በህዝባዊ ችሎቶች ምስክርነት ለመስጠት እና ለተጠየቀ ለውጥ ተጽዕኖ ለማድረግ ይነሳሳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

ይህ ኮርስ የ U.S. VA መንግስት ምረቃ መስፈርትን ያሟላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

### ኦነርስ ቨርጂኒያ እና የ U.S. ታሪክ

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የአሜሪካን ታሪክ ከተገኘበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን በመመርመር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ታሪኮች ላይ ያተኩራሉ። እንዲሁም ተማሪዎች የአሜሪካ ባህልን በጊዜ ቅደም ተከተል ዋና ዋና ጉዳዮችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ሰዎችን እና ክስተቶችን በያዘ የዳሰሳ ጥናት የዩናይትድ ስቴትስ እና የቨርጂኒያ ታሪክ ውስጥ ያስሳሉ። በዚህ ደረጃ የሚመዘገቡ ተማሪዎች ከክፍል ደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የንባብ እና የማዋቀር ክህሎቶች ሊኖሯቸው ይገባል። ኮርሱ ታሪካዊ ነገሮችን ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑትን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የትንታኔ እና የምርምር ክህሎቶችን እድገት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች ካርታዎችን፣ የኮሌጅ ደረጃ ንባቦችን፣ በሰነድ ላይ የተመሰረቱ የጥያቄ ድርሰቶችን፣ ሶቅራጢሳዊ ሴሚናሮችን፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ታሪካዊ ሰነዶች ትንተናን፣ ነጻ የምላሽ የምርምር ወረቀቶችን እና የቤተመጻህፍት ምንጮችን ያካተቱ በርካታ እንቅስቃሴዎችን እና ቁሳቁሶችን ያገኛሉ። ተማሪዎች በትምህርት አመቱ በሙሉ በርካታ አጠቃላይ የጽሁፍ ምደባዎችን እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11

### ኦነርስ የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል I

ይህ ኮርስ የአለም ታሪክን ከጥንት ጊዜ እስከ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ 1500 ዓ.ም ውስጥ ያለውን ይዳስሳል። በአለም ስልጣኔዎች እና ታሪካዊ እድገታቸው በኩል፣ ተማሪዎች ወቅታዊ በሆኑ የአለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን ያገኛሉ። ተማሪዎች በስነጽሁፍ፣ በስነጥበብ፣ በአርክቴክቸር፣ በሙዚቃ፣ በሃይማኖት፣ በፍልስፍና እና በጂኦግራፊ በኩል የባህሎችን የተለዩ ባህሪያት ይፈትሻሉ። የኦነርስ ክፍሎች የበለጠ በንባብ ላይ ያተኮሩ ናቸው እና ራሳቸውን በመቻል መማር እና ዘላቂ ጥረትን ይጠይቃሉ። ይህ ኮርስ ተማሪዎች ለ AP የአለም ታሪክ እንዲዘጋጁ የሚረዳቸውን ስትራቴጂዎች እና ክህሎቶችን አቅፏል። ዘመናዊ እና ጂኦግራፊ II በ 10ኛ ክፍል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

ወደዚህ የኦነርስ-ደረጃ ኮርስ ለመግባት የሚያስፈልጉትን ምደባዎች ለሚያጠናቅቅ ለማንኛዉም ተማሪ ክፍት ነው።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9

### ኦነርስ የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል II

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የኦነርስ የአለም ታሪክ ኮርስ ለተማሪዎች አጠቃላይ፣ ጥልቅ የሆኑ በአለም ታሪክ ውስጥ ዋና ዋና ክስተቶች እና ጭብጦች በመሆን ተማሪዎችን ለአካዳሚያዊ የኮሌጅ፣ የ AP እና የባለሁለት ምዝገባ ኮርሶች ለማዘጋጀት የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ይህ ኮርስ ከሲርካ 1500 ሬኔዛንስ ጀምሮ እስከ 21ኛው ክፍለዘመን የቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ድረስ ያለው የአለም ታሪክ የዳሰሳ ጥናት ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች ላሉበት የክፍል ደረጃ ተገቢ የሆኑ የማንበብ እና የቅንብር ክህሎቶች ሊኖሯቸው ይገባል። ኮርሱ ታሪካዊ ነገሮችን ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑትን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የትንታኔ እና የምርምር ክህሎቶችን እድገት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች በ 11ኛ ክፍል የ AP ታሪክ እና እንግሊዝኛ ሞዴሎች ላይ በመመስረት በርካታ አጠቃላይ የጽሁፍ ምደባዎችን እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በዚህ የኦነርስ ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል I እንዲወስዱ እና B ወይም የተሻለ ውጤት እንዲያገኙ ይመከራል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10

### ቨርጂኒያ እና የ U.S. መንግስት

ይህ ኮርስ የዩናይትድ ስቴትስ እና የቨርጂኒያ መንግስታት መነሻዎች እና ስራቸውን ይመረምራል። ተማሪዎች የዩናይትድ ስቴትስ እና የቨርጂኒያ ህገመንግስቶችን እንዲሁም ፖሊሲ ማዘጋጀትን፣ ኢኮኖሚክስን፣ የውጪ ጉዳይን እና የሰብአዊ መብቶችን ጨምሮ የእኛን የፌዴራል ስርዓት ይተነትናሉ። ተማሪዎች የጠቅላላ ህዝቡን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖችን እና በፖሊሲ ውሳኔዎች ውስጥ ያለ ሚዲያን ተጽዕኖ ያስሳሉ። በተጨማሪም፣ በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ነጻነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ላይ አጽንዖት በመስጠት፣ የዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ከሌሎች ሃገራት ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ጋር ተነጻጽረዋል። የኢኮኖሚክስ ክፍል የዩናይትድ ስቴትስ የገበያ ስርአትን፣ የአቅርቦት እና ፍላጎት መሰረቶች እና በኢኮኖሚው ውስጥ ያለ የመንግስት ሚናን ይሸፍናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 12

### ቨርጂኒያ እና የ U.S. ታሪክ

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የአሜሪካን ታሪክ ከተገኘበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን በመመርመር ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ታሪኮች ላይ ያተኩራሉ። እንዲሁም ተማሪዎች የአሜሪካ ባህልን በጊዜ ቅደም ተከተል ዋና ዋና ጉዳዮችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ሰዎችን እና ክስተቶችን በያዘ የዳሰሳ ጥናት የዩናይትድ ስቴትስ እና የቨርጂኒያ ታሪክ ውስጥ ያስሳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11

### የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል I

ይህ ኮርስ የአለም ታሪክን ከጥንት ጊዜ እስከ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ 1500 ዓ.ም ውስጥ ያለውን ይዳስሳል። በአለም ስልጣኔዎች እና ታሪካዊ እድገታቸው በኩል፣ ተማሪዎች ወቅታዊ በሆኑ የአለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን ያገኛሉ። ተማሪዎች በስነጽሁፍ፣ በስነጥበብ፣ በአርክቴክቸር፣ በሙዚቃ፣ በሃይማኖት፣ በፍልስፍና እና በጂኦግራፊ በኩል የባህሎችን የተለዩ ባህሪያት ይፈትሻሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

### የአለም ታሪክ እና ጂኦግራፊ ክፍል II

ይህ ኮርስ ከሲርካ 1400 ሬኔዛንስ ጀምሮ እስከ 21ኛው ክፍለዘመን የቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ድረስ ያለው የአለም ታሪክ የዳሰሳ ጥናት ነው። ኮርሱ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ እና አእምሮአዊ እንቅስቃሴዎችን በመተንተን በጊዜ ክፍሎች እና በበርካታ የአለም አካባቢዎች ያሉ ግንኙነቶችን ለማከናወን ይረዳል። ይህ ኮርስ የንባብ፣ የጽሁፍ፣ የትንታኔ፣ የግንኙነት እና የምርምር ክህሎቶች እድገት ላይ አጽንዖት ይሰጣል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10

# የማህበራዊ ትምህርቶች ተመራጮች

ለምረቃ የተረጋገጠ የክሬዲት ዩኒት ተማሪው ኮርሱን በአጥጋቢነት ማጠናቀቅ እና ለዛ ኮርስ በኮርሱ መጨረሻ የመማር ደረጃዎች ፈተና (SOL) የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ሰአት፣ የ SOL ታሪክ እና ለ U.S. ታሪክ፣ የአለም ታሪክ ክፍል I እና የአለም ታሪክ ክፍል II የማህበራዊ ሳይንሶች ሙከራዎች ይገኛሉ። የሚያስፈልጉ የተረጋገጡ ክሬዲቶች ቁጥር በምረቃ አመት እና በዲፕሎማው አይነት ላይ ይወሰናል። ገጽ 50ን ይመልከቱ።

### AP ኢኮኖሚክስ

ይህ በሁለት ሴሚስተር ረጅም የ AP ኮርሶች የተሰራ አመቱን ሙሉ የሚዘልቅ ኮርስ ነው። ማክሮኢኮኖሚክስ እና ማይክሮኢኮኖሚክስ ተማሪዎች በሁለቱም ሴሚስተር የሚቆዩ የ AP ኮርሶችን እንዲወስዱ በደንብ ይበረታታሉ።

ማክሮኢኮኖሚክስ ተማሪዎች የኢኮኖሚክስ ትንታኔ መርሆዎችን በአጠቃላይ በኢኮኖሚ ስርዓቱ ውስጥ የሚተገበር ጥልቅ ግንዛቤ ይሰጣል። ማክሮኢኮኖሚክስ በኢኮኖሚያዊ ተቋማት ጥናት፣ በህዝባዊ ፖሊሲ፣ በሃገራዊ ገቢ እና የዋጋ አወሳሰን ላይ የተለየ አጽንዖት ይሰጣል። በሚከተሉት ላይ አጽንዖት ይሰጣል፤ መሰረታዊ የኢኮኖሚክስ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ክላሲካል፣ ኪኔሺያን እና መኒተሪስት የኢኮኖሚ እይታዎችን፣ ፊዚካል እና መኒተሪ ፖሊሲን አካትቶ የኢኮኖሚያዊ አፈጻጸም ልኬት እና ሃገራዊ የገቢ ትንተና ላይ ። አለም አቀፍ ኢኮኖሚክ፣ የንግድ ጉዳዮች እና የባንኪንግ ፖሊሲዎች ውይይት ይደረግባቸዋል።

ማይክሮኢኮኖሚክስ ግላዊ ውሳኔ ማድረጎችን፣ ሸማቾች እና አምራቾች ሁለቱም በሰፊው የኢኮኖሚያዊ ስርዓት ውስጥ ባሉ ክንውኖች የሚተገበሩ የኢኮኖሚክስ መርሆዎች ጥልቅ ግንዛቤን ይሰጣል። እነዚህ ሸማቾች እና አምራቾች የሚያካትቱት የመኖሪያ ቤቶችን፣ የቢዝነስ ተቋማትን እና የመንግስት እና የማህበረሰብ ድርጅቶችን ነው። ኮርሱ በዋነኝነት የምርት ገበያዎች ተፈጥሮ እና አሰራሮች ላይ አጽንዖት ይሰጣል እና የሚያካትተውም በኢኮኖሚው ውስጥ የተሻለ ውጤት እና ፍትሃዊነትን ለማምጣት የተጽዕኖ ገበያዎች ጥናት እና የመንግስትን ሚና ያካትታል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

### AP የአውሮፓዊያን ታሪክ

ይህ የኮሌጅ ደረጃ ኮርስ የዘመናዊው ጊዜ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማቲክ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አርቲስታዊ፣ አእምሮአዊ እና ባህላዊ ተቋማትን ከ 1450 B.C.E ጀምሮ ባሉ የአውሮፓ ታሪክ ጥናት በኩል ያለውን አውድ የበለጠ ግንዛቤን ለማዳበር የተነደፈ ነው። ይህ አይነት ግንዛቤ በመጀመሪያ እና ሁለተኛ የሰነዶች ምንጭ ላይ በማተኮር በተመረጠ እውነተኛ እውቀት እና አግባብነት ባለው የትንታኔ እና የትርጉም ክህሎቶች ጥምረት ይልቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

### AP ሳይኮሎጂ

ይህ ኮርስ ለተማሪዎች አጠቃላይ እና ጥልቅ የሆነ የሰው ልጆች እና የሌሎች እንስሳት የባህሪይ እና የአዕምሮ ሂደቶች የሳይንሳዊ ትምህርትን ለማስተዋወቅ ተነድፏል። ተማሪዎች በሳይኮሎጂካዊ ምርምር እና እውነታዎች ውስጥ፣ መርሆዎች እና በሳይኮሎጂ ውስጥ ካሉ ከእያንዳንዱ ንዑስ ክፍል ጋር ለወቅቱ አካሄዶች ይጋለጣሉ። እንዲሁም እነሱ በሳይንስ እና በተግባር ስለሚጠቀሙባቸው የሳይኮሎጂስት ስነምግባር እና ዘዴዎች ይማራሉ። ሳይኮሎጂስቶች የተለመዱ እና ያልተለመዱ ግንዛቤዎችን፣ ሃሳቦችን፣ ስሜቶችን እና ተግባራትን ለማሰስ ስለሚጠቀሙባቸው ሂደቶች ለመማር ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች AP ሳይኮሎጂ ጥሩ አማራጭ ነው።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

### የአፍሪካ አሜሪካ ጥናቶች

የአፍሪካ አሜሪካዊ የታሪክ ኮርስ ተማሪዎች የአፍሪካ አሜሪካዊ ተሞክሮዎችን ሰፊ እይታ ለመስጠት እና የጥንት አፍሪካ ስለነበረው እንቅስቃሴ በዘመናዊ ጊዜያት ለማሰስ ነው። ኮርሱ በአካባቢያዊ የክፍል ካሪኩለም እና በአምስት የኦንላይን ሞጁሎች በመደገፍ አፍሪካዊያን ወደ አሜሪካ አህጉሮች የሄዱበትን እና ከ 1619 እስከ አሁን ያለውን የአፍሪካ አሜሪካ ተሞክሮን ይቃኛል። በተጨማሪም፣ ኮርሱ የአፍሪካ አሜሪካዊያንን የማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ አስተዋጽዖዎች ለአሜሪካ ማህበረሰብ አጉልተው ያሳያሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

**ርዝመት፦** ሙሉ አመት

### አለም አቀፍ ዋና ትምህርቶች

ይህ የሴሚተር ኮርስ በዩናይትድ ስቴትስ የአናሳ ተሞክሮን እና ሁሉም ዜጎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳመጣ የዳሰሳ ጥናት ያደርጋል። የዘር፣ የጾታ እና የባህል ጉዳዮች በአሜሪካ ማህበረሰብ ላይ ላሉ ለፖለቲካዊ፣ ለባህላዊ እና ለማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ውይይት እና ትንተና ይደረግባቸዋል። የተግባር ምርምር፣ የሶቅራጢቅ ሴሚናሮች፣ የውሂብ አተረጓጎም፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ምንጭ አነባበቦች፣ የቃል ዝግጅቶች፣ የምርምር ወረቀቶች እና የጽሁፍ ምላሽ ተማሪዎችን በጥናታቸው ለመምራት ይውላሉ። ተማሪዎች በ21ኛው ክፍለ ዘመን አለም አቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ ለስኬት ሲዘጋጁ በአዎንታዊ ንግግር ላይ ይሳተፋሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፦** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

## የግል አናናር እና ፋይናንስ

ግላዊ የመኖር እና የፋይናንስ አላማዎች ግላዊ የሆኑ የቢዝነስ እና የፋይናንሶች ለመቆጣጠር መመሪያን ይጠይቃሉ እና የሚያካትቱት ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሊወሰኑ የማያስፈልጋቸው የባንክ ሂሳብ መክፈት እና የባንክ አገልግሎቶችን ጥራት መፍረድ፤ ቼክቡክን ማመጣጠን፤ የብድር ማመልከቻን ማጠናቀቅ፤ የውርስ አንድምታ፤ የግላዊ ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች መሰረቶች፤ የሸማች መብቶች እና ግዴታዎች፤ ከሻጮች እና ከነጋዴዎች ጋር መገናኘት፤ የችርቻሮ እና የክሬዲት ካርድ እዳዎችን ያካተተ የእዳ አስተዳደር፤ የስቴት እና የፌዴራል ታክስ ስሌቶች፤ አካባቢያዊ የታክስ ምዘናዎች፤ በበርካታ ስልቶች የወለድ መጠኖች ስሌት፤ ቀላል ውሎችን መረዳት፤ እና ልክ ያልሆነ ሂሳብን እንዴት ማወዳደር እንደሚቻል ነው። ኮርሱ የሚያካትተው 21 የስራ ዝግጁነት ክህሎቶችን እንዲሁም ተማሪዎች ለ Commonwealth ፈተና እና/ወይም w!se ፈተና የስራ ቦታ ዝግጁነት ክህሎቶችን እንዲወስዱ ነው። ይህ ኮርስ የክሬዲት ዝግጅት በ IEP ውስጥ ለተሰናዳበት ቦታ ላይ ላሉ ከአካል ጉዳት ጋር ለሚኖሩ ተማሪዎች ብቻ ይገኛል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

3 መደበኛ ክሬዲቶች በታሪክ እና ማህበራዊ ትምህርቶች

## ሳይኮሎጂ

ይህ ኮርስ ለተማሪዎች የሳይኮሎጂ ግቦችን እና መርሆዎችን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች ታሪክን፣ ንድፈ ሀሳባዊ አቀራረቦችን እና የሳይኮሎጂ የምርምር ዘዴዎችን ይመረምራሉ። የባይሎጂካል ተጽእኖዎች ባህሪ፣ አስተሳሰብ እና መነቃቃት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ይማራሉ እንዲሁም ጤናማ ያልሆኑ ባህሪያት አይነቶችን ይመረምራሉ። እነሱ ከጓደኞች ጋር እንዴት በተሻለ መግባባት እና ግንኙነት ማድረግ እንደሚቻል እንዲሁም ስለራስ፣ ስለቤተሰብ እና ስለጓደኞች የተሻለ  ግንዛቤ ማድረግ እንደሚቻል ያውቃሉ። ይህ ኮርስ የሳይኮሎጂስቶችን ስራ በሚገዛ መልኩ በስነምግባራዊ ደረጃዎች ላይ እንዲሁ ያተኩራል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

## ማህበራዊ ፍትህ

በብጥብጥ፣ በሰላም እና ጦርነት፣ በአካባቢ ወይም በሰብአዊ መብቶች አይነት የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ፍላጎት ያለው ማንኛዉም ተማሪ ይህን ኮርስ ዋጋ እንዳለው ማግኘት አለበት። ትኩረቱ ሃሳባዊ እና ተግባራዊ ተብሎ ይከፈላል። ተማሪዎች የብጥብጥ-አልባ ታሪክ፣ ፍልስፍና እና ዘዴዎችን ይማራሉ እንዲሁም የብጥብጥ-አልባ ፍልስፍናን የአሁን አተገባበሮች ይመረምራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የግጭትን መነሻዎች በግንኙነቶቻቸው እና በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ ይመረምራሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

## ሶሲዮሎጂ

ይህ ኮርስ ተማሪዎች መሰረታዊ የሶሺዮሎጂ መርሆዎችን እና ከእሱ ጋር የተገናኙ በርካታ መስኮችን እና ሙያዎችን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች እንደ ባህላዊ እና የብሄር ግንኙነቶች፣ በደል፣ ወንጀል እና በተመረጡ የአሁን ርዕሶች ላይ ያሉ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የጉዳይ ታሪኮች እና ፈተና ላይ እንደቀረበው የተቀመጡ የማህበረሰብ ችግሮችን ይመረምራሉ። የሙከራ ጊዜ ሰራተኞች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች እና ሌላ የግብዓት ግለሰቦች ለመመርመር እና ለመወያየት ሰፊ ገደብ ያላቸውን ርዕሶች ያቀርባሉ። እንዲሁም ተማሪዎች የማህበራዊ ተቋማት ተግባራትን፣ የጾታ ሚና ለውጦችን፣ ከትምህርት እና ከሰው ልጅ እድገት ጋር የተገናኙ

ለውጦችን እና የአናሳዎች ተሞክሮን ይመረምራሉ። ተማሪዎች ለኢትኖግራፊ እና ማህበራዊ እርከን ትምህርት ይተዋወቃሉ።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

# የቴክኖሎጂ ትምህርት

### የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ

ተማሪዎች መዋቅሮችን ይገነባሉ እና በተግባራዊ ፕሮጀክቶች ላይ በመሳተፍ ለንግድ፣ ኢንዱስትሪያዊ፣ የመኖሪያ፣ የህዝባዊ ስራዎች እና የተቋማት ቴክኖሎጂዎች ላይ እንዲጋለጡ በማድረግ የግንባታ ሙያዎችን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ለመሳሪያዎች እና ለማሽነሪዎች አግባብነት ያለው የደህንነት ሂደቶችን፣ ከግንባታ፣ ከንድፍ ማንበብ እና ከአርክቴክቸር ጋር ከተገናኙ ምልክቶች እንዲሁም በግንባታ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የሂሳብ ጽንሰ ሃሳቦች እና መርሆዎች ላይ የቃላት ስብስብ እና ቃላትን ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

# ቲያትር

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

### የላቀ ቲያትር፡- ቲያትር ለውድድር እና ለማህበረሰብ ክንውን

በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች የትወና ክህሎታቸውን በክወና እና በማጥናት ይቀርጹታል። በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለ Virginia High School League (VHSL) ዲስትሪክት የ One-Act ውድድር፣ እንደ ዶክተሮች ወይም በአቅጣጫ ወይም በመድረክ አስተዳደር ሆነው እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶችን በቲያትር ውስጥ በማዘጋጀት ተግባራዊ ተሞክሮን እንዲሁ ያገኛሉ። ይህ ኮርስ በ Lincoln Center for the Arts Institute በኩል የማስተማር ስትራቴጂ ወርክሾፖች፣ የመድረክ አስተዳደር፣ በመኖሪያ ቤት ያሉ አርቲስቶች፣ ትወና፣ ሜካፕ እና አልባሳት በኩል የመበልጸግ ተሞክሮዎችን ያቀርባል። ክፍሉ ለክሬዲት ሊደገም ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ኦዲሽን

### መካከለኛ ቲያትር፡- ከገጽ ለገጽ

በዚህ ክፍል፣ ተማሪዎች የቲያትር፣ የቲያትር ታሪክ፣ የድራማዊ ስነጽሁፍ እና በተለይ ደግሞ ክንውን እውቀታቸውን የበለጠ ያሰፋታል። ለተማሪዎች ትዕይንቶች፣ ገጸባህሪያትን እና ከዘመናዊው ዘመን ያሉ ረዣዥም ንግግሮችን ያነባሉ እና ይተውናሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የራሳቸውን ትዕይንቶች፣ ሞኖሎጎች እና አጫጭር ጭውውቶችን በመጻፍ ባህሪይ የመፍጠር ሂደትን ያዳስሳሉ። ተማሪዎች በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ ትወናን ወይም ትወናዎችን በመጻፍ በቲያትር ውስጥ ተግባራዊ ክህሎትን እንዲሁ ያገኛሉ። ክፍሉ ለክሬዲት ሊደገም ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የቲያትር መግቢያ የገጸ ባህሪ ፈጠራ እና የቲያትር አድናቆት ወይም ኦዲሽን

### የቲያትር መግቢያ፡- የገጸ ባህሪ ፈጠራ እና የቲያትር አድናቆት

በዚህ ክፍል፣ ተማሪዎች ለቲያትር፣ ለቲያትር ታሪክ፣ ለስነጽሁፍ አንድ ክንውን አድናዎትን ያገኛሉ። ተማሪዎች ክስተቶችን እና ጨዋታዎችን ከጥንት እስከ ሬኔዛንስ ጊዜ ድረስ በገጸ ባህሪ ፈጠራ፣ ድምጽን እና አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም ያነባሉ እንዲሁም ይተገብራሉ። ተማሪዎች የራሳቸውን እና የሌሎችን ክንውኖች በደንብ የመተንተን ችሎታቸውን ለማጎልበት በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ያሉትን ድራማዊ ክንውኖች ይገመግማሉ። ተማሪዎች ለአንዱ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የድራማ ፕሮዳክሽን ቲያትር ውስጥ እንደ አስተናጋጅ በመሆን ተግባራዊ ተሞክሮን እንዲሁ ያገኛሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የመድረክ ጽሁፍ መጻፍ ክህሎት I

በስቴጅክራፍት I ውስጥ ያሉት ተማሪዎች የቲያትር ክንውን ያልሆኑ አካባቢዎች በክፍለ ጊዜ ንድፍ እና ግንባታ ላይ ያተኩራሉ ነገር ግን አልባሳት፣ ሜክአፕ እና የመብራት ንድፍ ላይም እንዲሁ ያካትታል። ተማሪዎች ለት/ቤት ማሳያ መሰብሰቢያዎችን የመሰሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። ተጨማሪ ማበልጸጊያ የዋና ክፍል ክፍለጊዜያትን፣ የአስተማሪ ወርክሾፖችን፣ በመኖሪያ ቤቶች ያሉ አርቲስቶች እናቲቴክኒካዊ የድጋፍ ክሊኒኮችን ይደግፋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የመድረክ ጽሁፍ መጻፍ ክህሎት II

የመድረክ ጽሁፍ መጻፍ ክህሎት II በመድረክ ጽሁፍ መጻፍ ክህሎት I የተመሰረተውን የቲያትራዊ ንድፍ እና የኮንስትራክሽን ክህሎቶች የበለጠ እርምጃ ያራምደዋል። ተማሪዎች የመሪነት ሚናዎችን እንዲቀበሉ እና በዲዛይን ቴክኒክ፣ በመሳሪያ አጠቃቀም እና በመድረክ አወቃቀር ኮርስ ሌሎች ገጽታዎች ላይ አዳዲስ ተማሪዎችን ለመምራት እንዲረዱ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች በት/ቤት ቲያትር እና በሙዚቃ ተግባራት ቴክኒካዊ ገጽታዎች ላይ ለመርዳት የበለጠ ሃላፊነትን እንዲያስቡ ይጠየቃሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በቀድሞ ቴክኒካዊ ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ የመድረክ ጽሁፍ መጻፍ ክህሎት I ወይም የአስተማሪ ጥቆማ።

### የቲያትር ልምምድ ትወና እና ዳይሬክቲንግ

በዚህ የቲያትር ልምምድ 8ኛው ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች በሴሚስተሩ በሚከናወነው የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዋና መድረክ የክንውን ገጽታዎች ላይ በተመዘገቡበት (የመኸር ጨዋታ ወይም የጸደይ ሙዚቃ) እንዲሳተፉ ተመርጠዋል። ተማሪዎች እንደ ተዋናይ፣ የተማሪ ዳይሬክተር ወይም የመድረክ ሃላፊ ሆነው ይሳተፋሉ። ክፍሉ ለልምምዶች በየቀኑ ይገናኛል። ለተሳትፎ የሚያስፈልግ የተሳካ ኦዲሽን እና/ወይም ቃለ መጠይቅ

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### የቲያትር ልምምድ ቴክ

በዚህ የቲያትር ልምምድ 8ኛው ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች በሴሚስተሩ በሚከናወነው የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዋና መድረክ የስልት ገጽታዎች ላይ በተመዘገቡበት (የመኸር ጨዋታ ወይም የጸደይ ሙዚቃ) እንዲሳተፉ ተመርጠዋል። ተማሪዎች በማስቀመጫ፣ በማብሪያዎች፣ ላልባሳት፣ በድምጽ፣ በመደገፊያዎች፣ በማስታወቂያ እና/ወይም ማርኬቲንግ

ላይ ሲሰሩ ይችላሉ። ክፍሉ ራሱን የቻለ ጥናት፣ የትንሽ ቡድን ትምህርት እና የሙሉ ክፍል ጥምረት ይሆናል። ልዩ የስብሰባ ጊዜያት በእያንዳንዱ ሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ይታተማሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 0.5

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

# ምስላዊ ስነጥበብ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የፋይን ስነጥበባት በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ።

### AP 2-D ስነጥበብ እና ንድፍ

የ AP ስነጥበብ እና የንድፍ ፕሮግራም ሶስት የተለያዩ ኮርሶችን እና የ AP ፖርትፎሊዮ  ፈተናዎችን አካትቷል – AP 2-D ስነጥበብ እና ንድፍ፣ AP 3-D ስነጥበብ እና ንድፍ እና AP ስዕል – ይህም ከኮሌጅ እና ከዩኒቨርሲቲ የመሰረተር ኮርሶች ጋር ተዛማጅ የሆነ ነው። ተማሪዎች በስነጥበብ እና ንድፍ፣ በሂደት ሰነድ አቀማመጥ እና በቀረበው ስራ ላይ የጽሁፍ መረጃ ቢኖርም ለማሳየት የስራ ፖርትፎሊዮ ይፈጥራሉ። በግንቦት ወር፣ ተማሪዎች በተወሰኑ መሰረቶች ላይ በመመስረት የግምገማ ፖርትፎሎዮዎችን ሊያስገቡ ይችላሉ ይህም የነገሮች፣ የሂደቶች እና የሃሳቦች ክህሎታዊ ውኅደትን እንዲሁም በልምምድ፣ በሙከራ እና በግምገማ በኩል ዘላቂነት ባለው ምርመራ በጥያቄዎች በመመራት ሊያካትት ይችላል። ተማሪዎች ማንኛዉም ወይም ሁሉንም የ AP ፖርትፎሊዮ ፈተናዎች ለማስገባት ሊመርጡ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በአስተማሪው የተመረጠ ወይም የተመከረ የ 3 አመት ስነ ጥበብ።

### AP 2-D ስነጥበብ እና ንድፍ

የ AP ስነጥበብ እና ንድፍ ፕሮግራም ሶስት የተለያዩ ኮርሶችን እና AP ፖርትፎሊዮ ፈተናዎችን – AP 2-D ስነጥበብ እና ንድፍ፣ AP 3-D ስነጥበብ እና ንድፍ፣ እና AP ስዕል – ከኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ መሰረት ኮርሶች ጋር የሚዛመዱትን አካትቷል። ተማሪዎች በስነጥበብ እና ንድፍ፣ በሂደት ሰነድ አቀማመጥ እና በቀረበው ስራ ላይ የጽሁፍ መረጃ በኩል ለማሳየት የስራ ፖርትፎሊዮ ይፈጥራሉ። በግንቦት ወር፣ ተማሪዎች በተወሰኑ መሰረቶች ላይ በመመስረት የግምገማ ፖርትፎሎዮዎችን ሊያስገቡ ይችላሉ ይህም የነገሮች፣ የሂደቶች እና የሃሳቦች ክህሎታዊ ውኅደትን እንዲሁም በልምምድ፣ በሙከራ እና በግምገማ በኩል ዘላቂነት ባለው ምርመራ በጥያቄዎች በመመራት ሊያካትት ይችላል። ተማሪዎች ማንኛዉም ወይም ሁሉንም የ AP ፖርትፎሊዮ ፈተናዎች ለማስገባት ሊመርጡ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

በአስተማሪው የተመረጠ ወይም የተመከረ የ 3 አመት ስነ ጥበብ።

### AP የስነጥበብ ታሪክ

ይህ ኮርስ ለአካዳሚክ ትምህርት በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ላላቸው ተማሪዎች የታለመ ነው። የስነጥበብ ታሪክ ከመደበኛው ዘመን (B.C.E.) እስከ አሁን ድረስ ትምህርት ይሰጥባቸዋል። ትምህርት፣ ቪዲዮ፣ የክፍል ውይይት፣ የሙዚየም ስራ እና የመልቲሚዲያ የጥናት ረጂዎች የንባብ እና የጽሁፍ ምደባዎችን ያስገባሉ። ተማሪዎች ዋና ዋና የድሮ እና የሩቅ ባህሎችን አርቲስታዊ አገላለጽ (አርክቴክቸርን ጨምሮ) እንዲሁም የራሳችንን ጊዜ እና አካባቢ የሆኑትን ይመረምራሉ። የስነጥበብ ስራዎችን በጥንቃቄና እውቀት እና ከማስተዋል ጋር እንዲሁም የተመለቱትን ስነጥበብ ለመግለጽ እና ለማበረታታት ይማራሉ። ተማሪዎች ሁሉንም የንባብ ምደባዎች ማጠናቀቅ፣ ማስታወሻ መያዝ፣ የክፍል ውይይቶች ላይ

መሳተፍ እና ሁሉንም የሙዚየም ምደባዎች እና ሁሉንም የጽሁፍ ስራ ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

### AP ስዕል

የ AP ስነጥበብ እና ንድፍ ፕሮግራም ሶስት የተለያዩ ኮርሶችን እና AP ፖርትፎሊዮ ፈተናዎችን – AP 2-D ስነጥበብ እና ንድፍ፣ AP 3-D ስነጥበብ እና ንድፍ፣ እና AP ስዕል – ከኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ መሰረት ኮርሶች ጋር የሚዛመዱትን አካትቷል። ተማሪዎች በስነጥበብ እና ንድፍ፣ በሂደት ሰነድ አቀማመጥ እና በቀረበው ስራ ላይ የጽሁፍ መረጃ በኩል ለማሳየት የስራ ፖርትፎሊዮ ይፈጥራሉ። በግንቦት ወር፣ ተማሪዎች በተወሰኑ መሰረቶች ላይ በመመስረት የግምገማ ፖርትፎሎዮዎችን ሊያስገቡ ይችላሉ ይህም የነገሮች፣ የሂደቶች እና የሃሳቦች ክህሎታዊ ውኅደትን እንዲሁም በልምምድ፣ በሙከራ እና በግምገማ በኩል ዘላቂነት ባለው ምርመራ በጥያቄዎች በመመራት ሊያካትት ይችላል። ተማሪዎች ማንኛዉም ወይም ሁሉንም የ AP ፖርትፎሊዮ ፈተናዎች ለማስገባት ሊመርጡ ይችላሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

በአስተማሪው የተመረጠ ወይም የተመከረ የ 3 አመት ስነ ጥበብ።

### ስነጥበብ I

ስነጥበብን እንደ ስራ ወይም ለባህል መጎልበት አድርገው ለመቀጠል ለሚፈልጉ ሰዎች መሰረት ሆኖ እንዲነደፍ፣ ይህ ኮርስ የመሳልን መሰረታዊያን፣ ቅርጻቅርጽ እና መሳልን በተለያይ አይነት ሚዲያ በማድረግ አጽንዖት ያደርጋል። ሳምንታዊ የቤት ስራ ምደባዎች መሰረታዊ የማስተዋል ክህሎቶችን ለማግኘት እና ለማሳደግ ይረዳሉ። እንደ ትንተና፣ ችግር መፍታት እና ግምገማ የመሳሰሉ የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎቶች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። ኮርሱ የሚያካትተው የስነጥበብ ታሪክ፣ ትችት እና ውበት እንዲሁም ፣ እንደ ሙዚየም የመስክ ተሞክሮ፣ የቤት ውስጥ አርቲስቶች እና የተማሪ ወርክሾፖችን የመሳሰሉ ተጨማሪ የማጎልመቻ ተሞክሮዎች ትምህርትን እንዲሁ ነው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### ስነጥበብ II

ስነጥበብ II የንድፍ እና የእነሱን የእውቀት አተገባበር አካላት እና መርሆዎች ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ተማሪዎች በመሳል፣ በመንደፍ፣ በመቅረጽ እና የህትመት ስራ ማድረግን ጨምሮ ስልቶችን እና ሂደቶችን በተለያየ ሚዲያ ይማራሉ። ኮርሱ እንዲሁ የሚያካትተው የስነጥበብ ታሪክ፣ ትችት እና ውበት ትምህርት ነው። እንደ ትንተና፣ ችግር መፍታት እና ግምገማ የመሳሰሉ የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎቶች በዚህ ኮርስ ሁሉ አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ስነጥበብ I

### ስነጥበብ III

ስነጥበብ III አራት ዋና የትኩረት አካባቢዎችን ያቀርባል፦ የመሬት አቀማመጥ፣ የሰው ልጅ ምስል፣ የተረጋጋ ህይወት እና ረቂቅ ነው። እያንዳንዱ አካባቢ የሚያካትተው ሰፊ የሚዲያ ድብልቅ ጋር ያለ ተሞክሮን እና በቅንብር፣ ፈጠራ እና ቴክኒካዊ ክህሎቶች እድገት ላይ ያተኩራል። እንደ ትንተና፣ ችግር መፍታት እና ግምገማ የመሳሰሉ

የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎቶች በኮርሱ ሁሉ አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስነጥበብ II

### ስነጥበብ IV (ኦነርስ)

ስነጥበብ IV ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ የስነጥበብ ፕሮግራም ለመግባት እየገመቱ  ላሉ ወይም ተጨማሪ የስነጥበብ እድገት ለሚፈልጉ ቁም ነገረኛ እና የተነቃቁ ተማሪዎች የተነደፈ ነው። እያንዳንዱ ተማሪ ለኮሌጅ እና ለቅጥር ግምገማ አመቺ የሆነ የተዘጋጀ ፖርትፎሊዮ ያጎለብታል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስነጥበብ III

### ሴራሚክስ I

ይህ ኮርስ የ 3-D ሽክላ ቅርጾችን ተግባራዊ እና የማስጌጥ የሴራሚክስ የስነጥበብ ስራዎችን በመፍጠር ያስሳል። ተማሪዎች በእጅ ግንባታ እና በጎማ መወርወር ላይ በርካታ ቴክኒኮችን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የሴራሚክ ችግሮችን በልዩ ሁኔታ ለመፍታት በፈጠራዊ እና በጥልቀት ያስባሉ። እያንዳንዱ ተማሪ የሃሳቦች እና የሂደቶች እድገት ተግባራዊ መጽሃፍ (የስዕል መጽሃፍ) ይይዛል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስነጥበብ I

### ሴራሚክስ II

ውስብስብ ችግር የመፍታት ክህሎቶች በእጅ በተገነቡ እና በጎማ የሚወረወሩ ፕሮጀክቶች የተለያዩ ኮንስትራክሽን ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል። ጥልቅ የሆነው ትኩረት በንድፍ፣ ግንባታ እና የእጅ ጥበብ ክህሎቶች ላይ ይሆናል። ተማሪዎች የፈጠሯቸውን የስነትበብ ስራዎች ምስሎች እና ነጸብራቆች የሚመዘግበውን ስኬችቦርድ ከዲጂታል ፖርትፎሊዩ ጋር እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስነጥበብ I እና ሴራሚክስ I

### ንድፍ

የሰስተኛው ደረጃ የአርት ኮርስ ግራፊክስ እና አኒሜሽን፣ ፋብሪክ፣ ፋሽን እና የአልባሳት ንድፍ፣ ፈርኒቸር እና የውስጥ እና የኢንዱስትሪ ንድፎችን ጨምሮ ለሰፊው የንግድ ስነጥበብ ተግባራት እንደ መግቢያ ሆነው ያገለግላሉ። ከተማሪዎች ጋር ኮምፒውተርን እና በእጅ የተሰሩ ቴክኒኮችን በመጠቀም የስነጥበብ አካላት እና የንድፍ መርሆዎች ላይ አጽንዖት ተሰጥቷል። ፕሮጀክቶች የደንበኛ አቀራረቦችን በአዕምሮ ውስጥ በማሰብ ይከናወናል እና በሁለቱም በግል እና የትብብር ቡድኖች ይከናወናል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስነጥበብ I እና ስነጥበብ II መርሃግብር ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ፣ ስነጥበብ II እና ንድፍ በአንድ አይነት የት/ቤት አመት ውስጥ ሊወሰዱ ይችላሉ።

# የአለም ቋንቋዎች

ሁሉም የአለም ቋንቋ ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ የምርጫ ክሬዲት ላይ ይተገበራሉ። ሁሉም ኮርሶች አንድ ሙሉ አመት ናቸው። ተማሪዎች በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቆይታቸው የአለም ቋንቋዎችን ለመጀመር ወይም ለመቀጠል በደንብ ይበረታታሉ። ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የአለም ቋንቋዎችን በሶስት፣ በአራት ወይም በአምስት አመት ትምህርት ውስጥ ለጨረሱ አመልካቾች በተሻለ ሁኔታ ይመለከቷቸዋል። ተማሪዎች የአለም ቋንቋን (ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ላቲን፣ እና ስፓኒሽ) ለመማር የተለያዩ እድሎችን ያገኛሉ፤

- እየመጡ ያሉ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች 6ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋን መማር ሊጀምሩ ይችላሉ እና የተመሳሳይ ቋንቋ ሶስት አመት ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ተማሪው ስድስተኛ ክፍል ላይ ሌላ ትምህርት ለማጥናት እንዲሁ ሊመርጥ ይችላል እና 7ኛ ክፍል ላይ የአለም ቋንቋ ትምህርትን ሊጀምር ይችላል፣ ይህም የዚህን ኮርስ ሁለት አመታት ጥናት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቀ በኋላ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያገኛል።
- የዚህን ኮርስ የሁለት አመት ትምህርት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ እየመጡ ያሉ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።
- በአለም ቋንቋ ትምህርት ቀድሞውኑ የተመዘገቡ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የአለም ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲትን ለማግኘት የሁለተኛ አመት ትምህርትን መቀጠል አለባቸው። የአለም ቋንቋ ትምህርታቸውን እስካሁን ያልጀመሩ እየመጡ ያሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በስምንተኛ ክፍል አመት ውስጥ የስፓኒሽ I በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ።

በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ውስጥ የተወሰደ ማንኛዉም የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የያዘ ኮርስ ውጤቶች ከተማሪው ትራንስክሪፕት ውስጥ እንዲቀር እና ተማሪው ለኮርሱ የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት ወይም የተረጋገጠ ክሬዲት እንዳያገኝ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከሌላ ት/ቤት ክፍሎች ወደ ACPS ለተላለፉ ተማሪዎች፣ ተገቢ የሆነ የጅማሬ ቋንቋ ምደባ ብቁ የሆነ ምዝገባ በመጠባበቅ ላይ ሆኖ ይቀርባል።

#### የአለም ቋንቋ ክሬዲት በፈተና

ከስድስተኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ከእንግሊዝኛ ውጪ በሆኑ ቋንቋዎች መረዳት እና መግባባት ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች ለአለም ቋንቋዎች እስከ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን የማግኘት እድል አሁን አላቸው። መመዘኛዎች የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ ከ 100 በሆኑ ቋንቋዎች ይገኛሉ። የአለም ቋንቋ ክሬዲት በፈተና የሚለው በአመት አንድ ጊዜ በመኸር ወቅት ይቀርባል። ለበለጠ መረጃ እባክዎ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ት/ቤቶችን ድረገጽ በ www.acps.k12.va.us/worldlanguagecreditላይ መጎብኘት ይችላሉ።

#### AP የቻይንኛ ቋንቋ እና ባህል

AP የቻይንኛ ቋንቋ እና ባህል ቻይንኛ በማንበብ በመጻፍ እና በማዳመጥ ያሉ ክህሎቶችን ማጣራት ላይ ያተኩራል። የንግግር ብቃትን ለማሻሻል የተለየ አጽንዖት ተቀምጧል። እንደ ታሪክ፣ ስልጣኔ፣ ፍልስፍና፣ ሙዚቃ እና ስነጥበብ ያሉ የባህል ርዕሶች በጥልቀት ትምህርት ይሰጥባቸዋል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች በርካታ ስራዎችን/ቅንጭብጭቦችን ያነባሉ እና ይተነትናሉ። ከባድ የቃላት ስብስብ እና የሰዋሰው ግምገማ የዚህን ኮርስ ዋና ክፍሎች ያረጋግጣል ይህም በአጠቃላይ በቻይንኛ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

የቻይና IV ኦነርስ ወይም እኩሌታው

**AP የፈረንሳይ ቋንቋ እና ባህል**

AP ፈረንሳይኛ V ፈረንሳይኛን በማንበብ በመጻፍ እና በማዳመጥ ያሉ ክህሎቶችን ማጣራት ላይ ያተኩራል። የንግግር ብቃትን ለማሻሻል የተለየ አጽንዖት ተቀምጧል። እንደ ታሪክ፣ ስልጣኔ፣ ፍልስፍና፣ ሙዚቃ እና ስነጥበብ ያሉ የባህል ርዕሶች በጥልቀት ትምህርት ይሰጥባቸዋል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በርካታ ስራዎችን/ ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች ቅንጭብጭቦችን ያነባሉ እንዲሁም ይተነትናሉ። ከባድ የቃላት ስብስብ እና የሰዋሰው ግምገማ የዚህን ኮርስ ዋና ክፍሎች ያረጋግጣል ይህም በአጠቃላይ በፈርንሳይኛ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ፈረንሳይኛ IV ኦነርስ ወይም እኩሌታው፣ እና/ወይም የአስተማሪው ፈቃድ

**AP የጀርመን ቋንቋ እና ባህል**

በ AP ጀርመን ቋንቋ እና ባህል ውስጥ፣ የንግግር ብቃትን ለማሻሻል ካሉ ልዩ አጽንዖት ጋር ተማሪዎች የማንበብ፣ የመጻፍ እና የማዳመጥ ክህሎቶችን ይጠራሉ። ተማሪዎች እንደ ታሪክ፣ ስልጣኔ፣ ፍልስፍና፣ ሙዚቃ እና ስነጥበብ ያሉ ባህላዊ ርዕሶችን በጥልቀት ይመረምራሉ እና ከበርካታ የስነጽሁፍ ዘውጎች ብዙ ስራዎችን/ቅንጭብጭቦችን ያነባሉ እንዲሁም ይተነትናሉ። ተማሪዎች የአንድ ሬዲዮ ገጸባህሪን፣ በርካታ አጫጭር ታሪኮችን እና ግጥሞችን እና በጀርመንኛ አጫጭር ሶስት ረጅም ልብወለዶችን ያነባሉ። ከባድ የቃላት ስብስብ እና የሰዋሰው ግምገማ የዚህ ኮርስ ዋና ክፍሎች ነው ይህም በአጠቃላይ በጀርመንኛ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ጀርመንኛ IV ኦነርስ ወይም እኩል የሆነ

**AP ላቲን**

በ AP ላቲን ውስጥ፣ ተማሪዎች የሮማን ግጥም ትርጉም እና አተናተን ላይ ያላቸውን ክህሎት ያሻሽሉታል። ተማሪዎች የቃል ንባብን ይለማመዳሉ እና ግጥም እና የተመረጡ ጸሃፊዎች ጋር ሲያመለክቱ እንደ ታሪክ፣ ስልጣኔ እና በርካታ ፍልስፍናዎችን ያሉ ባህላዊ ርዕሶችን ይማራሉ። ተማሪዎች የሰዋሰው መዋቅሮችን እንዲሁ ይገመግማሉ እና አዲስ የቃላት ስብስብ፣ የንግግር አይነት እና የአጻጻፍ መሳሪያዎችን እንዲሁ ይማራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ላቲን IV ኦነርስ

**AP ስፓኒሽ ቋንቋ እና ባህል**

በ AP ስፓኒሽ ቋንቋ እና ባህል ውስጥ፣ ተማሪዎች እንደታሪክ፣ ስልጣኔ፣ ፍልስፍና፣ ሙዚቃ እና ስነጥበብ የመሳሰሉ ባህላዊ ርዕሶችን

በጥልቀት ተምረው አጽንዖት በመስጠት የንግግር ብቃታቸውን ያጠራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች በርካታ ስራዎችን/ቅንጭብጭቦችን ያነባሉ እና ይተነትናሉ። ከባድ የቃላት ስብስብ እና የሰዋሰው ግምገማ የዚህን ኮርስ ዋና ክፍሎች ያረጋግጣል ይህም በአጠቃላይ በስፓኒሽ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ IV ኦነርስወይም እኩሌታው

### AP ስፓኒሽ ስነጽሁፍ እና ባህል

የ AP ስፓኒሽ ስነጽሁፍ እና የባህል ኮርስ ተማሪዎች የተወካይ የባህረ ገብ አካል እና የላቲክ አሜሪካዊያን የስነጽሁፍ ቃላትን ጥናት መደበኛ ትምህርት ያስተዋውቃል። ተማሪዎች በርካታ ዘውጎችን እና የንግግር አይነቶችን በመማር የስፓኒሽ ፕሮዝ ታሪክን ከ ዶን ዩዋን ማኑኤል እስከ ዘመናዊ ጊዜያት ያለውን እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። በኮርሱ ቆይታ፣ ተማሪዎች በተጨማሪ ትንተና፣ ትችት እና እውነተኛ የስነጽሁፍ ስራዎች ውይይት ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በስሂፓኒክ ስነጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች በመተዋወቅ በጥልቀት እንዲያነቡ እንዲሁም በስፓኒሽ ጥርት አድረገው እንዲጽፉ እና እንዲያወሩ ይማራሉ። ኮርሱ ሙሉ በሙሉ በስፓኒሽ ይከናወናል።

**ተመራጭ ክሬዲቶች፡-** 1

**ማስታወሻ:**

> በ AP ኮርሶች ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮርሱን የመጨረሻ AP ፈተና መውሰድ አለባቸው። የእነዚህ ፈተናዎች ወጪ በ ACPS ይከፈላል።

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ IV ኦነርስ ወይም እኩሌታው

### የላቀ የስፓኒሽ ባለሁለት ቋንቋ

ይህ ኮርስ ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቀጠለው የስፓኒሽ ባለሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ነው። በዚህ ኮርስ ውስጥ ተማሪዎች የሚተረጎም፣ በግለሰቦች መካከል ያለ አንድ የዝግጅት ግንኙነትን እንዲሁም የሂስፓኒክ ባህሎች እውቀታቸውን ክህሎቶች ያሻሽላሉ። ልብወለዶች፣ የዜና ጽሁፎች፣ ልብ ወለድ ያልሆኑ ጽሁፎች እና ትክክለኛ የድምጽ-ወምስል እቃዎችን ጨምሮ በይዘት የበለጸጉ ቁሶች ላይ አጽንዖት ተሰጥቷል። ይህ ከባለሁለት ቋንቋ A-C የሰዋሰብ ጭብጦች የተጣጣመ ግምገማ ነው። ይህ የሚያካትተው የአሁኑን፣ ትክክለኛ፣ ፍጹም ያልሆነ፣ የአሁን ተራማጅ፣ ሁኔታዊ፣ የወደፊት እና ንዑስ ጊዜዎችን ነው። የበለጠ ውስብስብ የሰዋሰው አወቃቀሮችን ከመማር በተጨማሪ፣ ተማሪዎች በስፓኒሽ ያላቸውን ግንኙነት ለማበልጸግ እና ክህሎታቸውን ለማሻሻል የቃላት ስብስባቸውን ያሳድጋሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ባለሁለት ቋንቋ ስፓኒሽ C

### በቻይንኛ ቋንቋ እና ባህል VI ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች

የዚህ አመት ኮርስ በቻይንኛ ይሰጣል እና በተፈጥሮ ጭብጥ ያለው ነው። እርሱ በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ እና በመጻፍ ጠንካራ መሰረታዊ ክህሎቶችን ከግምት ያስገባል እና በቀድሞ የጥናቱ ሁለት አመታት ውስጥ እንዲታወቁ የተደረጉትን የ AP ገጽታዎች ያሰፋል። በዚህም፣ ከቻይና ታሪክ፣ ወቅታዊ የቻይናዊ ህይወት እና የቻይናዊ የንግግር አለም ጋር የተገናኙ ሰፊ ርዕሶችን ይሸፍናል። በአሁኑ ክስተቶች

ላይ በመመስረት የተለዩ ክፍሎች ከአመት አመት ሊለያዩ ይችላሉ። የኮርስ ግቦች፦ በቻይንኛ ቋንቋ እና ባህል ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች በ ACPS ውስጥ በሚኖራቸው አመታት ውስጥ እየሰሩባቸው ባለው ቅልጥፍና ላይ ጥበቃ እና በመገንበት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለተማሪዎች ይፈልጋል። በጭብጦቹ ዙሪያ የሚሰናዱ በይዘት የጎለበቱ ርዕሶች ተማሪዎች ስለአለም ያላቸውን እንዲሁም በተለይ ደግሞ የቻይንኛ ተናጋሪ አለምን ግንዛቤ እንዲያሰፉ እድል ይሰጣል። ያልተስተጓጎለ የቋንቋ ጥናት ቅደም ተከተል ማቅረብ በኮሌጅ ላይ የተማሪ ሊኖር የሚችል ስኬትን ከፍ ያደርገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

AP የቻይንኛ ቋንቋ እና ባህል

### በፈረንሳይኛ ቋንቋ እና ባህል VI ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች

የዚህ አመት ኮርስ በፈረንሳይኛ ይሰጣል እና በተፈጥሮ ጭብጥ ያለው ነው። በንግግር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ እና በጽሁፍ ውስጥ ያሉ ጠንካራ የክህሎት መሰረቶችን ይገምታል እንዲሁም በባለፉት 2 የትምህርት አመታት ውስጥ በተዋወቁት የ AP ጭብጦች ላይ ይሰፋሉ። በዚህም፣ ከፈረንሳይ ታሪክ፣ ወቅታዊ የፈረንሳያዊ ህይወት እና የፈረንሳያዊ የንግግር አለም ጋር የተገናኙ ሰፊ ርዕሶችን ይሸፍናል። በአሁኑ ክስተቶች ላይ በመመስረት የተለዩ ክፍሎች ከአመት አመት ሊለያዩ ይችላሉ። የኮርስ ግቦች፦ በፈረንሳይኛ ቋንቋ እና ባህል ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች በ ACPS ውስጥ በሚኖራቸው አመታት ውስጥ እየሰሩባቸው ባለው ቅልጥፍና ላይ ጥበቃ እና በመገንበት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለተማሪዎች ይፈልጋል። በጭብጦቹ ዙሪያ የሚሰናዱ በይዘት የጎለበቱ ርዕሶች ተማሪዎች ስለአለም ያላቸውን እንዲሁም በተለይ ደግሞ የፈረንሳይኛ ተናጋሪ አለምን ግንዛቤ እንዲያሰፉ እድል ይሰጣል። ያልተስተጓጎለ የቋንቋ ጥናት ቅደም ተከተል ማቅረብ በኮሌጅ ላይ የተማሪ ሊኖር የሚችል ስኬትን ከፍ ያደርገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

AP/DE 1.0 ተጨማሪ የጥራት ነጥብ

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

AP የፈረንሳይ ቋንቋ እና ባህል

### በጀርመንኛ ቋንቋ እና ባህል VI ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች

የዚህ አመት ኮርስ በጀርመንኛ ይሰጣል እና በተፈጥሮ ጭብጥ ያለው ነው። እርሱ በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ እና በመጻፍ ጠንካራ መሰረታዊ ክህሎቶችን ከግምት ያስገባል እና በቀድሞ የጥናቱ ሁለት አመታት ውስጥ እንዲታወቁ የተደረጉትን የ AP ገጽታዎች ያሰፋል። በዚህም፣ ከጀርመን ታሪክ፣ ወቅታዊ የጀርመናዊ ህይወት እና የጀርመናዊ የንግግር አለም ጋር የተገናኙ ሰፊ ርዕሶችን ይሸፍናል። በአሁኑ ክስተቶች ላይ በመመስረት የተለዩ ክፍሎች ከአመት አመት ሊለያዩ ይችላሉ። የኮርስ ግቦች፦ በጀርመንኛ ቋንቋ እና ባህል ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች በ ACPS ውስጥ በሚኖራቸው አመታት ውስጥ እየሰሩባቸው ባለው ቅልጥፍና ላይ ጥበቃ እና በመገንበት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለተማሪዎች ይፈልጋል። በጭብጦቹ ዙሪያ የሚሰናዱ በይዘት የጎለበቱ ርዕሶች ተማሪዎች ስለአለም ያላቸውን እንዲሁም በተለይ ደግሞ የጀርመንኛ ተናጋሪ አለምን ግንዛቤ እንዲያሰፉ እድል ይሰጣል። ያልተስተጓጎለ የቋንቋ ጥናት ቅደም ተከተል ማቅረብ በኮሌጅ ላይ የተማሪ ሊኖር የሚችል ስኬትን ከፍ ያደርገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**ማስታወሻ:**

AP/DE 1.0 ተጨማሪ የጥራት ነጥብ

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

AP የጀርመን ቋንቋ እና ባህል

### በላቲን ቋንቋ እና ባህል VI ላይ ያሉ የላቁ ርዕሶች

በላቲን ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ርዕሶች ትክክለኛ፣ ያልተሻሻለ ክላሲካል የሆነ የላቲን ፕሮዝ እና ግጥም ያላቸው የንባብ ምርጫዎች ከሆኑና የላቲን አጠቃቀማቸው ጥብቅ እና ፈታኝ ደራሲያን በኩል የላቲን ትምህርት ጥናት ይቀጥላል። በቀድሞ የላቲን ኮርሶቻቸው ላይ ባሉ ስኬቶች ላይ በመመስረት ተማሪዎች ከተለያዩ ደራሲያን ያሉ የንባብ እና የላቲን ፕሮዝን እንዲሁም ግጥምን በመረዳት የክህሎት ብቃታቸውን ማጎልበት ይቀጥላሉ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ተማሪዎች የክላሲካል ጥንታዊነት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ምሁራዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ገጽታዎችን ይማራሉ። ተማሪዎች ወቅታዊ ስኮላርሺፕን ከማንበባቸው በተጨማሪ የላቲን ምርጫዎችን ከሌሎች ባህሎች ከመጣ ስነጽሁፍ ጋር የማነጻጸር እድል ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

AP ላቲን

### ቻይንኛ I

ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋ መዋቅሮችን የያዙ ቀላል አርፍተ ነገሮችን በመጠቀም ስለራሳቸው እና በአቅራቢያቸው ስለሚገኘው አካባቢ የሚገናኙበት ችሎታን ያጎለብታሉ። ይህ ግንኙነት በሁሉም አራቱም የቋንቋ ክህሎቶች፡- ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ በሚል በመረጃ ተደግፏል። ተማሪዎች በቃል የሚግባቡበት ችሎታ እና አጻጻፍ እድገት የኮርሱ ትኩረት ሆኖ ይቆያል። ተማሪዎች ከግል እና ከቤተሰብ ህይወት፣ ከት/ቤት እና ከማህበረሰብ ህይወት ጋር የተገናኙ የትምህርት ጭብጦችን መፈተሽ እና መማር ይቀጥላሉ። በኮርሱ መጨረሻ፣ ተማሪዎች የ 300 የቻይንኛ ቁምፊዎች በቀላል የአረፍተነገር መዋቅሮች ውስጥ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ ጋር ሰፊ እውቀት ይኖራቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### ቻይንኛ III

ተማሪዎች የራሳቸውን ብቃት በሁሉም አራቱም ክህሎቶች ለማሳደግ እና ለማጥራት ይቀጥላሉ፤በቃል እና በጽሁፍ ለመግባባት ላለው ችሎታ አጽንዖት በመስጠት መስማት፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ነው። በተለያዩ ርዕሶች ላይ የበለጠ ውስብስብ የቋንቋ አወቃቀሮችን በመጠቀምና ከሚዳሰስ ወደበለጠ ረቂቅ ጽንሰ ሃሳቦች በመሄድ ይግባባሉ። በዚህ ደረጃ፣ ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው እና ስለሚሰሟቸው ትክክለኛ ነገሮች ዋና ሃሳቦችን ይረዳሉ፣ እና ርዕሶቹን ሲያውቁ ወሳን የሆኑ ዝርዝሮችን ለመለየት ይችላሉ። ተማሪዎች መብቶችን እና ግዴታዎችን፣ የወደፊት እቅዶችን እና ምርጫዎችን፣ የታዳጊ ወጣቶች ባህልን፣ አካባቢን እና ሰብዓዊነትን በማጥናት በዙሪያቸው ያለውን ግንዛቤ ጥልቅ ያደርጋሉ። ከደረጃዎች I እና II ያሉ አንዳንድ የሚታወቁ ጭብጦች እና ርዕሶች በደረጃ III ውስጥ ዳግም ሊከሰቱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በጭብጥ ላይ የተመሰረተ የተወሳሰበ የተፈጥሮ መመሪያ፣ ተማሪዎች የግንኙነት ክህሎታቸውን እና የቋንቋ ውስብስብነትን በአዲስ የእድገት ደረጃ ላይ እንዳሉ እንዲያሳዩ ይጠይቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**የቻይና IV ኦነርስ**

ተማሪዎች የራሳቸውን ብቃት በሁሉም አራቱም ክህሎቶች ለማሳደግ እና ለማጥራት ይቀጥላሉ፤በቃል እና በጽሁፍ ለመግባበት ላለው ችሎታ አጽንዖት በመስጠት መስማት፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ነው። በተለያዩ ርዕሶች ላይ የበለጠ ውስብስብ የቋንቋ አወቃቀሮችን በመጠቀምና ረቂቅ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ በማተኮር ይግባባሉ። በዚህ ደረጃ፣ ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው እና ስለሚሰሟቸው ትክክለኛ ነገሮች ዋና ሃሳቦችን ይረዳሉ፣ እና ርዕሶቹን ሲያውቁ ወሳን የሆኑ ዝርዝሮችን ለመለየት ይችላሉ። ተማሪዎች የቻይና ባህላዊ፣ ማህበራዊ ህይወት፣ ትርፍ ጊዜያት፣ አካባቢ፣ ስራ እና ኮሌጅ ገጽታዎች በሆነችው ቤጂንግ በመማር በዙሪያቸው ያለውን ግንዛቤ ጥልቅ ያደርጋሉ። ከቻይንኛ I ፣ ቻይንኛ II እና ቻይንኛ III ያሉ አንዳንድ የሚታወቁ ጭብጦች እና ርዕሶች  ዳግም ሊከሰቱ ይችላሉ፣ ይሁን እንጂ የተጣመመ ተፈጥሮ ያለው በጭብጥ ላይ የተመሰረተ መመሪያ ተማሪዎች የግንኙነት ክህሎታቸውን እና  ውስብስብነትን በአዲስ የእድገት ደረጃ እንዲያሳዩ ይጠይቃል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**የፈረንሳይኛ ውይይት እና ባህል I -የበጋ ት/ቤት**

ይህ በተግባራዊ አደራረግ ላይ ተመስርቶ ከባህላዊ ክፍል ጋር የሆነ የተጠናከረ በሁኔታ ላይ የሚደገፍ የንግግር ኮርስ ነው። ኮርሱ በ Caen ፈረንሳይ ውስጥ ባለው የትብብር ት/ቤት ውስጥ በምናደርገው ልውውጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የታለመ ነው። ቅድሚያ የመልቀቅ መመሪያ ተማሪዎች ከፈረንሳይ ቤተሰብ ጋር በሚኖረው ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንት የቤት ቆይታ ሊኖር በሚችለው የእለት ሁኔታቸው እና የንግግር ልውውጥ እንዲያከናውኑ ያዘጋጃቸዋል። በፈረንሳይ እያሉ፣ ተማሪዎች መርሃ ግብር የወጣላቸውን ክፍሎች በመደበኛነት ይከታተላሉ እና በፈረንሳይኛ ቋንቋ እና ባህል ራሳቸውን ያስገባሉ። የዚህ ኮርስ አቅርቦት በተማሪው ፍላጎት እና ብቁ በሆኑ የአስተማሪ አለቆች መገኘት ላይ ይደገፋል። እያንዳንዱ ተማሪ የቤት ቆይታውን ሲጨርስ ፕሮጀክት ያዘጋጃል እና ያስገባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

[g2]የትምህርት ቤት ደረጃ፡- [/g2]የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ፈረንሳይኛ IA

**ፈረንሳይኛ III**

በፈረንሳይኛ III ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የውጤታማ እና ተቀባይነት ክህሎቶችን በማሻሻል ተማሪዎች በኢላማ ቋንቋ የግንኙነት ብቃት እድገት ላይ ትኩረታቸውን ማድረግ ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በፈረንሳይኛ ያሉ የቃል እና የጽሁፍ መልዕክቶችን ይረዳሉ እንዲሁም እርስ በእርሳቸው እና ከአስተማሪያቸው ጋር በቃል እና በጽሁፍ መስተጋብር ይፈጥራሉ። በቋንቋ ጥናት ሶስተኛ ደረጃ ላይ፣ ተማሪዎች የበለጠ ውስብስብ መዋቅሮችን መጠቀም ይጀምራሉ እና እየጨመሩ የሚመጡ ሰፋፊ ርዕሶች ላይ መነጋገር ይችላሉ። የጥናቱ ክፍሎች በተፈጥሮ ጭብጥ ያላቸው ናቸው እና የሰዋሰዋዊ ጽንሰ ሃሳቦች በአምድ ውስጥ ቀርበዋል እና ተተግብረዋል። ጭብጣዊ ክፍሎች የሚያካትቱት የወቅቱን ህይወት፣ ምርጫዎች እና የወደፊት እቅዶች፣ የታዳጊ ወጣቶች ባህል፣ አካባቢውን እና ሰብአዊነቶችን ነው። የደረጃ III ክፍል በዋነኛነት በፈረንሳይኛ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ፈረንሳይኛ IV ኦነርስ**

ደረጃ IV ፈረንሳይኛ በደረጃ I፣II እና III የተዋወቁትን አንዳንድ አስፈላጊ መዋቅሮች ይገመግማል እንዲሁም ዳግም ይጠቀማል። ተማሪዎች እነዚህን ቁልፍ ፅንሰሃሳቦች ደግመው ሲጎበኙ፣ በሁለቱም

የመጻፍ እና መናገር ውስጥ ባለው ትኩረቱ የግንኙነት ብቃት እድገት ላይ ይሆናል። የጥናቱ ክፍሎች በተፈጥሮ ጭብጥ ያላቸው ናቸው እና የሰዋሰዋዊ ጽንሰ ሃሳቦች አመቱን በሙሉ በአምድ ውስጥ ቀርበዋል እና ተተግብረዋል። የቃላት ስብስብ በአጫጭር ንባቦች፣ በወቅታዊ ጽሁፎች፣ ሙዚቃዎች እና ፊልሞች በኩል ተዋውቋል። በአመቱ የኮርስ ጊዜ ወቅት፣ ተማሪዎች ዋና የግስ ቴንሶች(tenses) ቁጥጥራቸውን ያጠራሉ እንዲሁም ግልጽ እና ወጥነት ባለው የቴንስ አጠቃቀም በተከታታይ ክስተቶች ውስጥ ያተኩራሉ። ኮርሱ በፈረንሳይኛ ይከናወናል እና ተማሪዎች ከአስተማሪ እና እርስ በእርሳቸው በክፍል ውስጥ የኢላማ ቋንቋውን እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ፈረንሳይኛ III

### ጀርመንኛ ውይይት እና ባህል I - የበጋ ት/ቤት

ይህ በተግባራዊ አደራረግ ላይ ተመስርቶ ከባህላዊ ክፍል ጋር የሆነ የተጠናከረ በሁኔታ ላይ የሚደገፍ የንግግር ኮርስ ነው። ኮርሱ በኦስትሪያ ውስጥ ባለው የትብብር ት/ቤት ውስጥ በምናደርገው ልውውጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የታለመ ነው። ቅድሚያ የመልቀቅ መመሪያ ተማሪዎች ከአውስትራሊያ ቤተሰብ ጋር በሚኖረው የሁለት ሳምንት የቤት ቆይታ ሊኖር በሚችለው የእለት ሁኔታቸው እና የንግግር ልውውጥ እንዲያከናውኑ ያዘጋጃቸዋል። በኦስትሪያ እያሉ፣ ተማሪዎች መርሃ ግብር የወጣላቸውን ክፍሎች በመደበኛነት ይከታተላሉ እና በኦስትሪያ ቋንቋ እና ባህል ራሳቸውን ያስገባሉ። የመስክ ጉዞ ስፍራዎች ሙኒክ፣ ሳልዝበርግ እና ቬየናን ያካትታሉ። የዚህ ኮርስ አቅርቦት በተማሪው ፍላጎት እና ብቁ በሆኑ የአስተማሪ አለቆች መገኘት ላይ ይደገፋል። ተማሪዎች ኮርሱን ሲያጠናቅቁ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃሉ እና ያስገባሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11

### ጀርመንኛ III

ተማሪዎች ውጤታማ እና ተቀባይነት ያላቸው ክህሎቶችን ሲያጎለብቱ የግንኙነት ብቃት እድገትን ይቀጥላሉ። የጥናቱ ክፍሎች በተፈጥሮ ጭብጥ ያላቸው ናቸው እና የሰዋሰዋዊ ጽንሰ ሃሳቦች በአምድ ውስጥ ቀርበዋል እና ተተግብረዋል። ጭብጣዊ ክፍሎች የሚያካትቱት የወቅቱን ህይወት፣ ምርጫዎች እና የወደፊት እቅዶች፣ የታዳጊ ወጣቶች ባህል፣ አካባቢውን እና ሰብአዊነቶችን ነው። ተማሪዎች በጀርመንኛ የቃል እና የጽሁፍ መልዕክቶችን ይረዳሉ እንዲሁም በቃልም ሆነ በጽሁፍ እርስ በእርሳቸው እና ከአስተማሪው ጋር መስተጋብር ይፈጥራሉ። በቋንቋ ጥናት ሶስተኛ ደረጃ ላይ፣ ተማሪዎች የበለጠ ውስብስብ መዋቅሮችን መጠቀም ይጀምራሉ እና እየጨመሩ የሚመጡ ሰፋፊ ርዕሶች ላይ መነጋገር ይችላሉ። የደረጃ III ክፍል በዋነኛነት በጀርመንኛ ይከናወናል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### ጀርመንኛ IV ኦነርስ

በዚህ የ pre-AP ኮርስ ተማሪዎች በሶስት የግንኙነት ብቃት ገመዶች ብቃታቸውን ለማሳደግ ይቀጥላሉ፤ ከቋንቋው ሌላ ተናጋሪ ጋር መስተጋብር መፍጠር፣ በኢላማ ቋንቋው ትክክለኛ የቃል እና የጽሁፍ መልዕክቶችን መረዳት እንዲሁም በኢላማ ቋንቋው የቃል እና የጽሁፍ አቀራረቦችን ማድረግ። ይህ በከፍተኛ ደረጃ ጥብቅ የሆነ ካሪኩለም ተማሪዎች እውነተኛ የሆኑ መሳሪያዎችን እንዲተነትኑ እና እንዲያዋህዱ እንዲሁም ከወቅታዊ እና ታሪካዊ ክስተቶች እና ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በርካታ ርዕሶች ላይ ያሉ አስተያየቶችን ከትምህርታቸው

ጋር ተመጣጣኝና ብቁ በሆነ ደረጃ እንዲለዋወጡ እና እንዲደግፉ ይጠይቃል። ተማሪዎች ከተለያዩ ትክክለኛ ምንጮች የንግግር እና የተጻፉ ጽሁፎችን ይረዳሉ እንዲሁም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በደንብ የጎለበቱ ሃሳቦችን የያዙ ጥንቅሮችን ያዘጋጃሉ። የጥናቱ ክፍሎች በተፈጥሮ ጭብጥ ያላቸው ናቸው እና የሰዋሰዋዊ ጽንሰ ሃሳቦች አመቱን በሙሉ በአምድ ውስጥ ቀርበዋል እና ተተግብረዋል። የቃላት ስብስብ በአጫጭር ንባቦች በ Hans Konig ከተዘጋጀው ከ “Das Mysteriose Konzert” አጫጭር የሬዲዮ ጭውውት እስከ ወቅታዊ ጽሁፎች፣ ቃለምልልሶች፣ ሙዚቃዎች፣ ፊልም እና ታዋቂ የህጻናት ልብወለድ ከሆነው በ Erich Kastner ከተጻፈው “Emil und die Detektive” ድረስ ያቅፋል። በአመቱ የኮርስ ጊዜ ወቅት፣ ተማሪዎች ዋና የግስ ቴንሶች(tenses) (የአሁን፣ የኋላ፣ የወደፊት እና ሁኔታዊ) ቁጥጥራቸውን ያጠራሉ እንዲሁም ግልጽ እና ወጥነት ባለው የቴንስ አጠቃቀም በተከታታይ ክስተቶች ውስጥ ያተኩራሉ። ኮርሱ በጀርመንኛ ይሰጣል እና ተማሪዎች ጀርመንኛን ከአስተማሪያቸው እና እርስ በእርሳቸው በክፍል ውስጥ እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፦**

ጀርመንኛ III

### ላቲን I

በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች የግንኙነት ብቃት እድገት ላይ እና የሮማ ባህል ላይ ስላላቸው መረዳት ያተኩራሉ። ተማሪዎች በመስማት፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ ውስጥ ያሉ ጎራዎች ውስጥ ጠንካራ እና አጠቃላይ መሰረት ይገነባሉ።
የመዝገበ ቃላት እና ሰዋሰው መዋቅሮች በታሪካዊ እና በእውነታው ህይወት አውድ ውስጥ ቀርቧል እና በተወሰኑ የግንኙነት ስራዎች ዙሪያ አድገዋል። በታሪክ፣ በባህል፣ በስነጽሁፍ እና በእለት ተእለት ህይወት ላይ ያተኩሩ ርዕሶች በመመሪያው ውስጥ ተካትተዋል እንዲሁም ከኢላማ ባህል በመነሳት ምርቶች እና ልምዶች ተወስደዋል። በቋንቋ-መማር ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ እንዴት እንደሚዋቀር፣ እንዲሁም የባህል እና የቋንቋ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ የመረዳት እይታዎችን ያገኛሉ። ተማሪዎች እንዲሁ ከትምህርት ክፍል ውጪ ላሉ ለበርካታ የመዝናኛ፣ ትምህርታዊ እና የስራ የላቲን ጠቀሜታዎች አድናቆትን አሳድገዋል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### ላቲን III

ተማሪዎች አጠቃላይ እውነተኛ የላቲን ጽሁፎች ከ ውስብስብ የቋንቋ አወቃቀሮች ጋር የተተገበሩትን የቋንቋ ክህሎቶች እድገት ይቀጥላሉ። ተማሪዎች የአርኪዮሎጂ ማስረጃን፣ ስነጥበብን እና ስነጽሁፍን እንደ ግሪክ-ሮማን እይታዎች እና ልምዶች ነጸብራቆች አድርገው ያሰፋሉ። እነሱ የሮማ ፓለቲካዊ ስርዓትን፣ የሮማ ግዛትን ብዙ የባህል እይታዎች እና እንዲሁም የጂኦግራፊ ሚና በውትድርና ታሪክ ውስጥ ይመረምራሉ እና እነዚህን ከተመሳሳይ የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ እና ጂኦግራፊ ጋር ያነጻጽራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፦** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፦** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፦** 9, 10, 11, 12

### ላቲን IV ኦነርስ

በላቲን IV ውስጥ፣ ተማሪዎች የሮማን ግጥም ትርጉም እና አተናተን ላይ ያላቸውን ክህሎት ያሻሽሉታል። ላቲንን መረዳት ከዋናው የዘመናዊ ቋንቋዎች ግብ በመለያየቱ ምክንያት፣ ኮርሱ ከግለሰብ-ግለሰብ ግንኙነት ይልቅ ጽሁፎችን መተርጎም ላይ ያተኩራል።

ተማሪዎች እንደ ንግግር አይነቶች፣ የቃላት አመራረጥ እና ሜትር ያሉ የስታይል ባህሪያትን ውጤቶች በተሰጠው የጸሃፊ ስራ ላይ ይተነትናሉ። የግሪክ-ሮም ስልጣኔን እይታዎች እና ልምዶች እውቀታቸውን ለማስፋት ፍልስፍናቸውን፣ ሃይማኖታቸውን፣ አፈታሪካቸውን እና የግላዊ ባህርይ ደረጃቸውን ይመረምራሉ። በተጨማሪም ሮማዊያን ለዘመናዊ ህግ፣ መንግስት ስነጥበብ እና አርክቴክቸር ያደረጉትን  አስተዋጽዖዎች ይወያያሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ላቲን III

**የበርካታ ቋንቋ አስተማሪ ረዳት**

ይህ ተመራጭ ኦነርስ ወደ አሌክሳንድሪያ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አለም አቀፍ ማህበረሰብ በርካታ የቋንቋ ክህሎቶችን ለሚያመጡ ተማሪዎች ነው። ሁለት ቋንቋ የሚችሉ ተማሪዎች በይዘት አካባቢ ክፍሎች ውስጥ ወይም በአለም ቋንቋ ክፍሎች ውስጥ የአስተማሪ ረዳቶች ሆነው በማገልገል በስትራቴጂያዊ የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ወይም በአለም ቋንቋ ክፍሎች እንደ ቋንቋ ሞዴሎች በመሆን አስተማሪዎችን ይረዳሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**የስፓኒሽ ውይይት እና ባህል I - የበጋ ት/ቤት**

ይህ በተግባራዊ አደራረግ ላይ ተመስርቶ ከባህላዊ ክፍል ጋር የሆነ የተጠናከረ በሁኔታ ላይ የሚደገፍ የንግግር ኮርስ ነው። ኮርሱ በሊሙ ፔሩ ውስጥ ባለው የትብብር ት/ቤት ውስጥ በምናደርገው ልውውጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የታለመ ነው። ቅድሚያ የመልቀቅ መመሪያ ተማሪዎች ከፔሩቪያን ቤተሰብ ጋር በሚኖረው ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንት የቤት ቆይታ ሊኖር በሚችለው የእለት ሁኔታቸው እና የንግግር ልውውጥ እንዲያከናውኑ ያዘጋጃቸዋል። በፔሩ እያሉ፣ ተማሪዎች መርሃ ግብር የወጣላቸውን ክፍሎች በመደበኛነት ይከታተላሉ እና በስፓኒሽ ቋንቋ እና ባህል ራሳቸውን ያስገባሉ። የዚህ ኮርስ አቅርቦት በተማሪው ፍላጎት እና ብቁ በሆኑ የአስተማሪ አለቆች መገኘት ላይ ይደገፋል። እያንዳንዱ ተማሪ የቤት ቆይታውን ሲጨርስ ፕሮጀክት ያዘጋጃል እና ያስገባል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ IA

## ስፓኒሽ III

በደረጃ III ስፓኒሽ፣ ተማሪዎች በሶስቱ የንግግር ብቃት ገመዶች ብቃታቸውን ለማጎልበር ቀጥለዋል፤ ከቋንቋ ሌሎች ተናጋሪዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር፣ በኢላማ ቋንቋው የቃል እና የጽሁፍ መልዕክቶችን መረዳት እና በኢላማ ቋንቋው የቃል እና የድምጽ አቀራረቦችን ማድረግ። በቋንቋው በተለያዩ ርዕሶች ላይ የበለጠ ውስብስብ መዋቅሮችን በመጠቀም እና ከሚዳሰስ ወደበለጠ ረቂቅ ጽንሰ ሃሳቦች በመሄድ ከትምህርታቸው ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ ይገናኛሉ። ተማሪዎች ያደመጡትን እና ያነበቡትን እውነተኛ ነገሮች ዋና ዋና ሃሳቦችን ይረዳሉ እና ርዕሶቹ የተለመዱ ሲሆኑ ጉልህ የሆኑ ዝርዝሮችን ለመለየት ይችላሉ። ተማሪዎች ከታሪካዊ እና ከወቅቱ ክስተቶች እና ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ርዕሶችን በኢላማ ቋንቋ የመወያየት ችሎታን ያዳብራሉ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

### ስፓኒሽ IV ኦነርስ

ተማሪዎች በሶስት የግንኙነት ብቃት ገመዶች ውስጥ ብቃታቸውን ማጎልበት ይቀጥላሉ፤ ከሌላ የቋንቋው ተናጋሪ ጋር መስተጋብር መፍጠር፣ በኢላማ ቋንቋው የቃል እና የጽሁፍ መልዕክቶችን መረዳት እና በኢላማ ቋንቋው የንግግር እና የጽሁፍ አቀራረቦችን ማድረግ ናቸው። ከወቅታዊ እና ታሪካዊ ክስተቶች እና ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያሉ የግል ሃሳቦችን ከትምህርታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ በብቃት ደረጃ ላይ ያሉ  የግል አስተያየቶችን ለመለዋወጥ እና ለመደገፍ ይችላሉ። ተማሪዎች ከተለያዩ ትክክለኛ ምንጮች የንግግር እና የተጻፉ ጽሁፎችን ይረዳሉ እንዲሁም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በደንብ የጎለበቱ ሃሳቦችን የያዙ ጥንቅሮችን ያዘጋጃሉ። ክፍሉ በስፓኒሽ ብቻ ይሰጣል ተማሪዎች የኢላማ ቋንቋውን በመጠቀም በሌሎች የትምህርት አካባቢዎች ያለ መረጃን ያገኛሉ እና የራሳቸው ባልሆኑ ቋንቋው በሚነገርባቸው ሃገራት የባህላዊ አካላቶችን ለማነጻጸር እና ለማቃረን ያስችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ III

### የስፓኒሽ ማንበብና መጻፍ ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች

ይህ ኮርስ ፈጣን የመማር እና የቋንቋ መቅሰምን ኢላማ ውስጥ ለሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ላሉ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ያስተዋውቃል። ይህ ደረጃ II/III ኮርስ ነው ምክንያቱም የተነደፈው እየመጡ ላሉ ታዳጊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማወቅ የመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ ላሉና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መሰረታዊ የስነጽሁፍ ክህሎቶችን ለማጎልበት ድጋፍ ለሚፈልጉ አንባቢዎች ነው፣ ይህም ለስፓኒሽ እና በሚከተሉት አካባቢዎች ውስጥ ላሉ ማለት ነው፤ የፎኖሎጂካል ግንዛቤ፣ የህትመት ጽንሰሃሳቦች፣ የእድገት ቃላት ስብስብ፣ የንባብ መረዳት፣ መጻፍ፣ ማንበብ እና ማዳመጥ። ይህ ኮርስ ከመነሻ መሰረታዊ የቋንቋ እውቀት እስከሚጨምሩ የተመሩ ደረጃዎች እና በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ ራሱን የቻለ መተላለፍ ያላቸው የተማሪዎች እንቅስቃሴን ይደግፋል። ስፓኒሽ ብቻ በክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ ይዉላል እና ክፍሉ የስፓኒሽ ተናጋሪ ባህል(ባህሎች) ያከብራል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ርዝመት፡-** ሙሉ አመት

**ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች I**

ይህ ኮርስ ስፓኒሽ በቃላቸው ብቁ ሆነው ለሚናገሩ ነገር ግን ከተወሰነ ደረጃ እስካለመቻል የደረሰ የንባብ እና የመጻፍ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የቋንቋውን የአወቃቀር እና የጽሁፍ ገጽታዎች ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ አጽንዖት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች የጽሁፍ ጥንቅሮች ማጎልበት ይጀምራሉ እና ከተለያዩ የስነጽሁፍ ዘውጎች ጋር ይተዋወቃሉ። ተማሪዎች እንዲሁ በሂስፓኒክ ባህል መካከል ያሉትን ልዩነቶች እና ተመሳሳይነቶች ያላቸውን ግንዛቤ እና አድናቆት ይጨምራሉ። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ ተማሪዎች ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች II ወደሚለው ሊያድጉ ይችላሉ። ስፓኒሽ በክፍል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ተናጋሪዎች ለቅርስ ተናጋሪዎች III**

ይህ ኮርስ የተማሪዎች ነባር የስፓኒሽ ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መጻፍ እና መናገር ላይ ያሉ ብቃቶችን ለሂስፓኒክ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ባህል እና የአሁን ክስተቶች በማጋለጥ ማሻሻል ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተማሪዎች እውነታዎችን፣ ሃሳቦችን እና ስሜቶችን ከፍ ባለ የንግግር እና የአጻጻፍ ተግባራት መግለጽ ይችላሉ። ተማሪዎች በርካታ አይነት እውነተኛ ጽሁፎችን ያነባሉ፣ ይተነትናሉ እንዲሁም ይተረጉማሉ እና የሰዋሰዋዊ መዋቅሮቻቸውን እውቀት እና አተገባበር ያሻሽላሉ። ተማሪዎች ባህላዊ እይታዎችን እና ልምዶችን ያጋራሉ እና በስነጽሁፉ አምድ በኩል ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን ያጎለብታሉ። በማንበብ፣ በማዳመጥ እና በውይይት እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ ተማሪዎች የቃላት ስብስባቸውን ማጎልበት ይቀጥላሉ። ይህንን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ ተማሪዎች ወደ ስፓኒሽ IV ወይም ስፓኒሽ V/AP የስፓኒሽ ቋንቋ እና ባህል ሊያድጉ ይችላሉ። ስፓኒሽ በክፍል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች፡-** 1

**የትምህርት ቤት ደረጃ፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የክፍል ደረጃ፡-** 9, 10, 11, 12

**ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

ስፓኒሽ ለቅርስ ተናጋሪዎች II ወይም የማውራት ብቃት በስፓኒሽ ንግግር፤ ስፓኒሽ በማንበብ እና በመጻፍ የተወሰነ ብቃት። በምደባ ሙከራ የሚታወቅ ብቃት።